መጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች።

ትርጓሜ።

1954 ዓ.ም።

ዳ.እ

ጎንደር።

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

ለእግዚአብሔርም ለኢትዮጵያም

መቅድም።

1. ቆሮንቶስ፤ የከተማው አቀማመጥና አኳኋን።
2. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን፤ የመመሥረቱ ታሪክ።
3. በቆሮንቶስ የነበሩ የክርስቲያናች ሁኔታ።
4. ወደ ቆሮንቶስ የተጻፈ የመልእክቱ አጻጻፍ።

    ሀ/ ሁኔታው።

    ለ/ አሳቡ።

    ሐ/ መተንተኑ።

    መ/ ጥቅሙ።

5. ወደ ቆሮንቶስ የተጻፈ የመልእክቱ ትርጓሜ።

1. ቆሮንቶስ፤ የከተማው አቀማመጥና አኳኋን።

ቆሮንቶስ በሐዋርያው በጳውሎስ ዘመን 600 ሺህ ሰው የኖረበት ታላቅ ከተማ ነበረ። በግሪክ አገር ሆኖ በሁለቱ የግሪክ አገር ጠቅላይ ግዛቶች በመቄዶንያና በአካይያ መካከል በነበረው ልላነ ምድር ላይ የተመሠረተ ነው። ባሕርና ባሕር እዚያ ስለሚገናኝ በስተ ቀኝ (በስተ ምሥራት) በኩል ከእስያ ከሶርያ ከፊንቄና ከግብፅ ከንክራአስ በሚባል ወደብ በኩል ንግድ ሲመጣለት በስተ ግራ (በስተ ምዕራብ) በኩል ከኢጣሊያ ከሲቺሊያና ከእስጳንያ ሊከዩም በመባል ወደብ ይመጣለት ነበር። በዚህ ምክንያት ግለት ንግድ በጣም በርከት ስላለው፤ ከተማው እጅግ ሀብታም ሆነ፤ ከሀብትም ጋር «የከፋት ሁሉ መደብ» እስኪባል ድረስ እጅግ የጋጠአት ከተማ ሆነ። ቆሮንቶስ የንግድ ጣቢያ ብቻ ሳይሆን ከሮማ ወደ ምሥራት የሚሄደው ዋና መተላለፊያ ነበረና የብዙ መንገደኛ ግረፊያና የብዙ ሰው መገናኛ ሆነ። በከተማ ነዋሪዎች መካከል ሮማውያን ግሪኮች አይሁድም ተገኙ። ያ ከፍለ ዓለም ሁሉ በዚያን ጊዜ በሮማ መንግሥት ግዛት ውስጥ ስለ ነበረ አገረ ገዥ ሮማዊ ነበረ የከተማ ሹማምንትና ከበርቴዎች ወታደሮችም ሮማውያን ነበሩ። በንግድ ረገድ የበረቱ ግን ግሪኮች ነበሩና የከተማው ቋንቋ ግሪክ ነበረ። በሌላም በኩል ደግሞ አይሁድ በብዙ ተገኝተውበታል፤ ምክንያቱም፡- 1ኛ፤ የአይሁድ ሃይማኖት ስለ ተወደደ ነው። 2ኛ፤ አይሁድ ከሮማ እንዲወጡ አቅሉዲዩስ ቂሳር ቢያዝዝ ብዙዎቹ በዚያ መተላለፊያ እየተጓዙ ወደ ቆሮንቶስ ስለ መጡ ነው። ከተማው ግን ትልቅ የሆነበት በንግዱ ብቻ ሳይሆን ቆሮንቶስ የአካይያ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ ሆና የሮማ «ምክትል ቆንሲል» የተቀመጠበትና የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሁሉ የተገኘበት ከተማ በመሆኑ ነው። በዚያ ደግሞ በየሦስቱ ዓመት «እስትሚያን» የተባለ የልላነ ምድር የአስፖርት ውድድር ይደረግ ነበረና በዓለም ሁሉ ዘንድ የቆሮንቶስ ከተማ ስም ለመታወቅ በቃ።

2፤ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን፥ የመመሥረቱ ታሪክ።

ቅዱስ ጳውሎስ አገርን ሁሉ ለማስተማር ሁለተኛ ጊዜ ሲወጣ፥ እርሱም በ52 ዓ.ም፥ አስቀድሞ በሶርያና በኪልቅያ አድርጎ በደርቤ በልስጥራን በገላትያም በኩል ወደ ጢሮአዳ መጣ። እዚያም በጢሮአዳ ላለ ራእይ ቢታየውና ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ቢጠራ ባሕርን ተሻግሮ ወደ ፈልጵስዩስ ደረሰ። (የሐዋ. 15፡36 - ም. 16፤8።*) በፈልጵስዩስ አስተምሮ መከራ ከተቀበለ በኋላ ወደ ተሰሎንቄ መጣ፥ እዚያም ደግሞ ተቃዋሚ ቢበዛ ጳውሎስ ከዚያ ለቅቆ ወደ ቤርያና የግሪክ አገር ዋና ከተማ ወደ ነበረው ወደ አቴና ተጓዘ። (የሐዋ. 17፤1፡10፡14፡15።) በአቴና ጥቂት ወራት ከተቀመጠ በኋላ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። (የሐዋ. 1፤1።) በቆሮንቶስም አቂላና ጵርስቅላ የተባሉትን አይሁድ አገኘ። እነኚህም ባልና ሚስት ሆነው ከሮማ የተሰደዱ ነበሩ፤ የሁለታቸውም፥ የጳውሎስና የአቂላ ሥራ አንድ ነበረና ጳውሎስ ወደ እነርሱ ገባ ባንድነትም ሲሠራ ቆየ። (የሐዋ. 18፤2፡3።) ወደዚያ አገር አስቀድሞ ቢመጣ በየሳምንቱ ሁሉ ወደ ምኩራብ ገብቶ ያስተምር ነበር በኋላ ግን ተሳዳቢዎች ቢነሡ ጳውሎስ ያመኑትን ሰዎች ከምኩራብ ለይቶ የለንበትን ስብሰባ በሰው ቤት አደረገ። (የሐዋ. 18፤4-7።) ይህ ሲሆን በቃሉ ያመኑና የተጠመቁ ብዙዎች ተገኙ በመካከላቸውም ኢዮስጦስ የተባለ ሮማዊና ቀርስጲስ የተባለ የምኩራብ አለቃ።

ነበሩ። መጀመሪያዎች የቆሮንቶስ ምእመናን እነኚህ ናቸው የቤተ ክርስቲያኑም መመሥረት ይህ ነው።

ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሲመጣ ከጌታ ዘንድ መልካም ተስፋ አግኝቶ ኖሮ አንድ ዓመት ተመንፈቅ ተቀመጠ ተቃዋሚም ተነሥቶ ላገረ ገዡ ስንኳ ምንም ቢከስስ እግዚአብሔር አወጣው፤ ቤተ ክርስቲያኑም እየጸና ሄደ። (የሐዋ. 18፤12-16።)

ከቆሮንቶስ በተሰናበተ ጊዜ ጳውሎስ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር ወደ ኤፌሶን ተሻገረ እነርሱም እዚያ ቢቆዩ እርሱ አግሬ መንገዱን ቀጥሎ ወደ አንጾኪያ መጣ። አቂላና ጵርስቅላ በኤፌሶን ተቀምጠው ሳሉ አገሩ እስክንድርያ የሆነ አጵሎስ የተባለ አይሁዳዊ ሰው መጣ፤ ይህ ሰው አንደበቱ የሰላና መጻሕፍትን የተማረ ሆኖ የጌታን ነገር በሚያጠልቅ መንፈስ ይስብክ ጀመር፤ ሆኖም የክርስቶስን ነገር ገና በቅጡ አላወቀም ነበር። አቂላና ጵርስቅላ ይህን ሰው ወስደው የእግዚአብሔርን መንገል በሚገባ አስተማሩት፤ እርሱም ወደ አካይያ ለመሄድ ባሰበ ጊዜ በቆሮንቶስ ለነበሩ ክርስቲያኖች የመታወቂያ ወረቀት ሰጡት። እንዲሁም በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከጳውሎስ ቀጥሎ ሁለተኛ አስተማሪ አጵሎስ ሆነ።

3፤ በቆሮንቶስ የነበሩ የክርስቲያን ሁኔታ።

ቅዱስ ጳውሎስ በም. 1፡ ቁ. 26 ላይ እንደሚያመለክተው በቆሮንቶስ ከነበሩ ክርስቲያኖች የሚበዙት ድሆችና ያልተማሩ ነበሩ። ቢሆንም እንደ ምኩራቡ አለቃ እንደ ቀርስጲስ፤ ጳውሎስንና ቤተ ክርስቲያኑንም ሁሉ እንደ አስተናገደው እንደ ጋይዩስ የከተማው መጋቢ እንደ ሆነም እንደ ኤርስጦስ የመሰሉት ክቡርቴዎችና ሀብታሞች ደግሞ ተገኝተውበታል። (የሐዋ. 18፤8። ሮሜ. 16፤ 23። 1 ቆሮ. 1፤ 14።) በማኅበራቸውም ጊዜያት አድልዎን የፈጠረ ይህ ነገር ሳይሆን አይቀርም። (ም. 11፤17-22።)

ሁለተኛም ደግሞ በልዩ ልዩ በኩል ኑሮአቸው አለቸጋሪ ነበረ። እነርሱም በታላቅ ከተማና በአረመኔ ሕዝብ መካከል ሆነው በቁጥራቸው አነሱ። ለምሳሌ ጳውሎስ ተለዩ ብሎአቸው ነበር። እንደምን ይለዩ? ዓለም በደጃፋቸው ላይና በዙሪያቸው ሁሉ ሲሆን ክርስቲያኖቹ እንደምን ይለዩ? (ም. 5፤9-11።) ከማንስ ጋር ይጋቡ? ከርስቲያኖች በሚቢቃ አልተገኙም፤ የአንዳንዶቻቸው ባለቤቶች እንኳ ገና አረመኔዎች ነበሩ። (ም. 7፤10-16።) ምንስ ይብሉ ደግሞ? በገበያ የሚሸጥ ሥጋ ሁሉ ለጣዖት የተሠዋ ሲሆን ንጹሕን ሥጋ ከየት ያግኙ? ስለዚህ ሁሉ በቆሮንቶስ የነበሩ የክርስቲያኖች ኑሮ አስቸጋሪ ሆነ።

ጳውሎስ መልእክቱን በጻፈ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ ገና አዲስ ነበረች። እርሱ መሠረቱን መሥርቶ ነበር። ከእርሱም በኋላ አጵሎስ ገብቶ ሠራ። በዚህም ዓለም ብዙ ጊዜ እንደሚሆነው አንዱ አስተማሪ ወጥቶ ሌላ ሲተካ ከመጀመሪያው ዘንድ የተማሩ ሰዎች እርሱን ሲያከብሩ ሁለተኛውን ያቃልላሉ እንደዚሁም ደግሞ ከሁለተኛው ዘንድ የሚማሩ ያን መጀመሪያውን እጅግ አያውቁትምና እርሱን ንቀው ሁለተኛውን ያከብራሉ። በቆሮንቶስም እንዲሁ ሆነ። የጳውሎስ ተማሪዎች አሉ፤ የአጵሎስም አሉ። ሲሆን ደግሞ ሦስተኛ ወገን እርሱም የጴጥሮስ ወገን ገባ። (በጽርዕ ቋንቋ «ኬፋ» ማለት ጴጥሮስ ማለት ነው።) (ዮሐ. 1፤42።) የዚህ ወገን ሰዎች የአይሁድን ነገር የወደዱ ይሆናሉ። ክርስቲያኖች ነበሩ ነገር ግን ጳውሎስ ያስተማረውን የነፃነትን ነገር ሳይወዱ በተለይ የአይሁድ ሐዋርያ የሆነውን የጴጥሮስን አስተያየት ወድደዋል። (ገላ 2፥7፡8። የሐዋ 21፥ 19-21። ገላ 2፥ 11-14።) በዚህ ምክንያት እነርሱ «ጴጥሮስ ሐዋርያ እንደሆነ ዓይነት ጳውሎስ ሐዋርያ አይደለም» ብለው እየሰበኩ «እኛ የጴጥሮስ ነን» አሉ። (ም. 9፥1-5።) ከእነዚህም ሌሎች ደግሞ ተነሥተው፡- «አይ! ይህ የወገን ወገን ነገር ምን ይረባል? እኛ የሰው ወይም የአንድ አስተማሪ ወገኖች ሳንሆን እንዲያው የክርስቶስ ነን» እያሉ አራተኛን ክፍል ፈጠሩ። (ም. 1፥11-16።) ክርስቲያኖቹ እርስ በርሳቸው ተለያይተው ነበር ማለት ነው።

እላይ የከተማውን አቀማመጥና አኳኋን ስንመረምር እንዳየነው ሁሉ የቆሮንቶስ ሰዎች እጅግ ሀብታሞች ነበሩ፤ ሀብትም ሲበዛ ኃጢአት ብዙ ጊዜ ይበዛልና ቆሮንቶስ ስለ ኃጢአቱ ብዛት በተለይም ይገኝበት ስለ ነበረው ሴሰኝነት፥ በዓለም ሁሉ ዘንድ ታውቆአል። ሴሰኝነትም በሃይማኖታቸው ተደግፎአል፤ ስለምን? ቢሉ አፍሮዲቴ የተባለች አምላካቸውን የሚያመልኩ ሴቶች ሰውነታቸውን ለአምላኪቱ ካህናት ይሰጡ ነበርና በቆሮንቶስ ክተማ ለአፍሮዲቴ የተቀደሱ 1 ሺህ ሴት አዳሪዎች (ሸርሙጣዎች) ነበሩ። ክርስቲያኖች በእንዲህ ያለ ክተማ በእንዲህም ያለ ኃጢአት መካከል ሲኖሩ ከክተማው ርኩሰትና ከክተማው ልማድ መለየት አለቸጋሪ ሆኖባቸዋልና በዚያ ርኩሰትና በዚያ ልማድ እንደ ተነኩ እናገኛለን። ለምሳሌ በመካከላቸው ዝሙት ተገኘ በፍርድ ቤቶችም መከራከርን ለምደዋል። (ም. 5፥1፡10። ም. 6፥1።)

ይህ ብቻ አልበቃቸውም በስብሰባቸውና በሥርዓታቸው ጊዜ ጥፋት ደግሞ አጠፉ። ከቁርባን በፊት በተደረገው ማኅበራቸው ቅለትና ለካር ጠብም ተለመደ። ወደ ቁርባን ሲገቡ መንፈሳቸው የተገባ ሳይሆን ቁርቶ ምሥጢሩን ሳይለዩ ጎብስቱንና ጽዋውን እንደ ተራ መብልና መጠጥ አድርገው ይበሉትና ይጠጡት ነበር። (ም. 11፥20-34።) ሴቶች ተገቢውን የዋህነት ሳያሳዩ ሳይከናነቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይገቡ ነበር። (ም.

11፥3-14።) ገብተውም ወንዶቹን ደፍረው ይናገሩ ነበር። (ም. 14።34-38።) ይህ ብቻ ሳይሆን ከክርስቲያኖቹ እንኳ ስዎች ተነሥተው፡- «ትንሣኤ ሙታን የለም» እያሉ የሐሰትን ትምህርት ያስተምሩ ነበር። (ም. 15፥12)።

ይህ ሁሉ ይሁን እንጂ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጉድለታቸውን ሳይመለከቱ በጥበባቸውና በነፃነታቸው በተሰጣቸውም መንፈሳዊ ስጦታ ተመክተው ሲፎካከሩ ተገኙ። (ም. 8፥1፡2። ም. 4፥8-10። ም. 6፥12። ም. 10፥ 23። ም. 12፥ 1፡20-31።) ግሪኮቹ የፍልስፍናን ክርክር ከመጠን በላይ አክብረው በዚህ ነገር እውቀታቸውንና ጥበባቸውን ለማሳየት እንደ ወደዱት ምሳሌ ክርስቲያኖች «የክርስቶስ ነገር እኮ ጥበብ ነው» እያሉ ይመኩ ነበር። (ም. 1፥17-ም. 2፥16።) አይሁድ ደግሞ በአሪት ሕግ አስራት ታስረው ሲኖሩ ክርስቲያኖች አርነትን አግኝተው ነበርና በነፃነታቸው ተመኩ። (ም. 6፥12-13።) በዚህ ምክንያት ሁሉ ኩራት አደረባቸው።

አንግዲህ በቆሮንቶስ የነበሩ የክርስቲያኖች ሁኔታ ባጭሩ ስንገልጠው ክዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው። ክርስቲያኖቹ ዳግመኛ የተወለዱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተቀደሱት እውነተኞች ክርስቲያኖች ቢሆኑም ያላደጉት ሕፃናት ሥጋውያንም ነበር። (ም. 3፥1-3።) እንደዚህም በመሆን የዛሬ የብዙ ክርስቲያኖች ምሳሌ ለመሆን በቁ። በዓለም ውስጥ በመኖራቸው ምክንያት ልዩ የሆነ ብዙ ችግር እንደ ገጠማቸው የታወቀ ሲሆን ለራሳቸውና ለማኅበራቸው አስፈላጊ ጥንቃቄ አላደረጉምና ልዩ ልዩ ጉድለትና ጥፋት ተገኝባቸው። በዚህም ደግሞ እነርሱ ብዙዎቹን የዛሬ ክርስቲያኖችን መስለዋል።

4፤ ወደ ቆሮንቶስ የተላከ የመልእክቱ አጻጻፍ።

ሀ/ ሁኔታው። መልእክቱ የተጻፈ በኤፌሶን ከተማ ነው። ጳውሎስ ከቆሮንቶስ በተሰናበት ጊዜ ወደ ኤፌሶን እንደ ሄደ ክዚያም አልፎ ወደ አንጾኪያ እንደ መጣ ከዚህ በፊት አይተናል። (የሐዋ. 18፥19-22።) በአንጾኪያ አያሌ ቀኖች ከተቀመጠ በኋላ እንደገና 3ኛ ጊዜ ወጥቶ በገላትያና በፍርግያ አገሮች የተገኙትን ክርስቲያኖች ለማጽናት ሄደ፥ ዞሮም ወደ ኤፌሶን መጣ በኤፌሶንም ሁለት ዓመት ተቀመጠ። (የሐዋ. 18፥ 23። 19፥1፡10።) እዚያ ሳለ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ወረቀት ደረሰው። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለ ልዩ ልዩ ነገር፥ በችግር ጊዜ ስለ መጋባት፥ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብላት፥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች፥ ለቅዱሳን ስለሚዋጣ ገንዘብ፥ ሊጠይቁት ወድደው ጽፈውለት ነበር። ወረቀቱ ገና ሳይደርሰው በፊት ጳውሎስ ቀሎዔ ክምትባለዋ ሌት አሽከሮች በኩል በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለሚደረገው ክርክር ሰምቶ ነበር። (ም. 1፥11።) እንደዚህም ዝሙት እንዳለባቸውና በቁርባን ሰዓት ምንና ምን ነገር ይደረግ እንደ ነበር ሰምቶአል። (ም. 5፥1። 11፥18-21።) ወረቀታቸው እንደ ደረሰው አስቀድሞ ጢሞቴዎስን በመቄዶንያ በኩል ሰደደላቸው። (የሐዋ. 19፥22። 1 ቆሮ. 4፥17፤ 16፥10።) ክዚያም በኋላ ደግሞ ስለ ሰማባቸው ወሬዎች ዘለፋንና ምክርን፥ ስለ ጠየቁት ጥያቄዎች መልስን፥ ስለ ትንሣኤ ሙታን ተጨማሪ ትምህርትንም ለመስጠት ተቀምጦ መልእክት ጻፈላቸው። የጻፈውም በ55 ወይም በ56 ዓ.ም. ይሆናል።

ለ/ አላቡ። አዲስ የተሰበሰበ (የተቋቋመ) ቤተ ክርስቲያን ወይም የክርስቲያኖች ማኅበር በዓለማውያን ወይም በእረመኔዎች ተከብቦ ሲገኝ ብዙ ችግር እንደሚገጥመው፥ አዲስ በመሆኑ ምክንያት ልዩ ልዩ ጉድለት እንደሚታይበት የታወቅ ነው። ይህ መልእክት ስለዚህ ችግርና ስለዚህ ጉድለት ይናገራል። ስለ ስውና ስለ እግዚአብሔር ጥበብ፥ ስለ ሰው መብት፥ ስለ ትንሣኤ ሙታን፥ እነዚህን ስለሚመሳስሉት ሌሎች ብዙ ነገሮች ተናግሮ ከፍ ያለ ዶክትሪን ቢኖርበትም መልእክቱ በተለይ አደራረግን ያስተምራል። መልእክቱ አዲስ የተሰበሰበ ቤተ ክርስቲያን ራሱን እንዴት እንደሚያደራጅ ይነገረናል፤ ከስው ጥበብና ከመለያየት ከዝሙትም በስብሰባ ሰዓት ከሚደረጉትም ጥፋቶች ያስጠነቅቀናል፤ በዚያም ቀን ዛሬም ክርስቲያኖችን ስለሚገጥማቸው ስለ ብዙ ነገሮች ምክርን ይሰጣል።

ሐ/ መተንተኑ። የመልእክቱ አሳብ ይህ ነውና በመተንተኑ ውስጥ ሁለት የተፈራረቁትን ነገሮች እናገኛለን። እነዚህም

1ኛ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ተደረገው ጥፋት የሐዋርያው መቀሳ።

2ኛ፤ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፉት ወረቀት ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የጳውሎስ መልስ ናቸው።

1ኛ ክፍል። ወቀሳ። ም. 1-6። ም. 1-4 ስለ ክርክር።

ም. 5 ስለ ዝሙት።

ም. 6 ስለ ሙግት።

2ኛ ክፍል። መልስ። ም. 7-10። ም. 7 ስለ መጋባት።

ም. 8-10 ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ።

3ኛ ክፍል። ወቀሳ። ም. 11። ስለ ሴቶች መሸፈኛና ስለ ጌታ እራት።

4ኛ ክፍል። መልስ። ም. 12-14 ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች።

5ኛ ክፍል። ወቀሳ። ም. 15። ስለ ትንሣኤ ሙታን።

6ኛ ክፍል። መልስ። ም. 16። ለቅዱሳን ገንዘብን ስለ ማዋጣትና ስለ አጵሎስ መምጣት።

መ/ ጥቅሙ የመልእክቱን ትርጓሜ አሁን ልንጀምር ነን ከመጀመራችንም በፊት ይህን የቆሮንቶስን መልእክት በማንበብ ምን ጥቅም እንደምናገኝ እናስብ። መልእክቱ የተጻፈ ከዛሬ ብዙ ዘመን በፊት ነው የተጻፈላቸውም ለጴሮ ለሌላም አገር ሰዎች ነው። ይህ ሲሆን ለዛሬ ዘመን ለዛሬ ስዎችም ምን ጥቅም አለው? እኔስ፥ ማንበብ ያስፈልገኛልን? ለዚህስ ላዲስ ዘመን የሚሆንን ትምህርት እገኝበታለሁን? እስቲ እንይ። ስመሆኑ የዛሬ ጥያቄ ምን ዓይነት ጥያቄ ነው? እንደሚከተለው አይደለምን?

1፤ ሰውን ስንመለከት ስናመዛዝንም እውነተኞች ክርስቲያናች በስብስባችንም ያሉ በተለይ የሚመጡበት ክዝቅተኛና ከድሀ የሰው ክፍል አይደለምን? ይህ ስለ ምንድር ነው?

2፤ የክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት ያለው ከሆነ ብዙዎች አዋቂዎችና ፕሮፌሰሮች መመህራንም፥ ብዙዎች ፕሬዚዳንቶችና ሚኒስትሮች ክበርቴዎችም፥ እውነተኞች ክርስቲያናች ያልሆኑበት በምን ምክንያት ነው?

3፤ ለሥራችን በሰማያት ዋጋ አለን፥ ያለ እንደ ሆነ ምን ዋጋ ነው?

4፤ የሚሻለው ሚስት ማግባት ነውን? ወይስ አለማግባት?

5፤ ለክርስቲያን የተፈቀደው ያልተፈቀደውም እንዴት ይታወቃል?

6፤ ቁርባን ልንቀበልም የሚገባን ሲሆን እውነተኛ አሳቡ ምንድር ነው? አቀባበሉስ እንዴት ነው?

7፤ በጥንት ልማድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ግዕዝ ነበረ። አሁን ግን በተራ ሕዝብ ዘንድ ያልታወቀ ስለሆነ በእግርኛ ቢለወጥ አይሻልምን?

8፤ ከሞት በኋላ ነገር በእርግጥ አለን? በዚያስ ጊዜ እንደምን እንሆናለን?

9፤ ስለ ገንዘባችንስ? ለቤተ ክርስቲያን መስጠት በእውነቱ ይገባናልን?

ይህ ነገር ሁሉ የዛሬ ዘመናችንና እኛን የሚነካ አይደለምን? ለዚህ ጥያቄ ሁሉ ለሌላም ብዙ ነገር በዚህ መልእክት ውስጥ መልሱ ይገኛል፥ ያም የጥርጥር መልስ ሳይሆን የሚታመንበት፥ በለው የተሰጠ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠ መልስ ነው። ስለዚህ መልእክቱን አስተውለን እናንብብ እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ሁሉ የሚለውን እንይ።

ትርጓሜ።

መጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች።

ምዕራፍ 1።

1፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ

2፤ ሊሆን የተጠራ ጳውሎስ ወንድሙም ሶስቴንስ፥ በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፥ የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየሥፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት፤

3፤ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

4፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ስላመናችሁ በተሰጣችሁ በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ሁልጊዜ ስለ እናንተ አምላክን 5፤6፤ እመሰግናለሁ፤ ለክርስቶስ መመስከሬ በእናንተ ዘንድ እንደ ጸና በነገር ሁሉ በቃልም ሁሉ በእውቀትም ሁሉ በእርሱ 7፤ ባለ ጠጎች እንድትሆኑ ተደርጋችኋልና። እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ስትጠባበቁ እንድ 8፤ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም፤ እርሱም ደግሞ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ያለ ነቀፋ እንድትሆኑ እስከ ፍፃሜ 9፤ ድረስ ያጸናችኋል። ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርሶትስ ጎብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው።

10፤ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በእንድ ልብና በእንድ አላብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን 11፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ። ወንድሞቼ ሆይ ብመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ 12፤ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና። ይህንም አላለሁ፡- እያንዳንዳችሁ፡- እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ 13፤ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰቀለን? ወይስ 14፤15፤ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን? በስሜ እንደ ተጠመቃችሁ ማንም እንዳይል ከቀርስጶስና ከጋይዮስ በቀር ከእናንተ አንድን እንኳ ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

16፤ የእስጢፋናስንም ቤተ ሰዎች ደግሞ አጥምቄአለሁ፤ ጨምሬ 17፤ ሌላ አጥምቄ እንደ ሆነ አላውቅም። ለማጥመቅ ክርስቶስ አላከኝምና፥ ወንጌልን ልሰብክ እንጂ፤ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም።

18፤ የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን 19፤ ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና። የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ 20፤ ተጽፎአልና። ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚህች ዓለም መርማሪስ የት አለ?

እግዚአብሔር የዚህችን ዓለም [21]፤ ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን? በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፥ በስብክት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር [22]፤ በጎ ፈቃድ ሆኖአልና። መቼም አይሁድ ምልክትን [23]፤ ይለምናሉ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፥ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም [24]፤ ሞኝነት ነው ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ [25]፤ የሆነው ክርስቶስ ነው። ክሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና፥ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና።

[26]፤ ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁን ተመልከቱ፤ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች ኃይለኞች የሆኑ ብዙዎች [27]፤ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ [28]፤ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም [29]፤ ነገር መረጠ፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት [30፤31]፤ እንዳይመካ። ነገር ግን፡- የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።

* * *
* * * * * *

1ኛ ክፍል።

(ም. 1-ም.6።) ስለ ተደረገው ጥፋት ወቀሳ።

ም. 1-ም. 4፤ ስለ ክርክር።

ም. 5፤ ስለ ዝሙት።

ም. 6፤ ስለ ሙግት።

ምዕራፍ አንድ።

ቁ. 1-3። መልእክቱን የሚጽፍ ጳውሎስ ነው እኮ! «ጳውሎስ!» ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይህ ስም ምን ያለ ስሜት ይሰጣል! ጳውሎስ በክርስቶስ የወለዳቸው አባታቸው ነው። (ም. 4 ቁ. 15።) ዓመት ተመንፈቅ በክተማቸው ተቀምጦ ነበር፥ በዚያን ጊዜም ለክርስቶስ ሲያጫቸው (2 ቆሮ. 11፥ 2) አመላለሱ ምን ያለ ያማረ ነበረ! በመካከላቸውም የነበረው ፍቅር እንደምን የጋለ ነበረ! ይሁን እንጂ፥ በፍቅር የሚመክራቸው አባታቸው ብቻ አይደለም። መጥምቁ ዮሐንስ ለክርስቶስ ሊመሰክር ከእግዚአብሔር እንደ ተላከ (ዮሐ. 1፤6) እንዲሁ ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ለመሆን በእግዚአብሔር የተጠራ ነበረ። እንግዲህ መልእክቱ የሚመጣላቸው በአባት ከእግዚአብሔር በተጠራም በሐዋርያ ስም ሥልጣን ነው። በዚያም ስም ብቻ አልነበረም ሶስቴንስ የተባለው በሐዋ. 18፤17 የተነገረለት የሆነ እንደ ሆነ መልእክቱ በእጥፍ ሥልጣን መጥቶአል፤ ስለምን? ቢሉ፥ ሶስቴንስ እንግዳ አይደለም የራሳቸው ነው፥ የምኩራባቸው አለቃ የነበረ ነው። በእውነት ይህ መልእክት በሥልጣን መጥቶአል ሊያደምጡትና ሊታዘዙለት ይገባቸዋል።

ጳውሎስና ሶስቴንስ የሚጽፉት «ለቤተ ክርስቲያን» ነው። ቤተ ክርስቲያን ሲል ሕንፃ ማለቱ ነውን? አይደለም! ቤተ ክርስቲያን ሲል የክርስቲያን ጉባኤ ወይም የክርስቲያኖች ማኅበር ማለቱ ነው። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ያሉትን «በክርስቶስ ኢየሱስ የተቀደሱት፥ ቁዱሳን ለመሆን የተጠሩት» ይላቸዋል። ቤተ ክርስቲያን የእነዚህ ዓይነት ሰዎች ጉባዔ ነው።

ሐዋርያው እነዚህን ሰዎች ቅዱሳን ይላቸዋል፤ ሆኖም በኋላ እንደምናየው ሁሉ በእውነቱ እጅግ የተቀደሱ ሆነው አልተገኙም። ክርክር፥ ዝሙት፥ እንደ ዓለማውያንም መሟገት ሲኖርባቸው እካሄዳቸው የቅድስና እካሄድ የነበረ አይመስልም። እንግዲያስ ስለምን ቅዱሳን ተባሉ? ቅዱሳን የተባሉበት ለክርስቶስ ኢየሱስ የተቀደሱ (ለክርስቶስ ኢየሱስ የተለዩ) በመሆናቸው ነው። ጳውሎስ ሐዋርያ ሊሆን በእግዚአብሔር የተጠራ እንደ ነበረ እንዲሁ እነዚህ ሰዎች ለክርስቶስ የተለዩ ይሆኑ ዘንድ በእግዚአብሔር ተጠርተዋል። ቅዱሳን የሆኑበት መልካም ነገር በራሳቸው ስለ ተገኘ አይደለም። መልካም ነገር አልተገኘባቸውም፥ ጳውሎስም በዚህ መልእክት ውስጥ በግይገባ እካሄዳቸው በብዙ ይወቅላቸዋል። እንግዲያስ ለምን ቅዱሳን ተባሉ? ለክርስቶስ የተቀደሱ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር ጠርቶአቸው ስለ ነበረ ነዋ! (ዮሐ. 6፥44። 15፥ 16። ሮሜ. 8፥30።) እነርሱም ጥሪውን ሰምተው ተቀብለው ክርስቲያኖች ሆነው ስለ ነበረ ነው። የክርስቶስ

የሆኑት ሁሉ «ቅዱሳን» ተባሉ። ቅድስና ተቆጥሮላቸዋልና አሁን በቅድስና እየተራመዱ በእውነት ቅዱሳን እንዲሆኑ ተጠርተዋል።

መልእክቱ የተጻፈ በቆሮንቶስ ለተገኙት ቅዱሳን ነው ሆኖም ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን «የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ለሚጠሩት ሁሉ» ነው። ጳውሎስ ለእነዚያም ለእኛም ሲጽፍ ጸጋና ሰላምን ይመኝላቸዋል ይመኝልናል።

ጸጋ ሥር ነው፤ የጸጋም ፍሬ ሰላም ነው። ጸጋ መነሻ ነው ሰላምም መድረሻ ነው። ጸጋ ክሌለ ሰላም የለም። ጸጋ የእግዚአብሔር የእባታችን ነው። ዙፋኑ ቀድሞ የቁጣና የፍርድ ዙፋን ነበረ፤ አሁን ግን የጸጋ ሆኖአል። (ዕብራ. 4፡ 17።) ከቁጣና ከፍርድ ወደ ጸጋ የተለወጠበት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ገብቶ አስታርቆአቸዋልና እግዚአብሔር አሁን ሰውን በአባትነት ዓይን ይመለከተዋል፥ ዙፋኑም የጸጋ ዙፋን ሆኖአል። ጸጋንና ሰላምን ሰጭ እግዚአብሔር አብ ነው፤ ያንም ሸጋና ሰላም ወደ እኛ ያደረሰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እነዚህ በረከቶች የሚገኙበት ከዚህ ብቻ ነው። ኢየሱስ በምን ደረጃ ላይ እንደ ሆነ ከዚህ ነገር ደግሞ እናስተውል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «ቅዱሳን» የተባለው ቃል እዚህ በ1 ቆሮ 1፤2:2 ላይ እንደዚህም ደግሞ በአዲስ ኪዳን በሌላ ሥፍራ ሁሉ ሲገኝ «ክርስቲያኖች» ማለት እንደ ሆነ እናስተውል። የሐዋ. 9፥13:32:51። ሮሜ 12፥13፥15:25፥26። 2 ቆሮ. 1፥1። ኤፌ 5፥3። 1 ጢሞ. 5፥10።) ከክርስቲያኖች የተሰየ ክፍል መሆናቸው ወይም ቅድስናቸው ከሌሎች ሰዎች የበለጠ መሆኑ አይደለም። በአዲስ ኪዳን ሁሉ «ቅዱሳን» የተባለ ቃል «ክርስቲያኖች» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። የቆሮንቶስ «ቅዱሳን» እጅግ የተቀደሱ አልነበሩም፤ ቢሆንም በእምነታቸው ለክርስቶስ የተለዩ ነበሩና «ቅዱሳን» ናቸው። (መዝ. 49፥5 እና ራእ. 14፥12 ደግሞ ማስረጃን ይስጣሉ።) በክርስቶስ ያመንን ሁላችን ቅዱሳን ነን።

ለ. «የተጠራ፤ የተጠሩ።» እነዚህ ቃሎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግመው እንደ ተነገሩ እናስተውል። (ቁ. 1:2:9:24:26:27።) ጳውሎስ ሐዋርያ ለመሆን ተጠራ፤ የቆሮንቶስ ሰዎች ቅዱሳን ለመሆን ተጠሩ፤ ስውም ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት ተጠራ። ሰው ክርስቲያን ወይም ሐዋርያ የሚሆነው ከራሱ አሳብ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጥሪ እንደሆነ በዚህ እንረዳለን። ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ ወንዶችንና ሴቶችን መረጠ። እነዚህ ሰዎች መመረጣቸውን አያውቁም ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ከዕለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር ይጠራቸዋል እነርሱም ጥሪውን ሰምተው ለእርሱ ይሆናሉ። (ኤፌ 1፥4። 2 ተሲ 2፥13። 1 ጴጥ. 1፥1:2። ራእ. 7፥9።) ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ ስመሆን ሲያስብ ተጠራ፥ (የሐዋ. 9፥ 15) ሐዋርያም ሆነ። (የሐዋ. 9፥1-16።) የቆሮንቶስ ሰዎች ነጋዴዎች ስመሆን አስቡ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ሐዋርያ መጥቶ ወንጌልን እሰማቸው፥ ቅዱሳንም ሆኑ። (የሐዋ. 18፥ 9-11።) ስው በገዛ መንገዱ ይሄዳል፤ እግዚአብሔር ይጠራዋል፥ ሕይወቱም በሙሉ ይለውጣል ያን የተጠራበትንም ይሆናል። ክርስቲያኖች «የተጠሩት» ናቸውና (ቁ. 24:26፤ ም. 7፥17) በጠራቸው በእግዚአብሔር ይመኩ እንጂ

ክርስቲያኖች በመሆናቸው የሚመኩበት ነገር እንደሌላቸው ያስተውሉ። (ዮሐ 15፥16። 2 ቆሮ. 5፥18።)

ሐ. በብሉይ ኪዳን፥ በኢዮኤል 2፥ 32 ላይ « የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» ተባለ። ይህ ጥቅስ በሮሜ 1፥13 ላይ ሲጠቀስ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተተረጎመ እናያለን፥ እዚህም ደግሞ በቁ. 2 ላይ ስዎች የሚጠሩት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም መሆኑን እንገነዘባለን። እንደዚሁም ደግሞ የሐዋ. 9፥14፤22፥ 16፤ 2ጢሞ.2:22 ተመልከት። ከዚህ ነገር የምንማራቸው 2 ነገሮች አሉ።

1ኛ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው። ፍጹም እምላክ መሆኑ ተረጋግጦአል ማለት ነው።

2ኛ፤ ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን ስም የሚጠሩ ናቸውና ያን ስም የማይጠሩ በእውነት ክርስቲያኖች አይደሉም።

ቁ. 4-9። እነዚህ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ስላመኑ ታላቅ በረከትን ተቀብለው ነበር። «በነገር ሁሉ በቃልም ሁሉ በእውቀትም ሁሉ በእርሱ ባለጠጎች እንድትሆኑ ተደርጋችኋል።» ሆኖም ጳውሎስ ጸጋ ተቀባዮች የሆኑትን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ሳያመሰግን ጸገ ስጭውን እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል። ስለምን? ቢሉ፥ እነርሱ እንዲህ እንዲሆኑ «ተደርገዋል» እንጂ እነርሱ ይህን ሁሉ በራሳቸው ኃይል አልሆኑም። በያዕ. 1፥16:17 ላይ እንደ ተጻፈ ነው። ቅዱስ ያዕቆብ «በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ ከብርሃናት አለቃ ይወርዳሉ» ይላል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የተቀበሉት ባለጠግነት እነርሱ ለራሳቸው ያበጁት ሳይሆን እግዚአብሔር በክርስቶስ ላመኑት የሚሰጠው ነው። ቢሆንም በረከቱ የሚያስመሰግን ነው። አነዚህ የቆሮንቶስ ስዎች ወንጌልን ለመናገርና ለማስተዋል ሁሉንም ለማወቅ ችሎታን አግኝተው በረቱ። እንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አልጎደለባቸውም። እግዚአብሔር በእውነት ባለጠጎች እድርጎአቸው ነበር። (ቁ. 4:5።) ይሁን እንጂ፥ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ለተሰጣቸው ጸጋ እግዚአብሔርን በማመስገን ፋንታ ከዚህ በመናገራቸውና በማስተዋላቸው በእውቀታቸውም ችሎታ ተመክተዋልና (ም. 2፥1፤ ም. 8፥1) ጳውሎስ ወደ ፊት በመልእክቱ ይገሥጻቸዋል። ከሚገባ በላይ ራሳቸውን ተመልከተዋልና በእነዚህ ቁጥሮች ላይ እግዚአብሔርንና ጸጋውን ያልቃል። ጸጋውን የሰጠ እግዚአብሔር ነው፥ (ቁ. 4) ባለጠጎች የሆኑ በክርስቶስ ኢየሱስ ነው፥ (ቁ. 5) የሚያጸናቸውም እግዚአብሔር ነው። (ቁ. 8:9።)

ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ መጥቶ ስለ ክርስቶስ መስክሮ ነበር፥ የተሰጣቸውም ጸጋ ምስክርነቱን እንደ ተቀበሉ አረጋግጦአል። ምስክርነቱን ካልተቀበሉ በክርስቶስም ካላመኑ ጸጋው ባልተሰጣቸውም ነበር። ተስጥቶአቸዋልና ቃሉን መቀበላቸው ተረጋግጦአል። ለዚህ የሚሆን ዋና ምልክቱ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ መጠባበቃቸው ነው። የእርሱ ባይሆኑ ኖሮ ባልተጠባበቁትም ነበር። ይጠባበቁት ነበርና የእርሱ መሆናቸው ተረጋግጦአል። ይህንም ጸጋ የሰጣቸው እግዚአብሔር በዚያው በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ቀን ያለ ነቀፋ እንዲሆኑ እስከ ፍጻሜ ድረስ ያጸናቸዋል። እግዚአብሔር አንድን ነገር ሲወጥን በመካከሉ ላይ አይተወውም ማለት ነው። የጀመረውን ይፈጽማል። (ፊልጵ.

1፥6። ሮሜ 8፥29፡30።))ወደ ልጁ ጎብረት ጠርቶአቸዋልና ወደዚያ በታማኝነት ሁሉ ያደርሳቸዋል። (ቁ. 6-9።።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «በክርስቶስ ባለጠጎች እንድትሆኑ ተደርጋችኋል።» (ቁ.5፡6።) ይህ እውነት ነው። ክርስቶስን የሚቀበል ሰው ታላቅ በረከትን ያገኛል። መጀመሪያ ክርስቶስን የተቀበለ ሰው ልጅነትን ያገኛል ከልጅነትም ጋር ጽድቅንና የዘላለምን ሕይወት ያገኛል። (ዮሐ. 1፥ 12፡13። ሮሜ 3፥21፡22። 1 ዮሐ 5፥13።) ይሁን እንጂ ይህ ብቻ አይደለም። ክርስቶስን መቀበል ለዛሬ ሕይወታችን ደግሞ ታላቅ በረከትን ይስጣል። እንደ ተዘጋ የውሃ ቧምቧ ነገር ነው። ክርስቶስን ሳንቀበል ወይም በእርሱ ላናምን በፊት የእግዚአብሔር የበረከቱ መንገድ ተዘግቶአልና ሕይወታችን ደረቅ ነው ልምላሜም የለውም። ክርስቶስን ስንቀበል ግን ያ የበረከት ቧምቧ ይከፈታልና ውሃው ይፈላል፥ ሕይወታችንም ሁሉ ይለመልማል። (ዮሐ. 7,7-39።) ምክንያቱም በአዳም ኃጢአት ምክንያት የሞተው የሰው መንፈስ (ዘፍጥ. 2፥11) በክርስቶስ ይድናልና (ሕያው ይሆንልናልና።) 1 ቆሮ. 15፥22። በዚያን ጊዜ ወንጌልን ለመናገርና ለማስተዋል ሁሉንም ለማወቅ አንበቃልን።።በዚያን ጊዜ ድሆች የነበርን ባለጠጎች ሕፃናት የነበርን ሙሉአን እንሆናለን። ደረቅ ሕይወታችንም ይለመልማል። (ቁ.5፡5-7። ቆላ.2፡10።)

ለ/ «የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ።» (ቁ.7።) የክርስቶስ መምጣት እንደ ሌላ ሰው ሁሉ መምጣት እይሆንምና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ «መገለጥ» ተባለ። (ሉቃ. 17፥30። 2 ተሰ.1፥6፡7። 1 ዮሐ 2፥28፥ 3፥2።) እንደ ሌላ ሰው ሁሉ መምጣት ላይሆን የመጋረጃ መወገድ ይሆናል። የተሠራ ሐውልት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እስከሚገልጡበት ቀን ድረስ በመጋረጃ ተሸፍኖ እንደሚኖር ሁሉ እንዲሁ አሁን ተሸፍኖ የሚኖረው ክርስቶስ በዚያ ቀን ይገለጣል። ተገልጦም ግን እንደ ሆነ፥ ለሰው ልጆችም ምን እንደ ሆነ ይታያል። እርሱ ላይገለጥ በፊት በእምነት ዓይን ብቻ ያየነው በዚያ ቀን በሥጋ ዓይን እናየዋለን። በመከከላችን ያለው መጋረጃ ይወገዳል ክርስቶስም ይገለጥልናል። (1 ቆሮ. 3፥12። 1 ዮሐ 3፥2።) ይህ መገለጡን መጠባበቅ በያገሩ ሁሉ የሙሉ ክርስቲያን ምልክት ነውና በአንዳንድ አገር ዛሬ ሲጠፋ ያሳዝናል፥ የዚያም አገር ቤተ ክርስቲያን ጤና ያጠራጥራል።

ሐ «የኢየሱስ ክርስቶስ ጎብረት።» (ቁ.9።) እኛ ክርስቲያኖች «ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎበረት» በእግዚአብሔር ተጠራን። ጳውሎስ ሐዋርያ ሲሆን እንደ ተጠራ፥ የቆሮንቶስም ሰዎች እኛም ቅዱሳን ለመሆን እንደ ተጠራን፥ እንዲሁ ደግሞ እኛ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎብረት በእኩል ጥሪ ተጠራን። ይህ ምንኛ ታላቅ ነገር ነው! ክቀትር በኋላ፥ ነፋስ በሚነፍስበት ጊዜ አዳምና እግዚአብሔር ይጨዋወቱ እንደ ነበር፥ (ዘፍጥ. 3፥8) ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንደ አደረገ፥ (ዘፍጥ.5፥24) እንዲሁ እኛ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎብረት ዘሬ ተጠራን። ሐዋርያት ይህን ጎብረት እፐኑ (1 ዮሐ 1፥3) እኛም እንድናገኘው እግዚአብሔር ጠርቶናል። ሰው ወዳጁን እንደሚያውቀው ከወዳጁም ጋር በጎብረት እንደሚመላለስ እኛ ክርስቶስን አናውቀዋለንን? ከእርሱም ጋር በጎብረት እንመላለሳለንን? እግዚአብሔር ወደዚህ

ጠርቶናል። ወደዚህ ጠርቶናልና እኛ በቅዱስ ኑሮ ሁሉ እንደምን ልንሆን ይገባናል? ያለ ነቀፋ እንድንሆን የምንጸና በክርስቶስ ጎብረት ለንኖር ነው። እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ወደ ክርስቶስ ጎብረት ጠርቶናልና አይጥለንም አይተወንም። (ሮሜ 11፥29። 2 ቆሮ. 1፥ 18-20። ሮሜ 5፥10።)

ቁ. 11-17። ሁላቸውም ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎብረት ከተጠሩ እርስ በርላቸው በጎብረት ተባብረው እንዲኖሩ ያስፈልግ ነበር፥ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ግን በመተባበር ፋንታ ተለያዩ። ክርስቶስ «እርስ በርለዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ ትጠፋለች፥ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም» ብሎ የተናገረውን ቃል (ማቴ.11፥25) ረስተው እርስ በርላቸው ተከፋፍለዋል። ስለዚህ ጳውሎስ «ወንድሞች» እያላቸው በክርስቶስ ስም ሥልጣን ይለምናቸዋል። እኩሌቶቹ ላስተማሩእችውና ላጠመቁእችው አድልተው «እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ የጴጥሮስ ነኝ» አሉ። ሌሎች ደግሞ ከእነርሱ ሁሉ ተለይተው «እኛ የክርስቶስ ነን» አሉ። እነዚህ አስተማሪዎቻቸው ሌላ ሌላ ወንጌልን ወይም ሌላ ሌላ ዶክትሪንን አንዳስተማሩ አይደለም። ትምህርታቸው ሁሉ አንድ ሆነ። ነገር ግን ሲያስተምሩ የማስተማራቸው ዘዴ ወይም ስጦታ ልዩ ልዩ ነበረ። በዚህም ምክንያት አንዱ ሰው ይህም አስተማሪ ሁለተኛውም ያን ወድዶአል። ለምሳሌ፥ አጵሎስ አፈ ጮሌ እንደ ሆነ እናውቃለን፤ እርሱ ሲያስተምር «በጽኑ» ያስረዳ ነበር። (የሐዋ. 18፥22-28።። ጳውሎስ ግን ስውን በንግግሩ ለማስደስት ሳይፈልግ ንግግሩንም ሳያሳምር ቀጥተኛ የሆነ የክርስቶስ የመስቀልን ነገር ብቻ ለመናገር እንደ ቆረጠና በንግግሩ የተናቀ እንደነበረ እናነባለን። እንደ አጵሎስ ሆኖ «በጽኑ» ላያስረዳ «በድካምና በፍርሃት በብዙም መንቀጥቀጥ» ያስተምር ነበር። (ገላ. 1፥ 10። 1 ቆሮ. 2፥2-4። 2 ቆሮ. 10፥10።) በዚህም ምክንያት አንዳንዶች ስሚዎች ጳውሎስን ሲወዱ ሌሎች እጵሎስን ወድደዋል። አንደዚህም ደግሞ ወደ አሪት ሕግ ያዘነበለውን ጴጥሮስን የሚወዱ ነበሩ። ስለዚህ በማኅበሩ ውስጥ ትንሽ ያለመስማማት ነገር ሆነ ይህም አለመስማማት ጎብረታቸውን አጠፋ። ሁላቸው የክርስቶስ አልነበሩምን? ክርስቶስ ተከፍሎአል እንዴ? በእርሱም ውስጥ ክፍል ክፍል አለን? በፍጹም የለም! ገላ. 3፥28።) ሁላቸው የክርስቶስ ናቸው እንጂ የጳውሎስ ወይም የአጵሎስ ወይም የጴጥሮስ ክቶ እይደሉም። ሆኖም «የጳውሎስ ነን» አሉ። እንደምን የጳውሎስ ሆኑ? በስሙ ተጠምቀዋልን? ስእረ አልተጠመቁም! ሁላቸው በክርስቶስ ስም ተጠምቀዋል እንጂ። (የሐዋ. 2፥38፤8፥16፤ 10፥48።) ወይም ደግሞ ወገን አለው እንዲባል ጳውሎስ ብዙ ሰውን አጥምቆ ኖሮአልን? አረ አላጠመቀም! ያጠመቃቸው እጅግ ጥቂቶች ነበሩ፤ ምክንያቱም ጥምቀት አስፈላጊ አለመሆኑ ሳይሆን ጌታ በተለይ ወንጌልን ለመስበክ ልኮት ስለ ነበረ ነው። ይህም የጌታ ልማድ ነበር (ዮሐ. 4፥2፥) ሐዋርያት ይህን ልማድ የተከተሉት ይመስላል። የሐዋ.8፥48።)

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን።» (ቁ. 10።) ይህ የሚያስያይ ክርክር እንደምን ክፉ ነው! ክርስቲያንን ከክርስቲያን ያለያያል፥ ፍቅርን ያጠፋል፥ በጳሎተ ሃይማኖት ላይ «እነዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን» የተባለችውን ያደክማል። ሁላችንም፥ እነርሱም እኛም፥ የአንድ ጌታ የአንድም መድኅን

የክርስቶስ መሆናችንን እናስብ ከመለያየትም እንጠንቀቅ። (ዮሐ. 17፥ 20-23። ኤፌ. 4፥1-6። ሮሜ፡ 16፥17፡18።)

ሊ. «በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?» (ቁ. 13።) ሰው ሲጠመቅ በሰው ስም እንጂ በቤተ ክርስቲያን ስም እንዳይጠመቅ መገንዘብ ለሁላችን የሚገባ ነገር ነው። እንዳንድ ጊዜ «እገሌ በዚይይ ቤተ ክርስቲያን ተጠምቆአልና የዚያ ቤተ ክርስቲያን ማኅበርተኛ ነው» ይባላል። ይህም የስሕተት ንግግር ነው። ሰው በቤተ ክርስቲያን ስም ሳይጠመቅ በክርስቶስ ስም ይጠመቃልና ኅብረቱ (እንድነቱ፥ መተባበሩ) ከክርስቶስና ከሠራው ሥራ ጋር ነው እንጂ ከዚያች ቤተ ክርስቲያን ጋር አይደለም። በክርስቶስ ስም ተጠምቆአልና በክርቶስ ውስጥ ተጨምሮአል ከክርስቶስም ጋር ተባብሮአል። (ሮሜ 6፥3-11። ገላ. 3፥27።) እነዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች እንደሚገባው ሁሉ በክርስቶስ ስም ተጠምቀዋል እንጂ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስም ሆነ በጳውሎስም ስም ሆነ አልተጠመቁምና (ቁ.15) እንድነታቸው መተባበራቸውም ከክርስቶስ ጋር ነው። ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንድ እንሆን ዘንድ ሳንጠመቅ ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንጠመቃለን ማለት ነው። የምንጨምርበቱ ወደ ክርስቶስ ነው እንጂ ወደ እንዲት ምድራዊት ቤተ ክርስቲያን አይደለም።

ጳውሎስም በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ ስለ ጥምቀት ሁለተኛ አሳብ ያቀርባል። በቁ. 17 ላይ «ለማጥመቅ አልላከኝም ወንጌልን ልሰብክ እንጂ» ብሎ ጽፎአል፥ ይህንም በመጻፉ ጥምቀትን የናቀ ይመስላል። በእውነቱ ግን ጥምቀትን መናቁ አይደለም፥ የሚያደርገው ስብከትን ማሳቅ ነው እንጂ። ጥምቀት እንደ ስብከት ሆኖ አስፈላጊ ነው፤ ቢሆንም ከሁለቱ የሚቀድመውና የሚበልጠው ስብከት ነው። ስለምን? ቢሉ፥ ወንጌል ካልተሰበከ አማኝ የት ይገኛል? ጥምቀትም የአምነት ምልክትና ማኅተም ነውና እውነተኛ አማኝ ከሌለ የሚጠመቅ የለም። (ሮሜ፡ 4፥11፤ 10፥14።) በዚህ ምክንያት ከጥምቀት የወንጌል ስብከት ይበልጣል። እግዚአብሔርም ጳውሎስን ሲልክ ለመጀመሪያ ሥራ እንጂ ለሁለተኛ አልላከውም። ይህስ ሲሆን በአገራችን አንዳንድ ጊዜ እንደሚደረገው ሁሉ የሚያምኑበትን ያህል ወንጌልን ለሕዝብ ሳይሰብኩ በፊት በብዙ መቶ ወይም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን ሰዎች ሲያጠምቁ እንደ ስሕተት ሆኖ ይቆጠር የለምን? ከማጥመቅ የወንጌል ስብከት መቅደም ይገባል ማለት ነው። (ማር. 3፥14።)

ሐ. «በቃል ጥበብ አይደለም።» (ቁ. 17።) ይህ በእውነቱ ለዛሬ ለእኛም የሚሆን ትምህርት ነው። የተማሩት የግሪክ ሰዎች የፍልስፍናን ነገር ወድደዋል አከብረውማልና በጳውሎስ ዘመን የተገኙ አንዳንዶች የወንጌል እስተማሪዎች «ወንጌልን የጥበብ ነገር ካላስመሰልን አይሰሙንም» በማለት ነገሩን እያሻሻሉ ይናገሩ ነበር። ዛሬም እንደዚሁ ይደረጋል። መምህራን እውቀታቸውን ለመግለጥ ወድደው ወንጌልን ለሊቃውንት የሚሆነውን ነገር ብቻ ያደርጉታል፤ ሰውንም በጥበብ ለማሸነፍ እሰበው የመስቀልን ቃል አስቀርተው ደግ ኑሮን ብቻ ይሰብካሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግን እንደዚህ አላደረገም። የሰው እምነት በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ፈልጎ «ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደ ተሰቀለ» ሌላ ነገር እንዳይሰብክ ቆረጠ። (ም. 2፥2-5።) ይህስ ምነው ዛሬም በተደረገ!

ሁለተኛው ደግሞ፤ እኛ መመህራን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ስንተረጉም «በተጻፈ ቃል ላይ ብርሃንን እንጥላለን» ስንል የማይጠቅመውን ከዘይቤው የወጣ ትርጉም በመስጠት ቃሉን ወድ ማጨለምና ዘይቤውን በሜራቭ ወደ መጥፋት እንደርስ የለምን? እሰቀድሞ እረኞችን ለመላሰሉት የተሰበከውን ወንጌል (ሉቃ. 2፥8-12) እሰቸጋሪ የሊቃውንትን ነገር በማሰመሰላችን ከሕዝብ መስደን የግል ገንዘባችንን እድርገነው የለምን? ይህም ብቻ ላይሆን ከፍ ያለ የሊቃውንትን ነገር ስላደረግነው ሰው በትምህርት ቤት ገብቶ አሥር ዓመት ያህል ካልተማረ ለሕዝብ ወንጌልን ለማስተማር አይችልም እንላለን! ጥበብ እየፈለግን የክርስቶስን መሰቀል በሕዝባችን ዘንድ ከንቱ እንዲሆን ማድረጋችን እይደለምን? እረ! ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ስለ እኛ ብሎ ስለ መሰቀሉም እንሰበከና የጳውሎስ ተከታዮች እንሁን።

ቁ. 18-25። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ሐዋርያው የመስቀል ቃል ከንቱ እንዳይሆን ያደረገውን ጥንቃቄ ያሳየናል። በእርሱ ዘንድ የመስቀል ቃል ሁሉ በሁሉ ነው። የወንጌል መሠረት፥ የወንጌልም ልብ ነው። የመስቀሉ ቃል የቀረ እንደ ሆነ የሰብከት ፍሬ ነገር ቀረ ማለት ነው። ሁለት ነገሮች እንዳሉ እናያለን፡- 1ኛ «የክርስቶስ መስቀል» (ቁ. 17፥) ይህም በቁ. 18 ላይ «የመሰቀሉ ቃል፥» በቁ. 23 ላይ ደግሞ «የተሰቀለውን ክርስቶስን መሰበክ» ይባላል። 2ኛ ደግሞ፥ «የቃል ጥበብ» እሰ። (ቁ. 17።) እላይ እንዳየነው ሁሉ፥ የቆሮንቶስ ሰዎች በነገር ሁሉ በቃልም ሁሉ በእውቀትም ሁሉ ባለጠጎች እንዲሆኑ ተደርገው ነበርና በዚህ በተሰጣቸው ጸጋ ምክንያት ይመኩ ነበር። ጳውሎስ ግን በእንዲህ ያለ ነገር ለመመካት ከቶ እሳሰበም። ቃሉን ለማሳመር ወይም ወንጌልን ለማሻሻል ሳይሞክር የክርስቶስን መስቀል ብቻ ለመስበክ ቆረጠ። እውነት ነው ይህ የክርስቶስ መሰቀል ነገር በብዙዎቹ ዘንድ የጥበብ ተቃራኒ የሆነ ሞኝነትን መሰሎ መሰናክያ ሆኖአል። ቢሆንም ጳውሎስና እንደ እርሱ የሚያምኑት ሁሉ የመስቀል ነገር የእግዚአብሔር ኃይል የእግዚአብሔርም ጥበብ እንደ ሆነ ተረድተዋል። ነቢዩ ኢሳይያስ እንደዚህ እንዲሆን እሰቀድሞ ተናግሮ ነበር። (ኢሳ. 29፥19፤33፥18።) እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ ሽሮአልና የመስቀል ነገር ሲሰበክ የዓለም ጥበበኛ የት አለ? አያስተውለውም እኮ! በእዲስ ኪዳን ዘመን ጸሐፊ የተባለው የመጽሐፍ አዋቂስ የት አለ? አረ! ሳያውቅ ቀረ! በጥንቃቄ መርምሮ ክርክርን የሚችለውስ የት አለ? ክርክሩ ሞኝነት በመሰለው በመስቀል ነገር ከንቱ ሆኖ ተደረገ። ዓለምን በድካምና በሞኝነት እርሱም በመስቀል ስብከትና በእምነት ብቻ ለማዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖአል። የመስቀል ስብከት ስለ መስቀል ስለ ተሰቀለውም ክርስቶስ መሰበክ ማለት፥ በብዙዎች ዘንድ ሞኝነትና ማሰናከያ ቢመስልም እግዚአብሔር በጠራቸው ዘንድ (ቁ. 1፡2፤9) የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ሆኖ ይታያል። ይህም በሰው ዘንድ ሞኝነት ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ሥራ ከሰው ጥበብ ይልቅ ስለ ተጠበበ ነው፥ በሰው ዘንድ ድካም ሆኖ የታየውም የእግዚአብሔር ሥራ ከሰው ኃይል ይልቅ ሰለ በረታ ነው።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «ለሚጠፉት፡ ... ለምንድን።» (ቁ. 18።) የመስቀል ቃል፥ ስለ ኢየሱስና ስለ መስቀሉ የተሰበከው ቃል ማለት፥ ለሚጠፉት ሞኝነት ለሚድኑትም የእግዚአብሔር ኃይል ነው ተብሎ ተጽፎአል። የመስቀሉ ቃል በሚጠፉትና በሚድኑት መካከል ይለያል ማለት ነው። እንደ መለኪያ ያለ ነገር ነው። ይህን

የመስቀልን ቃል ሲሰማ ሞኝነት የሆነለት ሰው የሚጠፋ ነው፤ የእግዚአብሔር ኃይል ግን የሆነለት ሰው የሚድን ነው። አንባቢ ሆይ፥ ይህን በመስቀል የተደረገውን ሥራ እንደምን ትገምተዋለህ? ለአንተስ ምንድር ነው? ሞኝነት ነውን? ወይስ የእግዚአብሔር ኃይል ነው? በምትሰጠው መልስ ዛሬ የምትራመደው መንገድ የጥፋት ወይም የደኅንነት እንደ ሆነ ልታስተውል ትችላለህ።

ሊ. «ጻሐፊ።» (ቁ. 20።) ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን ቢያውቅ እንኳ የመጻሕፍትንም ጥቅስ እየጠቀሰ ለአላቡና ለአምነቱ ሊከራከር ችሎታ ቢኖረው እንኳ የመጽሐፉን ፍች ሳያይ ዕውር ሆኖ ሊቀር ይችላል። ሰው የሚድንበት ቅዱሳት መጻሕፍትን በማወቅ ሳይሆን ቅዱሳት መጻሕፍት በሚመሰክሩለት ሰው እርሱም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው። (ዮሐ 5፥ 39።) ቅዱሳት መጻሕፍትን ማወቅ ወደ በለጠ ፍርድ ሊያደርሰን ይችላል። (ሉቃ. 12፥47፡48።)

ሐ. «በሰብከት ሞኝነት።» (ቁ 21።) «የሰብከት ሞኝነት» ማለት የተሰበከው ነገር ሞኝነት ማለት ነው። የክርስቶስ መስቀል ወንጌል ለብዙ ሰው ሞኝነት ሲሆን ማሰናከያም ሲሆን እኛ ሰውን አናሰናክልም በማለት በመስቀል ነገር ፋንታ ሌላውን ማናቸውንም ነገር ስንሰብክ የእግዚአብሔር ኃይል በሰብከታችን የለምና ጊዜ በከንቱ ማሳለፋችን ነው። አንድ ነገር ሳንጨምር ሳናጎድልም ስለ ክርስቶስና ስለ መስቀሉ ግን ስንሰብክ የእግዚአብሔር ኃይል ይኖርበታልና ብዙውን ሰው ወደ ማላመን እንደርሳለን። (የሐዋ. 2፥41።)

የዛሬ የዓለም መምሕራን ምነው ይህንን ነገር ባስተዋሉ! የመስቀል ነገር በዓለም ጥበብኞች ዘንድ ገና ዛሬ ሞኝነትና ድካም ሆኖ ይታያቸዋልና አንዳንዶች መምህራንና የሃይማኖት ሰባኪዎች ሊያሻሽሉት ጥበብንም ሊያስመስሉት ወድደው ወይም ፍልስፍናን ይጨምራሉ ወይም የመስቀልን ነገር ያጎድላሉ። ሃይማኖትን እናስተምራለን ሲሉ የሃይማኖት መሠረት የሃይማኖትም ልብ የሆነውን የመስቀልን ነገር ሲያስቀሩ የተሰለበ ወንጌልን ማስተማራቸው አይደለምን? ሐዋርያት እንደዚህ እንዳላደረጉ እነዚህ መምህራን ልብ ያድርጉ። በዓለም ጥበብ ምክንያት ሰው አይድንምና የእነዚህ የዛሬ መምህራን ሥራ ፍሬ ቢስ ነው። የእግዚአብሔርን ሰንፍና ቢያከብሩ ኖሮ ጌታ የሚድኑትን ዕለት ዕለት በምእመናን ላይ ይጨምር ነበር። (የሐዋ. 2፥47።)

ቁ. 26-31። ይህ ነገር እውነት እንደሆነ፥ ማለት እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ እንደ ሻረው፥ ክቆሮንቶስ ሰዎች ከራሳቸው አኳኋን ሊታይ ይችላል። መጠራታቸውን ይመልከቱ። በመካከላቸው እንደ ሰው ጥበበ ጥበቦች የሆኑ፥ ወይም ኃይለኞች የሆኑ፥ ወይም ደግሞ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም። እግዚአብሔር እነዚህን ሳይጠራ የዓለምን ሞኝ ነገር የዓለምን ደካማ ነገር፥ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንና በዓለም ዓይን ያልሆነውን ነገር መረጠ፥ መርጦም ጠራ። ፍሬ ነገሩ ይህ ነው። «ሰውን ስንመለከት ስናመዛዝንም አውነተኞች ክርስቲያኖች በሰብሰባችንም ያሉ በተለይ የሚመጡበት ከዝቅተኛና ከድሀ የሰው ክፍል ሲሆን ምክንያቱ ምንድር ነው?» ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሱ ይህ ነው። እግዚአብሔር እንዲህ እንዲሆን ስለ መረጠ ነው። በሰው ፈቃድ ወይም በሰው ሥራ ሳይሆን በእግዚአብሔር ምርጫ ነው። (ሮሜ 9፥10-18። ዮሐ. 15፥16።) በእግዚአብሔር፥ በምሕረቱና በጸጋው፥ ይመካ ዘንድ እንጂ ሥጋን የለበሰ

ሁሉ በጥበቡ በኃይሉ ወይም በጨዋ ልጅነቱ እንዳይመካ ብሎ እግዚአብሔር የሚመኩበት ነገር የሌላቸውን ሰዎች መረጠ።

የቆሮንቶስ ሰዎች በመንፈሳዊ ባለጠግነታቸውና በጥበባቸው ይመኩ ነበር። ሆኖም ጥበባቸው፥ ጽድቃቸው ቅድስናቸው፥ ቤዛነታቸው ሁሉም ስጦታ ሆኖ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣላቸው፥ ይህንም ሁሉ በክርስቶስ እንዳገኙ ልብ ያድርጉ። እነርሱ በክርስቶስ የሆኑት ክእርሱ ነው እንጂ ከራሳቸው ወይም ከሌላ አይደለም። ሁሉም በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ነው። ክርስቶስ የዓለምን ጥበብ ያሳፈረ የእግዚአብሔር ጥበብ ነበረ። በእርሱም ሁሉ ተገኘ እንጂ ከራሱ ዘንድ ጽድቅን ሆነ ወይም ቅድስናን ወይም ቤዛነትን ሊያገኝ የሚችል ሥጋን ከለበሰ ማንም ሰው የለም። እንግዲህ የቆሮንቶስ ሰዎች በራሳቸው መመካታቸውን ትተው በክርስቶስ ባለው ከእግዚአብሔር ዘንድ በመጣላቸው ጸጋ ይመኩ።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «እግዚአብሔር ... መረጠ።» (ቁ. 27፡28።) እግዚአብሔር ከዝቅተኛና ከድሀ የሰው ክፍል ከሚድኑ የሚበዙትን መረጠ። በዚህ ክፍል የሆንን ሁሉ ጸጋውን እንወድስ፥ ምናልባትም ከዚያ ከፍ ካለው ወገን ተመርጠን ብንጠራ በቁ. 26 ላይ የተጻፈውን «ብዙዎች» የተባለውን ቃል አስታውሰን የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዲሁ እናመስግን። ተመርጠን ተጠርተናል እንጂ ከራሳችን ምንም አይደለንምና በደኅንነት የምንመካ በእግዚአብሔር እንመካ።

ለ. «ቤዛነት።» (ቁ. 30፡31።) ይህ ቃል ከጥበብና ከጽድቅ ከቅድስናም በኋላ በመጨረሻ ላይ በመጻፉ «ቤዛነት» የመዳን ሁሉ መጨረሻ ነገር መሆኑን እንረዳለን። የዳንንበት በፍጹም ማዳን ነውና ይህ ሰውነታችን እንኳ ሊድን ነው። ሐዋርያው «ቤዛነት» ሲል ስለ ሰውነታችን ቤዛ (መዳን) ሲናገር ነው። ይህ የተዋረደ ሥጋችን እንኳ የክርስቶስ ክቡር ሥጋ እንዲመስል ይለወጣል። (ፊልጵ. 3፥21።) ክርስቲያን ሲሞት ሥጋው ለጊዜው ይቀበራል፥ ነገር ግን ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ ሲገለጥ የዚያ ክርስቲያን ሰውነት ተለውጦ ክርስቶስን ይመስላል። (1 ዮሐ 3፥2።) ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ነገር ደጋግሞ ጽፎአል። (ሮሜ. 8፥18-23። 1 ቆሮ. 15፥48-57። 1 ተሰ. 4፥16፡17።) ይህ የሰውነታችን መዳን የሚፈጸመው በመጨረሻ ቀን ነውና (ኤፌ. 1፥14፤4፥30) ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ ሲቀርብ ቤዛነታችን አብሮ ቀርቦአልና በዚያን ጊዜ አሻቅበን ራሳችንን እንድናነሣ ጌታ ራሱ መክሮናል። (ሉቃ. 21፥ 28።) ያ የሰውነታችን ቤዛ ቀን እጅግ የሚያስደስት የክብራችን ቀን ነውና በታላቅ ተስፋ እንጠባበቀው። (በተለይም በ1ኛ. 15፥51-58 ላይ የተጻፈውን ነገር ተመልከቱ።)

* * * * * *

ምዕራፍ 2።

1፤ እኔም ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቱን ለእናንተ

2፤ እየነገርሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደ ተሰቀለ ሌላ ነገር 3፤ እንዳላውቅ ቆርጫ ነበርና። እኔም በድካምና በፍርሃት። 4፤5፤ በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤ እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፥ ቃሌም ሰብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር እንጂ፥ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም።

6፤ በሽማግሌዎች መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን፥ ነገር ግን የዚህችን ዓለም ጥበብ አይደለም የሚሻሩትንም የዚህችን።

7፤ ዓለም ገዦች ጥበብ አይደለም፥ ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፥ ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር።

8፤ እንናገራለን። ከዚህችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም።

9፤ ነበር፤ ነገር ግን - ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት።

10፤ ያዘጋጀው ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን። መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሰንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።

11፤ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ስለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ስለእግዚአብሔር ያለውን ማንም።

12፤ አያውቅም። እኛ ግን ከእግዚአብሔር የሆነውን እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ 13፤ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም። መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም።

14፤ ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ 15፤ ሆነ ሊያውቀው አይችልም። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን 16፤ ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም። እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ ሁለት።

ቁ. 1-5። ሐዋርያው «እኔም» ብሎ ይጀምራል። ግለት፥ ሌሎች እንዲያደርጉ የመከራቸውን ምክር እርሱ ራሱ ፈጽሞአል። በም. 1 ላይ ስለ ሰው ጥበብ ከንቱነት ስለመስቀሉም ቃል ኃይል እጫውቶአቸው ነበር፥ አሁንም በም. 2 ላይ «እኔም እንደዚህ አድርጌአለሁ» ይላል ልእግዚአብሔር ሊመሰክር ወደ ቆሮንቶስ በመጣ ጊዜ ቃሉን አስተካክሎ ለመናገር ወይም የሰበከውንም የትምህርቱን ቅደም ተከተሉን መልካም አድርጎ ለማደራጀት አልመጣም። ሊቅ ነበረና ቢፈቅድ ኖሮ ይህን ለማድረግ በቻለ ነበር። ነገር ግን አልፈቀደም። ምክንያቱም ወደ ቆሮንቶስ ሳይመጣ በፊት ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደ ተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳይናገር ቆርጦ ነበርና። ሲመጣም የሰው ኃይልና ጥበብ አልተገኘበትም። ሰውነቱ ደካማ ነበር። ንግግሩም የተናቀ ነበረ። (2 ቆሮ. 10፥10።) ቢሆንም ብዙ ፍሬ ተገኘ። የቆሮንቶስም ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመ ይህም የእግዚአብሔር ኃይል በስብከቱ እንደ ነበረ ይገልጣል። «እንደዚህ ስምን አደረገ?» ቢባልም ሐዋርያው ለምክንያት አደረገው፥ እርሱም እምነታቸው በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «በቃልና በጥበብ ብልጫ ... አልመጣሁም።» (ቁ. 1።) ዛሬ ደግሞ እንደዚህ የሚመጡ እንዳንዶች አሉ። ሲሰብኩ ቃላቸው ከሌላ ሰው ቃል ይልቅ እያምርም፥ የስብከት ሙያቸውም ከሌላ ሰው ሙያ አይበልጥም። ይሁን እንጂ በስብከታቸው ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ኃይል አለና ብዙ ሰው ያምናል። ዛፍ ከፍሬዋ ትታወቃለች እንደተባለው የእነዚህ ሰዎች ሥራ ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግልጥ ነው። (ማቴ. 12፥33። ማር. 11፥3።) ሌሎች ግን :- «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም» የተባለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል (ዮሐ. 6፥44) ረስተው «ለአዲስ ዘመን አዲስ ብልሃት ያሰፈልጋል» እያሉ ሰውን ወደ ወንጌል ለማጥመድ አስበው መሳቢያ የተባለውን ልዩ ልዩ ነገርን በወንጌል ላይ ይጨምራሉ። ይህ ፈጽሞ ስህተት ነው፤ ስለምን? ቢሉም፥ የሚሰብ የእግዚአብሔር መንፈስና የእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ በሰው የተፈጠረ የጥበብ ነገር አይደለም። አንድ ክርስቲያን የተሳበው በሰው ጥበብና ኃይል ከሆነ መከራ ወይም ፈተና በመጣ ጊዜ ወደ ኋላ ሳያፈገፍግ አይቀርም፥ መሳቢያው ግን፥ ወይም የቆመበት መሠረቱ የእግዚአብሔር ኃይል ከሆነ ሁሉን ታግሦ በእምነቱ ጽንቶ ይኖራል።

ለ/ «ለእግዚአብሔር ምስክርነቱ።» (ቁ. 1።) ወንጌልን መስበክ ምን እንደ ሆነ ይኸው ተገለጠ! ለእግዚአብሔርና እርሱም በክርስቶስ ለሰው ልጆች ላደረገው ማዳን መመስከር ነው እንጂ ስለ ዓለማዊ ነገር ሆነ ስለ መንፈሳዊም ያማረውን ዲስኩር ማድረግ አይደለም። ይህን ልብ እናድርግ!

ሐ/ «በድካምና በፍርሃት በብዙም መንቀጥቀጥ።» (ቁ. 3።) እንደ ቅዱስ ጳውሎስ የመሰሰ ብርቱ ሐዋርያ ሲያስተምር እንደዚህ በመሆኑ እንገረም ይሆናል። በእኛ ዘንድ ነገሩ ብዙ ጊዜ ሌላ ነው። አብዛኛውን ጊዜ እኛ ሰንሰብክ በራሳችን መቻልና በእውቀታችን ብቃት ታምነን በድፍረትና በአለኝታ እንሰብክ የለምን? የሆነ ሆኖ

እንደዚህ ስንሰብክ ብዙ ፍሬን እናያለን። ኃይሉ የእኛ የሰው ነውና ስብኩቱ የሰውን ሕሊና አይነካም ሰውም አያምንም። ቅዱስ ጳውሎስ ግን በድካሙ ምክንያት በብዙ ደስታ ይመካ ነበር። ስለምን? ቢሉ ሰው ሊደክም የእግዚአብሔር ኃይል መግቢያን ያገኛልና። በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የሰሚዎችን ልብ ይወቅሳል፥ ብዙም ሰው ያምናል። ቅዱስ ጳውሎስ «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝ» ብሎአል። (2 ቆሮ. 12፥9፡10። ዮሐ. 16፥8።)

ቁ. 6-16። እንግዲያስ የምንናገረው የምናስተምረውም ወንጌል በእውነት ሞኝነት መሆኑ ነውን? ከቶ አይደለም! የዚህች ዓለም ጥበብ አይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። የዓለም ገዦች ጥበብ ብዙ ነው፥ ቢሆንም የእነርሱ ጥበብ እይደለም። ከእነርሱ ጥበብ ይህ ጥበብ ይበልጣል። ገዦቹ ከነጥበባቸው ይሻራሉ፥ ይህ ጥበብ ግን አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ጀምሮ የተወሰነ ሆኖ ጸንቶ የቆየ ጥበብ ነው። ዓለም እይወቀው እይቀበለው እንጂ «ሽማግሌዎች» እውቀውታል፥ በደስታም ይቀበሉታል። ለዚህች ዓለም ሰው ተሰውሮአል፥ ሐዋርያት ግን ምሥጢሩን ገልጠው ይናገሩታል። የዓለም ከበርቴዎችና አዋቂዎች ሊጠልቁት አልቻሉም፥ ምልክቱስ የክብርን ጌታ ሰቀሉ፤ በሰቀሉትም ጊዜ እርሱ ራሱ «የሚደርጉትን እያውቁም» ብሎ መስክሮአል። (ሉቃ. 23፥34።) መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለ ነው፤ ዓይን ሊያየው ጆሮ ሊሰማው ልብ ሊያስበው አልቻለም። የዓለም ሰው በፍጹም አልጠሰቀውም ማለት ነው ከዓይናቸውና ከጆሮአቸው ከልባቸውም ተሰወረ። ሆኖም ምሥጢሩ፥ እርሱ ግለት እግዚአብሔር ሰሚወዱት ያዘጋጀው ነገር፥ በዚያን ጊዜ ለሐዋርያት በአሁኑም ጊዜ ለእማኞች ክርስቲያኖች ተገለጠ። አነርሱም ተናግረውታል እኛም እንናገረዋለን፥ ሲናገሩትም ስንናገረውም የዓለም ሰው ሞኝነት ይለዋል! እግዚአብሔር ለሐዋርያትና ለእማኞች ምሥጢሩን የገለጠው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው። የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ለማወቅ የሚችል ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ማንም የለም። ስለዚህ ኢየሱስ «እርሱ መንፈስ ቅዱስ ለእኔ ካለኝ ወሰዶ ይነግራችኋል» አለ። (ዮሐ. 16፥14።) መቼም ነገሩ ግልጥ ነው። የእግዚአብሔር ሆነ የሰውም ሆነ በውስጡ ያለውን ጥልቅ ነገር የውጭ ሰው ሊያውቀው እይችልም። ይህን ሁሉ ሊያውቅ የሚችል መንፈሱ ብቻ ነው። እኛ እማኞች ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ፥ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል እርሱም የእግዚአብሔርን ምሥጢር እናውቅ ዘንድ ያስችለናል። አውቀነዋልና እንናገረዋለን። ስንናገርም መንፈስ ቅዱስ የምንናገርበትን ቃል ስንኳ ያስተምረናልና መንፈሳዊ ነገርን በሰው ጥበብ ቃል ሳይሆን በመንፈሳዊ ቃል እናስተምራለን። ይህንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን መንፈስ ነገር ሞኝነት ይመስላቸዋል! ይህስ ስለ ምንድር ነው? ቢሉ፥ ፍጥረታዊ ሰው፥ እርሱም ግለት ዳግመኛ በመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሰው፥ በምንፈስ እልተወለደምና መንፈሱ ሕያው ስላልሆነ ነው፥ የእግዚአብሔርንም መንግሥት ነገር (መንፈሳዊን ነገር) ሊያውቀው አይችልምና እይቀበለውም። የእግዚአብሔር መንግሥት ነገር ሞኝነት በመሆኑ እይደለም፥ ሰውየው ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሆኖ ፍጥረታዊ በመሆኑ ነው እንጂ። መንፈሳዊ ሰው ግን፥ እርሱም ግለት በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ የተወለደ ሰው፥ በመንፈስ ተወልዶአልና መንፈሱ ሕያው ሆኖአል፥ ሁሉንም መርምሮ ለማወቅ ይችላል። ይህ ሲሆን ግን እርሱን መርምሮ የእርሱን ጥልቅ ነገር ለማወቅ የሚችል ገና ፍጥረታዊ የሆነ ማንም ሰው የለም። መቼም ነቢዩ ኢሳይያስ በም. 40፥13 ላይ የተናገረው ቃል በዚህ ነገር ተፈጸመ። ነቢዩ «የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ፥ ወይስ እማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው?» ብሎ ጠየቀ። እውነት ነው፥ የእግዚአብሔርን

ልብ ለማወቅ የሚችል ተራ ሰው በፍጹም እንደማይገኝ እንዲሁ የክርስቶስ ልብ ያላቸውን ሰዎች ለማወቅ የሚችል የለም።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «ሽማግሌዎች።» (ቁ. 6።) እነኝህ በእምነት የሸመገሉ ናቸው። በዕብ. 5፥14 «ፍጹማን ሰዎች» ይባላሉ። 1 ቆሮ. 3፥1፡2 ከእብ. 5፥11-14 ጋር ማነጻጠር ያስፈልጋል። ዳግመኛ በእዲስ ልደት የተወለዱቱ እስቀድመው ሕፃናት ናቸው በኋላ ግን እድገው ወደ ሙሉ ቁመትና ሰውነት ደርሰው «ሽማግሌዎች» ወይም «ምሉእን» ወይም ደግሞ «ፍጹማን ሰዎች» ይባላሉ። በ1 ቆሮ. 2፥6 ላይ «ጥበብ» የተባለው በም. 3፥2 ላይ «ጽኑ መብል» ይባላል› በዕብ. 5፥12 ላይ «ጠንካራ ምግብ» ይባላል። ገና ሕፃናት የሆኑቱ የእግዚአብሔርን ጥበብ ምናልባት እያስተውሉም ይሆናል፥ ሽማግሌዎቹ ግን ያስተውሉታል። (ኤፌ. 1፥13-16 ደግሞ ተመልከት።) በዚህ በእምነት ረገድ ሰው ሽማግሌ ይሆን ዘንድ ብዙ ዓመት እንዲቆይ እያስፈልግም። በቁጥራቸው ጥቂቶች ናቸው እንጂ እነዳንዶች ክርስቲያኖች እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆነው ወዲያውኑ ይደርሱበታል።

ለ. «ለክብራችን።» (ቁ. 7።) ከዘመናት በፊት እግዚአብሔር ሰውን ለማክበር እንደ ወሰነ፥ የሚከበርበትን መንገድ ደግሞ እንደ ወሰነ ልብ እናድርግ። ደኅንነት በድንገት የታሰበ የእግዚአብሔር አሳብ ሳይሆን ከዘመናት በፊት የተወሰነ እሳብ ነው። (ሮሜ. 16፥25፡26። ኤፌ. 3፥5፡9። ቆላ. 1፥26። 2 ጢሞ. 1፥9።)

ሐ/ «ከዚህች ዓለም ገዦች እንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም።» (ቁ. 8።) በገጽ 14 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መልሱ እነሆ! የክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት ያለው ከሆነ ብዙዎች እዋቂዎችና ፕሮፌሰሮች መመህራንም፥ ብዙዎች ፕሬዚዳንቶችና ሚኒስትሮች ከበርቴዎችም፥ እውነተኞች ክርስቲያኖች ያልሆኑበት በምን ምክንያት ነው?» ተብሎ ተጠይቆአል። ምክንያቱም ወንጌል፥ እርሱም ክርስቶስና መስቀሉ፥ የሰው ጥበብ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጥበብ ስለ ሆነ ነው፥ ይኸውም የእግዚአብሔር ጥበብ ስለ ተሰወረ በሰውም ጥበብ ስለማይታወቅ ነው። «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው» እንደ ተባለው (ዮሐ. 3፥6) የመንፈስን ነገር ሊያስተውለው የሚችል ዳግመኛ ተወልዶ የእግዚአብሔርን መንፈስ የተቀበለ ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት የክርስቲያን ሃይማኖት የራስ (የማስተዋል) ነገር ሳይሆን የልብ (የእምነት) ነገር ንው። ሰው «በራሴ ካላስተዋልሁት በልቤ አላምንም» ቢል ከቶ እያስተውለውም ነገር ግን «ምንም ባላስተውለው አምንበታለሁ» ቢል ወዲያውኑ ተሰውሮበት የነበረው ምሥጢር ይገለጥለታል ያስተውላልም። እነዚያ እላይ የተጠቀሱት እዋቂዎችና ከበርቴዎች እውነተኞች ክርስቲያኖች ያልሆኑበት በዚህ ምክንያት ነው። የዚህችን ዓለም ጥበብ የያዙ ናቸው፥ የእግዚአብሔር ምሥጢር ግን በዚህች ዓለም ጥበብ አይታወቅምና እያስተውሉትም። በዚህም ምክንያት ደግሞ ክሚያምኑቱ የሚበዙት ያልተማሩ ሰዎች ናቸው። ወንጌልን ሊሰሙ ወዲያውኑ ያምናሉ፥ እግዚአብሔርም በመንፈሱ (በመንፈስ ቅዱስ) ምሥጢሩን ይገልጥላቸዋል። የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅ የሰው እውቀት ምንም እይረዳም ማለት ነው። እዋቂዎችም እላዋቂዎችም ሆነዋል። (ሮሜ. 1፥22። 2 ቆሮ. 4፥4። ማቴ. 21፥31፡32።)

መ/ «መንፈስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሰንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል።» (ቁ. 10 እና በቁ. 11 ላይ በተባለው ነገር መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን እንረዳለን። እርሱ የእግዚአብሔርን ነገር ሁሉ መርምሮ ያውቃል። የሰው መንፈስ በሰው ውስጥ ሆኖ ከሰው ጋር አንድ እንደ ሆነ ዓይነት እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ነው። ቢሆንም ሐዋርያው ስለ ሰው መንፈስ ሲጽፍ «በእርሱ ውስጥ ያለው» ሲል፥ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር እንደዚህ አይልም፤ ስለምን? ቢሉ፥ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያለው የእግዚአብሔር አሳብ ወይም ደግሞ ነፍስ ሳይሆን ከአብና ከውልድ ጋር የተተካከለ ከሥላሴዎች አንዱ ነው።

ሠ/ «ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ።» (ቁ. 12።) ይህስ ምንድር ነው? እግዚአብሔር እንዲያው የሰጠን ምንና ምን ያለ ነገር ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ይመስክር። ሮሜ 5፥15-18 መጽደቅና በሕይወት መንገሥ የጸጋ ስጦታ መሆኑን ይመስክራል። ሮሜ 6፥23 የጸጋ ስጦታ የዘላለም ሕይወት እንደ ሆነ ይገልጣል። ኤፌ 2፥8 የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ደኅንነት እንደ ሆነ ይነግረናል። 1 ዮሐ 5፥11 ደግሞ ስጦታው የዘላለም ሕይወት እንደሆነ ይመስክራል ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲያው የሰጠን፡- ጽድቅንና ደኅንነትን የዘላለም ሕይወትንም እንደ ሆነ እናስተውላለን።

* * * * * *

ምዕራፍ 3።

1፤ እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ 2፤ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት 3፤ አትችሉም ነበርና ወተት ጋትጓችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ እይደላችሁምን? 4፤ እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን? እንዱ፡- እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ ሁለተኛውም፡- እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናቸው አይደለምን?

5፤ አጵሎስ እንግዲህ ምንድር ነው? ጳውሎስስ ምንድር ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው፤ ለእያንዳንዳቸውም 6፤ ጌታ እንደ ሰጣቸው ያገለግላሉ። እኔ ተከልሁ አጵሎስም 7፤ አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤ እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተከል ቢሆን 8፤ ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም። የሚተክልና የሚያጠጣ እንድ ናቸው፥ ነገር ግን አያንዳንዱ እንደ ራሱ 9፤ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል። የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።

10፤ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ 11፤ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት 12፤ አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በእገዳ ቢያንጽ፥ 13፤ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፥ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። 14፤ ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን 15፤ የቀበላል፤ የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፥ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።

16፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም 17፤ መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ። 18፤ ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ ማንም በዚህች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ 19፤20 ይሁን። የዚህች ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና። እርሱ ጥበበኞችን በተንኮላቸው የሚይዝ፤ ደግሞም፡- ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ከንቱ እንደ ሆነ ያውቃል ተብሎ 21፤ ተጽፎአልና። ስለዚህም ማንም በሰው አይመካ ነገር 22፤ ሁሉ የእናንተ ነውና፤ ጳውሎስ ቢሆን አጵሎስም ቢሆን ኬፋም ቢሆን ዓለምም ቢሆን ሕይወትም ቢሆን ሞትም 23፤ ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን፥ ሁሉ የእናንተ ነው፥ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

* * * * * *

ምዕራፍ ሦስት።

ቁ. 1-9። ጳውሎስ «በሽማግሌዎች መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን» (ም. 2፥6) ደግሞም «እኛ . . . ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ ተቀበልን» (ም. 2፥12) ብሎ የቆሮንቶስን ሰዎች እንደ መንፈሳውያን ቆጥሮአቸው ነበር። ይህንም ሲያደርግ መልካም አደረገ፤ ስለምን? ቢሉ፥ በክርስቶስ በማመን ልጅነትን ተቀብለው በእርግጥ መንፈሳውያን ነበሩ። በመጀመሪያ ጊዜ ጳውሎስ በመካከላቸው ሳለ እንደ ሽማግሌዎች ወይም እንደ መንፈሳውያን ሲናገራቸው አልቻለም፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ገና ሕፃናት ነበሩና። በአዲስ ልደት ሕፃናት ነበሩና ትምህርቱን ከሕፃንነታቸው ጋር እስማምቶ ወተት የሚመስለውን ቀላል የሆነ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ብቻ አስተምሮአቸው ነበር። ሕፃን ልጅ ሥጋን ለመብላት ባለመቻሉ ምክንያት እንደማይወቀስ እንዲሁ የቆሮንቶስ ሰዎች ያን ጊዜ ጽኑ መብልን ባለመቻላቸው አይወቀሱም። ሆኖም ያ ሕፃን ልጅ ሳያድግ ቀርቶ እስከ ብዙ ዓመታት ድረስ ሥጋን መብላት ሲያቅተው «ይህስ አይገባም ልጁ ታሞአል» እንደሚባለው ሁሉ እንዲሁ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ገና ሥጋውያን ሆነው «እስከ ዛሬ ድረስ» ባለመቻላቸው የሚወቀሱ ናቸውና ሐዋርያው በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ይወቅሳቸዋል። መንፈሳውያን መሆን ይገባቸው ነበር፤ በክርስቶስ ብዙ ተቀብለው ነበር፥ ይመኩበትም ነበር። ይሁን እንጂ ጳውሎስ በጻፈ ጊዜ እኳኋናቸው መንፈሳዊ አልነበረም። መንፈሳውያን በመሆን ፋንታ ገና ሥጋውያን ነበሩ፤ ምልከቱም፥ ቅንዓትና ክርክር ተገኝቶባቸዋል። አንዱ፡- እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ ሁለተኛውም፡- እኔ የአፎሎስ ነኝ ይሉ ነበር። ዳግመኛ ከልተወለደ ከተራ ሰው በምን ተለዩ? አመላለሳቸው ለመንፈሳውያን እንደሚገባ ልዩ ሳይሆን (1 ዮሐ. 2፤ 6) እንደ ፍጥረታውያን አመላለስ ነው።

እንደዚህ ግን ሲከራከሩ በፍጹም የማያስፈልገውን ነገር አድርገዋል። አፎሎስና ጳውሎስ በእግዚአብሔር እጅ የሆኑት መሣሪያዎች ናቸው እንጂ ሥራው እግዚአብሔር ነው። (ሐዋርያው ሲጽፍ «ማን ነው?» ሳይል «ምንድር ነው?» ማለቱን አስተውል።) አሳዳጊው እግዚአብሔር ነውና የቆሮንቶስ ሰዎች ለምን ብለው እገልጋዮችን ተመለከቱ? በእነዚህ ፋንታ እግዚአብሔርን ብቻ መመልከት ይገባቸው ነበር። ጳውሎስ ተከለ አፎሎስም አጠጣ እውነት፤ ሆኖም አገልጋዮች ብቻ ናቸው። የቆሮንቶስ ሰዎች ጌትየውን ሳይመለከቱ አገልጋዮችን ለምን ይመለከቱዋቸዋል? ስለ እነርሱ ለምን ይከራከራሉ? ተካዩ ያለ አጠጪ አይሆንም አጠጪም ያለ ተካዩ አይሆንም፥ እነርሱ አንድ ናቸው በእኩልም ይከበራሉ ቢሆንም በዚህ ዓለም ላይ በሠራተኛ ሁሉ ዘንድ እንደሚደረገው ሁሉ እያንዳንዳቸው እንደየድካማቸው መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል። የቆሮንቶስ ሰዎች የጳውሎስ እርሻ ወይም የአፎሎስ አይደሉም፥ የእግዚአብሔር ናቸው እንጂ። ወይም ደግሞ በሌላ አርሱም በሕንፃ ምሳሌ፥ የጳውሎስ ወይም የአፎሎስ አይደሉም የእግዚአብሔር ናቸው እንጂ። ይሁን እንጂ «እኔ የጳውሎስ ነኝ እኔም የአፎሎስ ነኝ» ብለዋል። ሞኝነት እይደለምን?

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?» (ቁ። 4።) ክርስቲያኖች «ሰዎች ብቻ» ሳይሆኑ ከዚህ የበለጠ መሆን እንዲገባቸው እናስተውል። አዲስ እንዲወለዱ ብቻ ሳይሆን መንፈሳውያን እንዲሆኑ ነው። ሰው ዳግመኛ ሊወለድ ይችላል፥ ከዚህ በኋላ

ግን አመላለሱ መንፈሳዊ ሳይሆን ሥጋዊ፥ ወይም ደግሞ እንደ ዓለም ሰው አመላለስ፡ ይሆን ይሆናል። ይህም የማይገባ ነው። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ዳግመኛ የተወለዱ ነበሩ፥ ቢሆንም ክርክርና ቅንዓት ተገኝቶባቸዋልና፥ እነዚህም ነገሮች ከሥጋ ሥራዎች መካከል የሚቆጠሩ ናቸውና (ገላ 5፥19፡20) ጳውሎስ «ሥጋውያን» ይላቸዋል። እንዲህም ሲል እውነት መናገሩ ነው። ክርስቲያኖች ሲሆኑ እንደ ሰው ልማድ ተመላልሰዋል እንጂ እንደ መንፈሳውያን አልተመላለሱም። እኛሳ? በእኛ ዘንድ የሚገኙት የትኞቹ ናቸው? የሥጋ ሥራዎች ወይስ የመንፈስ ፍሬዎች? (ገላ። 5፥19-23።)

ለ. «እንደ ራሱ ድካም መጠን።» (ቁ። 8።) ደመወዙ እንደ ፍሬው ብዛት ወይም እንደ ሥራው መቅናት መጠን ሳይሆን እንደ ሠራተኛው ድካም መጠን እንደሚሆን እናስተውል። «የተቻላትን አደረገች» እንደ ተባለው ሁሉ (ማቴ። 14፥8) ተግቶ የሠራው ምስጉን ነው።

ሐ. «የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።» (ቁ። 8።) ይህ የተባለለት መቼም ለሠራተኛ ነው። ሠራተኛም ደመወዝን እንዲቀበል የተረጋገጠና በሁሉ ዘንድም የተገባ ነው። የዚህ ዓለም ሠራተኞች ደመወዝን እንደሚቀበሉ ሁሉ እንደዚሁ ለመንግሥተ ሰማያት የሚሠሩ ሁሉ ከጌታ ዘንድ ደመወዛቸውን ይቀበላሉ፥ እያንዳንዱም እንደ ራሱ ድካም መጠን ይቀበላል። በዚህ ዓለም ላይ እንዱ ሠራተኛ አራት መቶ ብር ሲቀበል ሁለተኛው አንድ መቶ ይቀበላል ሦስተኛውም ምናልባት ሠላሳ ይቀበላል። በመንፈሳዊ ነገር በሚያገለግሉ ሠራተኞች ዘንድ እንደዚህ መሆኑ ነው። አንዱ ይህን ያህል ሲያገኝ ሁለተኛው ያን ያህል ያገኛል። ደመወዛቸው ወይም ዋጋቸው አንድ ሳይሆን ልዩ ልዩ እንደ ሆነ በማቴ። 10፥40-42 ላይ እናያለን። በዚያ ቦታ የነቢይ ዋጋ፥ የጻድቁም ዋጋ፥ ደግሞም አንድ ሦስተኛ ዋጋ እንዳለ እናያለን። እንደዚህ እዚህ በ1 ቆሮ። 3፥8 ላይ «እያንዳንዱ የራሱን ደመወዝ ይቀበላል» ተባለ።

ደመወዙስ ምንድር ነው? ተብሎ ቢጠየቅ፥- በሉቃስ ወንጌል ም። 19፥11-26 ላይ የተናገረውን ምሳሌ መመልከት ያሻናል። በዚያ ምሳሌ ላይ የሚገኙት ባሪያዎች ሹመትን አንዳገኙ፥ እንደዚሁም ከእግዚአብሔር ጋር አብረው የሚሠሩት በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሹመትን ያገኙ ይሆናል። ከክርስቶስ ጋር እንደሚነግሡ እናውቃለንና በዚህ ዓለም ላይ ሳሉ ስለ መንግሥተ ለማያት የደከሙት ሁሉ ክርስቶስ በተመለሰ ጊዜ ሹመትን እንደሚቀበሉ ይመስላል። (ም። 3፥14፡15፤ 6፥2። ዳን። 7፥22። ማቴ። 19፥28። ራእ። 20፥4-6። 22፥12።) ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ስለ እክሊል ይናገራል። (ም። 9፥24-27።)

ቁ። 10-15። ሐዋርያው የሠራተኞችን አንድነት ለማሳየት «እኔ ተከልሁ አፎሎስም አጠጣ» ብሎ ነበር። ቀጥሎም የግብርናን ምሳሌ ለመፈጸም «የእግዚአብሔር እርሻ ናቸሁ» አለ። (ቁ። 9።) ከዚያ በኋላ ግን ወይም የመጀመሪያውን ነገር ትልቅነት አብዝቶ ለማስረዳት፥ ወይም የእያንዳንዱን ሠራተኛ የድካሙና የደመወዙን ነገር ለመከታተል ስለ ፈለገ፥ ምሳሌውን ለውጦ ከርስቲያኖቹን ወይም ቤተ ክርስቲያንን ሕንፃ፥ ሠራተኞችንም እናጺዎች፥ እድርጎአል። የሕንፃውን መሠረት የጣለ፥ እርሱም ማለት መጀመሪያ የወንጌልን ነገር የሰበከላቸውና የእግዚአብሔርን መቅደስ የጀመረ (ቁ። 16፤1 ጴጥ። 2፥5፥) ራሱ ጳውሎስ ነበረ። በዚያ መሠረት ላይ እንደ ግድግዳና እንደ ጣራ

የመሰለ ከፍ ያለ ትምህርትን በማስተማር ቤቱን ያነጹት ከጳውሎስ በኋላ የመጡት እነ አጵሎስን የመሰሉት አስተማሪዎች ነበሩ። እነዚያ በመሠረቱ ላይ የሚያንጹ ሰዎች ሥራቸው ልዩ ልዩ ሊሆን ይችላል፤ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ቤት የሚመሠረትበት መሠረት ግን ከአንዱ እርሱም ከኢያሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ ሊሆን አይችልምና መሠረቱ የሚያንጽ ያው ክርስቶስ ነው። በመሠረቱ ላይ የሚታነጽ ሥራ እንደ ሠራተኞቹ ፈቃድ ወይም የከበረ ወይም የተናቀ ሊሆን ይችላል። የሥራው ዓይነት ምናልባት ዛሬ አይታይም ይሆናል ሆኖም ከዕለታት አንድ ቀን ይታወቃል፤ የሰው ሁሉ ሥራ የሚገለጥበት ቀን ሊመጣ ነውና። (2 ቆሮ። 5፤10።) ያም ቀን ክርስቶስ በዳግም ምጽአት የሚመለስበት የፍርድ ቀን ነው። (ም። 4፤5።) አንጥረኛ በእሳት እንደሚፈትን እንዲሁ ያ ቀን የአያንዳንዱን ሠራተኛ ሥራ ይፈትነዋል። የከበረ ከሆነ ይጸናል፤ ሠራተኛውም ደመወዙን ይቀበላል፤ ሥራው ላይጸና፤ የተቃጠለበት ሠራተኛ ግን ይጎዳበታል፤ እንዳችንም ደመወዝ ላይቀበል ባዶ እጁን ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን።» (ቁ። 10።) ከዚህ በፊት በቁ። 5 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ «ጌታ እንደ ሰጣቸው ያገለግላሉ» ብሎ ጽፎአል። መንፈሳዊ አገልግሎት «ጌታ እንደ ሰጣቸው፤» የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን፤» ነው እንጂ በገዛ ጥበቡ ወይም በገዛ ኃይሉ ሊያገለግል የሚችል የለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ» ቢሆንም አገልግሎቱ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠው መጠን ብቻ ነበርና ክብርና ምስጋና ለእርሱ ለሠራተኛ አይገባም። ጳውሎስ ይህን የሚልበት ምክንያቱ ክብር ሁሉ ለጌታ እንዲሰጥ ስለሚፈልግ ነው። (ኤፌ። 3፤7።)

ለ/ «ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም።» (ቁ። 11።) ከቁ። 10 እስከ ቁ። 15 ድረስ ሐዋርያው ስለ ማስተማር ሥራ ይናገር እንደሆነ (እንደ ቁ። 5-8፤17) ወይም ስለ ምእመናን ማኅበር «ሕንፃ» ይናገር እንደሆነ (እንደ ቁ። 9 እና ቁ። 16) አልታወቀም። ቀጥሎ የሚናገረው ቃል ግን ለሁለቱ፤ ወይም ለትምህርት ወይም ለሕንፃው ሊተረጎም ይችላል። የክርስቲያን ሃይማኖት ሁሉ መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ያለ እርሱ የክርስቲያን ሃይማኖት የለም። እንደዚሁ ደግሞ፤ ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች እንደሚናገረው ሁሉ፤ ለመንፈሳዊ ትምህርት ሆነ ወይም ለአንድ የክርስቲያን ማኅበር ሌላ መሠረት በፍጹም የለም። ሰው (አገልጋይ) ሃይማኖትን ሊያስተምር ቢወድ መሠረቱን፤ እርሱም ክርስቶስን፤ መመሥረት ያስፈልገዋል። ይህን መሠረት አስቀርቶ ከእርሱ ከፍ ያለውን ትምህርት ሊያስተምር የሚያስብ አገልጋይ የሚፈርስ ቤትን ብቻ ያንጻል። በመሠረት ላይ ያልታነጸ ቤት እንደሚፈርስ እንዲሁ በክርስቶስ ላይ ያልተመሠረተ መንፈሳዊ ትምህርት ሆነ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ፈራሽ ነው። መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሆን ያስፈልጋል።

ሐ. «እርሱ ራሱ ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።» (ቁ። 15።) ሐዋርያው ስለሚድኑትና ስለማይድኑት ሳይሆን መልካምንና ክፉን ስለሚሠሩት ስለ ሠራተኞች ይናገራል። የሚናገረው ስለ ምእመናንና ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ብቻ ነው። እነዚህ ሁሉ መሠረቱን የጣሉ ናቸው፤ እርሱም ማለት

በክርስቶስ ያመኑ ናቸው። መሠረቱን ከዚህ በፊት ጥለዋልና አሁን በመሠረቱ ላይ ሥራ ሠርተዋል። ሥራን ሳይሠራ በፊት መሠረቱ አስቀድሞ እንዲጣል የግድ አስፈላጊ ነው፤ ስለምን? ቢሉ ሰው በክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር አስቀድሞ ካልታረቀ እግዚአብሔር ሥራውን አይቀበልም አይቆጥርለትምም። (ኢሳ። 64፤4።) መሠረቱ ግን ከተጣለ ሥራ ወዲያው እንዲቀጥል ታስቦአል። (ሉቃ። 6፤ 46። ያዕ. 2፤ 14-26።)

ይህ በቁ። 15 ላይ የምናገኘው ሰው በመልካም አልሠራምና ሥራው ተቃጥሎበታል። በዚህ ዓለም ላይ ሥራውን በደህና ያልፈጸመ ሠራተኛ ከደመወዙ እንደሚቆጣ (ደመወዙ እንደሚቆረጥ) እንዲሁ ይህ ሰው ደግሞ ከደመወዙ ይጎዳል። መሠረቱን ጥሎ ነበርና፤ እርሱም ግለት በክርስቶስ አምኖአልና፤ የዳነ ሰው ነው ይድንማል። ሥራው ግን መልካም አልሆነምና በክርስቶስ ወንበር ፊት ሲቆም ደመወዝን ሳያገኝ በአንድ ቤት ውስጥ እሳት በሌሊት በድንገት ተነሥቶ እንደሚሆነው ሁሉ እንዲሁም ይህ ሰው ባዶ እጁን ከእሳት አምልጦ ይወጣል። እርሱ ራሱ ከእሳት ይድናል ከደመወዙ ግን ይጎዳል።

ቁ. 16፤17። ሐዋርያው «የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ» ብሎ ስለ ሕንፃ ተናግሮ ነበር። ያን ሕንፃ ስለሚሠሩት ሠራተኞች ተናግሮአል፤ አሁንም በተለይ ስለ ሕንፃው ራሱ ይናገራል። ስለ ሕንፃው የሚናገርበቱ ምክንያት የቆሮንቶስ ሰዎች የእግዚአብሔር ሕንፃ መሆናቸውን ስለ ረሱ ነው። በዱሮ ቤተ መቅደስ ውስጥ እግዚአብሔር አድሮአል፤ ክብሩም በላዩ አርፎአል። (ዘጸአ. 40፤34፤ 35። 1 ነገ. 8፤10፤11።) እንደዚህም የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነበሩ። ሆኖም ይህን ረስተው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንደ ተራ ጎጆ አድርገው በቅንዓትና በክርክር በዝሙትና በክፉ ሥራ ሲያረክሱት ተገኙ። ይህንም እንደ ትንሽ ነገር አይቁጠሩት። የእግዚአብሔርን ቤት የሚያፈርስ ቢናር እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሳልና ታላቅ ጥፋት ነው።

ማስገንዘቢያ።

«ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል።» (ቁ. 17።) ይህ እጅግ የሚያስፈራ ነገር ነው። ስለ ምእመናን ሆነ ስለ ትምህርትም ሆነ ቢናገር ይህ ቃል ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ለእኛም ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። ክርስቲያኑ መጥፎ ሥራውን አስተማሪውም እውነት ያልሆነውን ትምህርቱን ይተው። መጥፎ ሥራና የማይገባ ትምህርትም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያፈርሳልና እግዚአብሔር እኛን እንዳያፈርሰን እንጠንቀቅ። ዛሬ የሚጎዳው በኋላ የተጎዳ ይሆናል።

ቁ. 18-23። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የተላላቱበት በዚህች ዓለም ውስጥ ጥበበኞች ለመሆን ስለ ፈለጉ ነበረና ሐዋርያው አሁን ወደ ቀድሞው አሳቡ ተመልሶ የዚህች ዓለም ጥበብ የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅ ከንቱ፤ በእግዚአብሔርም ዘንድ ሞኝነት እንደ ሆነ ደግሞ ይነግራቸዋል። የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገር በሌላ ዓይነት ጥበብ እንጂ በዚህች ዓለም ጥበብ አይታወቅምና ሰው በዚህች ዓለም ጥበብ ሞኝ ይሁን። ለምሳሌ፦ ጠቢብ የሆነ ዓሣ የሰውን ነገር ለማወቅ እንደምን ይቻለዋል? አይቻለውም። በውኃው ውስጥ ሆኖ ጠቢብ ይሁን፤ በደረቁ ላይ ያለውን የሰውም ምሥጢር ግን ለማወቅ አይችልም። እንደዚህም ሁሉ የዚህች ዓለም ሰው በዓለሙ ውስጥ ምንም ጠቢብ ቢሆን የመንግሥተ

ሰማያትን ነገር ለማወቅ አይችልም። ይሁን እንጂ በዚህች ዓለም ውስጥ ሞኝ ሆና የሚታየው ዝቅተኛው ክርስቲያን እንኳ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ለማወቅ ይችላል። ለዚህ ነገር ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራ መስክሮአል። በኢዮብ. 5፥13፥ ደግሞ በመዝ. 93፥11፥ እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንደ ያዛቸው ሥራቸውንም እንዳስታጎለ፥ ሥራን መሥራት ሳይጀምሩ በፊት እንኳ አላባቸው የማይሳካላቸው መሆኑን እንዳወቀ ተነግሮናል። ነገሩ እንደዚህ ነውና ይልቅስ የእግዚአብሔርን ነገር የሚያውቁት የዚህች ዓለም ሞኞች ናቸውና በሰው መመካት ምን ያስፈልጋል? ጳውሎስ ቢሆን አጵሎስም ቢሆን ኬፋም ቢሆን ሦስቱ የእነርሱ ናቸውና ሁሉቱን አስቀርተው በአንዱ ብቻ ለምን ይወሰናሉ? እንደዚህ ሲያደርጉ ይደኸዩ የለምን? ሦስቱ የተሰጡበት ምክንያቱ እንዲጠቀሙባቸው ነው። ሦስቱ የእነርሱ ናቸው፥ ሦስቱም ብቻ ላይሆኑ ዓለም፥ ሕይወትም፥ ሞትም (ም. 15፥55-57። ፊልጵ. 1፥21።)፥ አሁን ያለው ሁሉ፥ ወደፊት ሊመጣ የሚችልም ሁሉ፥ ሁሉ የእነርሱ ነው፥ እንዲጠቀሙበትም ተሰጥቶአልና። (ሮሜ. 8፥28፥32።) በሁሉ ይጠቀሙ! ቢሆንም አንድ ነገር አይርሱ፥ ይኸውም ይህን ሁሉ ያገኙ የክርስቶስ ስለ ሆኑ ብቻ ነው። የክርስቶስ ናቸውና «ለራሳችን ነን» ብለው ላይመኩ (ም. 6፥20) ለክርስቶስ ገንዘቦች የማይመችን ሥራ ሁሉ ትተው አመላለሳቸውን በትሕትና ያላምሩ። ምነው? ይህን ሁሉ ሀብት የተቀበሉ የክርስቶስ የሆኑ ሰዎች ሥጋውያን ሆነው እንደ ሰው ልማድ ይመላለሳሉን? (ቁ. 3።) ክቶ አይገባም! ሁላችሁ የእግዚአብሔር ነውና በእርሱ ይመኩ እርሱንም ያክብሩ እንጂ በአሽከሮቹ አይመኩ።

ማስገንዘቢያ።

«ክርስቶስ የእግዚአብሔር ነው።» (ቁ. 23።) ይህስ እንደምን ይሆናል? ክርስቶስ እግዚአብሔር አይደለምን? ከአብ ጋር የተተካከለ አይደለምን? ነው! እንግዲያስ ክርስቶስ እንደምን የእግዚአብሔር ይሆናል? መልሱ፡-

1ኛ፤ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ (ወልድ) ነው። በዓለም ላይ «አገሌ የማን ልጅ ነው?» ሲባል መልሱ «የአገሌ ነው» ይባል የለምን? እንደዚሁ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ነው። አባትም ክልጅ ይበልጣልና ኢየሱስ «ከእኔ አብ ይበልጣል» ብሎአል። (ዮሐ. 14፥28።)

2ኛ፤ ምሥጢረ ሥጋዊ አለ። በመጀመሪያው የነበረው ቃል (ዮሐ. 1፥1-3) ሥጋ በሆነ ጊዜ ሰው ሆኖ ለአባቱ ተገዛ። (ዮሐ. 5፥19፤ 8፥28፤ 12፥49፤ 14፥10።) የተፈተነበትም የታላቁ ፈተና ምክንያት ይህ ነበር፥ ዲያብሎስ ለአባቱ ለእግዚአብሔር ከመገዛቱና ከመታዘዙ ሊነጥለው ሲሞክር ነበርና። (ማቴ. 4፥4፥7፥10።)

3ኛ ደግሞ ምሥጢረ ሥላሴ አለ። ጌታችን ሁለት ጊዜ እግዚአብሔርን «አምላኬ» ሲል እንዴት ነው? (ማቴ. 27፥46። ዮሐ. 20፥17።) እግዚአብሔር የእኛ አምላክ እንደ ሆነ ዓይነት ሁሉ የኢየሱስ አምላክ ባይሆን እንኳ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ «የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ» ተብሎአል። (2 ቆሮ. 1፥3። ኤፌ. 1፥3፥17። 1 ጴጥ. 1፥3። ራእ. 1፥6።) በም. 15፥28፥ ላይ ደግሞ «በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል» ተባለ። ምሥጢሩን ልንፈታ አንችልም ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ምንም ባህላዊው ክአብ ጋር የተተካከለ ቢሆን ሊሠራ ከመጣበቱ

ሥራ የተነሣ ለአባቱ ዝቅተኛን ቦታ ያዘ። (ፊልጵ. 4፥ 6፥7።) ሥራውንም ሲጨርስ ሥራውንም ራሱንም ለአባቱ ያስረክባል። (ም. 15፥24።) ከእግዚአብሔር ያነሰ መሆኑ አይደለም ነገር ግን በገዛ ፈቃዱ እንዳነሰ ሆኖ መሥራቱ ነው።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 4።

1፤ እንዲሁ ለው እኛን እንደ ከርስቶስ ሎሌዎችና እንደ 2፤ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቁጠረን። እንደዚህም ሲሆን፥ በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል። 3፤ ነገር ግን በእናንተ ዘንድ ወይም በሌላ ሰው ዘንድ ብፈረድ ለእኔ ምንም እይደለም፤ እኔም በራሴ እንኳ አልፈርድም፤ 4፤ በራሴ ላይ ምንም አላውቅምና፥ ነገር ግን በዚህ 5፤ አልጸድቅም፤ እኔን የሚፈርድ ግን ጌታ ነው። ስለዚህም በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሃን የሚያወጣ የልብንም ምክር የሚገልጥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ፤ በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል።

6፤ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ እንዱ በእንዱ ላይ እንዳችሁም እንዳይታበዩ፥ - ከተጻፈው አትለፍ የሚለውን በእኛ ትማሩ ዘንድ፥ ይህን በእናንተ ምክንያት ስለ ራሴና ስለ አጵሎስ 7፤ እንደ ምሳሌ ተናገርሁ። አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?

8፤ አሁን ጠግባችኋል፤ አሁንስ ባለ ጠጎች ሆናችኋል፤ ያለ እኛ ነግሣችኋል፤ እኛ ደግሞ ከእናንተ ጋር እንድንነግሥ 9፤ ብትነግሡ መልካም ይሆን ነበር። ለዓለም ለመላእክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ 10፤ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና። እኛ ስለ ከርስቶስ ሞኞች ነን እናንተ ግን በከርስቶስ ልባሞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን እናንተ ግን ኃይለኞች ናችሁ፤ እናንተ የከበራችሁ 11፤ ናችሁ እኛ ግን የተዋረድን ነን። እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፥ እንድጠማለን፥ እንራቆታልን፥ እንነሰማለን፥ 12፤ እንከራተታለን፥ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደከማለን፤ ሲሰድቡን እንመርቃለን፥ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፥ ከፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፥ እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል።

14፤ እንደምወዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልገሥጻችሁ እንጂ 15፤ ላሳፍራችሁ ይህን አልጽፍም። በክርስቶስ አእላፎች ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የላችሁም፤ እኔ በክርስቶስ 16፤ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና። እንግዲህ እኔን የምትመስሉ 17፤ ሁኑ ብዬ አለምናችኋለሁ። ስለዚህ የምወደውንና የታመነውን በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ፥ እኔም በየስፍራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደማስተምር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚሆነን መንገዴን 18፤ እርሱ ያሳስባችኋል። እንዳንዱ ግን ወደ እናንተ የማልመጣ 19፤ እየመሰላቸው የታበዩ አሉ፤ ነገር ግን ጌታ ቢፈቅድ ፈጥኜ ወደ እናንተ እመጣለሁ፥ የትዕቢተኞችንም ኃይል አውቃለሁ 20፤ እንጂ ቃላቸውን አይደለም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት 21፤ በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና። ምን ትወዳላችሁ? በበትር ወይስ በፍቅርና በየውሃት መንፈስ ልምጣባችሁን?

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ አራት።

ቁ. 1-5። ሐዋርያው ገና የእስተግሪዎችን ነገር ይዘጋኣል። የቆሮንቶስ ከርስቲያኖች በእስተግሪዎቻቸው መካከል ልዩነት እድርገው እንዱን ከእንዱ ጋር እያመዛዘኑ ስለ እንዱ በእንዱ ላይ ይከራከሩ ነበር። ጳውሎስ በም. 3 ላይ የእግዚአብሔርን ልውልነትና የሐዋርያት ኢምንትነት ለማስረዳት ጥሮ እስቀድሞ የገበሬዎችን፥ ቀጥሎም የአናጺዎችን ምሳሌ መሰለላቸው። አሁን ደግሞ እላቡን በመቀጠል ሐዋርያትን እንደ ሎሌዎችና እንደ መጋቢዎች ያደርጋቸዋል። ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ የሾመው ባሪያ የጌታውን እንጀራ ለባልንጀሮች ባሪያዎች እንደሚሰጥ እንዲሁም ጳውሎስና አጵሎስ የእግዚአብሔርን ምሥጢር፥ እርሱም ማለት እግዚአብሔር በከርስቶስ ያደረገልንን ሥራ ሁሉ የሚገልጥ ወንጌልን፥ ለሰው ሁሉ አካፈሉ። (ማቴ. 24፥45-51። ኤፌ. 3፥4-6።) የሚያስተዳድሩት እምጥተውም ለሌሎች የሚያካፍሉት የራሳቸው ሀብት ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው። እንደዚህም ሲሠሩ ታማኞች ሆነው እንዲገኙ ከሁሉ ይልቅ ተፈላጊ ነው ቢሆንም ታማኝነታቸውን የሚመረምር ጌታቸው የሆነ እግዚአብሔር ነው እንጂ የቆሮንቶስ ሰዎች ወይም ሌሎች እይደሉም። (ሮሜ. 14፥4።) ይህ ነውና እነርሱ ቢፈርዱበት ለጳውሎስ ምንም እይደለም። (መርምረው ፈርደውበት እንደ ነበር በዚህ በቅሬ. 3 እና በም. 9፥3 ላይ እናያለን።) ጳውሎስ ራሱ የገዛ መጋቢነቱን ሲመረምር በታማኝነቱ ላይ ምንም አላየም፥ ቢሆንም ይህ አላጸደቀውም። ሥራውን ብቻ ሳይመለከት የልቡንም ምክር የሚገልጥ ይመጣል፥ እርሱም ከሰው ዓይን የተሰወረውን ወደ ብርሃን ያወጣል። (ም. 13፥12።) በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ሎሌና መጋቢ የሆነ ሠራተኛ ሁሉ የተገባውን ምስጋና ይቀበላል፥ ይኸውም ከሰው ዘንድ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «በራሴ ላይ ምንም አላውቅም፥ ነገር ግን በዚህ አልጸድቅም።»ቁ.4 ሐዋርያው «አልጸድቅም» ሲል ምን ማለቱ ነው? ስለ ደኅንነት ወይም ስለ ዘላለም ሕይወት አይናገርም፥ ስለ ፍርድ ነገር መናገሩ ነው እንጂ። «በእናንተ ዘንድ ወይም በሌላ ሰው ዘንድ ብፈረድ ለእኔ ምንም አይደለም» ካለ በኋላ በራሱ ዘንድ ቢፈረድ እንኳ እንደማይጸድቅ ያሳስባል። «መጽደቅ» የሚል ቃል ደንበኛ የፍርድ ቤት ቃል ነው። ዳኛ ተቀምጦ ነገሩን ሁሉ ከሰማ በኋላ በፈቱ የቀረበውን ተከላሽ ያጸድቀዋል። (ነፃ ያደርገዋል) ወይም ይፈርድበታል። በቁ. 4 ላይ እንደዚህ ነው። ጳውሎስ «እኔ በራሴ እንኳ ፈርጂ በመጋቢነቴ ዝንድ የታማኝነት ጉድለት ምንም ባላገኝ እልጸድቅም» ይላል፤ ምክንያቱም ስመፍረድ በቂ እውቀት ስለሌለው ነው። ልብን መርምሮ የልብን ምሥጢር የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነውና ሊያጸድቅ የሚችል እርሱ ብቻ ነው።

ለ. «ስለዚህ ... ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ።» (ቁ 5።) ሰው በእግዚአብሔር እገልጋይ ወይም በመንፈሳዊ እገልግሎቱ ላይ ሲፈርድ ምን ያለ ሞኝነት ነው! ሰው ላይ ላዩን ብቻ ያያል፥ ውስጥ ውስጡ አይታየውም። በመጥፎ አሳብ ወይም በመጥፎ ምክንያት የተሠራ መልካም ሥራ በሰው ዘንድ መልካም ሆኖ ይታይ ይሆናል፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን አስጸያፊ ነው። እኛ ብንፈርድ ፍርዳችን ምናልባት ልክ አይሆንምና የውስጥ ውስጡ ተገልጦ ሁሉ እስኪታወቅ ድረስ

በክርስቶስ ሎሌዎችና በእግዚአብሔር መጋቢዎች ላይ እንፍረድ። (1 ሳሙ. 16፥7። ሮሜ 14፥4።)

እንተሰ የክርስቶስ ሎሌ ሆይ፣ ለው ፈርዶብሃልን? አይዞህ! የለው ፍርድ ምንም እይደለም። ጌታ መጥቶ የተሰወረውን ወደ ብርሃን እስኪያወጣ ድረስ ነፍስህን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ስጥ። (1 ጴጥ. 4፥19።)

ሒ «በጨለማ የተሰወረው።» (ቁ 5።) ይህ የጨለማ ጊዜ ነውና ዛሬ ሁሉም አይታይም። (ም. 13፥12። ኤፌ 6፥12።) ሰው አንድ ሥራ ሲሠራ በምን ምክንያት እንደ ሠራው አልታወቀም። «በጨለማ የተሰወረው» ማለት በሰው ልብ ውስጥ የተደበቀው ምሥጢራዊ ምኞትና ምክንያት እሳብም ሁሉ ማለት ነው። (ሮሜ 2፥16።)

ቁ. 6-13። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ አንዱ ሰው በሌላው ላይ እንዳይፈርዱ ራሱንና አጵሎስን ምሳሌ አድርጎ ነበር። ስለ እነርሱ ብቻ ሊናገር አላሰበም፥ ነገር ግን ራሱንና አጵሎስን ምሳሌ አድርጎ በጠቅላላ ስለ ሰው ሁሉ ተናግሮአል። ትምህርቱንም ለመግለጥ ሦስት ጥያቄዎች ይጠይቃል።

1ኛ፣ አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል?

2ኛ፣ ያልተቀበልኸው ምን አለህ?

3ኛ፣ የተቀበልህ ከሆንህ እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?

ለ1ኛው ጥያቄ መልሱ «እግዚአብሔር አድርጎአል» ነውና መመካታቸው የማይገባ ሆኖ ተገኝቶአል።

ለ2ኛው ጥያቄ መልሱ «ያልተቀበልሁት ምንም የለኝም» ነውና መመካታቸው እንደዚሁ የማይገባ ሆኖ ተገኝቶአል።

ለ3ኛው ጥያቄ መልሱ ደግሞ «ተሳስቼ ነው» የሚል ነውና የሚመኩበት ነገር እንደገና የሳቸውም። በእውነት ብዙ ተቀብለው ነበረ (ም. 1፥5።) ሆኖም የተሰጣቸው የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነበር። (ም. 1፥4።) አሁንም የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለ አንዱ የክርስቶስ አገልጋይ በአንዱ ላይ መታበይ በፍጹም ተገቢ አለመሆኑን ሊረዱ ይችላሉ።

ይሁን እንጂ እንደምን ታበዩ! በጳውሎስ ግምት ሕፃናት ሥጋውያን፥ እንደ ሰውም ልማድ የሚመላለሱ ሲሆኑ (ም. 3፥ 1-3) በራሳቸው ግምት ሙሉአን፥ ፍጹማን ፥ ነገሥታትም ነበሩ፥ (ም. 4፥8።) ሐዋርያው «ገና አትችሉም» (ም. 3፥2) እና «እስከ አሁን ድረስ አትችሉም» (ም. 3፥3) ሲላቸው እነርሱ ወደ መጨረሻ የደረሱ መስሎአቸው አሁን ጠግበናል፥ አሁንስ ባለጠጎች ሆነናል፥ ነግሠናል» አሉ! ግምታቸው ምንኛ ተሳሳተ! «ጠግበናል» ቢሉ በግቴ. 5፥6 ላይ የተጻፈውን ምነው በተመለከቱ! «ባለጠጎች ሆንን» ቢሉ በራእ. 3፥17 ላይ የተጻፈውን ደግሞ ምነው በተመለከቱ! «ነግሠናል» ቢሉ እመላለሳቸው የንጉሥ የድል አመላለስ ነበረን? አልነበረም፥ በብዙ ነገር ተሸነፉ እንጂ! «ሙሉአን ነንና ሐዋርያት የሆኑት እነጳውሎስ ዛሬ አያስፈልጉንም» አሉ። ይሁን እንጂ በሐዋርያት ዘንድ «ነግሠናል» የሚል ስሜት በፍጹም አልነበረምና

የቆሮንቶስ ሰዎች ክነገሡ ሐዋርያት ከእነርሱ ጋር መንገሥ እንደምን በወደዱ ነበር! የሐዋርያት ሁኔታ በዚያ ዘመን እንኳ በፍጹም የመንገሥ ተቃራኒ ነበረ። የቆሮንቶስ ሰዎች «እሁን . . . አሁን›። እያሉ ቀደም ብለው በመድረሳቸውና በመንገሣቸው ሲኮሩ (ቁ. 8) ሐዋርያት «እስከዚህ ሰዓት ድረስ . . . እስከ እሁን ድረስ» እያሉ ለሰዎች መጫወቻ ከሁሉም ይልቅ የኋለኞች ገና መሆናቸውን አዋዩ። (ቁ. 11-13።) ይህም እውነት እንደ ሆነ አንድንረዳ ይህ መልእክት ከመጻፉ ጥቂት ወራት በፊት በኤፌሶን ክተማ በጳውሎስ ላይ የተደረገውን ሁከት እናስብ። (የሐዋ. 19፥ 21-41።) ሐዋርያት ሞኞችና ደካሞች ሲሆኑ የቆሮንቶስ ሰዎች «ልባሞችና ጥበቦች ነን» እሉ። ሐዋርያት በሰው ሁሉ ዘንድ ተዋርደው የተናቁ ሲሆኑ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ተከበሩ። ሐዋርያት ሲራቡ የቆሮንቶስ ሰዎች ጠገቡ። (ቁ. 8።) ሐዋርያትም በቀን እያስተማሩ ሌሊቱን ሁሉ ብርቱ ሥራን በእጃቸው ይሠሩ ነበር። (1 ተሰ. 2፥9። 2 ተሰ. 3፥8።) የቆሮንቶስ ሰዎች ግን በክተማቸው የሚኖሩ ግሪኮች ሁሉ እንደሚያደርጉት ሥራ የባሪያ ጉዳይ ነው» እያሉ ኮርተው ተቀመጡ። ቢሆንም ሐዋርያት በሁሉ የክርስቶስን ቃል ፈጸሙ። (ሉቃ. 6፥27-31።) መንገሥ? የለም፥ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ይንገሡ እንጂ ሐዋርያት ገና እልነገሡም! በመንገሥ ፋንታ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ናቸው። ይህስ ሲሆን በክርስቲያኖችና በሐዋርያት፥ በተግሪዎችና በአስተማሪዎች፥ በልጆችና በአባታቸው መካከል ምንና ምን ያለ ልዩነት ተገኘ! ሐዋርያት በእርግጥ ክርስቶስን መስለዋል፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ግን ክርስቲያናችን በፍጹም አልመሰሉም።

ማስገንዘቢያ።

ሀ. «ክተጻፈው አትለፍ የሚለውን በእኛ ትማሩ ዘንድ።» (ቁ. 6።) መጽሐፍ ቅዱስ በትምህርቱና በታሪኩ በራሳችን እንዳንታበይ ነገር ግን ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ ያስተምረናል። (ሮሜ 15፥4። 1 ቆሮ. 10፥6፡11።) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የተጻፈውን ለምን አላሰቡም? የተጻፈውን እስበው ቢሆን ኖሮ የሠሩትን ታላቅ ስሕተት ባላደረጉም ነበር። እንባቢ ሆይ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን አንተ ታውቀዋለህን? የተጻፈውንስ ተገንዝበህ ትፈጽመዋለህን? ይህን ታደርግ እንደሆነ ክብዙ ስሕተት ይጠብቅሃል።

ሊ «መጫወቻ ሆነናል።» (ቁ 9።) ይህ «መጫወቻ» የተባለው ቃል በእውነት የቲያትር ትይንት ማለት ነው። (ዕብ 10፥33።) በጳውሎስ ዘመን የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ዓመፀኞች ወደ ሕዝብ ጨዋታ ስፍራ ተመርተው ሕዝብ እንዲጫወትባቸውና እንዲዘብትባቸው በግልጥ ይታዩ ነበር። ሐዋርያትም በእንዲህ ያለ ሁኔታ ይኖሩ ነበር፥ ሌላም ጨዋታ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ሐዋርያት የኋለኞች ሆነው ሕዝብን ለማስደሰት ቀረቡ። (ሮሜ. 8፥36። 2 ቆሮ. 11፥23-30።)

ሒ «ለመላእክት ... መጫወቻ ሆነናል።» (ቁ. 9።) መላእክት በዓለም ላይ የሚደረገውን እንዲመለከቱ እናስተውል። መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ይሆናሉ። (ገላ 3፥19። ሉቃ. 1፥11፡26።) በእግዚአብሔር ለሚታመኑት ሰዎች ያገለግላሉ ያግዙማል። (መዝ. 33፥7። ዕብ 1፥14።) ከሚያዩትም ነገር የተነሣ ሊቀየሙ ይችላሉ። (1 ቆሮ. 11፥10።) እገልግሎታቸውን አላቋረጡምና እናስባቸው።

መ. «እኛ ... እናንተ ግን ... » (ቁ. 10።) በቆሮንቶስ ከርስቲያኖችና በሐዋርያት መካከል ትልቅ ልዩነት ነበረ፤ እኛም ስንፈርድ «የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ተሳስተዋል» ብለን ከእነርሱ ይልቅ ሐዋርያትን እናጻድቃለን። ይህም ሲሆን እኛ የዛሬ ክርስቲያኖች ማናቸውን እንመስላለን? የዚያ ዘመን ሁኔታና የዛሬ ዘመን ሁኔታ አንድ አለመሆኑ እርግጥ ነው። የዚያ ዘመን የሮማ መንግሥት የክርስቲያንን ሃይማኖት ሲጠላ የኢትዮጵያ መንግሥታችን ይወደዋል። ይሁን እንጂ ሁኔታችን አኳኋናችንም ልዩ ሲሆን መንፈሳችን የማናቸውን ይመስላል? የቆሮንቶስ ሰዎችን ወይስ የሐዋርያትን? እግዚአብሔር ትሕትናን ሰጥቶ ከኩራት ይጠብቀን! እነዚያ ሐዋርያት የከበሬታን ስፍራ የከበሬታንም ወንበር ሳይፈልጉ (ማቴ. 23-26) ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች ሆኑ። እግዚአብሔር የሐዋርያትን መንፈስ ይስጠን!

ቁ. 14-21። ሐዋርያው ከቁ. 8 እስከ ቁ. 13 ድረስ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖችና በሐዋርያት መካከል የነበረውን ልዩነት የገለጠላቸው ሲያሳፍራቸው ሳይሆን ሊገሥጻቸው ነው። እርሱ መንፈሳዊ አባታቸው ነው ፥ እነርሱም ልጆቼ ናቸው። በሃይማኖታቸው እንዲያድጉ የሚረዱአቸው ብዙ ረዳቶችና አስተማሪዎች ይኑሩአቸው እንጂ በወንጌል የወለዳቸው አባታቸው እርሱው ነው። አባትም ስለ ሆነ ሊገሥጽ እንዲሁም ለማሳፈር መብትና ሥልጣን አለውን አንዳንድ ጊዜ ይገሥጻቸዋል አንዳንድ ጊዜም ደግሞ ያሳፍራቸዋል። (ም. 6፥5፤ 15፥34።) እነርሱም ልጆቼ ናቸውና የወለዳቸውንም አባት ምነው በመሰሉ! ያባታቸውን መልክና መንገድ ረስተዋል እንዴ? ይበሉ እንግዲያው፥ አንድ ሌላ ልጁ የሆነ ጢሞቴዎስ የሚባል ሰው ወደ ቆሮንቶስ ሲመጣ በመንገድ ላይ ነው፤ እርሱ ሲደርስ ያላስባቸዋል። በሐዋርያው ፋንታ ጢሞቴዎስ ስለሚመጣ አንዳንዶች «ጳውሎስ ራሱ አንዳይመጣ ፈርቶአል! ብለዋልን? ይሁን እንጂ ሐዋርያው በእርግጥ ይመጣል፤ ሲመጣ አቅዶአል ለመነሣትም ተዘጋጅቶአል፥ የሚጠባበቀው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ነው። ሲመጣም እውነትን ያውቃል! የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው፤ ማለት የእግዚአብሔር ነገር ባለበት ዘንድ ኃይል ይኖራል በኃይልም ይታወቃል። ለምሳሌ፥ ጳውሎስ በሰበከ ጊዜ ቃሉ ስብከቱም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር። (ም. 2፥4፡5።) ኃይል መኖሩም በሚያምኑት ቁጥር ታውቆአል። እነዚህ በቆሮንቶስ ያሉት የጳውሎስ ተቃዋሚዎች እንዲህ ያለ ኃይል አላቸውን? ሐዋርያው ሲመጣ ያውቃል! ሁለተኛ ደግሞ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት «ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ» ብሎ መናገር ብቻ አይደለም፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው እንጂ። (ማቴ. 7፥21።) እነዚህ በቆሮንቶስ ያሉት ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ኃይል አላቸውን? ይቆዩ! ሐዋርያው ሲመጣ ያውቃል! ሲመጣ ሁሉ ይገለጣል።

ታዲያስ አባታቸው እንዴት ይምጣ? በትርን ይዞ ይምጣን? ወይስ በእርሱና በእነርሱ መካከል ያለው ዝምድና ሳይቀዘቅዝ ሳይሰናከልም ይምጣ? ቃሉን ሰምተው ካልተጸጸቱ በትር ይሆናል፤ የሰሙለት እንደ ሆነ ግን ፍቅርና ኅብረት ደስታም ይሆናል። ይምረጡ።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «እንደምወዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልገሥጻችሁ እንጂ ላሳፍራችሁ ይህን አልጻፍሁም።» (ቁ. 14።) አባቶች የሆኑት ሁሉ በምክርና በተግሣጽ ልጆቻቸውን እንዲያሳድጉ ያስፈልጋል። (ኤፌ. 6፥4።) ይህንም ሲያደርጉ አንዳንድ ጊዜ

እውነቱን በግልጥ በቀጥታም መናገር ተገቢያቸው ይሆናል። ሆኖም ኩራትን መገሠጽ ምን ጊዜም አስቸጋሪ ነውና አባቶች ለመናገር ፈርተው አንዳንድ ጊዜ ዝም ይላሉ። ይህ ግን ከቶ አይገባም። ቀጥተኞን ነገር እንደዚህ የሚናገሩቱ ልጆቻቸውን ሊያሞርዱ ወይም ሊጎዱ ሳይሆን እውነተኛ ጥቅማቸውን በመፈለግ ነውና በሥጋ ሆነ በመንፈስም ሆነ አባቶች የሆኑት ሁሉ የጳውሎስን መንገድ ተከትለው ተገቢ ሥራቸውን እያጓድሉ። ልጆችም እንደዚህ አባቶቻቸው ይህን የሚያደርጉት ስሌትን እንደሚስሉ አድርገው ለልጆቻቸው ነፍስ ሲታገሉ እንደ ሆነ ተረድተው (ዕብ 13፥17) በአባቶቻቸው ሳይማረሩ አባቶቻቸውንም ሳያኮርፉ ተግሣጹን በትሕትና ሁሉ ይቀበሉ።

ለ/ «ሞግዚቶች።» (ቁ. 15።) እነኝህ «ሞግዚቶች» የተባሉ ሰዎች ልጆችን የሚያግዙ ባሪያዎች ነበሩ። በጳውሎስ ዘመን የሮማዊ ጌታቸውን ልጆች ወደ ትምህርት ቤት የሚያደርሱ ነበሩ፥ ወይም ደግሞ እነዚያን ልጆች የሚያስተምሩ ነበሩ። ልጆቹን እየጠበቁ ይወዱአቸው ይሆናል፥ ልጆችም ደግሞ ሞግዚቶችን ይወዱ ይሆናል። ቢሆንም ከሞግዚት አባት በሁሉ በኩል ይበልጣል።

ሐ/ «እኔን የምትመስሉ ሁኑ።» (ቁ. 16።) ከእኛ መካከል ይህን ለማለት የምንደፍር ስንቶች ነን? «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።» (ም. 11፥1።) በሐዋርያት ዘመን ለክርስቲያን የተገባውን አካሄድ የሚያስተምር መጽሐፍ ገና አልተጻፈም ነበርና ሐዋርያት ራሳቸው ምሳሌዎች ወይም ሥዕሎች የሆድ ሆኑ። ዛሬ መጽሐፍ አለ፥ ቢሆንም የምናስተምረውን ወንጌል ልናስመሰግን ብንፈልግ በሕይወታችን (በአካሄዳችን) ኃይሉን እንግለጥ።

መ/ «የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለም።» (ቁ. 20።) ከርስቲያን «ከርስቲያን ነኝ» የሚል ብቻ ሳይሆን በሕይወቱ የክርሰቶስን ኃይል የሚገልጥ ነው። (1 ዮሐ. 3፥7።) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች «ነግሠናል» አሉ። (ቁ. 8።) ሆኖም ጳውሎስ «በሕይወታችሁ ውስጥ ኃይል አለ ወይ?» ብሎ ጠይቆአል። ግድረግ የሚገባቸውን ሲያውቁ ሲያደርጉት ይችላሉ ወይ? (ሮሜ. 7፥22፡23።) በተፈተኑ ጊዜ ፈቃዱን ለማሸነፍ ኃይል አላቸው ወይ? ወይስ ቃል ብቻ ነው? እኛስ? ያላደረግን እንደሆነ መናገር ምን ይጠቅማል? የምናስተምረውንስ እኛ ራሳችን ያልፈጸምን እንደ ሆነ ማስተግራችን ከንቱ አይደለምን? (ሮሜ. 2፥17-23።) «ነግሠናል» ብለን በቃላችን ብናስተምር በሕይወታችን እንደ መንፈላውያን ነገሥታት ሆነን በኃይል እንኑር።

* * * * * * * *

ምዕራፍ 5።

[1] በአጭር ቃል በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ [2] ነው፥ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው ይኖራልና። እናንተም ታብያችኋል፤ ይልቅስ እንድታዝኑ አይገባችሁምን? ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ።

[3፤4] እኔ ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን፥ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ፥ ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ ይህን እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጀበታለሁ፤ እናንተና መንፈሴም ከጌታችን [5] ከኢየሱስ ክርስቶስ ሃይል ጋር ተሰብስበን፥ መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው።

[6] መመካታችሁ መልካም አይደለም። ጥቂት እርሾ ሊጡን [7] ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን? እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ። [8] ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፤ ስለዚህ በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ አንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም።

[9] ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ። [10] በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞችን፥ ወይም ገንዘብን የሚመኙትን ነጣቂዎችንም፥ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩትን አላልሁም፥ ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር። [11] አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖት የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ አጽፍላችኋለሁ፤ እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ። [12] በውጭ ባሉ ሰዎች ላይ መፍረድ ምን አግዶኝ? [13] በውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ እናንተ አትፈርዱምን? በውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ አምስት።

ቁ. 1-8። ሐዋርያው እስከ አሁን ድረስ ነገሩን ሳያጸናባቸው ለዘብ ባለው በትምህርት ቃል ኩራታቸውንና ትምክህታቸውን አመልክቶ ነበር፥ አሁን ግን የተሰማባቸውን ወሬ በግልጥ ይነግራቸዋል። አነርሱ በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ በተሰጣቸው በእግዚአብሔር ጸጋ ሲኮሩ በመካከላቸው እንደ ጭንቁር የሚባላ ነገር ተገኘ፥ አርሱም ሴሰኝነት። «ይወራል» አለ። ስለምን? ቢሉ፥ እንዲህ ያለ ነገር ሊኖር ሳይገለጥ ይቀራልን? አይቀርም! የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስም በሚጠቀስበት ስፍራ ሁሉ በክርስቲያኖቹ መካከል አንድ ልዩ ነገር እንዳለ በሰው ሁሉ ዘንድ ታውቆአል። ሰው ሁሉ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው እንዳለ ያውቃል። ወሬው ተሰምቶአል ነገሩም ተገልጦ ታውቆአል። አሕዛብና እረመኔዎች ስንኳ የማያደርጉት ነገር ነው፥ በብሉይ ኪዳንም አንዳንድ ጊዜ ሲደረግ ጠንቁ ከባድ ሆኖአል። (ዘሌዋ. 18፥8፤20፥11። ዘፍጥ. 35፥22፤49፥4። 1 ዜና. 5፥1። ደግሞ 2 ሳሙ. 16፥22፤20፥3።) ይሁን እንጂ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል ተደርጎአል፥ በሁሉም ዘንድ ታውቆአል፥ የቆሮንቶስ ማኅበርም ዝም ብሎአል። ታላቁ ጥፋት ይህ ነው። ኃጢአቱ ራሱ ከፍ ያለ ቢሆንም የቤተ ክርስቲያን ዝምታ (እንዳችን አለማድረግ) የባሰ ነው። ይህን የሚመስል ነገር በመካከላቸው በመገኘቱ ምንኛ ማዘን ይገባቸው ነበር! ያ ሰው ከመካከላቸው እንዲወገድ ከቁጥራቸውም እንዲቀነስ ይገባ ነበርና እነርሱ እንደ ሞተ ወንድም ቆጥረውት ማልቀስ ይገባቸው ነበር። ዳሩ ግን በማስወገድና በማልቀስ ፋንታ ታበዩ! (ሮሜ. 1፥32።) በተሰጣቸው ጸጋ ይኩሩ እንጂ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያናቸው ሁኔታ በዚህ ነገር ምንኛ ተገለጠ! የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ረከሰ፥ እነርሱም ዘም አሉ!

እነርሱ ዝም ይበሉ አይፈርዱም እንጂ ሐዋርያው ከአሁን አስቀድሞ ፈርዶአል። በሥጋ ከእነርሱ ጋር አይደለም፥ ቢሆንም በመንፈስ ከእነርሱ ጋር ነውና ለመፍረድ ይችላል። እርሱ በሩቅ አገር ሆኖ ነገሩን አንሥቶ መርምሮ የተገባውን ፍርድ ሰጥቶአል። አሁንም ማኅበሩ እንደዚሁ ያድርግ። ከዚህ በፊት እንደዚህ ማድረግ ይገባቸው ነበርና አሁን ማኅበርተኞቹና ሐዋርያው (በመንፈስ) ከጌታ ኃይል ጋር ይሰብሰቡ በሙሉ ሥልጣንም ይፍረዱ ሰውየውንም ለሰይጣን አሳልፈው ይስጡ። ይህንም የሚያደርጉት መጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለማጥራት ነው፤ ሁለተኛም ደግሞ፥ የበደለኛውን መንፈስ ለማዳን ነው።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ተመክተዋል፤ ሆኖም የሚመኩበት ነገር ብዙ አልነበራቸውም። በእውነቱ ከመመካት ይልቅ ማፈር ይሻላቸው ነበር። «ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል» የሚል ተረት አለ። (ገላ. 5፥9።) ጥቂት እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያቦካ ሁሉ እንዲሁም ትንሽ የመሰለ ኃጢአት ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ያረክሳል። ሐዋርያውም አይሁዳዊ ነውና «እርሾ» ሲል ወዲያውኑ ስለ ፋሲካ በዓል የግድ ያስባል። ምክንያቱም እሥራኤላውያን ከምድረ ግብፅ ባርነት በወጡበት ቀን ዋዜማ የፋሲካን በግ ካልቦካ እንጀራ ከቂጣ ጋር በልተዋል። ያ ቀን ያም ሥርዓት ዝክር ሆነላቸው በዓመት በዓመትም ይጠብቁት ነበር። ፋሲካውም የበዓል መጀመሪያ ቀን ነበረ፥ በዚያም ቀን እርሾ ከቤታቸው ተወገደ። ከዚያም ቀን ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ የቂጣ በዓል ተደረገ እርሾም አልተበላም። እግዚአብሔር በእነዚያ በበዓል ቀኖች ውስጥ እርሾ ያለበትን የሚበላ

ሁሉ ይጥፋ አለ። (ዘፀአ. 12፥6፡ 14፡ 15፥ 13፥ 3-10። ዘዳግ. 16፥ 1-8።) ስለዚህ አሁን ጳውሎስ «እርሾ» ሊል ወዲያውኑ ስለ በጎ አሰበ። በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ እርሾ የሚያረክስ የኃጢአት ምሳሌ ነው። (ሉቃ. 12፥ 1።) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ነጽተው ነበርና (ዮሐ. 15፥ 3) ሐዋርያው «ያለ እርሾ አላችሁ» ይላቸዋል። ከሰይጣን ተገዢነት ወጥተው ነበር ይሽውም በእውነተኛ በፋሲካ በግ፥ ማለት በክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ለእነዚህ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ፋሲካ ሆኖ ታርዶላቸው ነበርና እነርሱ አሁን የቂጣ በዓል እንዲያደርጉ ያስፈልግ ነበር፥ ማለት እርሾን (ኃጢአትን) ከመካከላቸው በፍጹም ማስወገድ ያስፈልጋቸው ነበር። አዲስ ሊጥ ሆነው ነበርና አሮጌውን እርሾ ማለት ክፋትንና ግፍን፥ አስወግደው በቅንነትና በእውነት መኖር ይገባቸው ነበር።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ።» (ቁ. 2።) ሐዋርያው ያለበትን ኃላፊነት ተረድቶ የቆሮንቶስን ሰዎች ከመቆጣትና ከመገሠጽ አልቀረም ነበር። (ም. 4፥ 14፡ 11-21።) እርሱም እኔን የምትመስሉ ሁኑ ብሎ ለምናአቸዋል። ታዲያስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ያለባቸውን ኃላፊነት ተረድተው ይህን ሥራ በሠራው ሰው ላይ ላይፈርዱ ለምን ቀሩ? እውነት ነው፥ ተቀምጦ ዝም ማለት ይቀላል፤ ቢሆንም ምእመናን ማኅበራቸውን ንጹሕ እንደ ሆነ ለመጠበቅ ኃላፊነት አላቸውና መፍረድ ሰውየውንም ማስወገድ ይገባቸው ነበር። ኃላፊነታችሁን ለምን አልፈጸማችሁም? ብሎ ሐዋርያው በመገረም ጠየቃቸው። መገሠጽና መፍረድ የተገባ ሊሆን ቸል ብሎ መቀመጥ መጥፎ ነው መጥፎም ፍሬ ያፈራል። ካህኑ ዔሊ ልጆቹን አልከለከለምና እግዚአብሔር ፈረደበት። (1 ሳሙ. 2፥29፤ 3፡ 14።) ንጉሥ ዳዊት ነፍስ ገዳይ የሆነ ልጁን አቢሴሎምን እንደሚገባ ሁሉ ላይፈርድበት ስለ ቀረ በዚያው ልጅ ከዙፋኑ ተባረረ። (2 ሳሙ. 13፥28፤ 14፥28-33፤ 15፥13-16።) አባት ልጁን ለመቅጣት ታዝዞአል። (ምሳ. 13፥24፤29፥17።) አስተማሪ ተማሪዎቹን ሐዋርያ ክርስቲያኖችን፥ ቤተ ክርስቲያን አባሎችዋን ለመገሠጽና ለመቅጣት ኃላፊነት አላቸው፥ ይህንም መፈጸም የግድ ያስፈልጋቸዋል። ከመፈጸምም ቢቀሩ ተወቃሾች ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ «በሌሎች ኃጢአት አትተባበር፤ ራስህን በንጽሕና ጠብቅ» ብሎአል። (1 ጢሞ. 5፥22።)

ተወቃሾች ብቻ የሚሆኑ አይደለም፥ ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚያመለክተው ሁሉ ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል፤ ማለት፥ ካልታከመ ቁስሉ ይስፋፋል በሽታውም ይበረታል። የበሰበሰ ፍሬ ሌሎችን ፍሬዎች እንደሚያበላብስ እንዲሁ አንድ ኃጢአተኛ ቤተ ክርስቲያንን ሁሉ ወደ ማርከስ ያደርሳል። የአካንን ታሪክ እናስብ። (ኢያ. 7፥ 1፡ 10፡ 11።) ከተከለከለው ነገር የወሰደ አንድ ሰው እርሱም አካን ብቻ ነበረ፥፤ ቢሆንም እግዚአብሔር «እሥራኤል ኃጢአትን ሠርተዋል» አለ። የአካን ኃጢአት እሥራኤልን በምላ አረከሰ ማለት ነው። ኃጢአት ተላላፊ በሽታ ነውና ዝም ልንለው አንችልም። በቤተ ክርስቲያን (በክርስቲያን ማኅበር) ኃጢአት የትም ዘንድ ቢገኝ ኃጢአትንም የሠራው ሰው ማናቸውም ቢሆን ክፉው ከመካከል እንዲወጣ የግድ አስፈላጊ ነው። (ቁ. 13።) ይህ ነገር ስንቱን ጊዜ ይረሳል! እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፥ ዓይናቹ ክፉን እንዳያዩ ንጹሐን ናቸው (ዕንባ. 1፥13) ፥ ወገናቹም እንደ እርሱ ቅዱስ ይሆኑ

ዘንድ ይፈልጋል። (1 ጴጥ. 1፥15፡16።) በማኅበር (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ኃጢአት ይኖር ዘንድ መፍቀድ የእግዚአብሔርን በረከትና ኃይል ማላጣት ነው። ማኅበሩ (ቤተ ክርስቲያኑ) ንጹሕ ሆኖ ይጠበቅ ዘንድ ከሁሉ አስፈላጊ ነውና አስቀድሞ አገልጋዮቹ፥ ከዚያም በኋላ ማኅበርተኞቹ ሁሉ፥ በእግዚአብሔር ፊት በቅድስናና በንጽሕና ሁሉ አንዲራመዱ ለማየት የማኅበሩ ባለሥልጣኖች ዓይነተኛ ተግባራቸው ነው።

ለ/ «መንፈሱበጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው።» (ቁ. 5።) «ለሰይጣን መስጠት» ምን ማለት ነው? ተብሎ ቢጠየቅ፡- ቁ. 5 በቁ. 2 ና በቁ. 13 ይተረጎማል። በቁ. 5 ላይ «ለሰይጣን እንዲሰጥ» ሲባል በቁ. 2 ላይ «ከመካከላችሁ ይወገድ» በቁ. 13 ላይም «ከመካከላችሁ አውጡት» ተባለ። እንግዲህ ለሰይጣን መስጠት ማለት ከቤተ ክርስቲያንና ከኅብረትዋ ማስወገድ ወይም ማውጣት ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን የደኅንነት ክልል ነው፥ ከቤተ ክርስቲያንም ከልል ውጭ ያለው የዚህ ዓለም ገዢ የሰይጣን ግዛት ነው። (ሉቃ. 4፥6። የሐዋ. 26፥18። ቆላ. 1፥13። 1 ዮሐ5፥19።) ስለዚህ ከቤተ ክርስቲያን ማውጣት ማለት ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት ማለት ነው። እንደዚህ ማውጣት አስቀድሞ ለቅዱስ ጴጥሮስ ከዚያም በኋላ ለሐዋርያት ሁሉ የተሰጠ የማሰርና የመፍታት (የግዝት) ሥልጣን ነው። (ማቴ. 16፥19፤ 18፥18።) «ማሰር» እና «መፍታት» አዲስ በሐዋርያት ዘመን የተጀመረ ነገር ላይሆን በአይሁድ ዘንድ አጅግ የታወቀ ሥርዓት ነበረ፤ ምክንያቱም የቤተ መቅደስ ካህናት በብሉይ ኪዳን ዘመን የያዙት ሥልጣን ነው። «ማሰር» ማለት «መከልከል»፥ «መፍታት» ማለት «መፍቀድ» ማለት ነው። የብሉይ ኪዳን ካህናት በአንብሮተ እድ በተሾሙ ጊዜ ሰው ወደ ቤተ መቅደስ እንዲገባ ለመፍቀድ፥ እንዳይገባም ለመከልከል ሥልጣንን ተቀብለዋል፥ በጌታችንም ዘመን ገና ሲሠሩበት ተገኝተዋል። (ዮሐ 9፥ 22፡34፤12፥42። ሉቃ. 6፥22።) እንደዚሁ ደግሞ የሃይማኖትን ትምህርት መርምረው «ይህ እውነት ነው» ብለው ለመፍታት «ይህስ ሐሰት ነው» ብለውም ለማሰር ሥልጣን ነበራቸው። ክርስቶስ ይህን ሥልጣን ለቤተ ክርስቲያን አስተላልፎአል። እርዮስ አቡሊናሪስ፥ ንእስጥሮስ፥ አውጣኬ፥ እነዚህንም የመሳሰሉት በተነሡ ጊዜ አብያተ ክርስቲያናት በጉባኤ ተሰብስበው ትምህርታቸውን መረመሩ፥ የሀሰት መሆኑን ፈርደው አሰሩት፥ መናፍቃንንም ገዝተው ከቤተ ክርስቲያን አስወጡአቸው፥ እግዚአብሔርም ፍርዳቸውን አጸደቀ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 18፥17 ላይ «ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ» ሲል ደንቡን አመልክቶአል፥ ቅዱስ ጳውሎስም በሌላ ስፍራ ፈጸመው (1 ጢሞ. 1፥20)፥ እዚህም በ1 ቆሮ. 5፥5 ላይ የቆሮንቶስ ሕዝብ ክርስቲያን፥ በተለይ የቤተ ክርስቲያን ቀላውስት፥ እንዲፈጽሙት መክሮአቸዋል። ሰውየውን ከቤተ ክርስቲያን ማውጣት ተገቢአቸው ነበረ። የዛሬ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ይህን በመፈጸም ራስዋን ማንጻት፥ ንጹሕም ሆና መጠበቅ ይገባታል።

ይሁን እንጂ ለሰይጣን የሚሰጡት መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ትድን ዘንድ ነው እንጂ ሰውየው ለዘለዓለም እንዲጠፋ ከቶ አይደለም። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ተመልሶ እንዲድን ይፈልጋል እንጂ እንዲጠፋ አይፈልግም። (ሕዝ. 33፥11።) የቆሮንቶስም ሰዎች ይህን ሰው ከቤተ ክርስቲያን ሊያወጡት ጥቅሙን እንጂ ጉዳቱን መፈለጋቸው አይደለም።

መንፈሱ ትዳን እንጂ ሥጋው እንዲጠፋ ታስቦአል። ይህስ እንደምን ይሆናል? ለዚህ ነገር ሁለት ትርጓሜዎች አሉ።1 ኛ፡ ሐዋርያው በጻፈው በግሪክ ቋንቋ በዚህ ቁጥር (ቁ. 5) ላይ የሚገኘው «ለሥጋው» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በቁ. 3 ላይ ደግሞ «በሥጋ» ተብሎ ከተተረጎመው ቃል ልዩ ነውና በቁ. 3 ላይ ስለ ሰውነቱ ሲናገር በቁ. 5 ላይ ስለ ሌላ ነገር እርሱም ስለ ሥጋዊነቱ ተናገረ ይባላል። «ሥጋዊነቱ እንዲጠፋ» ማለት ሥጋዊ ምኞቱ እንዲጠፋ ማለት ነውና ከቤተ ክርስቲያን ያወጡት ከየት ዘንድ እንደ ወደቀ አስቦ ከኃዘንና ከእፍረት ብዛት ከብቸኝነቱም ስሜት የተነሣ በሠራው ኃጢአት እንዲጸጸትና ከሥጋዊ ምኞቱ ሸሽቶ እንዲድን ነው። መጸጸቱ ወደ ሥጋዊ ምኞቱ ጥፋት ያደርሰዋል ማለት ነው። (መላ. 23፡14።) ይህስ ይቻላል። 2ኛ ትርጓሜ ግን አለ፡ እርሱም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡- በዚያ ዘመን የሥጋ በሽታ ሞትም ስንኳ ኃጢአት በሠሩት ክርስቲያኖች ላይና ቤተ ክርስቲያን በገሠጻቸው ላይ ይደርስ እንደ ነበር ግልጥ ነው። ም. 11፡30። የሐዋ. 5፡1-11።) እንደዚህም ደግሞ ሰይጣን የሥጋ በሽታን ሊያመጣ እንደሚችል ግልጥ ነው። (ሉቃ. 13፡16። 2 ቆሮ. 12፡7።) ይህም ስለ ሆነ ሐዋርያው በእውነት ስለ ሥጋ በሽታ የተናገረ ይመስላል። ይሁን እንጂ፡ ከቤተ ክርስቲያን በመውጣቱ በደለኛው ለዘለዓለም እንዲጠፋ አልታሰበም። ሥጋው ይጠፋ ይሆናል፡ በኋለኛው በጌታ ቀን ግን መንፈሱ ድኖ እርሱ በጌታ ወገኖች መካከል እንዲገኝ ታስቦአል። ግዝት ከቤተ ክርስቲያን እንጂ ከመንግሥተ ሰማያት አያወጣም።

ቁ. 9-13። ሐዋርያው ከዚህ በፊት ወረቀት ጽፎላቸው ኖሮ ከሴሰኞች ጋር እንዳይተባበሩ አስጠንቅቆአቸው ኖሮአል። ይህንም ሲጽፍ የተናገረው ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ነበረ እንጂ ስለ ዓለም ሁሉ ሰው አልነበረም። በዓለም፡ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ካሉት ሴሰኞችና እነርሱን ከሚመሳሰሉት ጋር እንዳይተባበሩ ሳይሆን ወንድም ከተባለ ሴሰኛ ክርስቲያን ጋር እንዳይተባበሩ ነግሮአቸዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች ግን ተሳስተው በጠቅላላው ስለዚህ ዓለም ሴሰኞች የተናገረ መስሎአቸው በነገሩ ተቸግረው «ይህ እንደምን ይቻለናል?» ብሰው ሊጠይቁት ጽፈው ነበር። አሁንም በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ጳውሎስ «የለም! የተናገርሁት ስለ ክርስቲያኖች ነበረ እንጂ ስለ ውጭ ሰው አልነበረም» ብሎ መልሶ ጽፎአል። መቸገራቸውን መቼም የምንገነዘበው ነው፤ ምክንያቱን በቆሮንቶስ ከተማ እንዲህ ያለ ኃጢአት እንደ በዛ ከዚህ በፊት አይተናል። በጠቅላላውም ከእነዚህ ኃጢአተኞች ጋር ከመገናኘት ከተከለከሉ እንደምን በኖሩ ነበር? ሐዋርያው ግን የጻፈው የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና እንዲጠብቁና «ክርስቲያን» ተብሎ እንዲህ ያለውን ኃጢአት በሠራው ሰው ላይ እንዲፈርዱና ከመካከላቸው እንዲያወጡት ፈልጎ ነው። ይህም የአሁኑን ኃጢአተኛ ከመካከላቸው የሚያወጡበት ሁለተኛ ምክንያት ነው። መጀመሪያ ምክንያቱ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዳያረክስ ሲሆን (ቁ. 1-8) ሁለተኛው ምክንያት ሐዋርያው እንደዚህ ካለ ሰው ጋር እንዳትተባበሩ ከእርሱም ጋር መብል እንኳን አትብሉ ብሎ አዝዞአቸው ስለ ነበረ ነው። (ቁ. 9-13።) ጳውሎስ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ባሉት ሰዎች ላይ ለመፍረድ አላሰበም፤ በእነርሱ ላይ እግዚአብሔር ይፈርዳል። ሆኖም በቤተ ክርስቲያን ላይ መፍረድና የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕናና ቅድስና መጠበቅ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ነውና ጳውሎስ «እናንተ አትፈርዱምን?» ብሎ ይጠይቃቸዋል። መፍረድ የእርሱ ኃላፊነት ሳይሆን የእነርሱ ነበረ፤ መፍረድም ይገባቸው ነበር፡ ነገር ግን አላደረጉትም። መጽሐፍ ቅዱስ «ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት»

ብሎ አዝዞአል። (ዘዳግ. 17፡7። 21፡21። 22፡21፡22-24።) እነርሱ ግን ይህን ሰው እላወጡምና በደለኞች ሆነው ተገኙ።

ማስገንዘቢያ።

«ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ።» (ቁ. 11።) ሐዋርያት ከሰጡት ትእዛዛት አንዱ ይህ ነው። እነዚህ ሰዎች ወንድሞች (ክርስቲያኖች) ቢባሉም ከእነርሱ ጋር እንዳንተባበር ከእነርሱም ጋር አንዳንበላ ታዝዘን። (እነዚህን የሚመሳሰሉቱ «ክርስቲያኖች» እንደ ተባሉ እንጂ ክርስቲያኖች በእውነት እንዳልሆኑ እናስታውስ።) ከእነርሱም ጋር የማንተባበር የማንበላም እነማን ናቸው? «ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ» የተባሉት ናቸዋ!

«ሴሰኛ» ሁለት ሚስቶች ያሉት፡ እየተፋታ የሚኖር፡ በሴተኛ አዳሪ ቤት የሚያመሽ፡ የዝሙት ጨዋታን የሚወድ በመካከላችን (በማኅበራችን) ይገኛልን? ሐዋርያው «ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ ከእርሱም ጋር መብል እንኳን አትብሉ፡ ከመካከላችሁ አውጡት እንጂ» ብሎአል።

«ገንዘብ የሚመኝ» «ሕይወት እኮ ገንዘብን መስብሰብ ነው» የሚል ለነዳያንና ለቤተ ክርስቲያን ሳይሰጥ፡ ገንዘቡን ሁሉ በራሱ ላይ የሚያውል፡ ጉቦን የሚቀበል የመንግሥትን ገንዘብ የሚሰርቅ በመካከላችን (በማኅበራችን) ይገኛልን? ሐዋርያው «ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ ከእርሱም ጋር መብል እንኳን አትብሉ፡ ከመካከላችሁ አውጡት እንጂ» ብሎአል።

«ጣዖትን የሚያመልክ» በቡና ሰዓት ለመናፍስት የምትበትንና የምትጥል፡ በተቸገረ ጊዜ ወደ ቃልቻ ቤት የሚሄድ (ዘዳግ. 18፡9-12)፡ ከሞከብትን እየቆጠረ መድኃኒት እየማሰና እየቆረጠም አምልኮ ባዕድን የሚያደርግ በመካከላችሁን (በማኅበራችን) ይገኛልን? ሐዋርያው «ከእርሱ (ወይም ከእርሰዋ) ጋር እንዳትተባበሩ ከእርሱም (ከእርሰዋም) ጋር መብል እንኳን አትብሉ፡ ከመካከላችሁ አውጡት (አውጡአት) እንጂ» ብሎአል።

«ተሳዳቢ» አንደበቱን የማይገታ፡ (ያዕ 1፡26)፡ በወንድሙ ላይ ተቆጥቶ የሚሳደብ፡ (ማቴ. 5፡22)፡ በአጉል ቃል የሚናገር ሰው በመካከላችን (በማኅበራችን) ይገኛልን? ሐዋርያው «ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ ከእርሱም ጋር መብል እንኳን አትብሉ፡ ከመካከላችሁ አውጡት እንጂ» ብሎአል።

«ሰካር» የሰካርን ጓደኞች ተመልከቱ!˜ በዚህ ቁጥር ላይ የተጻፉት ናቸው። እነኚህ ሁሉ አንድ ዓይነት ሰዎች ናቸው። ሰካር በመካከላችን (በማኅበራችን) ይገኛልን? ሐዋርያው «ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ ከእርሱም ጋር መብል እንኳን አትብሉ፡ ከመካከላችሁ አውጡት እንጂ» ብሎአል።

«ነጣቂ»

የማይገባውን ያህል የሚወስድ፥ በንግዱ ወይም በሸቀጡ የሚያታልል፥ ከድሆችና ረዳት ዘመድ ከሌላቸው ዘንድ የሚነጥቅ የሚቀማም በመካከላችን (በማኅበራችን) ይገኛልን? ሐዋርያው «ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ ከእርሱም ጋር መብል እንኳን አትብሉ፥ ከመካከላችሁ አውጡት እንጂ» ብሎአል።

ክርስቲያን ነኝ ብሎ ሕይወቱ ክርስቲያንነቱን ከሚክድ ሰው ጋር እንዳንተባበር ታዝዘናል። ማኅበራችንን ብናጣራ አይሻልምን? እስከ አሁን ድረስ በእነዚህ ላይ ከመፍረድ ለምን ቀረን?

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 6።

1፤ ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ 2፤ ይደፍራልን? ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን? በዓለምስ ላይ ብትፈርዱ ከሁሉ ይልቅ ትንሽ ስለሚሆን 3፤ ነገር ልትፈርዱ አትበቁምን? የትዳር ጉዳይ ይቅርና በመላእክት 4፤ እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን? እንግዲህ ስለ ትዳር ጉዳይ የፍርድ ቤት ቢያስፈልጋችሁ በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን 5፤ ሰዎች ፈራጆች አድርጋችሁ ታስቀምጣላችሁን? አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ። እንደዚህ ነውን? በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ 6፤ ዘንድ አይገኝምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል፥ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን?

7፤ እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በእርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ 8፤ አይሻልምን? ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ፥ ያውም ወንድሞቻችሁን።

9፤ ወይስ ዓመጸኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም 10፤ ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካራሞች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም 11፤ ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።

12፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም። 13፤ መብል ለሆድ ነው፥ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ 14፤ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሥጋ ነው፤ እግዚአብሔርም 15፤ ጌታንም አስነሣ እኛንም በኃይሉ ያስነሣናል። ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? 16፤ አይገባም። ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ 17፤ ተብሎአልና። ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ 18፤ ነው። ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው 19፤20 ላይ ኃጢአትን ይሠራል። ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ ስድስት።

ቁ. 1-11። በም. 5 ላይ እንደተመለከተው ሁሉ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ከባልንጀራዎቻቸው አንዱ በእሕዛብ ስንኳ የማይገኝ ዓይነት ታላቅ ኃጢአት ቢሠራ ሊፈርዱበት አይቸኩሉ እንጂ ከመካከላቸው አንዱ ከባልነጀራው ጋር ከሁሉ ይልቅ ትንሽ በሆነ ነገር ለመሟገትና ነገሩን ለፍርድ ቤት ለማድረስ እንዳልቆየ በም. 6 ላይ እናያለን። ሐዋርያው ከሰማባቸው ነገሮች ይህ ሦስተኛው ነው። መጀመሪያው የክርክር ነገር ነበረ፥ (ም. 1-4)፥ ሁለተኛውም የዝሙት ነገር (ም. 5)፥ አሁንም ሦስተኛው የሙግት ነገር አለ።

እነዚህ እርስ በርሳቸው የተሟገቱ ክርስቲያኖች በማኅበሩ ፊት በመፋረድ ፋንታ ከርስቲያን ባልሆኑት ዳኞች ፊት ተፋረዱ። ክርስቶስ በማቴ. 18፥15-17 ላይ ለክርስቲያን የተገባውን ሥርዓት አመለከተ። ጉዳዩ በወንድምና በወንድም መካከል በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ይጠበቃል እንጂ የተበደሰው ሰው ነገሩን ወደ ውጭ ወደ ፍርድ ቤት እንዲያደርሰው አልታሰበም። ይህ ደግሞ በእሥራኤላውያን መካከል ደንብ ነበረ። እነርሱ በእሕዛብ ፊት ሳይፋረዱ ነገሩን በመካከላቸው በሽማግሌዎች ይጨርሱ ነበር። እንደዚሁም ክርስቲያኖች ነገሩን እርስ በርሳቸው ሊጨርሱ ይችሉ ነበር፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለ ነገር በሽምግልና እንዲጨረስ እንጂ ወደ ፍርድ ቤት አንዳይደርስ የግሪክና የሮማ ሕጎች ፈቅደዋል። ስለዚህ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በቅዱሳን (በክርስቲያኖች) ፊት በመፋረድ ፋንታ ክርስቲያን ባልሆኑት (በዓመፀኞች) ፈት በመፋረዳቸው ታላቅ ጥፋት አጥፍተዋል ሐዋርያውም በነገሩ ተደንቆአል።

ክርስቲያኖችም ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄዱ አስፈላጊ አልነበረም። ስለምን? ቢሉ፥ ከማያምኑ ሰዎች (ከዓመፀኞች) ፍርድ ይልቅ የሚያምኑት (የቅዱሳን፥ የክርስቲያኖች) ፍርድ ይሻላልና። የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ ከተነገረ 9ማቴ. 19፥28። ዳን. 7፥22። ራእ. 20፥4) እነዚያ ቅዱሳን ከሁሉ ይልቅ ትንሽ ስለሚሆን ነገር ዛሬ ለመፍረድ የበቁ አይደሉምን? ምእመናን በመላእክት ስንኳ የሚፈርዱ ሲሆኑ፥ የሚሟገቱበትም ስለ ትዳር ጉዳይ ሲሆን፥ እነርሱ ራሳቸው ሊጨርሱት አይችሉምን? አላምረው ይችላሉ! ታዲያስ ዳኛ ሲያስፈልግ ቤተ ክርስቲያን የምትንቃቸውን የውጭ ሰዎችን፥ አረመኔዎችን፥ ፈራጆች ለምን አድርገዋቸዋል? በእውነቱ የሚያሳፍር ነገር ነበረና ሐዋርያው በማላፈር ወደሚገባው ሊቀስቅሳቸው ወድዶአል። ከዚህ ቀድም የቆሮንቶስ ሰዎች በአስተዋይነታቸው ተመክተው ነበር፥ አሁንስ አስተዋይ ወዴት ጠፋ? በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል የለም እንዴ? በወንድማማች መካከል የእርስ በርስ ሙግት በጭራሽ እያስፈለግምና ሙግት በመካከላቸው በመገኘቱ ስንኳ ጉድለታቸው ተገለጠ። ይልቁንስ እንደዚህ ቢሆን ይሻላል ብሎ ክርስቶስ አስተምሮናልና (ማቴ. 5፥39-41፤ 18፥32-35) ለእየራሳቸው መርታትን ላይፈልጉ ሙግትን ሁሉ አስቀርተው ቢበደሉና ቢታለሉ ይሻላል። ይህን ግን በማድረግ ፋንታ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች አውቀው በደሉ አታለሉም፥ ያውም የውጭ ሰዎችን ሳይሆን ወንድሞቻቸውን!

የያዙት መንገድ እኮ የዓመፀኞች፥ በክርስቶስ ያላመኑት የዚህ ዓለም ሰዎች መንገድ ነበረ። ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱምና እንደ እነርሱ ሆነው

ከበደሉና ካታለሉ ከእነርሱ ጋር እንዳይኮነኑ ይጠንቀቁ! ዱሮ በቅሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል አንዳንዶቹ እንደነዚህ የሚመላለሉውን ኃጢአት ይሠሩ ነበር፥ ዛሬ ግን ታጥበዋል፥ ተቀድሰዋል፥ ጸድቀዋልና ዓመፀኞችን መምሰል በፍጹም አይገባቸውም።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቁ. 6 ላይ « ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል›። ሲል ቀጥሎም በቁ. 7 ላይ «እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው» ሲል በክርስቲያኖች መካከል ጭቅጭቅ በፍጹም እንዳይደረግ ማለቱ ነው። ጭቅጭቅ የሚመጣ ከጥል ነው፥ ጥልም የሚመጣ ከቁጣ ነው ክርስቶስም «በውንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል» ብሎአል። ((ማቴ.5፥22።) ቅዱስ ያዕቆብም «ለው ሁሉ ከቁጣ የዘገየ ይሁን፤ የለው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና» ብሎአል። (ያዕ. 1፥19፡20።) ከቁጣ በተለይም በወንድም ላይ ከመቆጣት እንጠንቀቅ ወደ ፍርድ ቤት የሚያደርሰን ቁጣ ነውና።

ክርስቲያኖች የሆንን ይህን ነገር ልብ እናድርገው። እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ተጠርተናልና፥ ክርስቲያንም ሁሉ ወንድማችን ነውና፥ እንደምን አድርገን ነገሩን አጽንተን እስከ ፍርድ ቤት እናደርስዋለን? ይህንስ ብናደርግ በደለኞች ሆነን እንገኝ የለምን? ጳውሎስ እንዲህ ያለውን ነገር ማድረግ ፈጽሞ ጉድለት ነው ይላል። በዚህ ፋንታ እኛ ራሳችን ብንበደል ተበድለንም ብንታገስና ይቅር ብንል በጣም ይሻላል።

እርግጥ ነው፥ ክርስቲያን የሚኖረው በዓለም ነውና (ዮሐ. 17፥11) በዓለም ጉዳይ ተይዞ ወደ ዳኞች ፈት የሚሄድበት ጊዜ የግድ ይኖረዋል። ይሁንና ክርስቲያን ክርስቲያንን እንዲከስ ከቶ አያምርም፥ ቢከስም በማያምኑ በውጭ ሰዎች ሳያደርገው በቤተ ክርስቲያን ፈት ይክሰስው። እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው ራሱን ለማጽደቅ አይቸኩል ወደ ፍርድ ቤትም አይሩጥ።

ለ/ «ጉድለት።» (ቁ. 7።) እዘው «ጉድለት» ተብሎ የተተረጎመውን የግሪክን ቃል ሲተረጉሙት «መረታት» ወይም ደግሞ «ድል መሆን» ብለው ተርጉመውታል። የነገሩ ውጤት ምንም ቢሆን እንዲያው ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ስንኳ «መረታት» ነው። ክርስቲያን አንድ ነገር በፍርድ ቤት ሲወጥን (ፋይል ሲከፍት) እንዲያው መረታቱ ነው፤ በተቃራኒው ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ ፋንታ ግፉን ታግሦ ለመበደልና ለመታለል ቢፈቅድ መርታቱ ነው።

ሐ/ «ነገር ግን ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ፥ ያውም ወንድሞቻችሁን።» (ቁ. 8።) እነዚህ የቆሮንቶስ ቅዱሳን ለመሆን ከሚገባቸው ምንኛ ወደ ኋላ ቀሩ! ይህን ሁሉ በመሥራታቸው ከዓመፀኞች፥ ማለት ከማያምኑት፥ ከውጭ ሰዎች በምንም አልተለዩም። እነዚህን በቁ. 9ና 10 ላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ሁሉ እንዳደረጉ ማለቱ እይደለም ነገር ግን ባደረጉት ነገር፥ ወንድሞቻቸውን በመበደልና በማታለል፥ ዓመፀኞችን መሰሉ፥ ዓመፀኞችም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። እንደ ዓመፀኞች ለመሆን ወድደዋልን? ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነው።

መ/ «ዓመፀኞች።» (ቁ. 1:9።) ዓመፀኞች የተባሉት እነማን ናቸው? በቁ. 1 ላይ «በቅዱሳን ፈት በመፋረድ ፋንታ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን?» ሲል

«ዓመፀኞች» የቅዱሳን ተቃራኒዎች እንደ ሆኑ ያስረዳል። «ቅዱሳን» የተባሉቱ ክርስቲያኖች ናቸውና «ዓመፀኞች» የተባሉቱ ክርስቲያን ያልሆኑት ናቸው። ከዚህም ጋር ቁ. 6 ይስማማል፡ ስለምን? ቢሉ፡ በቁ. 1 ላይ ‹‹በዓመፀኞች ፈት›› ሲል በቁ. 6 ላይ «በማያምኑት ፈት» ይላል። ስለዚህ «ዓመፀኞች» በክርስቶስ ያላመኑት ናቸው። በክርስቶስ ያላመኑት ሰዎች ምልክቶች በቁ. 9ና 10 ላይ የተጻፉት ናቸው። «ዛፍ ሁሉ ከፍሬው ይታወቃል» እንደ ተባለው ሁሉ (ሉቃ. 6፡44) ሰው በሚሠራው ሥራ ይታወቃል። የዓመፀኞች ሥራ ይህ በቁ. 9ና 10 ላይ የተጻፈው ነው፤ ይህንም ሥራ የሚሠራ ሰው ዓመፀኛ ነው። አንድ ሰው «ክርስቲያን» ወይም «ወንድም» ይባል ይሆናል (ም. 5፡11) ፍሬው ግን በቁ. 9ና 10 ላይ እንደ ተጻፈው ከሆነ ክርስቲያን ወይም ወንድም ሳይሆን ዓመፀኛ ነው። ምልክቶችም እንደዚህ የሆኑለት ሰው አዲስ ያልተወለደ በእውነትም ያላመነ መሆኑን ልናውቅ እንችላለን። ይህም ሰው ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላል እንጂ መንግሥተ ሰማያትን አይወርስም።

ሠ/ «ነበራችሁ፤ ነገር ግን ታጥባችኋል።» (ቁ. 11።) ዱሮ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሁሉ ዓመፀኞች ሆነው ነበር (ኤፌ. 2፡3)፤ አሁን ግን ታጥበዋል፤ ተቀድሰዋል፤ ጸድቀዋል። ዱሮ ምናልባት በቁ. 9ና 10 ላይ የተዘረዘረውን ኃጢአት ሠርተው ይሆናል፤ ዛሬ ግን ከታጠቡና ከተቀደሱ ከጸደቁም እንዲህ ያለውን ሥራ እንዲሠሩ አልታሰበም። ከኃጢአታቸው በክርስቶስ ደም ታጥበዋል (ራእ. 1፡5)፤ መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸዋልና ተቀድሰዋል (ም. 3፡16)፤ በእግዚአብሔርም ፊት ጸድቀዋል። (ሮሜ. 4፡25።) በእኳኋናቸው ታላቅ ልዩነት ተደርጎአልና በአካሄዳቸው ደግሞ ታላቅ ልዩነት እንዲኖር ያስፈልጋል። በዚያን ጊዜ ያላመኑ ሲሆኑ ያላመነውን ሰው ምልክቶች ያሳዩ ነበር፤ ዛሬ ግን ክርስቲያኖች ናቸውና ምልክቶቻቸው (ፍሬዎቻቸው) የቅድስና እንዲሆኑ ታስቦአል። (ሮሜ 6፡21-23።) እኛስ በሕይወታችን ምን ምልክቶች እናሳያለን? ፍሬዎቻችን በቁ. 9ና 10 ላይ የተጻፉት ከሆኑ፤ ውሸት ነው፤ ክርስቲያኖች አይደለንም። እንባል ይሆናል እንጂ አይደለንም። ሰው ሴሰኛ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ፤ ወይም አመንዝራ ወይም ቀላጭ ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠራ ወይም ሌባ ወይም ገንዘብ የሚመኝ ወይም ሰካር ወይም ተሳዳቢ ወይም ነጣቂ ቢሆን ክርስቲያን አይደለም የእግዚአብሔርንም መንግሥት አይወርስም። ክርስቲያን ከዓመፀኛ ፈጽሞ ልዩ ነውና ሥራውም ኑሮውም ሁሉ ልዩ መሆን ይገባዋል። ዓመፀኛ (በክርስቶስ ያላመነ የዓለም ሰው) የሚሠራውን ሥራ ክርስቲያን አይሠራም፤ ሲሠራም ቢገኝ ክርስቲያንነቱ በጣም ያጠራጥራል። እኛ ደግሞ የተዘረዘሩትን ኃጢአቶች ዱሮ ምናልባት እንሠራ ነበር፤ ዛሬ ግን እኛ ደግሞ ታጥበናል፤ ተቀድሰናል፤ ጸድቀናልምና እንዴት አድርገን ለንሠራቸው እንገኛለን? ይህን ሁሉ እንደሚሠሩት ነበርን፤ አሁን ግን ታጥበናል፤ ተቀድሰናል፤ ጸድቀናልም። በዚያን ጊዜ እንሠራቸው ነበር፤ አሁን ግን አይሆንልንም። ዓመፀኞች ነበርን፤ አሁን ግን ክርስቲያኖችን ነን፤ አካሄዳችንም ልዩ እንዲሆን ያስፈልጋል።

ቁ. 12-20። «ሁሉ ተፈቅዶልኛል።» ይህ የቆሮንቶስ ሰዎች በጻፉት ወረቀት ላይ የሚጠቅሱት የሐዋርያው ቃል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ በተሰጣቸው ነፃነት ጸንተው ከሕግ ቀነበር በታች ከመሆን እንዲወጡ ዘወትር ያስተምራቸው ነበርና (ገላ. 4፡21፡31፤ 5፡1፡23) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ይህን ቃሉን ጨብጠው አጣምመው

ለሥራቸው ሁሉ መሠረት አደረጉት። ሐዋርያው «እናንተ ለእርነት ተጠርታችኋል» ካለ በኋላ ጨምሮ «ብቻ እርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት አይሰጥ» ማለቱን ረስተው «ሁሉ ተፈቅዶልናል» ብለው የእባቱን ሚስት ያገባ ሰው በመካከላቸው እንዲቀመጥ ስንኳ ፈቀዱ። (ገላ. 5፡13፤1 ቆሮ. 5፡1፡2።) «መብል ለሆድ ነው፤ ሆድም ለመብል ነው» የሚለውን ተረት ደግሞ አነሡ፤ ለሴሰኝነታቸውና ለዝሙታቸውም ፈቃድን ያገኙ መሰላቸው። ለዚህ ሁሉ ግን ጳውሎስ በቂ መልስ ሰጥቶአል። ስለ መጀመሪያ ቃሉ፡- እርግጥ ነው፤ ክርስቲያን በክርስቶስ ነፃነት አለው፤ ይሁንና ለዚያ ነፃነት ወሰን ወሰን አለ። ስለ ሁለተኛው ስለ ተረትም ደግሞ፡- መብል ለሆድ ይሁን፤ ሆድም ለመብል ይሁን፤ ዳሩ ግን በዚያ መሠረትና ምሳሌ «ዝሙት ለሰው አካል ነው፤ አካልም ለዝሙት ነው» ቢባል፤ ውሸት ነው! የቆሮንቶስ ሰዎች «መብል የተሰጠ ለሆድ ነው፤ ሆድም የተፈጠረ መብልን ለመቀበል ነው። ይህም ስለሆነ የሆድን አምሮት ለማጥገብ መብልን መብላት የተፈቀደ ነው፤ የተፈቀደም ብቻ ሳይሆን የተገባ ነው» አሉ። ይህንም መሠረት አድርገው «እንደዚሁም ሁሉ የሰው አካል ሲፈጠር ፍትወት አብሮ ተፈጥሮአል፤ ፍትወትን የሚያጠግብ ዝሙት ነው፤ ስለዚህ ፍትወትን ለማጥገብ ዝሙት የተፈቀደ የተገባም ነው» ብለው እርስ በርሳቸው ተስማሙበት። ጳውሎስ ግን «እንዲህ አይደለም» ይላል። እውነት! የሆድን አምሮት ለማጥገብ መብል አለ፤ መብልንም ለመብላት ሆድ አለ። ይሁን እንጂ የሰው አካል ለዝሙት ሳይሆን ለጌታ ነው ጌታም ለሰው አካል ነው። እግዚአብሔር መብልን ለሆድ እንደ ፈጠረ ሁሉ ዝሙትን ለሰው አካል አልፈጠረም፤ የሰውን አካልም ለዝሙት አልፈጠረም። ተረቱና የተሰጠው ትርጉም ተመሳሳይ አይደለም። ምክንያቱም ደግሞ፤ ሆድና መብል ጠፊዎች ናቸው። እነርሱ ለዚህ ዓለም ብቻ ተፈጥረው ከመንግሥተ ሰማያት ጋር ግንኙነት የላቸውም። ጌታና የሰው አካል ግን ሁለቱም ከሙታን ተነሺዎች ሆነው ለዘለዓለም የሚኖሩ ናቸው። ጌታ በሥጋው ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ የጌታ የሆኑት በሥጋቸው ይነሣሉ በዳግም ምጽአቱም አብረውት ይመጣሉ። (ም. 15፡20-23። ሮሜ. 8፡11። ፊልጵ. 3፡21። 1 ተሰ. 4፡14።) በዚህ ምክንያት ይህ ሥጋችን (አካላችን) በንጽሕና ሁሉ እንዲጠበቅ ያስፈልጋል። ደግሞም ሌላ አሳብ አለ፤ እርሱም ሥጋችን (አካላታችን) የክርስቶስ ብልቶች መሆኑ ነው። ሐዋርያም ይህን ትምህርት በም፡. 11፡12-28 እና በኤፌ. 5፡23-33 ያስፋፋዋል። ሰው በክርስቶስ ባመነ ጊዜ የክርስቶስ ብልት ሆኖ ወደ ክርስቶስ ይጨመራል። ሴሰኝነትና ዝሙት ለክርስቲያን እጅግ መጥፎ የሆኑበት በዚህ ምክንያት ነው። የክርስቶስን ብልቶች ወስደን የጋለሞታ ብልቶች እናድርጋቸውን? ከቶ አይገባንም! እግዚአብሔር «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም» ብሎ ባልና ሚስትን አጣምሮአልና ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር ሰው ከእርሷ ጋር አንድ ሥጋ ነው። ያ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር ሥጋ ግን የክርስቶስ ብልት ሲሆን እንደዚህ ማድረግ ምንኛ መጥፎ ነው! ምእመናን ግን ከጌታ ጋር የተባበሩ ናቸውና ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ናቸው፤ ይህም የመንፈስ አንድነት ከሥጋ (ከባልና ከሚስት) አንድነት እጅግ የቀረበ ነውና ክርስቲያን ያን አንድነት በጥሶ እንዴት አድርጎ ወደ ጋለሞታ ይሄዳል? የቆሮንቶስ ሰዎች በክርስቲያንነታቸው ተመክተው «ሁሉ ተፈቅዶልናል» አሉ። ይሁን እንጂ ከጋለሞታዎች ጋር መገናኘት ዝሙትንም መሥራት ይገባልን? በፍጹም አይገባምና ከዝሙት ይሸሹ። የሚሸሹበትም ሁለተኛ ምክንያቱ ዝሙት በተለይ ክፉ ስለሆነ ነው። እንዴት? ቢባል፤ ሰው ሌላውን ኃጢአት ሁሉ ሲሠራ ከአካላት ውጭ

በሆነው ነገር ይፈጽመዋል፥ ዝሙትን የሚሠራ ግን የገዛ አከላቱን የኃጢአት መሣሪያ አድርጎ አከላቱን ይበድላል። የሚሸሹበት ሦስተኛው ምክንያት፦ ሥጋቸው የእግዚአብሔር ቅድስተ ቅዱሳን ስለ ሆነ ነው። ሐዋርያው በም. 3፥16 ላይ መላው ማኅበሩ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አስረድቶ ነበር፤ አሁን ግን ስለ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይጽፋል። ክርስቶስን የግል መድኃኒቱ ያደረገው ሰው መንፈስ ቅዱስን በውስጡ ተቀብሎአልና ሥጋው የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው። ስቅድስተ ቅዱሳን (ለሕንፃው) የማይገባ ወይም የማያምር ማናቸውም ነገር የእግዚአብሔር ቅድስተ ቅዱሳን ለሆነ ለክርስቲያን ሰው ሥጋ የማይገባ የማያምርም ነው። አንድ የመጨረሻ ምክንያት ደግሞ አለ። የቆሮንቶስ ሰዎች የራሳቸው አይደሉምና እንደ ገዛ ፈቃዳቸው ሊሠሩ አይገባቸውም። እግዚአብሔር በታላቅ ዋጋ፥ እርሱም በአንድያ ልጁ ደም፥ የእርሱው ይሆኑ ዘንድ ገዝቶአቸዋል። (ዮሐ. 3፥16። የሐዋ. 20፥28።) ሰው ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነበረ፥ እግዚአብሔር ገዛው፥ ከዚያም ባርነት እርነት አውጥቶት የራሱ አደረገው። (ዮሐ. 8፥34-36።) እንግዲህ ሥጋቸው የራሳቸው ሳይሆን የእርሱ ነው። የሌላ ሰው የሆነውን ንጹሕ ዕቃ ወስደው ያቆሽሹትን? ሉሪ አይሆንም! ስለዚህ በመንፈላቸው ብቻ እግዚአብሔርን ላያክብሩ አከላታቸውን በንጽሕና በመጠበቅ በሥጋቸው ደግሞ ያክብሩት።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ሁሉ ተፈቅዶልኛል።» (ቁ. 12።) ቃሉ መቼም እውነት ነው። ክርስቲያን ከሕግ በታች እይደለምና ሁሉ በእውነት ተፈቅዶለታል። ሁሉ ቢፈቀድለት ቅሉ ሁሉ ግድረግ ይገባዋል ማለት አይደለም። በቁ. 12 ላይ ጳውሎስ ራሱ ሁለት ውሳኔ ለቃሉ ሰጥቶአል፤ 1ኛ፦ «ሁሉ ግን አይጠቅምም።» 2ኛ፦ «በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም።» ይህም ማለት፥ ግድረግግ እችላለሁ፥ ግድረግ ግን ምናልባት አይጠቅምም። ግድረግስ እችላለሁ፥ ያደረግሁት እንደ ሆነ ግን ምናልባት ባሪያ ያደርገኛል ማለት ነው። የማይጠቅመውን ለምን አደርጋለሁ? ባሪያስ የሆንሁ እንደሆነ አርነቴ የት አለ? ስለዚህ፥ ሁሉ ተፈቅዶልኛልና ግድረግ እችል ይሆናል፤ ሁሉን ባላደርግ ግን ይሻላል ማለት ነው። «ተፈቅዶልኛ?» ተብሎ ስለ አንድ ነገር ቢጠየቅ፥ እምን ተፈቅዶለኛ፤ ነገር ግን ወይም ጥቅም የማይሰጥ ነገር፥ ወይም ባሪያ የሚያደርገኝ ነገር፥ የሆነ እንደሆነ ያን ነገር ባላደርግ ይሻላል። ዮሐንስ አፈወርቅ «ሁሉ በሥልጣኔ ውስጥ ነው፥ በእኔ ላይ ግን አንድም አይሠለጥንብኝም» ብሎአል።

ብዙዎች ከርስቲያናች ሲጃራ የማያጨሱ መጠጥም የማይጠጡ በዚህ ምክንያት ነው። ሕግ አይከለክልም፥ ሁሉም ተፈቅዶልናል። ሆኖም በአንድ በኩል እነዚህ ነገሮች ጉዳት እንጂ ጥቅም አይሰጡም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ባርነት ያደርሳሉ። ሲጃራ ማጨስ እጅንና እስትንፋስን ያቆሽሻል፥ ጉሮሮንና ሳምባን ይጎዳል። እንደዚህም ደግሞ መጠጥን ማብዛት እፍረትንና ድህነትን ያመጣል እንጂ ጥቅም የለውም። ሁለቱም አያንዳንዳቸው ወደ ባርነት ያደርሳሉ። ሲጃራን የሚያጨስን ሰው፥ «ሲጃራህን ተው!» መጠጥን የሚያበዛን ሰው፦ «መጠጥህን ተው!» ብትላቸው አይችሉም። የሲጃራና የመጠጥ ባሪያዎች ሆኑ ማለት ነው። ጌቶች ሆነው በፈቃዳቸው የጀመሩና ወሰን ወሰን አስቀድመው ያናሩ ሲሆኑ አሁን በፈቃድ ላይሆን የግድ ያደርጉታል፥ በወሰኑለትም ወሰን ሲይዙት እይችሉም። ባሪያዎች ሆኑ ማለት ነው።

እንዳንዶች ሰዎች አመካኝተው፦ «ሉረ! ክፉው ግብዛት ነው እንጂ ሁሉ በልክና በመጠን ቢደረግ ክፉ አይደለም» ይላሉ። በዚህም ቃላቸው የውነት ግማሽ አለ፥ ቢሆንም ይህም ለመፈጸም የሚችሉ በቁጥራቸው በጣም ያነሱ ናቸውና መርዙን አለመጀመር ይሻላል እንላለን። ስለምን? ቢሉ፥ ነገሩ ሲለመድ ልግዱ ይጸናል፥ ልግዱም የባለቤቱን ፈቃድ ጥሶ የግድ ያሠራውና ባሪያ ያደርገዋል። «ብርቱ ክርስቲያን የሆነ እገሌ ያደርገዋል» ቢባልም እንኳ ሕይወታችንን በጌታ ቃል እንጂ በሰው አድራጎት እንመሥርተው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው ሁሉ፥ ከሁሉ በተሻሉ ሰዎች ዘንድ እንኳ ስሕተት አልጠፋም። «ሁሉ ተፈቅዶልኛል» ተባለ። ይሁን፤ ነገር ግን ሁሉ አይጠቅምም። «ሁሉ ተፈቅዶልኛል» ተባለ። እውነት፤ ነገር ግን በእኔ ላይ አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም። በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያልተከለከሉ ነገሮች ይኖራሉ፤ ይሁንና የእነዚህ ነገሮች ውጤት ለክርስቲያን የማይገቡ ያደርጋቸዋልና ክርስቲያን የሆነ ሰው እነዚህን ነገሮች ባያደርግ በጣም የተሻለ ነው።

ለ/ «እግዚአብሔር ጌታንም አስነሣ እኛንም በኃይሉ ያስነሣናል።» (ቁ. 14።) ሐዋርያው በሆድና በመብል በጌታና በሥጋም መካከል ያለውን ልዩነት ሲያስረዳ ነው። ስለ ሆድና ስለ መብል ሲናገር «እግዚአብሔር ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል» ይላል። ስለ ጌታና ስለ ሥጋ ግን ሲናገር «እግዚአብሔር ጌታንም አስነሣ እኛንም በኃይሉ ያስነሣናል» ይላል። ጌታ እንደ ተነሣ እንዲሁ የሰው ሥጋ ይነሣል ማለቱ ነው። ይህም በቅዱስ አትናቴዎስ የሃይማኖት ሥርዓት ላይ «እርሱም በሚመጣበት ቀን ሰው ሁሉ በሥጋው ይነሣል» ከሚለው ቃል ጋር ይስማማል። ሰው በሞተ ጊዜ ሥጋው እንደ ተነቀለ ድንኳን ሆኖ ይወድቃል ይበሰብሳል። (2 ቆሮ. 5፥1-5።) ጌታ በሚመጣበት ቀን ያ ሥጋ ይነሣል፥ ተለውጦም መንፈላዊም ሆኖ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል። (ሮሜ. 8፥23። 1 ተሰ. 4፥16። 1 ቆሮ. 15፥35-53።) ለዚህ የሚሆን ማረጋገጫ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መነሣት ነው። እርሱ የሰውን ሥጋ ለብሶ ፍጹም ሰው ሆነ፥ ሰውም ሆኖ ሞተ። መበስበስን እንዳያይ 3 ቀንና 3 ሌሊት ብቻ በመቃብር ቆየ ከዚያም በኋላ በሥጋው ተነሣ። ሥጋውም አሁን ሲነሣ ልዩ ነው። በተዘጋ በር ያልፋል (ዮሐ. 20፥19)፥ ከዓይን ይሰወራል (ሉቃ. 24፥31)፥ ልዩ ሆኖ ታይቶ እንዳንድ ጊዜ እንዳይታወቅ ሰውን ድንግርግር ያደርገዋል። (ዮሐ. 20፥11-16። ሉቃ. 24፥13፥31።) የእርሱ ሥጋ ነው፥ የችንካርና የጦር ምልክቶች ገና አሉበት፥ ቢሆንም ልዩ ነው፥ መንፈላዊ ነው፤ በደመናትም ውስጥ አልፎ ወደ ሰማይ አረገ። የጌታ ሥጋ እንደ ተነሣ እንዲሁ የሰው ሥጋ ይነሣል።

ሐ/ «ከዝሙት ሽሹ።» (ቁ. 18።) «ሽሹ» እንጂ «ቆማችሁ ታገሉ» አለመባሉን እናስተውል። «ሽሹ» ለምን ተባለ? ወደ ኃጢአት የሚያደርሰው ፍትወት በሥጋችን ውስጥ ነውና በፈተና ላይ ቆመን ብናመነታ በእርግጥ ስለምንወድቅ ነው። ዝሙት ሰውነቱን ያዋርዳልና ያቃተለዋል ያጠፋውማል። ስለዚህ ሳንጠመድ በፊት እንደ ዮሴፍ ሆነን ዝሙት ከሚፈጸምበት ቦታ ሸሽተን መንገዳችንን እንሂድ። (ዘፍጥ. 39፥12።) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሦስት ነገሮች እንድንሸሽ ታዝዘናል። 1ኛ፤ ከዝሙትና ከክፉ የኃልግላነት ምኞት። (1 ቆሮ. 6፥18። 2 ጢሞ. 2፥22።) 2ኛ፤ ጣዖትን ከማምለክ። (1 ቆሮ! 10፥14።) 3ኛ፤ ገንዘብን ከመውደድ። (1

ጢሞ. 6፥11።) እነዚህ 3 ነገሮች ለሰው ከፉ ወጥመዶች ይሆናሉና ቆመን ከእነርሱም ጋር ሳንታገል እንድንሸሽ ታዝዘናል።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 7።

1፤ ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው 2፤ መልካም ነው። ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ 3፤ ባል ይኑራት። ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት 4፤ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ። ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም 5፤ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፤ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ 6፤ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ። ዳሩ ግን ይህን እንደ ፈቃድ እላለሁ 7፤ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም። ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ።

8፤ ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ፦ እንደ እኔ ቢኖሩ 9፤ ለእነርሱ መልካም ነው፤ ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።

10፤11፤ ሚስትም ከባልዋ አትለያይ፥ ብትለያይ ግን ላታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ተታረቅ፥ ባልም ሚስቱን እይተዋት ብዮ የተጋቡትን እዛቸዋለሁ፥ እኔ ግን አላዝም፥ ጌታ እንጂ።

12፤ ሌሎችንም እኔ እላለሁ፥ ጌታም አይደለም፤ ከወንድሞች ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርስዋም ከእርሱ 13፤ ጋር ልትቀመጥ ብትስማማ፥ አይተዋት፤ ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርስዋ ጋር ሊቀመጥ ቢስማማ፥ 14፤ አትተወው። ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና፥ ያላመነችም ሚስት በባልዋ ተቀድሳለች፤ አለዚያ ልጆቻችሁ ርኩሳን ናቸው 15፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው። የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤ ወንድም ቢሆን ወይም እኅት እንዲህ በሚመስል ነገር 16፤ አይገዙም፤ እግዚአብሔር ግን በሰላም ጠርቶናል። አንቺ ሴት፥ ባልሽን ታድኚ እንደ ሆንሽ ምን ታውቂአለሽ? ወይስ፥ አንተ ሰው፥ ሚስትህን ታድን እንደ ሆንህ ምን ታውቃለህ?

17፤ ብቻ ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደ ከፈለለት እያንዳንዱንም እግዚአብሔር እንደ ጠራው እንዲሁ ይመላለስ። 18፤ እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እደነግጋለሁ። ማንም ተገርዞ ስለ ተጠርቶ እንደ ሆነ፥ ወደ አለመገረዝ አይመለስ፤ 19፤ ማንም ሳይገረዝ ተጠርቶ እንደ ሆነ አይገረዝ። መገረዝ ቢሆን አለመገረዝም ቢሆን ከንቱ ነው፥ የእግዚአብሔርን 20፤ ትእዛዝ መጠበቅ ነው እንጂ። እያንዳንዱ በተጠራበት 21፤ መጠራት አንደዚሁ ይኑር። ባሪያ ሆነህ ተጠርተህ እንደ ሆነ አይገድህም፤ አርነት ልትወጣ ቢቻልህ ግን እርነትን 22፤ ተቀበል። ባሪያ ሆኖ በጌታ የተጠራ የጌታ ነጻ ነውና፤ እንዲሁም23፤ ነጻ ሆኖ የተጠራ የክርስቶስ ባሪያ ነው። በዋጋ ተገዝታችኋል፤ 24፤ የሰው ባሪያዎች እትሁኑ። ወንድሞች ሆይ፥ እያንዳንዱ በተጠራበት እንደዚሁ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይኑር።

25፤ ስለ ደናግልም የጌታ ትእዛዝ የለኝም፥ ነገር ግን የታመንሁ እሆን ዘንድ ከጌታ ምሕረትን የተቀበልሁ እንደ መሆኔ 26፤ ምክር እመክራለሁ። እንግዲህ ስለ አሁኑ ችግር ይህ መልካም ይመስለኛል፥ ሰው እንዲህ ሆኖ ቢኖር መልካም 27፤ ነው። በሚስት ታስረህ እንደ ሆንህ መፋታትን አትሻ፥ በሚስት 28፤ አልታሰርህ እንደ ሆንህ ሚስትን አትሻ።

ብታገባ ግን ኃጢአት አትሠራም ድንግሊቱም ብታገባ ኃጢአት አትሠራም፤ ነገር ግን
እንዲህ በሚያደርጉ በሥጋቸው ላይ መከራ [29] ይሆንባቸዋል፥ እኔም እራራላችሁ ነበር።
ዳሩ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህን እናገራለሁ፤ ዘመኑ አጭር ሆኖአል፤ ከእንግዲህ [30]
ወዲህ ሚስቶች ያሉአቸው እንደሌላቸው ይሁን፥ የሚያለቅሱም እንደማያለቅሱ፥ ደስ
የሚላቸውም ደስ እንደማይላቸው፥ [31] የሚገዙም ምንም እንደሌላቸው፥ በዚህችም
ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደማይጠቀሙባት ይሁን፤ የዚህች ዓለም መልክ አላፊ
ነውና።

[32] ነገር ግን ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን [33] እንዴት ደስ
እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል፤ ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት
የዓለምን [34] ነገር ያስባል፥ ልቡም ተከፍሎአል። ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም
በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ፤ የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ
እንድታሰኘው የዓለምን [35] ነገር ታስባለች። ይህንም ለራሳችሁ ጥቅም እላለሁ፤ በአገባብ
እንድትኖሩ ላትባክኑ በጌታ እንድትጸኑ ነው እንጂ ላጠምዳችሁ ብዮ አይደለም።

[36] ዳሩ ግን ግግባት ወደሚገባው ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ሰሰ ድንግልናው ያፈረ ሰው
ቢኖር፥ የወደደውን ያድርግ፤ [37] ቢያገባም ኃጢአት የለበትም። ሳይናወጥ በልቡ የጸና
ግን ግድ የሰበትም፥ የወደደውን እንዲያደርግ ተፈቅዶሰታል፤ ድንግልናውንም በልቡ
ይጠብቅ ዘንድ ቢጸና፥ መልካም እደረገ። [38] እንዲሁም ድንግልን ያገባ መልካም እደረገ
ያላገባም የተሻለ አደረገ።

[39] ሴት ባልዋ በሕይወት ላለ የታሰረች ናት፤ ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ
የወደደችውን ልታገባ ነጻነት [40] አላት። እንደ ምክሬ ግን እንዳለች ብትኖር ደስተኛ
ናት፤ እኔም ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ያለ ይመስለኛል።

* * *
* * * * * *

2ኛ ክፍል።

(ም. 7- ም. 10።) ሰተጠየቀው ጥያቄ መልሰ።

ም. 7፤ ሰለ መጋባት።

ም. 8-10፤ ሰጣያት ሰለ ተሠዋ ሥጋ።

ምዕራፍ ሰባት።

በቆሮንቶስ የነበሩ ክርስቲያኖች ወደ መንፈሳዊ አባታቸው ወደ ሐዋርያው ቅዱስ
ጳውሎሰ ዘንድ ወረቀት ጽፈው ልዩ ልዩ ጥያቄ አቅርበውለት ነበርና ሐዋርያው አሁን
ለዚህ ጥያቄ ሁሉ እንድ በአንድ መልስን መስጠት ይጀምራል። በምዕራፍ 7 ላይ
የምናገኘው የመጋባትን ነገር ነው። መጀመሪያው እኩሌታ፥ ከቁ. 1 ጀምሮ እስከ ቁ.
24 ድረስ፥ ስለ መጋባትና ስለ መፋታት ሲናገር ሁለተኛው እኩሌታ፥ ከቁ. 25 ጀምሮ
እስከ ቁ. 40 ድረስ፥ ስሰ ደናግልና ባሎቻቸው ሰሰ ሞቱባቸው ሴቶች ይናገራል።

ቁ. 1-9። ጳውሎስ «ሰሰ ጻፋችሁልኝ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ሰሰው መልካም
ነው» ይላል። አለመገናኘት አለማግባት ማለት ነውና ሐዋርያው አለማግባት መልካም
ነው ማለቱን እንረዳለን። «መልካም ነው» እንጂ «የተሻለ ነው፥» ወይም ደግሞ
«ምግባራዊ ነው።» አለማለቱን እናስተውል። «መልካም» የሆነበት ምክንያት፡- 1ኛ፤
«ስለ አሁኑ ችግር» (ቁ. 26፥) 2ኛ፤ «ዘመኑ አጭር ስለ ሆነ» (ቁ. 29) ነው። በዚህ
ምዕራፍ ላይ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ሐዋርያው በዚህ ሁለት ምክንያት
ድንግልና መልካም ነው ይላል እንጂ ምን ጊዜም የተሻለ ነው አይልም። ምዕራፉን ስናነብ
ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈበትን ዘመንና የዘመኑን ሁኔታ ማሰብ ያስፈልገናል።

«ሰሰ አሁኑ ችግር።» አስቸጋሪ ዘመን ነበረ። በሌሎች አገሮች ዘንድ በክርሰቲያኖች
ላይ መከራና ስደት በየጊዜው ሁሉ ይነሣ ነበር። አዋጅ በድንገት ይወጣ ነበር፥ ተከሰውም
ወደ ፍርድ ቤት ይጎተቱ ነበር፥ ከቀን ወደ ቀንም ምን እንዲሆንባቸው አያውቁም ነበር።
እውነት ነው፥ ሰጊዜው በቆሮንቶስ ከተማ ክርስቲያኖቹ ክቡራን ናቸው፥ ቢሆንም
የወደፊቱን ግን እወቀ? በተጠራጣሪ ኑሮ ምክንያት ብቻውን የሆነ ሰው ቢጨነቅ ባለ
ሚስትና ባለ ልጆች የሆነ እንዴት እብዝቶ ይጨነቅ! የቆሮንቶስም ሰዎች ወደዚህ ወደ
ባሰ ችግር እንዳይደርሱ ሐዋርያው ራርቶ «ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው»
ይላል።

«ዘመኑ እጭር ሰሰ ሆነ።» ሐዋርያው በተለይ ሰለ ወንጌል ሥራ ሲያስብ «ዘመኑ አጭር
ነው» ይላል። በእነዚያ በቀደሙት ክርሰቲያኖች ፊት የተቀመጠው ሥራ ታላቅ ነበር፥
ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ የተጣለባቸው እደራ ከፍ
ያለ ነበር። ጳውሎሰ «ዘመኑ እጭር ነው» ሲል ስለ ክርስቶስ መምጣት ያስብ እንደ ነበረ
ወይም ምናልባት በቆሮንቶስ ከተማ እኛ ዛሬ የማናውቀው እንዳች ነገር ይነሣ እንደ ነበረ
አናውቅም፥ ቢሆንም ዘመኑ አጭር ሆኖ ታየውና «ከሴት ጋር አለመገናኘት ሰሰው
መልካም ነው» አለ።

ሐዋርያው «መልካም ነው» ይልና ወዲያውኑ «ነገር ግን» ብሎ ይቀጥላል። ከሴት ጋር አለመገናኘት መልካም ነው፥ ይህ ግን ለሁሉ አይቻልም ይላል። ምክንያቱስ፥ «ስለ ዝሙት ጠንቅ» ይላል። ማለት፥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው ንጽሕ ፍቅር በአዳም ኃጢአት ምክንያት ወደ ፍትወት ስለ ተለወጠ፥ ሰው ከሴት ጋር ሳይገናኝ ብቻውን ለመኖር ቢያስብ ዝሙት የተባለ ነገር እንዳይገባ ያስፈራል። ሰው ከሴት ጋር ሳይገናኝ ለመኖር ቢችል መልካም ነው፤ ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ሰው ሁሉ ቢያገባ ይሻላል ብሎ ሐዋርያው ምክሩን ይሰጣል። ይህም ብርቱ ወሰን ነው። ዝቅ ብሎ በቁ. 5 ላይ ራስን ስለ አለመግዛት ይናገራል፥ ከዚያም በታች ደግሞ በቁ. 8 ላይ «በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ» ይላል። ጉዳዩ ራስን መግዛት በመቻል ላይ ተንጠልጥሎአል፥ ይህም ራስን መግዛት መቻል ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው። ሰው ራሱን መግዛት ቢችል ከሴት ጋር ባይገናኝ መልካም ነው፤ ባይችል ግን «ስለ ዝሙት ጠንቅ» ያግባ።

የተጋቡም ሲሆኑ በአገባብ ሁሉ ይኑሩ። «ለአያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለአያንዳንዲቱም ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት» ማለቱ፥ ሰው ባለ ሁለት ሚለቶች አንዳይሆን ሚስቱንም እንዳይፈታ ሲከለክል ነው። (ቁ. 2) እዚህ ላይ ደግሞ የባልና የሚስት መብት አኩል እንደ ሆነ አናያለን፥ ሐዋርያው፡- «ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ አንደዚህም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ ታድርግለት» ይላልና። (ቁ. 3) አንዳቸውም ያለ ሌላው በስተቀር በሥጋቸው ላይ ሥልጣን የላቸውምና መጋባት በሥጋ ነገር በኩል በሁለቱም ላይ ኃላፊነትን ይጥላል። በሥጋ ነገር ወንዱ አንደ ገዛ ፈቃዱ ሊያደርግ አይችልም፥ ሚስቲቱም እንደዚሁ አትችልም። ከተጋቡ ወዲያ አንድ ሥጋ ናቸውና ወይም ወንዱ ወይም ሴቲቱ በገዛ ሰውነታቸው ላይ ሙሉ ሥልጣን የላቸውም። ባልየው ለሚስቲቱ ያስብ፥ ሴቲቱም ለባልዋ። ታላቅ ምክንያት ካልሆነ በቀር አርስ በርሳቸው አይከላከሉ፤ አንዲህ ያደረጉ አንደሆነ ሰይጣን በፍትወት ረገድ ይፈታተናቸዋልና። ሐዋርያው ይህን ግለቱ ከዝሙት ጠንቅ ለማምለጥ አንዲጋቡ ፈቃድ ሲሰጣቸው ነው እንጂ እርሱ በእውነቱ «ለለ አውኑ ችግር፥ ዘመኑም አጭር ስለ ሆነ» የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች እንደ እርሱ፥ ሚስት አንዳላገባው ቢሆኑ በወደደ ነበር። ቢወድም ቅሉ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ እንደ ሆነ ሁሉም ሰው የራስን መግዛት መቻል ስጦታ እንዳልተቀበለ ተገንዝቦ ነበር። አንግዲህ አሳቡ በጠቅላላው በቁ. 8 እና 9 ላይ አንደ ተጻፈው ነው። አስከ አውን ድረስ ላላገቡትና አውን መበለቶች ለሆኑት «እንደ እኔ ቢኖሩ ለአነርሱ መልካም ነው፤ ነገር ግን በፍትወት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ» ይላል። ቢችሉ ሳያገቡ ቢኖሩ «መልካም ነው»፥ ባይችሉ ግን ያግቡ።

ማስገንዘቢያ።

የድንግልና ወይም ያለማግባት ኑሮ ለሰው ሁሉ ላይሆን በእውነቱ በቁጥራቸው አጅግ በጣም ላነሱ ብቻ ነው። ከጥንት ጀምሮ ሰው ይህን ነገር ምነው በተረዳ! አግዚአብሔር «ለሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» ሲል (ዘፍጥ. 2፥18) ሰው «በድንግልና መኖር ለሰው ሁሉ መልካም ነው የተቀደሰም ነው» ብሎአል። ይህንም በማለት ስንቱን መበላሸት፡ ስንቱን ርኩሰት፥ ስንቱን ጭካኔ፥ ስንቱን ግብዝነት፥ ስንቱን አበሳ፥ ስንቱን ኃዘን ፈጥሮአል! ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከቶ አልሆነም። አርሱ የራስን

መግዛት መቻል የጸጋ ስጦታውን ለጥቂቶች (ለአንዳንዶች) ሰዎች ብቻ ሰጥቶአል፡ አነርሱንም ብቻ በድንግልና እንዲኖሩ ወድዶአል አንጂ የቀሩት ሁሉ እንዲያገቡ ፈቃዱ ነበረ። ብዙ ሰዎች ግን ባለማስተዋል ምክንያት የአግዚአብሔርን አሳብ ለተው በድንግልና መኖር ይበልጣል ብለው በድንግልና መኖር አስበዋል። ይህንም በማድረጋቸው በዓለም ሁሉ ላይ በገዳማትም ውስጥ ታላቅ ጥፋት ፈጥረዋል። በዚህ ነገር ላይ የሐዋርያውን የመጨረሻ ቃል አንስማ፡- «አንደ እኔ ቢኖሩ መልካም ነበር፤ ነገር ግን በፍትወት ከመቃጠል (ዝሙትን ከመሥራት) መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ» ይላል። በቁ. 28 ላይ ደግሞ ድንግል ቢያገባ ኃጢአት አይደለም ተብሎአልና ድንግልናቸውን ሊጠብቁ ያልቻሉ «ደናግል» ቢያገቡ የተሻለ ነው።

ቁ. 10-16። አውንም ስለ መፋታት አናነባለን። አስቀድሞ በቁ. 10 እና 11 ላይ ሁለቱም ሰዎች ክርስቲያኖች ሲሆኑ የሚገባውን እናያለን፥ ከዚያም በኋላ ደግሞ ከቁ. 12 አስከ ቁ. 17 ድረስ ከተጋቡት ሰዎች እንዱ ገና በክርስቶስ ያላመነ ሲሆን የሚገባውን አናገኛለን። ለፊተኞቹ ሁለቱም ክርስቲያኖች ሲሆኑ ማለት፥ የክርስቶስ ሕግ ጸንቶ ቆሞአል። በዚህ ነገር ጌታ ቃሉን ስጥቶአልና ክርስቲያን ሁሉ ተይዞበታል። ጌታ «አይለያዩ» ብሎ አዝዞአል። (ማቴ. 5፥32፤19፥9።) ለጌታም ትአዛዝ እንቢ ብላ የምትለያይ ብትኖርም ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ ባልየውም ደግሞ ሚስቱን አይተዋት። የእነርሱ ነገር ግልጥ ነው። ጌታ አዝዞአልና ክርስቲያን ባይታዘዝ ለነፍሱ ጉዳት ነው።

ምናልባት ግን ከተጋቡቱ አንዱ አውነተኛ ክርስቲያን ባይሆንስ? ያላመነው አማኙን አያረክሰውምን? ያረክሰውም አንደሆነ ክርስቲያኑ ክርስቲያን ያልሆነውን ቢፈታ አይሻልምን? አንዲህ ብለው የቆሮንቶስ ሰዎች ሐዋርያውን ጠይቀውት ነበር። ጳውሎስ ግን «ዋና ነገሩ ሰላምና ስምምነት ነው» ይላል። ከሁለቱ ሰዎች ክርስቲያኑ በቁ. 10 እና 11 ላይ በተጠቀሰው ቃል አንደ ታሰረ ነው። መለያየት የሚሆን ከሆነ እንኳ በአርሱ ወገን አይወጥን፤ እርሱም የነገሩ አንሽ ከቶ አይሁን። ያላመኑቱ ከአማኞች ጋር ሊቀመጡ ከተሰማሙ ይቀመጡ። የለም፥ የቆሮንቶስ ሰዎች አንዳሰቡት አይደለም። ቅዱሳን ርኩሳንን ይቀድሳሉ አንጂ ርኩሳን ቅዱሳንን አያረክሱም። ይህ ቢሆን ኖሮ ልጆቻቸው ርኩሳን በሆኑ ነበር፤ ነገር ግን ሐዋርያው «አይደሉም፥ የተቀደሱ ናቸው አንጂ» ያላል። ስለዚህ ሰውየው አውነተኛ ክርስቲያን ሲሆን ሚስቱም ያልተግረች የክርስቶስንም ነገር ያልተቀበለች ስትሆን ክርስቲያኑ እርስዋን ፈትቶ ክርስቲያን የሆነችውን አይፈልግም፥ አርስዋ ልትቀመጥ ብትስማማ ትቀመጥ አንጂ። ያላመነው ደግሞ ባልየው ሲሆን ነገሩ አንደዚሁ ሁሉ ነው። «የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤ ይህም ሲሆን ክርስቲያኑ አንዲህ በሚመስል ነገር አይገዛም» ተባለ። «አይገዛም» ማለቱ፥ ይህ ሲሆን ክርስቲያኑ ጋብቻውን ለማጽናት ኃላፊነት የለበትም ማለት ነው። ጥፋቱ ባላመነችው በኩል ነው እንጂ በአርሱ በኩል አይደለም። ጋብቻውን ለማጽናት አርሱ ሞክሮአል፥ እርስዋ ግን አንቢ ብላ ሄደች። አንግዲህ ክርስቲያኑ ከኃላፊነት ነፃ ወጥቶአል። ይህም ሲሆን ሌላይቱን ሊያገባ ይችላል የሚሉ ብዙ መምህራን አሉ፤ ሌሎች ግን አይሆንም ይላሉ። በአያንዳንዱ ጊዜ ሁሉ መንፈለ ቅዱስ በአንዲህ ያለ ነገር መሪ ይሁን። በዚህ ነገር ሁሉ መምሪያ ሕጉ ሰላም ነው። አግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው (ሮሜ. 15፥23)፡ ክርስቲያኑም ሰላም የሚለጠውን መንገድ ይከተል። ሁልጊዜ በጭቅጭቅና በኃዘን በመኖር ፋንታ ቢለያዩ እንኳ ይሻላል። ምናልባት ወደ ደኅንነት እመራዋለሁ ወይም እመራታለሁ ብሎ ተስፋ

በግድረግ እንዲህ ያለውን ጋብቻ ለማጽናት መሞከር ከንቱ ነው። ውጤቱ እንደዚህ ሁሉ ተጠራጣሪ ሲሆን ዕድሜውን ሁሉ በጭቅጭቅ ማሳለፍ እይረባም። ክርስቲያኑ ወደ መፋታት የሚመራውን መጀመሪያ እርምጃ አይራመድ እንጂ የማታምን ብትለይ ትለይ። ስለ ሴቲቱም የተናገረው ሁሉ ስለ ወንድዮ ደግሞ ያገለግላል፤ ለሁለቱም መንገዱ አንድ ነው።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ያሰበው ቀድሞውኑ ስለ ተጋቡት ሰዎች ነው እንጂ ያመነ ሰው ያላመነችን ሚስት እንዲያገባ፥ ወይም ደግሞ ያመነች ሴት ያላመነ ባል እንድታገባ ከቶ አላሰበም። ለክርስቲያን ሁሉ መጋባት «በጌታ» እንዲሆን ያስፈልጋል (ቁ. 39)፤ ማለት ክርስቲያን ክርስቲያንን ብቻ ያገባል። ይህን በመርሳት ስንቶች ክርስቲያኖች ተቸግረዋል! ክርስቲያን ክርስቲያን ያልሆነችውን ሊያገባ፥ ወይም ክርስቲያን ሴት ክርስቲያን ያልሆነውን ሰታገባ፥ ሁልጊዜ ስሕተት ነው። ጭቅጭቅና ፀፀት መራራ ልቅሶም ዘወትር ያመጣል። ከዚህም በላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። (2 ቆሮ. 6፥14።) እንግዲያስ ክርስቲያን የሆነ ማናቸውም ሰው ይህን ሕግ ለመተላለፍ ቢያስብ የሚከተለውን ጉዳት አስቀድሞ ያስብ፤ አስበም ሲያበቃ የእግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነ ነገር ራሱን ይጠብቅ።

ለ/ «አለዚያ ልጆቻችሁ ርኩሳን ናቸው፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።» (ቁ. 14።) ይህ እንዴት እንደሚሆን በቅጡ ባይታወቅ እንኳ ቅዱሳን በዙሪያቸው በሚገኙት ሰዎች ዘንድ እንዳችን ልዩነት እንዲያደርጉ የተረጋገጠ ነገር ነው። (ዘፍጥ. 18፥26፤30፥27። 1 ነገ. 15፥4፡45።) ይህም ስለሆነ እንዳንዶች መምህራን ያላመነው ባል ወይም ደግሞ ያላመነች ሚስት በአማኝ ባለቤቱ እንደሚቀደስ (እንደምትቀደስ) እንዲሁ ልጆቻቸው በአማኙ ተቀድሰዋል ይላሉ፤ ይህንም በማለት ይህን ቁጥር ለሕፃናት ጥምቀት መሠረትና ምክንያት ያደርጉታል። ሌሎች ግን ሐዋርያው በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የሚናገረው ስለ መፋታት ነው እንጂ ስለ ጥምቀት አይደለምና ቃሉ ከዚህ እንደሚከተለው ይተረጎማል ይላሉ። ሐዋርያው ባልና ሚስት አይለያዩ ብሎ ማስተማሩ ነውና የማይለያዩበትን ብርቱ ምክንያት መስጠቱ ነው፥ እርሱም በልጆቻቸው ነገር የሚለያዩ እንደሆነ ልጆቻቸውን ዲቃሎች (ርኩሳን) ያደርጉእቸዋል ይላል። አማኙ ክርስቲያን ከባለቤቱ ቢለይ «ከቀድሞው ጀምሮ መጋባታችን ያላገባብ (የማይገባ) ነበረ» ማለቱ ነውና የተወለዱላቸውን ልጆች ወዲያውኑ ዲቃሎች ያደርጋቸዋል። ይህም በእውነቱ እንዳይለያዩ ብርቱ ምክንያት ነው።

ሐ/ «ምን ታውቂአለሽ? ... ምን ታውቃለህ?» (ቁ. 16።) እንዲህ መናገሩ ሐዋርያው አማኙ የማታምነውን እንዲያስቀምጥ ማለቱ ነውን? ወይስ ለመሄድ እንዲተዋት ማለቱ ነው? መምህራን በአሳባቸው ተከፋፍለዋል። እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የሆኑት አንዳንዶቹ እንዲያስቀምጥ ማለቱ ነው ይላሉ። ሌሎች ግን «አይደለም! በቁ. 15 ላይ «ይለይ» ብሎአል፥ ቀጥሎም «ወንድም ቢሆን ወይም እኅት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም» ብሎአል፥ ሦስተኛ ደግሞ በቅፌ 16 ላይ «ታድኚ እንደሆንሽ ምን ታውቂአለሽ?... ታድን እንደሆንህ ምን ታውቃለህ?» ብሎ በነገሩ ላይ ጥርጥር ጥሎአልና «አታድኚውም ...

አታድናትም» ማለቱ ነውና ለመሄድ እንዲተዋት ማለቱ ነው» ይላሉ። ከሁለቱ አስተያየት ይህ ነው ለማለት ያለቸግራል።

ቁ. 17-24። ሁኔታቸው ከመጠን በላይ ሁከታዊ ለሆነ ለጥቂቶች ሰዎች ሁኔታቸውን ለማሻሻል ሐዋርያው ባለፉት ቁጥሮች ላይ ፈቃድን ሰጥቶአል። አሳቡ ግን ሰው ክርስቲያን ሲሆን ወዲያውኑ በሃይማኖት ረገድ ባህሉን፥ ወይም በሰዎች መካከል አቀማመጡን እንዲለውጥ ከቶ አይደለምና በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሦስት ጊዜ ደግሞ «እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንደዚሁ ይኑር» ብሎ ይድፋል። እስቀድሞም የግርዘትን ነገር ያነሣል። በዚያ ዘመን ግርዘት እንደ ታላቅ ነገር ተቆጠረ፥ በሰውና በሰውም መካከል ከፍ ያለ ልዩነት አደረገ። ለክርስቲያን ግን እነኝህ የሃይማኖት የባህል ልዩነቶች እንደ ቁም ነገሮች አይቆጠሩም። ሰው ክርስቲያን ቢሆን ቢገረዝ ባይገረዝ ያው ነው፥ መለወጥም አያስፈልግም። የባሪያነት ነገር እንደዚሁ ነው። አንድ ሰው ባሪያ ሆኖ ቢጠራ ነፃ ሆኖም ቢጠራ ያው ነው። በክርስቶስ ዘንድ ማኅበራዊ ወይም ማዕረጋዊ ልዩነት የለም። (ሮሜ. 2፥11። ገላ. 3፥28።) ሆኖም ያ ባሪያ አርነት በመውጣት ክርስቶስን በበለጠ እኳኋን ሊያገለግል ቢችል፥ አርነትም ሊወጣ ቢቻለው፥ አርነትን ይቀበል። በክርስቶስ ዘንድ ያለው አቀማመጡ ያው ነው፤ ነገር ግን የበለጠ ሊያገለግል ቢችል ይህ ጠቃሚ ነገር ነውና አርነትን ይቀበል። ሆኖም ያ ባሪያ በእውነት ባሪያ አይድለም፥ የጌታ ነፃ ነው እንጂ። እንደዚሁም ሁሉ ያ ነፃ የሆነ ሰው ጌታ ሲጠራው የጌታ ባሪያ ነው፤ ስለዚህ ሁለቱም በክርስቶስ እኩል ናቸው። (ሮሜ. 1፥1። ፊልሞ. 16።) ቀጥሎም ደግሞ ሐዋርያው «በዋጋ ተገዝታችኋል፤ የሰው ባሪያዎች አትሁኑ» ይላል። ይህም፥ በሥጋችሁ የሰው ባሪያዎች ብትሆኑም ራሳችሁን እንደ ጌታ ባሪያዎች እንጂ እንደ ሰው ባሪያዎች አትቁጠሩ ማለት ነው። የሰው ባሪያዎች ብትሆኑም በእውነቱ የክርስቶስ ነፃዎች መሆናችሁን አስባችሁ በነፃነት መንፈስ ኑሩ ማለት ነው።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ጳውሎስ አስቀድሞ ስለ ሃይማኖት ባህል ልዩነቶች ሲናገር «አይሁዳዊ አሕዛባዊም ለመምሰል አይፈልግ፥ አሕዛባዊም አይሁድን ለመምሰል አይሞክር፤ ሁለቱ ግን ክርስቲያኖች ሆነው በተጠሩበት ይኑሩ» ይላል። (ቁ. 18፡19።)

እነኝህ የትውፊትና የባህል ልዩነቶች በእውነት በፍጹም ምንም አይደሉም። አንድ ሰው ክርስቲያን ሊሆን የዱሮውን ክዶ እዲሱን መያዝ አያስፈልገውም። እርግጥ ነው፥ ከዱሮዎቹ በእንዱ ውስጥ ኃጢአት ቢኖር ወይም ክማይገባ ነገር ጋር መስማማት ቢያስፈልግ ያን ጊዜ ያን መተው የግድ ይሆንበታል፤ በለመዳቸው ባህሎች ግን ኃጢአት ወይም እጉል መስማማት በፍጹም ከሌለ እርሱ ክርስቲያን በመሆኑ ምክንያት ብቻ እንዲተዋቸው አያስፈልግም፥ አይገባምም። ለምሳሌ፥ ለያገሩ የራሱ ባህል አለ። የኢትዮጵያ ባህል አለ፥ የግዶ አገርም ባህል አለ። እስከ አሁን ድረስ በአገሩ ባህል የኖረ ኢትዮጵያዊ፥ እውነተኛ ክርስቲያን በመሆኑ ምክንያት ብቻ፥ የአገሩን ባህል ትቶ የፈረንጆችን መያዝ በፍጹም ያልተገባ ነው። ባደገበት በአገሩ ባህል ውስጥ ኃጢአት ባይኖር ወይም ከማይገባ ጋር መስማማት ባያስፈልግ ሰው አውነተኛ ክርስቲያን ሊሆን የሌላ አገር ትውፊትና ባህል ሳይቀበል በዚያ ባደገበቱ ባህል መኖር ይችላል፥ ሐዋርያውም «በዚያ ባህል መኖርስ ይገባዋል» ይላል።

ለ/ «ባሪያ ሆነህ ተጠርተህ እንደሆነ አይገድህም።» (ቁ. 21።) እግዚአብሔር ጠርቶናል፥ ሁኔታችንንም የከፈለልን እርሱ ነው። ዋና አሳባችን በእርሱ መጠራታችን ይሁን እንጂ አኳኋናችንና ሁኔታችንን ያለ መጠን እንመልከት። ከተመረጠ ወገን ቢሆን ካልተመረጠም፥ አሽከር ቢሆን ጌታም፥ ይህ ሁሉ ከቁም ነገር አይቆጠርም። «የክርስቶስ ነኝ!» ዋና አስተያየቴ ይህ ይሁን። ክርስቲያን ግንም ቢሆን በማንኛውም ሁኔታ ሁሉ ውስጥ ቢገኝ ክርስቶስን ለማክበር ሕይወቱን ያደራጅ።

ሐ/ «በዋጋ ተገዝታችኋል።» (ቁ. 23።) አንባቢ ሆይ፥ ሳትወለድ በፊት በዋጋ መገዛትህን እውቀሃልን? ከምን እንደ ተገዛህ በምንስ እንደ ተገዛህ አስብ። የእርሱ ነበርህ፤ ሸፍተሃልን? በል! ተመለሰለት፥ ከእንግዲህም ወዲህ ለራስህ ሳትኖር ስለ አንተ ለሞተውና ለተነሣው ኑር። (2 ቆሮ. 5፥15።)

ቁ. 25-40። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ እኩሌታ ላይ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለ መጋባትና ስለ መፋታት ላቀረቡለት ጥያቄ መልስ ሰጥቶአል፤ አሁንም በሁለተኛ እኩሌታ ላይ ሁለተኛ ጥያቄአቸውን አንሥቶ ስለ ደናግልና ባሎቻቸው ስለ ሞቱባቸው ሴቶች ይጽፋል። ጥያቄአቸው፡- ደናግል፥ ባሎቻቸው የሞቱባቸውም ሴቶችሳ? ያግቡን ወይስ አይግቡ? የሚል ነበረ።

ሐዋርያው «ስለዚህ ነገር የጌታ ትዕዛዝ የለኝም» ይላል። ጌታ በዓለም ላይ በነበረ ጊዜ ስለዚህ ነገር አልተናገረም፥ ጳውሎስም ስለ ነገሩ ልዩ ራእይ አልተቀበለም። ቢሆንም፥ ለጌታው እንደ ታመነ እገልጋይ ሆኖ የራሱን አሳብ ሳይናገር ጌታ እንደዚህ ቢሆን ይወድ ይመስለኛል ብሎ ምክሩን ይሰጣል፤ ምክሩንም ሲሰጥ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ያለ ይመስለዋል።(ቁ. 40።)

በዚህ በድንግልና ነገር ደግሞ «ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው» የሚል አሳቡን ይዞአል። ምክንያቱም፥ የበለጠ ወይም ደግሞ ምግባራዊ የሆነ ኑሮ ስለ ሆነ አይደለም፥ «ስለ እሁኑ ችግር» መልካም ስለ ሆነ ነው እንጂ። ዘመኑ እስቸጋሪ ነውና ጳውሎስ «አንዳላችሁ ብትቀመጡ ይሻላል» ይላቸዋል። ሆኖም በቁ. 2 ላይ ደግሞ እንዳመለከታቸው ቢያገቡ ኃጢአት አይደለም። የእርሱ ዋና አሳብ ከመከራ ሊጠብቃቸው ነው። አስቸጋሪየሚያስጋም ዘመን ነውና ብቻቸውን ሊቀመጡ ቢችሉ ይሻላቸዋል ይላል። ዘመኑ ግን አጭር ሆኖ ነበር። ማለት ወንጌልን ለማስተማር ቤተ ክርስቲያንንም ለማጽናት የቀረላቸው ዘመን በእንድ ምክንያት በድንገት እጥሮባቸው ነበር። ይህ ምክንያት ወይም ይህ ነገር ምን እንደ ሆነ እኛም ዛሬ ባናውቅ ቅሉ የቆሮንቶስ ሰዎች አውቀውታል፥ የጳውሎስንም ወረቀት ሲያነቡ አሳቡ ይገባቸዋል። ከዚህ ምክንያት የተነሣ፥ ደግሞ ሁለተኛ የዚህች ዓለም መልክ ዘላለማዊ ሳይሆን አላፊ ስለ ሆነ ሐዋርያው በድንግልና ብትቀመጡ መልካም ነው ይላል። በዓለም ውስጥ ናቸውና የግድ በዓለም ነገሮች፥ በልቅሶና በደስታ በኑሮም ጉዳይ ይያዛሉ፤ ሆኖም እንዲጸመዱበት እይፈልግም። የሚያለቅሱ በልቅሶአቸው እይዋጡ፥ ደስ የሚላቸውም በዚህች ዓለም ቅሌት እይስከሩ። ሀብት ያላቸው፥ በሉቃ. 14፥18፡19 ላይ እንደ ተጻፈላቸው ጥሪውን እንደ ናቁት ሰዎች እይሁኑ። በዚህች ዓለም ሊጠቀሙ ይችላሉ፥ ነገር ግን ከመጠን በላይ እይጠቃቀሙባት፤ ከዚህች ዓለም በኋላ መንግሥተ ሰማያት አለና። «የሚዘምተው ሁሉ

ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም» የተባለውን ቃል ያስቡ። (2 ጢሞ. 2፥4።) (ቁ. 25-31።)

አሁንም ያላገቡ እንዲሆኑ የወደደበትን ጠቅላላ ምክንያቱን እናገኛለን። ያለ አሳብ ጌታን እንዲያገለግሉ ነው። «አሳብ» ሲል በማቴ. 6፥25-33 ላይ እንደምናገኘው የጭንቀት አሳብ ነው። ያገባ ሰውና የተጋባች ሴት ጌታን ያለ አሳብ ሊያገለግሉ አይችሉም። ልባቸው ተከፍለዋል፤ ጌታን ደስ ለማሰኘት ያስባሉ፥ ቢሆንም ባለቤቶቻቸውን ደግሞ እንዴት ደስ እንዲያሰኙ ማሰብ አለባቸው። ባልተጋቡት ዘንድ ግን እንዲህ ያለ ጭንቀት የለም፤ እነርሱ የጌታን ነገር ብቻ ሊያስቡ ይችላሉ። ዘመኑ አጭር ሆኖአልና ጳውሎስ «ያለ አሳብ» እንዲሆኑ ይወዳል። ይወዳል እንጂ አያስገድዳቸውም። የተናገረው እንዲጠቀሙ ነው እንጂ ወጥመድ ሊጥልባቸው አይደለም። (ቁ. 32-35።)

ስለ አሁኑ ችግር፥ ዘመኑ አጭር ስለ ሆነ፥ የዚህች ዓለም መልክ አላፊ ስለ ሆነ፥ ደናግል እንዲህ ሆነው ቢኖሩ መልካም እንደ ሆነ ሐዋርያው አስቦአል። ይሁንና በእንድ ምክንያት በድንግልና መኖር የማያምር ቢሆን፥ ወይም ምናልባት ፍትወት ቢያስገድዳቸው ደናግል ቢያገቡ ኃጢአት ይሆንባቸዋልን? ሐዋርያው «እይሆንባቸውም፥ ያግቡ፥ መልካም ነው» ይላል። ነገር ግን የግዴታ ነገር ከሌለ በድንግልናቸው ሊጸኑ ቢችሉ አሳይ ስለ ተጻፈው ምክንያት ሲሉ ድንግልናቸውን ቢጠብቁ የተሻለ ነው። (ቁ. 36-38።)

አሁንም እንድ መጨረሻ ነገር አለ። ባልዋ የሞተባት ሴትሳ? የእርስዋ ነገር እንዴት ነው? ዳግመኛ ታግባን? ወይስ ብቻዋን ትቀመጥ። ለዚህ ጥያቄ ጳውሎስ አስቀድሞ መሠረታዊ የሆነ የእግዚአብሔርን ሕግ ይጠቅሳል። ሞት እስራትን እስኪበጥስ ድረስ ባልና ሚስት እንድ ሥጋ ናቸውና ተሳስረው እንዲኖሩ የታወቀ ነው። ሞት ግን እስራትን ሁሉ ይበጥሳልና የጋብቻቸው እስራት በሞት ከተበጠሰ በኋላ በኋላ በጌታ ይሁን እንጂ ባልዋ የሞተባት ሴት ዳግመኛ ልታገባ ትችላለች። (ሮሜ. 7፥1-3።) ጳውሎስ ግን እንደገና፥ አራተኛ ጊዜ፥ «እንደ ምክሬ እንዳለች ብትኖር ደስተኛ ናት» ይላል። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ አሳቡ አንድ ነው። ስለ አሁኑ ችግርና ስለ ዘመኑ ማጠር ስለ ጌታም እገልግሎት በእነዚህ 3 ምክንያቶች «ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው» (ቁ. 1)፤ «ሰው እንዲህ ሆኖ ቢኖር መልካም ነው» (ቁ. 26)፤ «ድንግልናውን ይጠብቅ ዘንድ ቢጸና መልካም እደረገ» (ቁ. 38) «እንዳለች ብትኖር ደስተኛ ናት» (ቁ. 40) ይላል። በዚህም ሁሉ ውስጥ የሚያቀርበው የራሱን አሳብ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ያስተግረውን የጌታን አሳብ እንደ ሆነ ይተግመናል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «የጌታ ትእዛዝ የለኝም።» (ቁ. 25።) እነሆ ለእግዚአብሔር የታመነ ሐዋርያ! ቃሉ የጌታ እንደ ሆነ አያስመስለውም። የእርሱ ቃልና የጌታ ቃል አኩል እንደ ሆነ አያስብምና የእርሱ ቃል ብቻ ሲሆን በግልጥ ያምነዋል። ይሁንና ሰው ጥያቄ ሲያቀርብልን መልሱን በጌታ ቃል ልንሰጥ ብንችል መልካም ነገር ነው። የጌታ ቃል ሲኖር ሁልጊዜ በጌታ ቃል እንመልስ። ጳውሎስ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ዘንድ ያለ ይመስለዋልና ቃሉ የእርሱ ብቻ ቢሆን እንኳ መልሱን በድፍረት ይሰጣል፥ እኛም እንደ እግዚአብሔር ቃል አንደ ሆነ ልንቆጥረው አንችሳለን።

ለ/ «ዘመኑ አጭር ሆኖአል።» (ቁ. 29።) በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ፊት ዘመኑን ያሳጠረው ምን እንደ ሆነ ባናውቀውም ቅሉ፥ ቤተ ክርስቲያናችንን ለማደስና በኢትዮጵያ አገራችን ወንጌልን ለማስፋፋት፥ አፍሪካንም ወደ ክርስቶስ ለማድረስ፥ በእኛ ፊት ያለው ዘመን አጭር እንደ ሆነ መዘንጋት አይገባንም። ዘመኑ ስምንተኛ ሽህ ሲሆን ጌታ የተናገራቸውም ምልክቶች ለመፈጸም ሲጀመሩ (ማቴ. 24፥32፡33)፥ ያሁኑ ዘመን ወደ መጨረሻው መድረሱንና በፊታችን ያለው የጸጋ ዘመን (ዓመተ ምሕረት) አጭር መሆኑን እናውቃለን። እንግዲያስ ክርስቲያን ሁሉ ዓይነተኛ ተግባሩን ያስብ እንጂ በማይረባ በቀላል ነገር ጊዜውን አያሳልፍ።

ሐ/ «ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ።» (ቁ. 32።) ጳውሎስ ድንግልናን የወደደበት ምክንያቱ ያሳገባ ሰው ያለ አሳብ ስለሚኖር ነው፥ ያለ አሳብ በመኖሩም ጌታን የበለጠ ሊያገለግል ስለሚችል ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አሳብ ነገር እንዲህ ብሎ ተናግሮአል፡- «የዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት ገብተው ቃሉን ያንቃሉ፥ የማያፈራም ይሆናል።» (ማር. 4፥18፡19። አሳብስ ከወዴት ይመጣል? ወይስ በእነማን ዘንድ ይገኛል? ብዙው የሚመጣው ከመጋባት ኑሮ ነው። የተጋቡ ሰዎች በዓለማዊ ነገር የግድ ይያዛሉ። ባልየው የበለጠ ገንዘብ ማግኘት የግድ ይኖርበታል። ሚስቱን ደስ ከማሰኘቱም በላይ ለልጆቹ መብል፥ ለልጆቹ ልብስ፥ ለልጆቹ ትምህርት ማሰብ አለበት። ሚስቲቱም እንደዚህ። እርስዋ በቤት ሥራ፥ ልብስ በማጠብና በመስፋት፥ ይህንም በሚመሳሰል በሌላ ብዙ ነገር ሰዓትዋን የግድ ታሳልፈዋለች። ባለ ትዳር የሆኑ ሰዎች ይህን ሲያደርጉ ጌታን ለማገልገል ጊዜአቸው ያነስ ነው። ያላገቡ ሰዎች ግን አሳባቸው በአንድ በኩል ብቻ ነው። ይህ ጣጣ ሁሉ ሳይኖርባቸው ጌታን ብቻ ደስ ለማሰኘት ሊያስቡ ይችላሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን በድንግልና መኖር ለወንጌል ሥራ ለቤተ ክርስቲያንም መስፋፋት በዚያ ዘመን እንደ ሆነ ሁሉ እንዲሁ በዛሬው ዘመናችን ምንኛ ጠቃሚ ነው! መከራና ስደት ለጊዜው ባይሆንብንም በፊታችን ያለው ሥራና በቆሮንቶስ ክርስቲያኖችም ፊት የነበረ ያው ነው። በኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ ወንጌልን ገና ያልሰሙት፥ ወይም ደግሞ ያልተረዱት፥ ሰንትና ሰንት ናቸው! ሚስት ያለችው ክርስቲያን ግን ሚስቱንና ልጆቹን አስከትሎ እህልና ውኃ ሕክምናም ወደማይኖበት ለፍራ እንደምን ሊሄድ ይችላል? ሉረ አይችልም! አግብቶአልና ቤተ ሰዎቹን እየጠበቀ ልጆቹን እያሳደገ እቤቱ መቀመጥ የግድ ያስፈልገዋል። (1 ጢሞ. 5፥8።) ሚስት ላገባ ሰው ወደ በረሃ መሄድ ችግር ነው የማይገባም ነው። በዚህ ምክንያት፥ ሚስት ያላገባ ሰው እስከ አገሩ ዳርቻ ሁሉ ድረስ ሄዶ ወንጌልን ያለ አሳብ ለማስተማር ይችላልና፥ ዛሬም ገና «ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።»

ያላገባችሁ ሰዎች ሆይ፥ ይህን ነገር እለቡ ልብም አድርጉ። ጳውሎስ ‹‹ስው እንዲህ (በድንግልና) ሆኖ ቢኖር መልካም ነው» ይላል። በውነትም መልካም ነው። በጌታ አንልግሎት ረገድ በድንግልናና የማይባክን ሆኖ መኖር መልካም ነው። ይሁን እንጂ ሐዋርያው ሁለቱን ኑሮ አመዛዝኖ ከማግባት ድንግልና ሁልጊዜ ይሻላል ብሎ አለማስተማሩን አንዘንጋ።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 8።

[1] ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋም፥ ሁላችን እውቀት እንዳለን እናውቃለን። እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል። [2] ማንም አንዳች የሚያውቅ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው [3] ገና አላወከም፤ ማንም ግን እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው።

[4] እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብላት፥ ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ ከአንዱም በቀር ማንም [5] አምላክ እንደሌለ እናውቃለን። መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም [6] ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከአርሱ የሆነ እኛም ለአርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በአርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።

[7] ነገር ግን ይህ እውቀት በሁሉ ዘንድ አይገኝም፤ አንዳንዶች ግን ጣዖትን እስከ አሁን ድረስ ስለ ለመዱ፡-ለጣዖት የተሠዋ ነው ብለው ይበላሉና ሕሊናቸው ደካማ ስለ ሆነ [8] ይረክሳል። መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም፤ ባንበላም ምንም አይጎድለንም ብንበላም ምንም አይተርፈንም። [9] ዳሩ ግን ይህ መብታችሁ ለደካሞች እንቅፋት እንዳይሆንባቸው ተጠንቀቁ። አንተ እውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ስትቀመጥ እንድ ሰው ቢያይህ፥ ደካማ ሰው ቢሆን ለጣዖት የተሠዋውንም ለመብላት ሕሊናው አይታነጽበትምን? [11] በእንተ እውቀትም ይህ ደካማ ይጠፋል፥ እርሱም ክርስቶስ [12] የሞተለት ወንድም ነው። እንዲህም ወንድሞችን እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ [13] ክርስቶስን ትበድላላችሁ። ስለዚህም መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ፥ ወንድሜን እነዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ ሰምንት።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ አባታቸውን የጠየቁት ሁለተኛ ጥያቄ ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ ነበረ። ይህን ሥጋ መብላት ይገባችዋል አይገባቸውም? ስለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነው በም. 8 በም. 9 እና በም. 10 ላይ ተጽፎ ይገኛል።

በም. 8 ላይ ሐዋርያው «እውቀት አላችሁና ስመብላትስ በእውነት መብት አላችሁ፥ ወንድማችሁን ታሰናክሉ እንደሆነ ግን በመብታችሁ ባትጠቀሙ ይሻላል» ይላቸዋል።

በም. 9 ላይ ሐዋርያው «እኔማ መብት ነበረኝ፤ ግን ሰውን ስመጥቀምና እክሲልን ለማግኘት ስል እኔ በመብቴ አልተጠቀምሁም» ብሎ ራሱን እንደ ምሳሌ ያደርጋል።

በም. 10 ላይ ሐዋርያው «ይህን ሥጋ መብላት እጅግ ያስፈራል፤ ሆኖም መብላት ከጠቀመ ተጠንቅቃችሁ ብትበሉት አይጎዳም» ብሎ መጨረሻ ውሳኔውን ይሰጣል።

ይህን ምዕራፍ ማስተዋል ስንወድ ዘመኑንና የቤተ ክርስቲያንን ሁኔታ መገንዘብ ያስፈልገናል። ቆሮንቶስ ታላቅ ከተማ ነበረ፥ ሕዝቡም አረመኔዎች ነበሩ። አረመኔዎች ሆነ ብዙ አማልክትን እያመለኩ ጣዖታትን አበዙ። በየበዓላቱ ቀን፥ ሕፃንም ሲወለድ፥ ሰው ሚስት ሲያገባ ወይም ሰው ሲሞት፥ ለእነዚህ ጣዖታት መሥዋዕትን ይሠዉ ነበር። ይህም ብቻ ላይሆን ለማኅበር ሲሰበሰቡ ወይም ሰው ወደ ዝመድ ቤት ተጠርቶ ግብዣ ሲደረግ ሥጋ ታርዶ መሥዋዕት ይቀርብና እድምተኞቹ ባንድነት ይበሉት ነበር። ይህም እጅግ የጸና በሰው ሁሉ የተደረገ የአገር ደንብ ነበረ። ለመሥዋዕት ከቀረበው ሥጋ ጥቂቱ በመሠዊያ ላይ ሲቃጠል የቀረው ግማሹ ለካህን ግማሹም ለአቅራቢው ተሰጥቶ፥ ወይም በግኅበር ይበላ ወይም በገበያ ይሸጥ ነበር። በዚህ ምክንያት በጣዖት ቤት ተሰብስቦ መብላት ደንብ ነበረ፤ ከዚህም የተነሣ በገበያ ከሚገኘው ሥጋ የሚበልጠው ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ሆነ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች ተቸገሩ። በጣዖት ቤት ወደሚደረገው ግብዣ ይሂዱ አይሂዱ? ባይሄዱ መቼም ማስቀየም ራስንም ከባልንጀራ ሁሉ መለየት አይቀርም ነበር። እንደዚሁም ሁሉ በገበያ የሚገኘውን ሥጋ አንበላም ቢሉ በቤታቸው መቸገር ብቻ ላይሆን የሥራ ጓደኞቻቸው ወደ ቤታቸው ቢጠሩአቸው ይቸገራሉ። ከእነዚያ የሥራ ጓደኞች የሚበዙት አረመኔዎች ይሆናሉና የቀረበው ሥጋ ለጣዖት የተሠዋ ይሆናል። ታዲያስ ይሂዱ አይሂዱ? ቢሄዱና ይህን ሥጋ ቢበሉ ከጣዖት ጋር የተስማሙ ይመስል የለምን? ክርስቲያኖች እንግዲህ ተቸገሩ። እኩሌቶቹ፡- ሉረ! ሰው ሁሉ ጣዖት ምንም እንዳይደለ ያውቃልና በጣዖት ሞኝነት የሚታለል የለም፤ ስለዚህ ብንሄድ ብንበላም ምን አለበት? ሲሉ ሌሎቹ ተጠራጠሩ፥ ሊሄዱም ሊበሉም አልወደዱም።

ቁ. 1-6። ይህ የምዕራፉ መጀመሪያ ከፍል የእውቀት ክፍል ነው። ሐዋርያው መልስ ሲጽፍ ከእነርሱ ዘንድ በመጣው ደብዳቤ ላይ የተገኙትን ብዙ ቃሎች ይጠቅሳል። ለምሳሌ፡- የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በእውቀታቸው ተመክተው፡- «ሁላችን እውቀት አለን»። አሉ። ጳውሎስም ቃላቸውን መነሻ አድርጎ «እውቀትስ አላችሁ፥ እውቀት ግን ብቻውን ሲሆን የታመነ መሪ አይሆንላችሁም» ብሎ መለሰላቸው። እውቀት ብቻ ያስታብያል በሌሎችም ሰዎች ድካም ያሥቃል፤ ስለዚህ እውቀት ብቻውን ሲሆን ሰውን ወደ መበደል ያደርሳልና እውነተኛ መሪያችን ሲሆን አይችልም። ፍቅር ግን ሲኖርበት

ደካማው ላይበደል ይታነጻል። ሁለተኛ ደግሞ፥ የዛሬ እውቀት ጎደሎ ነውና (ም. 13፥13) ሰው ሌሎችን እስኪንቅ ድረስ በእውቀቱ ቢኮራ ገና ምንም አልተማረም ማለት ነው። ስለዚህ ማንም ሰው ዛሬ በእውቀቱ መኩራት አይገባውም። ዋጋ ያለው ነገር ማወቅ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ መታወቅ ነው። (2 ጢሞ. 2፥19። ገላ. 4፥9።) ስለዚህ መሪአችን እውቀት ሳይሆን ፍቅር ቢሆን ይሻላል።

አሁንም ደግሞ ጳውሎስ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብላት ሲጠይቁት «ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ እናውቃለን» ደግሞ «ከአንዱ በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን» ብለው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የጻፉትን ቃል ይጠቅሳል። በቃላቸውም ተስማምቶአል፤ ምክንያቱም ይህ ከጥንት ጀምሮ መሠረታዊ የአይሁድ እምነት ኖሮአል። (ዘዳግ. 4፥39፤6፥4) ክርስቲያኖችም ተቀብሰውት አጽንተውታል። ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ ከሌለ፥ መኖሪያቸው እኩሌቶቹ በሰማይ (የሐዋ. 14፥11) እኩሌቶቹም በምድር (በተራራ ላይ) እንደ ሆነ የታሰበ ሌሎች አማልክትና በአሊም (ጌቶች፥ ሆሴ. 2፥16፡17) አንዳሉ ቢባልም እንኳ እነርሱ ከንቱዎች እንደ ሆኑ በእውነትም በፍጹም እንደሌሉ ታውቆአል። ለሌሎቹ ሰዎቹ እንኳ አማልክትና ጌቶች የተባሉት ቢኖሩም ለክርስቲያኖች አንድ አምላክ ብቻ አንድ ጌታም ብቻ አለ። አምላክ፥ የሁሉ ምንጭ የሆነ እብ ነው፤ (ኤፌ. 4፥6) ጌታ፥ ሁሉ የተደረገበቱ አድራጊ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ዮሐ. 1፥3። ቆላ. 1፥15-17። ዕብ. 1፥2።) እነዚህም ሁለቱ አንድ እግዚአብሔር ናቸው። (1 ጢሞ. 2፥5።) ሌላም አምላክ ሌላም ጌታ የለም።

ቁ. 7-13። የምዕራፉ ሁለተኛ ክፍል የፍቅር ከፍል ነው ከዚህም በላይ እንዳየነው ሁሉ ከእውቀት ፍቅር ይበልጣል። ሐዋርያው «ሁላችን እውቀት አለን»። ብለው የቆሮንቶስ ሰዎች የተናገሩትን ቃል ይደግፋል። ሆኖም ይህ እውቀት በሁሉ ዘንድ ስለማይገኝ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ መብላት ገና ተገቢ አይሆንም ይላል። ምክንያቱም፥ እንበላ እንደሆነ ደካማ ወንድማችንን አናሰናክል ይሆናል፤ ማለት፥ እውቀት የሚፈቅደውን ፍቅር ምናልባት ይከለክላል ማለት ነው።

ዘመኑንና ሁኔታውን ደግመን እናስብ። የቆሮንቶስ ሰዎች እንደ ተሰሎንቄ ሰዎች ሆነው አሁን በቅርቡ ብቻ ስሕያውና ለእውነተኛ አምላክ ያገለግሉ ዘንድ ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር ዘወር ብለው ነበር። (1 ተሰ. 1፥9፡10።) ዕድሜአቸውን ሁሉ ጣዖታትን ለምደው ነበር፥ ጣዖታትም ሕይወታቸውን በሙሉ ገዝተው ነበር። እንግዲያስ የጣዖትን ነገር በአንድ ጊዜ ለመተው ቀላል ነገር አልነበረም። ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ፥ ከአንድም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ በአእምሮአቸው አውቀዋል፤ ሆኖም አለ የሚል ስሜት ገና አልሰቀቃቸውም። ሌሎች አማልክትና ሌሎች ጌቶች እንደሌሉ ቢያውቁም የዱሮ አሳብና ልማድ ጸንቶባቸዋልና አንዳች ዓይነት ነገር፥ ወይም መናፍስት ወይም ገገሮች፥ እንዳሉ ይሰማቸዋል። ይህም ስለ ሆነ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ሲበሉ ያ ስሜት ያሰናክላቸዋልና በጥርጥር ስለሚበሉት ሐሊናቸው ይረክሳል። (ሮሜ. 14፥23።) እንግዲያስ ለምን ብለው ይብሉት? መብልን መብላት ወይም አለመብላት ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል እንዴ? ባንበላ በእርሱ ዘንድ ጎደሎዎች ሆነን እንገኛለንን? ወይስ ብንበላ ደግሞ አብዝተን አንዳች ነገር መጨመራችን ነውን? ከቶ አይደለም።

የቆሮንቶስ ሰዎች «ለመብላት መብት አለን»። አሉ። መብትማ አላቸው። መብታቸው ግን ለሌሎች ሰዎች እንቅፋት ቢሆንባቸውስ? ለምሳሌ፥ እውቀት ያለህ የጸናህ ክርስቲያን

ስትሆን በጣዖት ቤተ በማዕድ ተዘልለህ ተቀምጠህ ሳለህ ሕሊናው የደከመ ሰው ያይሃል። እንደዚህ ማድረግ የማይገባ መሆኑን ሕሊናው ያስታውቀዋል፥ እንተ ግን ብርቱው እዚያ ተቀምጠህልና እርሱ የማይገባ እንደ ሆነ የሚቆጥረውን ነገር ለማድረግ ይታነጻል (ሮሜ. 14፥14)፥ ማለፊያ በሆነም በእንተ እውቀት ይህ ሰው ለዘላለም ይጠፋል፥ ሕሊናውን በድሎአልና። ግነጽስ ይገባሃል (ቁ. 1)፥ ወደ ጥፋት ታንፀው እንደሆንላ? ይፈርድብህ የለምን? ይህ ሰው ደግሞ የውጭ ሰው አይደለም፥ ወንድም ነው እንጂ። (ከቁ. 11 ጀምሮ እስከ ቁ. 13 ድረስ ‹‹ወንድም» የተባለው ቃል 4 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል።) ወንድም ብቻ ላይሆን ሰው የሞተለት ወንድም ነው። ተራ ሰው የሞተለትም ወንድም ብቻ ላይሆን ክርስቶስ የሞተለት ወንድም ነው። (ሮሜ. 14፥15።) ይህንንስ መበደል ምንኛ ከፉ ነው! እርሱንም ብቻ መበደልህ አይደለም፥ ክርስቶስን ትበድላለህ እንጂ። (ማቴ. 10፥40-42፤25፥40፥45።)

እንግዲያስ «ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ መብላት ይገባል አይገባም?» ብለው የቆሮንቶስ ሰዎች ላቀረቡት ጥያቄ ሐዋርያው «እውቀት አላችሁና ለመብላት መብት አላችሁ፥ እኔው ግን መብል ወንድሜን የሚያሰናክል ከሆነ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ይቅርና ስለ ፍቅር ብዬ ማንኛውንም ዓይነት ሥጋ ሁሉ ለዘላለም አልበላም» ይላል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ሁላችን እውቀት እንዳለን እናውቃለን።» ቁ.1።) ይህን ምዕራፍ የምናነብ ክርስቲያኖች ከዚህ በላይ የተጻፈውን ቃል ሁሉ እጅግ በጣም ልብ እናድርገው። በእኛ ዘንድ ደግሞ ይህ የእውቀት ዘመን አይድለምን? ዛሬም ሰው ሁሉ ያውቅ የለምን? ከዱሮ ጨለማ ወጥተን ብርሃንን አገኘን፥ ከዱሮም እስራት ሁሉ ነፃነት ተሰጠን። እንግዲያስ እንጠንቀቅ፥ እውቀት ያለታብያልና! እውቀት መጥፎ እንደ ሆነ እይድለም፥ እውቀት እጅግ መልካም ነው! ሆኖም ገቢራችንን በትምህርት ባገኘነው እውቀት ብቻ ብናደራጅ ከፍ ያለ ስሕተት እናደርግ ይሆናል። «እውቀት አለን፥ ሰውን ሁሉ እናክላለን ክብዙም እንበልጣለን» ስንል ወንድማችንን በመናቅ ምክንያት እንዳንበድል መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ታላላቅ የሃይማኖት ነገሮች፥ ስለ ጽድቅና ስለ ዘላለም ሕይወት በክርስቶስ ስለማመን ሳይሆን ዕለት ዕለት ስለሚገጥሙን ዝቅ ስላሉ ነገሮች መናገሩ ነው። ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ እንደ መብላት ያሉ ነገሮች ናቸው። የተማረ ሰው እነዚህን ነገሮች ምንም እንዳይደሉ ያውቃልና ይንቃቸው ይሆናል። በሰው ሁሉ ዘንድ ግን ይህ ታላቅ እውቀቱ አይገኝምና ሌሎቹ እነዚህን ነገሮች ገና ሲያከብሩ ይኖራሉ። ይህም ሲሆን ያ አዋቂ ሊንቃቸውና እነርሱ የለመዱትን ነገር ገና አሁንም እንደሚፈጽሙ ሲያይ መሣቅ ወይም መዘበት አይገባውም። እውነተኛ ክርስቲያን ራሱን ለማላቅ ላይሆን ሌሎቹን ለማነጽ ተጠርቶአል። አንዳንዶች ክርስቲያኖች ግን ሰው እነዚህን ነገሮች ሁሉ ወዲያውኑ ወይም ካልተወ ወይም ሳላደረገ እርሱ እውነተኛ ክርስቲያን አይደለም ይላሉና ወይም አንዲተዉት ወይም እንዲያደርጉት ያደፋፍሩአቸዋል ይቆለቁሉአቸዋልም። እውነት። እንደዚህ ሲያደርጉ ወንድማቸውን በሃይማኖቱ ለማነጽ ያስቡ ይሆናል፤ ቢሆንም ሳያንጹት ያሰናክሉትና ወደ ጥፋት ያደርሱት ይሆናል። እውቀት ያለው ሰው በእውቀቱ ወንድሙን እንዳያጠፋ ምንኛ መጠንቀቅ ያስፈልገዋል! ተምሬአለሁ፥ ወደ

ውጭ አገርም ሄጀአለሁ ብሎ ተመልሶ ውንድሞቹን በእውቀቱ ለሚያስት ሰው ወዮለት! «እውቀት ያስታብያል፥ ፍቅር ግን ያንጻል» የተባለውን ቃል ልብ ያድርግ።

ለ/ «ሕሊናቸው ይረከሳል፤ ሕሊናቸውን ታቆስሳላችሁ።» (ቁ. 7፥12።) ሕሊናችንን ማርከስ ወይም ደግሞ የሌላውን ሰው ሕሊና ማቁሰል ምን ያለ አበሳ ነው! ሕሊናችንን ከምንሰማ ይልቅ ሰውን ብንሰማ ሁልጊዜ ስሕተት መሆኑን ልብ እናድርግ። ለምሳሌ፥ እነዚያ ሕሊናቸው ደካማ የሆነ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ መብላት የማይገባ መሆኑ ሲሰማቸው አዋቂዎች ክርስቲያኖች ሲበሉት አይተው ሕሊናቸው ቢጸየፍባቸው እንኳ ለመብላት ተደፋፈሩ። መብላትማ ከፉ አልነበረም፥ ተጠራጥረው ስለ በሉ ግን ሕሊናቸው ረክሶአል፥ እነርሱም ተኮነኑ። (ሮሜ. 14፥14፥23።) የረከሰ ሕሊና ምን ያለ መጥፎ ነገር ነው! የረከሰ ሕሊና ወደ መከንከንና ወደ እፍረት፥ ወደ ኩነኔና ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ መለየት ያደርሳል። ሕሊናን ማርከስ እጅግ በጣም መጥፎ ነገር ነውና ቅዱስ ጳውሎስ «በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለበት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ» ብሎአል። (የሐዋ. 23፥1፤24፥16።) ስለዚህ የአንድ ነቢይን ቃል ሰምቶ ሕሊናውን በደፈረ ባልታዘዘው ነቢይ ላይ የደረሰውን ጉዳት እናስብና ሕሊናችን ሊከለክለን ሲጥር የአንድ አዋቂ ሰው ቃል በመስማት ሕሊናችንን ከማርከስ እንጠንቀቅ። (1 ነገ. 13፥7-22።)

እንደዚሁም ሁሉ፥ ሕሊናው የተጠራጠረውን ለማድረግ በመደፋፈር የሌላውን ሰው ሕሊና ብናቆስል በእርሱም በእኛም ላይ ኩነኔን እናመጣለንና እንዲህ ያለውን እበላ ከመሥራት እግዚአብሔር ይጠብቀን።

ሐ/ በእውኑ እነዚህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ እንደ መብላት የሚመሳሰሉ ዝቅተኞች ነገሮች ደኅንነታችንን ይነካሉን? ብናደርጋቸው ባናደርጋቸውም ወደ እግዚአብሔር ያቀርቡናልን ወይስ ያርቁናልን? ሁለተኛ ደግሞ፥ መብሳቴ ወይም አለመብላቴ፥ ይህን ታናሽ ነገርም ማድረጌ አለማድረጌ፥ ወደ እግዚአብሔር መቅረቤ ወይም ከእግዚአብሔር መራቄ ምልከትና ሚዛን ይሆናልን? ቅዱስ ጳውሎስ «መብል ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም፥ ባንበላም ምንም አይጎድለንም ብንበላም ምንም እይተርፈንም» ብሎ ይህን አሳብ ሳይደግፍ ቀረ። (ቁ. 8።)

መ/ «ይህ መብታችሁ ለደካሞች እንቅፋት እንዳይሆንባቸው ተጠንቀቁ።» (ቁ. 9።) በመቅድሙ ውስጥ «ለክርስቲያን የተፈቀደው ያልተፈቀደውም እንዴት ይታወቃል?» ለሚል ጥያቄ መልሱ በዚህ መልእክት ውስጥ ይገኛል ብለናል። የመልሱ ግማሽ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደ ተጻፈው ነው። ጥርጥር የሚደረግበት ማንኛውም ነገር ቢገጥመን ያን ነገር ለማድረግ የተፈቀደ እንደሆነ ያልተፈቀደም ልናውቅ ስንፈልግ ሁለት ነገር አስቀድመን ማሰብ ወይም ሁለት ጥያቄ አስቅድመን መጠየቅ ያስፈልገናል። እነዚህም 1ኛ ሕሊናችን ተስማምቶበታልን? 2ኛ፥ ፍቅርስ ያደርገው ነበርን? የሚሉ ናቸው።

1ኛ፥ እኛ ሁላችን ዛሬ እውቀት እንዳለን እናውቃለንና ሕሊናችን ከተስማማበት ያን ነገር እንዳናደርግ በእኛ ወገን በኩል ማሰናከያ የለም። ሕሊናችን ግን የተጸየፈበት እንደሆነ ወይም ቢጠራጠር ለዘላለም ከቶ አናድርገው።

2ኛ፥ ከርስቲያን ሌሎችን ለማነጽ ተጠርቶአልና ወንድማችንን ደግሞ ማሰብ ያስፈልገናል። ያ ነገር ለእኛ ፈጽሞ የተፈቀደ ነገር ይሆን ይሆናል፥ እኛ ግን ስናደርገው ወንድማችን ቢሰናከልበት ያን ነገር ማድረግ ከቶ አይገባንምና ለእኛ ደግሞ ያልተፈቀደ ነገር ይሆናል። ስለዚህ መሪአችን ፍቅር ይሁን። ፍቅር ያደርገው እንደሆነ እናድርገው፤ ፍቅር ግን እይሆንም ቢል እናድርገው። ፍቅር እይታበይም፥ የማይገባውን እያደርግም፥ የራሱንም እይፈልግም (ም. 13፥4፥5)፤ ስለዚህ በእንድ ነገር ላይ ጥርጥር ወይም ክርክር ቢነግ ፍቅር መሪአችን ሊሆን ይችላል።

እንግዲያስ የተፈቀደውን ያልተፈቀደውንም ልናውቅ ስንፈልግ በራሳችን በኩል ሕሊና፥ በሌሎችም በኩል ፍቅር ይፈቅድልን እንደሆነ እስቀድመን እናስብ። (ደግሞ በም. 6፥12 ላይ በማስገንዘቢያ ሀ፥ በም. 10፥31 - ም. 11፥1 ላይም በሚገኘው ማስገንዘቢያ የተጻፈውን ተመልከት።)

ሠ/ «እንተ እውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ስትቀመጥ እንድ ሰው ቢያይህ ...» (ቁ. 10።) ከርስቲያን የትም ዘንድ ቢገኝ ለሌሎች ሁልጊዜ ምሳሌ ነው። ስለሆነም፥ በራስቸው መልካም በሆኑ ነገሮች እንኳ ሌሎችን ልናስት ልናጠፋም እንችላለንና በእነዚህ በመልካሞች ነገሮች ስንኳ መጠንቀቅ ያስፈልገናል። በሐዋርያው ዘመን አንድ ሰው በጣዖት ቤት በማዕድ የተቀመጠውን ከርስቲያን በማየቱ ተሰናክሎ ወደ ጥፋት ለመድረስ እንደ ቢቃ፥ እንደዚሁም ሁሉ ዛሬ እንድ ሰው እኛን በዳንስ ቤት፥ በሲኒማ ቤት፥ በጠጅ ቤት በመብታችን ተጠቅመን ስንቀመጥ፥ ሲጃራን ስናጨስ ወይም ከዓለማውያን ጓደኛዎች ጋር ስንደሰት ቢያየን ተሰናክሎ ለዘላለም ይጠፋ ይሆናል። ከርስቲያን ዘላለማዊ ነፍሰን እንዳይገድል በጣም ይጠንቀቅና ሌሎችን ስለሚያሰናክሉት የተባለውን የጌታን ቃል ያስብ። (ማቴ. 18፥6፥7።) በእውቀታችንና በብርሃናችን፥ በነፃነታችንና በመብታችን እንመካ፤ ነገር ግን «እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?» ብሎ መጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ በተናገረው ቃል ለማመካኘት ሳናስብ (ዘፍጥ. 4፥9) በእኛ አብነት እንድ ወንድማችን ለዘላለም እንዳይጠፋ ብለን እካሄዳችንን ሁሉ እየተመለከትን ራሳችንን ከመልካሙም እንኳ እንጠብቅ።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ9።

1፤ እኔ ነጻ አይደለሁምን? ሐዋርያስ አይደለሁምን? ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስንስ አላየሁትምን? እናንተስ በጌታ ሥራዮ [2]፤ አይደላችሁምን? የሐዋርያነቴ ማኅተም በጌታ እናንተ ናችሁና ለሌሎች ሐዋርያ ባልሆን ለእናንተስ ምንም ቢሆን ሐዋርያ ነኝ።

[3፤4]፤ ለሚመረምሩኝ መልሴ ይህ ነው። ልንበላና ልንጠጣ [5]፤ መብት የለንምን? እንደ ሌሎች ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች እንደ ኬፋም፥ እኅት ሚስታችንን ይዘን ልንዞር 6፤ መብት የለንምን፡ ወይስ ሥራን ለመተው መብት የሌለን [7]፤ እኔና በርናባስ ብቻ ነን? ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? ወይስ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማን ነው? ወይስ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማን ነው?

[8]፤ ይህን በሰው ሥልጣን ብቻ እላለሁን? ሕግስ ደግሞ [9]፤ ያን አይልምን? የሚያበራየውን በሬ አፉን እትሰር ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፎአልና። እግዚአብሔርስ ስለ በሬዎች [10]፤ ይገደዋልን? ይህን የሚለው ፈጽሞ ስለ እኛ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ ሊያርስ የሚያበራይም እንዲካፈል በተስፋ ሊያበራይ ስለሚገባው በእውነት ስለ እኛ ተጽፎአል። [11]፤ እኛ መንፈሳዊን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተን የሥጋዊን [12]፤ ነገር እኛ ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን? ሌሎች በእናንተ ላይ ይህን መብት የሚካፈሉ ከሆኑ እኛማ ይልቁን እንዴታ?

ነገር ግን የክርቶስን ወንጌል እንዳንከለክል በሁሉ [13]፤ እንታገግለን እንጂ በዚህ መብት አልተጠቀምንም። በመቅደስ ነገር የሚያገለግሉ ከመቅደስ የሆነውን ነገርን እንዲመገቡ፥ በመሠዊያውም የሚጸኑ ከመሠዊያው እንዲካፈሉ [14]፤ እታውቁምን? እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል።

[15]፤ እኔ ግን ከእነዚህ ሁሉ ምንም አልተጠቀምሁም። እንዲህ እንዲሆንልኝ ይህን አልጽፍም፤ ማንም ትምክህቴን [16]፤ ከንቱ ከሚያደርግብኝ ሞት ይሻለኛልና። ወንጌልን ብሰብክ እንኳ የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኝ ነውና፤ ወንጌልንም [17]፤ ባልሰብክ ወዮልኝ። ይህን በፈቃዴ ባደርገው ደመውዝ አለኝና፤ ያለ ፈቃዴ ግን ባደርገው መጋቢነት በእደራ ተሰጥቶኛል። [18]፤ እንግዲህ ደመወዜ ምንድር ነው? ወንጌልን እየሰበክሁ በወንጌል ካለኝ መብት በሙሉ እንዳልጠቀም ወንጌልን ያለ ዋጋ ብናገር ነው።

[19]፤ ከሰው ሁሉ እርነት የወጣሁ ስሆን የሚበልጡትን [20]፤ እንድጠቅም እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ። አይሁድንም እጠቅም ዘንድ ከእይሁድ ጋር እንደ እይሁዳዊ ሆንሁ፤ ከሕግ በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ፥ እኔ ራሴ ከሕግ በታች ሳልሆን፥ ከሕግ በታች ላሉት ከሕግ በታች [21]፤ እንዳለሁ ሆንሁ፤ ሕግ የሌላቸውን እጠቅም ዘንድ ያለ እግዚአብሔር ሕግ ሳልኖር ነገር ግን በክርስቶስ ሕግ በታች ሳለሁ፥ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደ ሌለን ሆንሁ፤ [22]፤ ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ እንዳንዶችን እድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር [23]፤ በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ። በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ።

[24]፤ በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት፥ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን እንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል እታውቁምን? [25]፤ እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ። የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ስውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል [26]፤ ሊያገኙ ነው፥

እኛ ግን የማይጠፋውን። ስለዚህ እኔ ያለ እሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ እልሮጥም፥ ነፋሰን እንደሚነስም [27] ሁሉ እንዲሁ እልጋደልም፤ ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየነሰምሁ አስገዛዋለሁ።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ ዘጠኝ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በም. 8 ላይ ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ ሲጽፍ ለደካማ ወንድማቸው ሲሉ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመብታቸው እንዳይጠቀሙ መክሮሰቸዋል። እሁን በም. 9 ላይ ራሱን ምሳሌ አድርጎ ያን ምክር ያትማል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ከእሪት ነፃ እንደ ሆኑ እንዲሁም ጳውሎስ ነፃ ነው፤ እነርሱ ክርስቲያኖች እንደ ሆኑም እርሱ ከተራ ክርስቲያን የሚበልጥ ሐዋርያ ነው፤ እነርሱ መብት እንዳላቸው እንዲሁም እርሱ መብት አለው። በመብታቸው እንዳይጠቀሙ ጽፎላቸዋል፥ እርሱም ደግሞ በመብቱ አልተጠቀመም። እድርጉ ያላቸው እርሱ ራሱ ያደረገውን ነው፥ እርሱንም ይመስሉ ዘንድ ይወዳል። (ም. 11፥1)

ጳውሎስ በዚህ በም. 9 ላይ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑን አስቀድሞ በማረገገጥ (ቁ. 1-3) መብት እንዳለው (ቁ. 4-14)፥ ነገር ግን በዚያ መብት እንዳልተጠቀመ (ቁ. 15-27) ያስረዳል።

ቁ. 1-3። እነኝህ ቁጥሮች የምዕራፉ መሠረት ናቸው። ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን አልተቀበለምና እንዳንዶች ጠላቶቹ «ሐዋርያ አለመሆኑን ቢያውቅ ነው» እሉ። ይህን ስሕተት ለማረምና መብት እንዳለው ለማረጋገጥ ጳውሎስ ሁለት ማስረጃዎች በማቅረብ ሐዋርያነቱን ያረጋግጣል።

1ኛ ማስረጃ፥ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ማየቱ

2ኛ ማስረጃ፥ በሐዋርያ ኃይል መሥራቱ።

1ኛ፥ ሐዋርያት የትንሣኤ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋልና ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ያልተገለጠለት ሰው ሐዋርያ ለመሆን አልበቃም። ስው ሐዋርያ የሚሆን ከሆነ ከሙታን የተነሣውን ክርስቶስን ያየ እንዲሆን የግዴታ ነበረ። (የሐዋ. 1፥21፡22፤2፥32።) ጌታ ላይስቀል በፊት ጳውሎስ አይቶት እንደ ሆነ እናውቅም፤ ሆናም በደማስቆ መንገድ ላይ ሳለ ጌታ እንደ ተገለጠለት፥ ጳውሎስም እንዳየው ታውቆአል። (የሐዋ. 8፥1-8። 1 ቆሮ. 15፥8።) ስለዚህም ሐዋርያ ለመሆን በቃ።

2ኛ፥ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ መጥቶ ነበር። እዚያም በእግዚአብሔር ኃይል ሠርቶ የቆሮንቶስን ሰዎች አሳምኖ የክርስቲያን ማኅበር እጀቁሞ ነበር። ስለዚህ የቆሮንቶስ ምእመናን ራሳቸው የሐዋርያነቱ ማኅተም ነበሩ። ሌሎች ሰዎች ቢጠራጠሩትና «ሐዋርያ አይደለም» ቢሉ እንኳ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሊጠራጠሩት አይችሉም። ለእነርሱ ምንም ቢሆን ሐዋርያ ነው። ፈትነውና «ሐዋርያ አይደለም» ብለው ለፈረዱበት ሰዎች መልሱ ይህ ነበር።

ቁ. 4-14። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ ነውና እንደ ቀሩት ሐዋርያት ሁሉ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ኪሣራ ሊበላና ሊጠጣ፥ ሚስቱንም ይዞ ለመዞር፥ ሥራን ሊተውና በቤተ ክርስቲያን ሊቀለብ መብት አለው። መብት እንዳለው የሚያስረዱ 5 ነገሮች አሉ። እነዚህም፡- የሌሎች ሐዋርያት ልማድ (ቁ. 5)፤ የዕለት ዕለት የተፈጥሮ ተገቢነት (ቁ. 7፥ አሪት (ቁ. 8፡9)፥ የካህናት ደንብ (ቁ. 13)፥ የክርስቶስም ቃል (ቁ. 14) ናቸው። እውነት ነው፥ ጳውሎስ ሚስት አልነበረችውም፤ ይሁንና ብትኖር

ኖሮ ይዞአት ለመዞር መብት ነበረው። በመብቱ አልተጠቀመም። የቀሩት ሐዋርያት ደግሞ ሥራን ትተው በቤተ ክርስቲያን ይቀሰቡ ነበር፤ ጳውሎስ ግን በእጁ እየሠራ ራሱን ችሎአልና በዚህ መብት ደግሞ አልተጠቀመም። ይሁን እንጂ ይህ መብት ሁሉ ነበረው። ወታደር ክቀጠረው፥ እትክልተኛ ከፍሬው፥ ባለ ከብት ከመንጋው ለመጠቀም ያስቡ የለምን? ሉረ ያስባሉ! ይህም የሰው አሳብ ብቻ ሳይሆን እረት ያዘዘው ነገር ነው። በዘዳግ. 25፥4 ላይ «የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር)። ተባለ። ግለት፥ «ሲሠራ ላለ በሥራው ከመጠቀም አትከልክለው።» ያን ምዕራፍ ግን ብንመረምር ስለ ሰው እንዲናገር እንጂ ስለ ከብት እንዳይናገር እናገኛለንና እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ ሲሰጥ ዓይነተኛ አሳቡ ስለ ሰው እንደ ሆነ እንረዳለን። የሚለፋ ሁሉ በልፋቱ እንዲጠቀም፥ ክለፋበቱም ለማግኘት ተስፋ እንዲያደርግ የተፈጥሮ ተገቢነት ነው። ጳውሎስ መንፈሳዊን ነገር በልግስና ሁሉ ዘርቶላቸው ነበር፤ አሁን አስፈላጊውን የሥጋን ነገር ሊያጭድ ተስፋ ቢያደርግ መጥፎ ነውን? ሌሎች፥ ሞገዚቶች የሆኑት፥ እነአጵሎስ እነኬፋም ምናልባት፥ በእነርሱ ላይ ይህን መብት የሚካፈሉ ሲሆኑ በወንጌል የወለዳቸው አባታቸው ጳውሎስ አይካፈልምን? ሙሉና ፍጹም መብት አንዳለው አይጠረጠርም።

ታዲያስ? በመብቱ አልተጠቀመም! መብት ነበረው፥ የብሉይ ኪዳን ካህናት ከመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ተቀሰቡ (ዘኁል. 18፥9፡19። ዘዳግ. 18፥1-5)፥ ክርስቶስ ሌሎቹን ሰብዓ በላከ ጊዜ «ለሠራተኞቹ ደመወዙ ይገባዋል» በማለት (ሉቃ. 10፥7) የእዲስ ኪዳን አገልጋዮች ከወንጌል እንዲቀለቡ ደንግጎአል። ጳውሎስ ግን በመብቱ አልተጠቀመም። ምክንያቱስ? ሌሎችን ሰዎች ስለ ተመለከተ ነዋ! ሌሎችን ተመልክቶ አልቀበልም አለ። በም. 8 ላይ እንደ ሰጠው ምክር ነው። እዚያ፥ «መብት ምንም ቢናረኝ እኔ በማደርገው ነገር ወንድሜን እንዳላሰናክል በመብቴ አልጠቀምም» እንዳለ እንዲሁም እዚህ «ለመቀበልስ መብት አለኝ፥ ቢሆንም ወንድሜን አስናክዮ የክርስቶስን ወንጌል እንዳልከለክል አልቀበልም» ይላል። «አናንተ እንዲህ አድርጉ» ብሎ የመከራቸውን እርሱ ራሱ ያደርገዋል ግለት ነው። መብትማ አለው፥ በመብቱ ለመጠቀም ግን አልወደደም።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ « እንደ ሌሎች ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች እንደ ኬፋም።» (ቁ 5።) እዚህ ላይ የተጻፈውን የሐዋርያትን ልማድ እናስተውል። ቅዱስ ጳውሎስ ባለ ሚስት አልነበረም ነገር ግን «ሌሎች ሐዋርያትና የጌታ ወንድሞች ጴጥሮስም»። አግብተው ነበር፤ ሚስታቸውም «እኅት»፥ ግለት ያመነች ክርስቲያን፥ ስትሆን እነርሱ ወንጌልን ለማስተማር በወጡበት ቁጥር ሚስታቸውን ይዘው ይመላለሱ ነበር፥ ያውም በቤተ ክርስቲያን ኪግራ። ከዚህም ልማድ እኛ ሁለት ነገሮች እንማራለን። 1ኛ፥ ሐዋርያት ሚስታቸውን አብራቸው እንድትሄድ እንዳሰቡ። 2ኛ፥ ቤተ ክርስቲያን የሴቲቱን መሄድ ጠቃሚ መሆኑን እንደ ቆጠረና ለመሄድ እንድትችል እንደ ከፈለላት።

በጳውሎስ ዘመን ለሴት ወንድን ማስተማር ነውር ነበርና ሴቶች በማኅበር መካከል እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም ነበር። (1 ጢሞ. 2፥11፡12። 1 ቆሮ. 14፥34፡35።) እንደዚህም ዛሬ «ነውር ነው» የሚሉ አሉና ሴቶች በመላ ማኅበር ፊት መናገር ገና ዛሬ አልተፈቀደላቸውም ይሆናል። ይሁንና ሴቶች በማኅበር ሆነ በቤታቸውም ሌቶችን

ሊያስተምሩ ይችላሉና የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑት የዛሬ ወንጌላውያን በሥራቸው ላይ ላሉ አኅት ሚስታቸውን በቤትዋ ላያስቀሩአት ይዘዋት ቢሄዱ መልካም ነገር ነው። ስለምን? ቢሉም፥ ክርስቶስ ለወንዶች እንደ ሞተ እንዲሁም ለሴቶች ሞቶአልና ለወንዶች ወንጌልን ለመስማት አስፈላጊ በሆነበት መጠን በዚያ መጠን ደግሞ፥ ያውም ምናልባት በበለጠ፥ ልጆችን የሚያስተምሩ እነርሱ ናቸውና ሴቶች እንዲማሩ ያስፈልጋል። ማንስ ያስተምራቸው? በማኅበር (በቤተ ክርስቲያን) መቼም ወንዶች ያስተምሩአቸዋል፥ በውጭ ግን ሴትን ለማስተማር ለወንድ አስቸጋሪና የማያምር ነውና ሴቶች ያስተምሩአቸው። ይህን ነገር እንርሳና የተቻለ እንደ ሆነ ወንጌላውያን ሲወጡ እኅት ሚስታቸውን ይዘው ይሂዱ።

ሁለተኛ ደግሞ፥ ያች ሚስት ከባልዋ ጋር ስትሄድ ቀለብዋን ከቤተ ክርስቲያን ትቀበል እንደ ነበር እንዘንጋ። ቤተ ክርስቲያኑ የሴቲቱን እብራ መሄድ ጠቃሚ መሆኑን ቆጠረውና ለመሄድ እንድትችል ቀሰብዋን ሰጣት። ይህ ለዛሬ ደግሞ ማስረጃና ምሳሌ ሊሆንልን ይችላል። እነርሱ እንዳደረጉ እኛም እናድርግ።

ለ/ «እንደ ጌታ ወንድሞች።)። (ቁ 5።) እነኘህ «የጌታ ወንድሞች» እነማን ናቸው? ስማቸው ያዕቆብና ዮሳ ለምዖንም ይሁዳም ናቸው። (ማቴ. 13፥55። ማር. 6፥3።) በልዩ ልዩ ቦታ ደግሞ ተጠቅሰዋል። (ማቴ. 12፥46። ማር. 3፥31። ዮሐ 2፥12፤7፤3፡5፡10። የሐዋ. 1፥14። 1 ቆሮ. 9፥5።) ያዕቆብ ተብሎ በመካከላቸው የተገኘው የቤተ ክርስቲያን አለቃ የሆነ ነው (የሐዋ. 12፥17፤15፥13፤21፥18። ገላ 1፥19) እርሱም በእዲስ ኪዳን ውስጥ «የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት» የተባለውን መልእክት ጽፎአል። ሰኔታም፥ ወንድሞች ብቻ ላይኖሩት እኅቶች ደግሞ መኖራቸውን እናውቃለን። (ማቴ. 13፥56። ማር. 6፥3።) እነኘህ ወንድሞች የተባሉት በጌታ አላመኑምና (ዮሐ 7፥5) መንፈላውያን ወንድሞች ሊሆኑ እይችሉምና የሥጋ ወንድሞችና እኅቶች መሆናቸው ነውን? ሰዚህ ጥያቄ 3 መልሶች ተሰጥተዋል።

1ኛ፥ ሊቁ ኢየሮም «ማርያም የተባለች የእመቤታችን እኅትና የቀለዮጳ ልጆች ሆነው የጌታ ዘመዶች ናቸው» ይላል። ይህም ይቻላል፤ ሆኖ እንደ ቤተ ሰብዋ ተቆጥረው ከእመቤታችን ጋር እንጂ ክቀለዮጳ ሚስት ከማርያም ጋር አልኖሩምና (ማቴ. 12፥46፤13፥55። ዮሐ. 2፥12፤7፥3) ይህ እውነተኛ አሳብ አይመስልም።

2ኛ፥ ኤጲፋንዮስ ኤዲስ ቆጰስ ዘደሴተ ቆጵሮስ «ዮሴፍ እመቤታችን ማርያምን ሳይወስድ በፊት አግብቶ ወልዶ ነበርና እነዚህ የዮሴፍ ልጆች ናቸው» ይላል። ይህም የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን እምነት ነው፥ ብዙዎችም የያገሩ ሊቃውንት ደግፈውታል። ይህ ትውፊት ገና በሁለተኛው መቶ ዓመት (ገዳ) ውስጥ ታውቆአልና መሠረት ያለው ይመስላል።

3ኛ ሄልቪድዮስ የተባለው ሊቅ ደግሞ «ከኢየሱስ በኋላ የተወለዱ የዮሴፍና የማርያም ልጆች ናቸው» ይላል። በመጋባት ነውር ወይም ርኩሰት የለምና ይህ የሚቻል አሳብ ይሆን ይሆናል። ኢየሱስ በድንግልናዋ ተወለደ፤ ይሁንና ስው የሚታጭ በኋላ እንዲያገባ ነውና፥ ተጫጭተው የነበሩት ዮሴፍና ማርያም በኋላ ተጋብተዋል ልጆችንም ወልደዋል ይባላል። ነገር ግን ይህን አሳብ የሚያስናክሉ 2 ነገሮች አሉ። መጀመሪያው፥ እነዚህ ወንድሞችና እኅቶች የሥጋ ቢሆኑም መሆናቸውም ቢታወቅ፥ በተለይ ደግሞ ከእነርሱ

እንዱ የኢየሩሳሌም ጳጳስ በመሆኑ በክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ እጅግ የታወቀ ሲሆን፥ ገና በሁለተኛው መቶ ዓመት (ገጻ) ውስጥ «እመቤታችን የዘላለም ድንግል ነበረች» የሚል ትውፊት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደምን መነሣት ቻለ? ከተነሣም ከክርስቲያኖች የሚበዙቱ ለምን አመኑት? አምነውታልና። ሁለተኛው ደግሞ፥ እነዚያ ወንድሞቹ በኢየሱስ ባያምኑ እንኳ እመቤታችን ገና 4 ወንዶች ልጆች ካሳት ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ ሌላ ልጅ እንደሌላት አድርጎ እናቱን «እነሆን ልጅሽ!» ለምን አለ? ለቅዱስ ዮሐንስም አደራ ለምን ሰጣት? (ዮሐ. 19፥26፡27።) ስለዚህ ወንድሞቹ የተባሉት የሥጋ ወንድሞች ነበሩ ለማለት ያስቸግራል።

ሐ/ «የክርስቶስን ወንጌል እንዳንክለክል።» (ቁ. 12።) የወንጌል ሠራተኛ ከቤተ ክርስቲያን ዘንድ ቀለብን (ደመወዝን) በመቀበል ወንጌልን እንደምን ይክለክለዋል? ቢባል መልሱ እንደሚከተለው ነው።

1ኛ፥ ደመወዝን ከማኅበሩ (ከቤተ ክርስቲያኑ) የሚቀበል ሰው በማኅበሩ በመከበድ ምክንያት (2 ቆሮ. 11፥ 9፤12፡14) ሁለተኛ ሠራተኛ እንዳይወጣ ይከለክል ይሆናል፥ ይህንም በማድረግ ወንጌል እንዳይስፋፋ ይከለክላል።

2ኛ፥ የወንጌል ሠራተኛ ባለ ደመወዝ ሲሆን የሚያዩት ሰዎች «ውንጌልን የሚሰብከው እኮ ስለ ደመወዙ ነው» ይላሉ፥ በዚህም ምክንያት ሥራውን ይንቅፋሉ፥ ወንጌልም ይከለከላል።

እኛ ዛሬ ወንጌልን የምንሰብክ ሰዎች እነዚህን 2 ነገሮች እናስብ። ወንጌልን መስበክ በሁላችን ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የደረሰ ዕዳና መጋቢነት ነውና ከሰው ዘንድ ደመወዝን መቀበል ተገቢነት የለውም። (ሮሜ. 1፥14። 1 ቆሮ. 9፥16፡17።) ሆኖም ሰው ሁሉ ራሱን እየቻለ መስበክ አይችልምና ለእንዳንዶች ሰዎች ደመወዝን ከማኅበሩ መቀበል የግዴታ ነገር ይሆናል። ይሁን እንጂ እንደ ሐዋርያው እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆነን ራሳችንን እየቻልን ብንሰብክ በጣም መልካም ነገር ነው።

ቁ. 15-27። ሐዋርያው መብት እንዳለው ከቁ. 4-14 አስረድቶናል፤ አሁንም በዚያ መብት እንዳልተጠቀመ ያልተጠቀመበትንም ምክንያት በዚህ ክፍል ላይ ይገልጣል። በመብቱ አልተጠቀመም፥ ማለት ከቤተ ክርስቲያን ዘንድ ቀለብ አልተቀበለም፥ ወደፊትም ሊቀበል አልወደደም። ምክንያቱስ? ምክንያቱም ከሥራው የሚመነበትን እንዳች ነገር ለማግኘት ስለ ወደደ ነው። ወንጌልን መስበክ የተጫነበት ተግባር ነበረና ወንጌልን ባይሰብክ ወዮለት እንጂ በመስበኩ ትሩፋት የለውም። እግዚአብሔር መጋቢ አድርጎት ነበረና የተሰጠውን አደራ በታማኝነት እንዲፈጽም የግዴታ ነገር ነበረ። (ም. 4፥1፡2።) ይሁን እንጂ ይህን ሲያደርግ ከቤተ ክርስቲያን ዘንድ ቀለብ ለመቀበል መብት ነበረው። በዚህ መብቱ ባለመጠቀሙ በወንጌል ሰብክቱ ላይ እንደ ስጦታ ዓይነት ታናሽ ነገርን እንደ መጨመር ሆነለት። ማለት ወንጌልን በፈቃድ፥ ያለ ደመወዝ፥ ሲሰብክ እንዳች ነገር ከራሱ ከዶ ለእግዚአብሔር መስጠቱ ነውና በዚህ መስጠቱ ሊመካ ችሎአል። ስለዚህ የጳውሎስ ትምህርትና ደመወዝ ይህ በነፃ መሰበኩ ነው። ያለ ዋጋ ግገልገል ዋና ዋጋው ነው! በቁ. 18 ላይ «በሙሉ እንዳልጠቀም» የተባለው ቃል ያው በም. 7፥31 ላይ ያገኘነው ነው።

ይህን ሁሉ ሲል ሐዋርያው ራሱን ምሳሌ ሊያደርግላቸው ብቻ ሳይሆን፥ እነርሱ «በመብቱ አለመጠቀሙ ሐዋርያ አለመሆኑን ያረጋግጣል)። ማለታቸውን ስሕተት እንደ ሆነ ሊያሰረዳቸው ነው። ያልተጠቀመ በምክንያት ነው!

ሐዋርያው በቁ. 1 ላይ «እኔ ነፃ አይደለሁምን?» ብሎአቸው ነበር፥ አሁንም ደግሞ በቁ. 19 ላይ «ከሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ሰሆን እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ» ይላል። አሳቡ ገና ያው በመብት ያለመጠቀም አሳብ ነው። ጳውሎስ ባለ መብት አይደለምን? ሉረ በብዙ ብዙ በኩል መብት አለው! ታዲያስ? በመብቱ አልተጠቀመም! በምን ምክንያት? «የሚበልጡትን እንድጠቅም» (ቁ. 19)፥ «በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ» ቁ.22 «በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ (ቁ.23) ነው! ያደረገው ለሌሎች ሲል ነው። አሳቡ ሌሎችን ይጠቅም ዘንድ ነው እንጂ ራሱ በመብቱ እንዲጠቀም አይደለም። (ቁ. 20-22።) ለዚህ ምክንያት ወይም ለእነዚህ ምክንያቶች ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መብቱን ሁሉ እንደ ጉዳትና እንደ ጉድፍ ቆጠረው! (ፊልጵ. 3፥4-11።)

ጳውሎስ ሮማዊ ነበረና ከሰው ሁሉ አርነት የወጣ ነበረ። በዚያ ዘመነቱ ይኮራ ነበር (የሐዋ. 16፥37፡38፤22፥25-29)፥ ሆኖም በመብቱ ሳይጠቀም ራሱን ለሰው ሁሉ እንደ ተናቀ ባሪያ አስገዛ። እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ሆኖ እግዚአብሔር መብልን ሁሉ እንዳነጻ አውቆአል፥ ጌታም በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረውን ግድግዳ እንዳፈረሰ አውቆአል (የሐዋ. 10፥15። ኤፌ. 2፥14)፥ ቢያውቅም ቅሉ ከሕግ በታች በነበሩት በአይሁድ መካከል ሲገኝ እንደ አይሁዳዊ ሆኖ በመብቱ ሳይጠቀም እርሱ ራሱ ከአይሁድ ሕግ ነፃ መሆኑን እያወቅ (ሮሜ. 14፥14። ገላ. 2፥15፡16፤5፥1) ጢሞቴዎስን በመገረዝና በዓላትን በማክበር ስዕለት ያለባቸውንም በመርዳት የእነርሱን ፈቃድ ፈጸመ። (የሐዋ. 16፥3፤20፥16፤21፥23-26።) ሕግም በሌላቸው በአሕዛብም መካከል ሲገኝ እንደዚህ አደረገ። በመብቱ ላይጠቀም በመካከላቸው ከእነርሱ እንዳንዱ ሆኖ ተቀምጦ (ገላ. 2፥11-16) እነርሱ የወደዱትን አደረገ። (ይህን ሲል ልዩ የሆነ ስለ አይሁድ ሕግ መናገሩ ነው እንጂ ሕግን ሁሉ እንደ ጣሰ ማለቱ አይደለም። በእይሁድ ሕግ በኩል ነፃ ይሁን እንጂ ሐዋርያው ለእግዚአብሔር እየተገዛ የክርስቶስን ሕግ ይጠብቅ ነበር።)

ጳውሎስ ራሱ ኃይለኛ ሲሆን በመብቱ ሳይጠቀም እንደ ደካማ ሆኖ የደካሞችን ድካምና ጥርጥር ታገሠ። (ም. 8፥7። ሮሜ. 15፥1።) ይህንም ሁሉ ያደረገው ሌሎች ብዙዎችን እያነጻ ከእነርሱ ጋር በወንጌል ተካፋይ ይሆን ዘንድ ነው። ሁሉንም ሲያደርግ በፍቅር እንጂ በእውቀት ብቻ አልተመራም ማለት ነው። (ም. 8፥2።)

በምዕራፉም መጨረሻ ላይ ሐዋርያው በቆሮንቶስ ከተማ አቅራቢያ በየሦስቱ ዓመት የተደረገውን የእስትሚያን የአስፖርት ውድድር ጠቅሶ ሩዋሮች ቢሆኑ የሚታገሉም ከብዙዎች ነገሮች ተከልክለው ሰውነታቸውን በስንት ጥንቃቄ እንዳሰገዙ ያሳስባቸዋል። ብዙዎች ይሩጡ እንጂ ሽልማት የሚያገኝ አንድ ብቻ ነው። እንደዚሁም በዓለም ላይ ብዙዎች ክርስቲያኖች ይኖራሉ፥ በመካከላቸው ግን የሚበዙቱ በመብታቸው በሙሉ ሊጠቀሙ ስለሚወዱ ጥቂቶች ብቻ አክሊል ይቀበላሉ። ክርስቲያኖች የሚጋደሉ በቅርቡ ለሚጠመልግ ለጥድ ጉንጉን ብቻ ሳይሆን ለዘላለም ለማይጠፋ ክብር ነውና ከእነዚያ ሩዋሮች ይልቅ ሰውነታቸውን ምንኛ መጠበቅ ይገባቸዋል! ሐዋርያው ራሱ ፍጻሜ ምልክትን ተመልክቶ (ፊልጵ. 3፥14) አክሊል እንደሚያገኝ ሰው ይሮጣል፥ ለሌሎች

ደግሞ ከሰበከ በኋላ በመጨረሻ ላይ «አይበቃም» እንዳይባልበት በመብቱ ሳይጠቀም ሥጋውን እየጎሰመ ያስገዛዋል።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ለማያት ስለ ተሠዋ ሥጋ ሲጠይቁ «እኛ ሁላችን እውቀት አለን፥ ነፃነት አለን፥ ለመብላት መብት አለን!» በለው ነበር። አሁንስ? ይህን ምዕራፍ ካነበቡ በኋላ ምን ይላሉ? መንፈሳዊ አባታቸው ጳውሎስ በመብቱ ሳይጠቀም ለወንጌል ብሎ ራሱን እስከዚህ ድረስ ማዋረዱን፥ ሰውነቱንም እስከዚህ ድረስ ማስገዛቱን ሲያዩ ምን ይላሉ? «ነፃነት አለን፥ መብት አለን፥ እንብላ!» ይሉ ይሆንን? ሉረ ከቶ አይሆንም! ይሁንና በም. 10 ላይ ያን ሥጋ የማይበሉበት ከዚህ እንኳን የበለጠ ምክንያት ይሰጣቸዋል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ፥ በሁሉ መንገድ ሁሉን እደርጋለሁ።» (ቁ. 19፡22፡23።) የሐዋርያው ሕይወት ሁሉ በእንድ አሳብ ተገዝቶአል፥ ይህም «የሚበልጡትን እንድጠቅም» (ቁ. 19)፥ «አንዳንዶችን አድን ዘንድ» (ቁ. 22)፥ «በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ» (ቁ. 23) ነው። ሰውን ማዳን! ዓይነተኛ ዓላማው ይህ ነው፥ ይህንም ዓላማ በምን ያለ ብርታት እንደ ተከተለው በዚህ ምዕራፍ ላይ እናያለን። ሰውን ለማዳን ብሎ ምን ጊዜም መከራን ሁሉ ለመቀበል፥ ሁሉን ለመሆን፥ ሁሉንም ለማድረግ ፈቅዶአል። ለዚህ ብሎ ባለኝ መብት ሁሉ አልጠቀምም ብሎአል ከሁሉ ነፃ ሲሆን የሁሉ ባሪያ ሆነ። ከአይሁድ ወለን ሁሉ የተፈታ ሲሆን በእነርሱ ለመጥበብ ፈቀደ። ባለ መብት አሥራሌላዊ ሲሆን ከአሕዛብ ጋር ለመብላት ፈቀደ። (ፊልጵ. 4፥12።) በእምነት ኃይለኛ ሲሆን ደካማ ሆኖ ለመቆጠር እንቢ አላለም። ምንም ቢሆን፥ በሚቻለው መንገድ ሁሉ፥ ሰውን ለማዳን ጣረ። ስለዚህ በመጨረሻ ላይ «መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፥ ሩጫውን ጨርሻለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ» አለ። ስለዚህም ደግሞ የተጣለ ሳይሆን (ቁ. 27) በመጨረሻ ላይ «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ያ ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ያለረክባል» ለማለት በቃ። (2 ጢሞ. 4፥7፡8።)

አንባቢ ሆይ፥ ይህን አክሊል ለማግኘት አንተ ምን ያህል መከራ ለመቀበል፥ ምን ለመሆንስ፥ ምንስ ለማድረግ ትፈቅዳለህ? ከመብቶችህ ሁሉ በየትኛው ነው «የሚበልጡትን አንድጠቅም፥ ስለ አክሊልም ስል፥ አልጠቀምበትም» የምትለው? በሕይወታችን መጨረሻ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረው ሁሉ እኛም እንድንናገር እግዚአብሔር አያንዳንዳችንን በጸጋው ያብቃን!

ለ/ «ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ።» (ቁ. 22።) ጳውሎስ ይህን ሲል «እውነትን ትቼ ሐሰትን ያዝሁ፥» ወይም «ከማይገባ ነገር ጋር ተስማማሁ፥» ወይም «ሕሊናዮን እየበደልሁ አደረግሁ» ማለቱ ሳይሆን «በእነዚህ ዝቅተኞች ነገሮች የራሴን ፈቃድ ሳልፈጽም የሌሎችን ፈጸምሁ» ማለቱ ነው። በነገሩ ውስጥ ክፍ ያለ የሃይማኖት ነገር ባይኖር ሐዋርያው ከሰው ጋር ለመስማማትና ሰውን ለማዳን ብሎ የራሱን አሳብና የራሱን ፈቃድ ለመተው ሁልጊዜ ዝግጁ ነበረ።

ዛሬ እንደዚህ ለማድረግ ማን በሰጠን! በሚበዛ እኛ ያን ሰው ወደ እኛ አሳብና ፈቃድ የግድ ልንጎትተው እንጥር የለምን? ልክ እንደ እኛ ካላለበና ካላደረገ ክርስቲያን መሆኑን

ስንኳ ልናምን እንፈቅድም። ወደ አፍቃሪው ወደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መንፈስና አላብ ምነው በተመለስን!

ሐ/ «ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን።» (ቁ. 27።) ሐዋርያው ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው? ምናልባት ለዘላለም እንደሚጠፋ ማለቱ ነውን? አይደለም! በክርስቶስ አምናለና የዘላለም ሕይወት አለው። (ዮሐ 6፥47።) ሊጠፋ አይችልም። ይሁንና እውነተኛ ክርስቲያን፥ ሐዋርያ ስንኳ በመጨረሻ ላይ ምናልባት እንደሚጣል ያሰኛል። «በመጣል» አንግዲህ ምን ማለት ነው? ሐዋርያው በዚህ ክፍል ላይ ስለ ምን ነገር ይናገር እንደ ነበር መገንዘብ ያስፈልገናል። ስለ ሩዋጭና ስለ አክሊል ነገር ነው። ሩዋጮቹ ሁሉ ይደርሱ ይሆናል፥ አክሊል የሚያገኝ ግን አንድ ብቻ ነው። ጳውሎስ ስለ ዘላለም ደኅንነት ወይም ስለ ዘላለም ጥፋት በዚህ ክፍል ውስጥ አይናገርም፥ አክሊል ስለ ማግኘት ነው እንጂ። ሐዋርያው ስለ መዳኑ እልተጠራጠረም፥ የተጠራጠረበት አክሊልን ያገኝ ወይም አያገኝ እንደ ሆነ ነው። «የተጣልሁ እንዳልሆን» ማለት፥ አክሊል ሳላገኝ እንዳልቀር ማለት ነው። የማይበቃ ሩዋጭ አክሊልን ለማግኘት ተስፋ አድርጎ ወደ ዳኛው ቀርቦ የተጣለ እንደሚሆን አፍሮም እንደሚሄድ፥ እንዲሁም ጳውሎስ ምናልባት ያልበቃ ሆኖ ተገኝቶ የተጣለ እንዳይሆን ማለቱ ነው። እርሱ ሌሎችን ካስተማረና ከገሠጻ ከመከረም በኋላ ቢጣል እፍረቱ ከፍ ያለ ይሆናል።

እንደዚሁም ሁሉ በሁለተኛ ልደት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ክርስቲያን እስከ ፍጻሜ ድረስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው እንጂ ከልጅነቱ ሊቀር አይችልም። የጠፋ ልጅ እንኳ ገና የአባቱ ልጅ ነው። (ሉቃ. 15፥21፡24።) ክርስቲያኑ ልጅነቱ አይቀርበትም፥ አክሊል ግን ሊቀርበት ይችላል። በ1 ቆሮ. 3፥15 ላይ እንደ ተጻፈው ነገር ይሆናል፡- «እርሱ ራሱ ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።» ይሁንና ስለ ደኅንነት እንኳ እጅጉን መጠንቀቅ እንደሚያስፈልገን በመጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ብዙ ቦታ እናያለን።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 10።

1 ወንድሞች ሆይ፥ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳልሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች
ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል 2 ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና
በባሕር 3 4 ተጠመቁ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፥ ሁሉም ያን መንፈሳዊ
መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ 5 ድንጋይ ጠጥተዋልና፥ ያም ድንጋይ
ክርስቶስ ነበር። እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፥ በምድረ በዳ
ወድቀዋልና።

6 እነዚህም ክፉ ነገር እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ 7 ይህ ምሳሌ ሆነልን።
ሕዝብም ሊበሉ ሊጠጡም ተቀመጡ ሊዘፍኑም ተነሡ ተብሎ እንደ ተጻፈ ከእነርሱ
እንዳንዶቹ 8 እንዳደረጉት ጣዖትን የምታመልኩ እትሁኑ። ከእነርሱም እንዳንዶቹ እንደ
ሴሰኑ በእንድ ቀንም ሁለት እልፍ 9 ከሦስት ሺህ እንደ ወደቁ እንሴሰን። ከእነርሱም
እንዳንዶቹ ጌታን እንደ ተፈታተኑት በእባቦቹም እንደ ጠፉ ጌታን አንፈታተን። 10
ከእነርሱም እንዳንዶቹ እንዳንጎራጎሩ በሚያጠፋውም 11 እንደ ጠፉ አታንጎራጉሩ።
ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፥ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን
12 ተጻፈ። ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ 13 ይጠንቀቅ። ለሰው ሁሉ
ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ
ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ
ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።

14 15 ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ። ልባሞች እንደ መሆናችሁ
እላለሁ፤ በምለው ነገር እናንተ ፍረዱ። 16 የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም
ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ 17 ሥጋ ጋር
ኅብረት ያለው አይደለምን? እንድ እንጀራ ስለ ሆኑ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን እንድ ሥጋ
ነን፤ ሁላችን ያን 18 አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና። በሥጋ የሆነውን እሥራኤል
ተመልከቱ፤ መሥዋዕቱን የሚበሉ የመሠዊያው ተጓበርተኞች 19 አይደሉምን?
እንግዲህ ምን እላለሁ? ለጣዖት የተሠዋ ምናምን ነው እላለሁን? ወይስ ጣዖት ምናምን
እንዲሆን እላለሁን? 20 አይደለም፤ ነገር ግን አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት እንዲሆን
እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሠዉ እላለሁ፤ ከአጋንንትም 21 ጋር ተጓበርተኞች
እንድትሆኑ አልወድም። የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ እትችሉም፤ ከጌታ
ማዕድና 22 ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም። ወይስ ጌታን እናስቀናውን? እኛስ
ከእርሱ ይልቅ እንበረታለንን?

23 ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥
ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም። 24 እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ
ሰንኳ የራሱን 25 ጥቅም አይፈልግም። በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ከሕሊና 26
የተነሣ ሳትመራመሩ ብሉ፤ ምድርና በእርስዋ የሞላባት 27 ሁሉ የጌታ ነውና። ከማያምኑ
ሰዎች እንዱም ቢጠራችሁ ልትሄዱም ብትወዱ ከሕሊና የተነሣ ሳትመራመሩ
የሚያቀርቡላችሁን 28 ሁሉ ብሉ። ማንም ግን፦ ይህ ለጣዖት የተሠዋ ነው ቢላችሁ
ከዚያ ካስታወቃችሁና ከሕሊና የተነሣ እትብሉ 29 ስለ ባልንጀራህ ሕሊና እንጂ ስለ
ገዛ ሕሊናህ አልናገርም። እርነቴ በሌላ ሰው ሕሊና የሚፈርድ ሉረ ስለ ምንድር ነውሀ
30 እኔም በጸጋ ብበላ፥ በነገሩ ስለማመሰግንበት ስለ ምን እሰደባለሁ?

31 እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውንም ነገር
ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር 32 33 እድርጉት። እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ
ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ
እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚኢአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማስናከያ
እትሁኑ።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ አሥር።

ሐዋርያው አሳቡን በመቀጠል የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች በአሥራኤላውያን ምሳሌ ያስጠነቅቃቸዋል። እነዚህ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች «ሁላችን እውቀት አለን፤ ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደሆነ እናውቃለን» እያሉ (ም. 8፥1፡4) ለጣዖት የታረደውን ሥጋ ለመብላት አስቡ። ጳውሎስ እውቀት እንዳላቸው ለመብላትም መብት እንዳላቸው ያምናል፥ መብላታቸውን ግን አልወደደም። ምነው? ቢሉም፥ 1ኛ፥ ይህን ሥጋ የበሉት አንደሆነ ሌሎችን እንዳያሰናክሉ ይፈራል፤ 2ኛ፥ «ሉረ እውቀት አለንና ብንበላ ምን እንጎዳለን?» ቢሉ እንኳ ይህን ሥጋ በመብላት ምናልባት እንዳይወድቁ ይፈራል። በም. 9 ላይ እርሱ ራሱ መብት እንዳለው፥ ነገር ግን በመብቱ እንዳልተጠቀመ፥ ያልተጠቀመበትንም ምክንያት አጫውቶአቸዋል። በዚያም ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ደግሞ የሩጭዎችን ምሳሌ ጠቅሶ አከሊል ለማግኘት ሲጥር እርሱ ራሱ የተጣለ እንዳይሆን ሥጋውን እየጎሰመ እንዳስገዛው አስረድቶአቸዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች «ሉረ ግድ የለም! ቆመናል፥ አንወድቅም» ሲሉ ሐዋርያው እርሱ ራሱ የተጣለ እንዳይሆን ይፈራል፤ እነርሱም እንዳይወድቁ ለሚፈራላቸው ፍርሃት መሠረት እንዳለ ለማሳየት የአሥራኤላውያንን ምሳሌ አሁን በም. 10 ያነሣል።

ቁ. 1-13። ልጆቹ የነበሩ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች አሁን አድገው ወንድሞቹ ሆነዋል። ሐዋርያው እውቀታቸውን ያመሰግናል፥ ነገር ግን ይህን የአሥራኤልን ታሪክ ደግሞ አውቀው ይረዱት ዘንድ ይወዳል። እነርሱ ከእግዚአብሔር ከለላ በታች ናቸውን? ከጨለማ ባርነት ወደ ብርሃን አርነት የወጡ ናቸውን? ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ ተጠምቀዋልን? ኅብስቱንም ጻዋውን፥ ቅዱስ ቁርባንን፥ ተቀብለዋልን? በዚህም ሁሉ ተደግፈው «ሉረ ግድ የለም፥ አንወድቅም» ይላሉን? እስቲ ያድምጡ! እነዚያ የዱሮ ዘመን አሥራኤላውያን ሁሉ አንደዚህ ከእግዚአብሔር ከለላ፥ ከደመና ዓምድ፥ በታች ነበሩ (ዘፀአ. 13፥21፡22)፥ ሁሉም እንደዚህ በቀይ (በኤርትራ) ባሕር መካከል ከባርነት ወደ አርነት ተሻገሩ (ዘፀአ. 14፥21፡22)፥ ሁሉም ከደመና ዓምድ በታች በመሆናቸውና ባሕሩን በመሻገራቸው «ከሙሴ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ ተጠመቁ» እስኪባል ድረስ ሙሴን ተባበሩ። (ዘፀአ. 14፥31። ዮሐ. 9፥28።) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ኅብስቱንና ጽዋውን አንደ ተቀበሉ ሁሉ እንደዚሁ አሥራኤላውያን ሁሉ መና የተባለውን የመላእክት እንጀራ በሉ፥ በተመታው ዓለት የወጣውንም ውኃ ጠጡ። (ዘፀአ. 16፥4፡13-15፡31። መዝ. 77፥24፡25። ዘፀአ. 17፥6።) የቆሮንቶስ ሰዎች ያላቸውን ሁሉ እስራኤላውያን ነበራቸው፤ ሆኖም ዳኛውን (እግዚአብሔርን) ደስ ሳያሰኙ ቀርተው ወደቁ። ይኸውም ጳውሎስ «ለሌሎች ከሰበኩሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን» ያለው ነገር አይደለምን? እነዚያ በእስትሚያን የአስፖርት ውድድር የሮጡት ሩዋጮች ዳኛውን ሳያስደስቱ ቀርተው አከሊሉን ለመቀበል እንዳልበቁ እንዲሁም ጳውሎስ ለሌሎች ከሰበከ በኋላ እግዚኢአብሔርን ሳያስደስት ቀርቶ እንዳይጣል ይፈራ ነበር። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችሳ? በፈታቸው የአሥራኤላውያን ምሳሌ ሲናር «አይ ግድ የለም! አንወድቅም» ብለው ያን ሥጋ መብላት ገና ይደፍራሉን? (ቁ. 1-5።)

ቅዱስ ጳውሎስ «ይህ ሁሉ የሆነ እኛን ክርስቲያኖችን ለማስጠንቀቅ ነው» ይላል። እነዚያ አሥራኤላውያን ሥጋን መብላት ተመኙ፥ ተመኝተውም ወደቁ። (ዘኍቁ. 11፥4፡33፡34።) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችም ለጣዖት እንደ ተሠዋ ሥጋ የሚመስለውን

ከፉ ነገር መብላት ይመኛሉን? ሉረ አይሆንም! እሥራኤላውያን ጥጃ (ጣዖት) ሠሩ፥ ለግብጥ ተሰበሰቡ፥ ተቀምጠውም ሥጋን በሉ መጠጥንም ጠጡ፥ ተነሥተውም ሊዘፍኑ ጀመሩ። በኋላም «ለድ ተለቀቁ»። (ዘፀአ. 32፥1-6፡25።) (የጣዖት ግብጥቸው ወደ ሴሰኝነትና ወደ መዳራት አደረላቸው ማለት ነው።) በቆሮንቶስ ከተማ የተደረጉት የጣዖት ግብጥዎች እንደዚህ ያሉ ሲሆኑም ከርስቲያኖቹ እንዲህ ወዳለ ግብጥ በመሄድ ጣዖትን ያመልካሉን? ሉረ አይሆንም! እነዚያም እሥራኤላውያን ተለይተው ተቅድሰው መቀመጥ ስልችቶአቸው ኖሮ ከእሥራኤል ወገን ያልሆኑት ሞአባውያን «ኑ ተጋበዙ»። ቢሉአቸው ሄዱ፥ ለአማልከታቸውም ሰገዱ። (ዘኍል. 25፥1-9።) ከሌሎች ጋር ለመተባበር ወድደ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እንደዚህ ያደርጋሉን? እሥራኤላውያን ይህን ስላደረጉ ስንቶች እንደ ወደቁ ከርስቲያኖቹ ያስቡ፥ ከማያምኑትም ጋር ለመተባበር አይመኙ። ከእሥራኤላውያን ደግሞ አንዳንዶቹ። «እስቲ እግዚአብሔር እንዳሰ እንይ፤ ያለ እንደሆነ ሥጋ አሁን ይስጠን!» ብለው ተፈታተኑት፥ ብዙዎችም ወደቁ። (ዘፀአ. 17፥2፡7። ዘኍል. 21፥5፡6። መዝ. 77፥18፡19።) ይህን እያዩ የቆሮንቶስ ከርስቲያኖች «እስቲ ጌታ ይቆጣን እንደሆነ!» ብለው ወደ ጣዖት ቤት ደፍረው ይሄዳሉን? ሉረ! እነርሱ ከእርሱ ይልቅ ይበረታሉን? እንደዚህ አያድርጉ! ወይስ ደግሞ ከእሥራኤላውያን አንዳንዶቹ እንዳንጉራጎሩ ሁሉ (ዘኍል. 11፥1-6፥10፡33) የቆሮንቶስ ሰዎች ያን ሥጋ እንዳይበሉ ከዓለማውያንም ጋር እንዳይተባበሩ ስለ ተከለከሉ ያንጉራጉራሉን? ሉረ ያስፈራል! ከእሥራኤላውያን እኮ በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ ወደቁ።

ይህም ሁሉ የተጻፈው የዛሬ ዘመን ሰዎችን ለመገሠጽ ነውና «ሉረ! ግድ የለም፥ አንወድቅም» የሚሉ የቆሮንቶስ ሰዎች ይገሠጹበት እንዳይወድቁም ይጠንቀቁ። እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ይፈተኑ ይሆናል፤ ይሁንና ልዩ ፈተና ምንም አልደረሰባችሁም፥ ወደ ፈትም ሊታገሡ የማይችሉት ፈተና እንዲደርስባቸው እግዚአብሔር አይፈቅድም። እንደ ተራራ የሚመስል ፈተና ቢከብባቸው ሊታገሡ እንዲችሉ እርሱ መውጫ መንገድ ሁልጊዜ ያደርግላቸዋል ያደርግልናልም። (ቁ. 6-13።)

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።» (ቁ. 1።) የእግዚአብሔር ወገኖች ከሆኑት እንኳ የሚበዙት ሊወድቁ እንደሚችሉ ከእሥራኤላውያን ታሪክ እንረዳለን። ከቁ. 1 ጀምሮ እስከ ቁ. 4 ድረስ «ሁሉ» የተባለ ቃል አምስት ጊዜ ይመጣል። እሥራኤላውያን ሁሉ ሮጡ ያውም ባንድነት፥ እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፥ በምድረ በዳ ወድቀዋልና፤ ከምድረ ግብጽ ከወጡትም ሁለት ሰዎች ብቻ፥ እነርሱም ኢያሱና ካሌብ፥ አከሌል ለግግንት በቁ።

እንደ እሥራኤላውያን ምሳሌ ሁሉ እኛ ደግሞ ልንወድቅ እንችላለን። እንደ እነርሱ ሆነን ከእግዚአብሔር ግኅበር እንሆናለን፤ በኢየሱስ ደምም ባሕር ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገርን እንሆናለን፤ እንደ እነርሱም ምሳሌ ደግሞ ከርስቶስን እንተባበር ዘንድ የተጠመቅን እንሆናለን፤ እነርሱ መናን እንደ በሉ እኛም ያን መንፈሳዊ መብል የሆነ ኅብስት የበላን እንሆናለን፤ እነርሱ ከድንጋይ (ከዓለት) የወጣውን ውኃ እንደ ጠጡ እኛም ያን መንፈሳዊ መጠጥ የሆነ ወይን (ጽዋውን) የጠጣን እንሆናለን፤ ነገር ግን እንደ እነርሱ ደግሞ እኛም እግዚአብሔርን ደስ ሳናሰኝ እንድንወድቅና እንድንጣል ይቻላል።

በእሥራኤላውያን እምላል እንዳንወድቅ እነርሱ የወደቁበትን ነገር እንይ። እነርሱ «ክፉ ነገርን» ተመኙ፥ እርሱም ሥጋ። ለክርስቲያን፥ «ክፉ ነገር» የተባለው ምን ነገር ይሆን? ክፉ ነገር ማለት የእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ ነገር ሁሉ ማለት ነው። (ማቴ. 4፥3፡4።) ለብዙ ሰው ንጹሕ ሆኖ የሚታይ ልማድ ሆነ ሥራ ወደሚያሰቅቅ ጥፋት እንዳያደርሰን በብዙ መጠንቀቅ ይገባናል። ክርስቲያን አክሊል ለማግኘት ቢወድ፥ «ክፉ ነገርን» ከመመኘት ይጠንቀቅ።

ከእሥራኤላውያን አንዳንዶቹ ጣዖትን የሚያመልኩ ሆኑ፥ የእግዚአብሔርም ቁጣ ተቃጠለባቸው። ክርስቲያንስ? ክርስቲያን ጣዖትን ያመልካልን? ጣዖት ማለት ክርስቲያኑን ከእግዚአብሔር ወይም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚያርቅ ማናቸውም ነገር ነው። መብል ይሆናል፥ መጠጥም ይሆናል፥ ዘፈንም ይሆናል፥ ከዓለማውያን ጋር መዛመድ ይሆናል። ክርስቲያኑን ከክርስቶስ የሚያስብ ማናቸውም ነገር ሁሉ ጣዖት ነው። (1ዮሐ. 5፥21።) ክርስቲያን አክሊል ለማግኘት ቢወድ ጣዖትን ከማምለክ ይጠንቀቅ።

ከእሥራኤላውያን አንዳንዶቹ ሴሰኑ ወደቁም፥ የደረሰባቸውም መቅሠፍት ፈጠነ ታላቅም ሆነ። ክርስቲያንንስ? ብዙ ሰዎች የወደቁበትና የሚወድቁበት ወጥመድ ይህ ነውና ክርስቲያን አክሊል ለማግኘት ቢወድ ሥጋ ገና በለበሰበት ጊዜ ሁሉ ከሴሰኝነት አጥብቆ ይጠንቀቅ። (1 ቆሮ. 6፥18።)

ከእሥራኤል አንዳንዶቹ ጌታን ተፈታተኑ፥ ይህንም ብዙ ጊዜ አድርገዋል። ጌታን መፈታተን ምን ማለት ነው? ጌታን መፈታተን ማለት እኛ እንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑ እየተሰማን ያን ነገር ስናደርግና «እስቲ እግዚአብሔር ይቆጣን እንደሆነ እንይ!» ስንል ነው። ስንል ነው። ክርስቲያን አክሊል ለማግኘት ቢወድ በሚያደርገው ነገር እግዚአብሔርን እንዳይፈታተን ይጠንቀቅ። (ሮሜ 14፡22 ሁለተኛ ግማሽ።)

ከእሥራኤላውያን አንዳንዶቹ አንጎራጎሩ፥ እግዚአብሔርም በታላቅ መቅሠፍት መታቸው። (ዘኍል. 11፥1-6፡ 10፥33።) ክርስቲያንስ? ክርስቲያኖች ስንሆን «ይህን ነገር መተው ይገባችኋል» ሲሉን ያን ነገር ከመመኘታችን የተነሣ በእግዚአብሔር ላይ አንዳንድ ጊዜ አናንጎራጉርምን? ወይስ በመረጠልን እድል አናንጎራጉርምን? ክርስቲያን አክሊል ለማግኘት ቢወድ ከማንጎራጎር ይጠንቀቅ። (ዕብራ. 13፥5፡6።)

ይህ ሁሉ በእሥራኤላውያን ደረሰባቸው፥ ክርስቲያን ደግሞ ይጠንቀቅበት። ማስተዋል ደግሞ የሚገባን አንድ ነገር አለ፡- መውደቅ አስፈላጊ አይደለም። በማንችለው ፈተና እንዳንፈተን አግዚአብሔር ራሱ ይጠብቀናል፥ ፈተናውንም ልንታገሥ እንድንችል እግዚአብሔር ከፈተናው ጋር ማምለጫ መንገድን ያደርግልናል። ስለዚህ «መውደቃችን የግድ ነው» ብለን እናስብና እንሳሳት። መውደቅ ለክርስቲያን አስፈላጊ አይደለም። (ይሁዳ ቁ. 24።)

ለ/ «ይክተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋልና፥ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበር።» (ቁ. 4።) ይህ ምን ማለት ነው? መጀመሪያ «ያ ድንጋይ ክርስቶስ ነው» የተባሉ ቃሎች በማቴ. 26፥26 ላይ «ይህ ሥጋዬ ነው» የተባሉትን መስለው ያ ድንጋይ የክርስቶስ ምሳሌ እንደ ነበረ ያስረዱናል። እሥራኤላውያን ከተመታ ዓለት በወጣው ውኃ ሁለት ጊዜ ጥማቸውን አርክተዋል። (ዘፀአ. 17፥6። ዘኍል. 20፥10፡11።) ዓለቱ ሲመታ ውኃ ፈሰሰላቸው። እንደዚሁ ሁሉ ክርስቶስ ውኃ

ልትቀዳ ከሰማርያ ለወጣቸው ሴት «የእግዚአብሔርን ስጦታና ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ግን መሆኑንስ ብታውቂ፥ አንቺ ተሰምኚው ነበርሽ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር» አላት። (ዮሐ 4፥10።) እርሱ ከተመታ (ከተሰቀለ) በኋላ ያን ውኃ ለሰው ሁሉ እንደሚሰጥ ሲያስረዳ ነው። ያ በምድረ በዳ የተገኘው ድንጋይ ክርስቶስን መሰለ ማለት ነው። እሥራኤላውይን በምድረ በዳ ሳሉ የመጣላቸው በረከት ሁሉ ከእርሱ (ከክርስቶስ) መነጨላቸው፥ ያም የበረከት ምንጭ በሄዱበት ሁሉ ተከተላቸው።

በብሉይ ኪዳን በብዙ ሥፍራ እግዚአብሔር «ድንጋይ» ወይም «ዓለት» ተባለ፤ አሁን ሐዋርያው ኢየሱስን «ድንጋይ» ሲለው ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከሉን እንረዳለን። ሁለተኛ ደግሞ «ያ ድንጋይ ክርስቶስ ነበር» ሲል ክርስቶስ ከእመቤታችን ሳይወለድ በፊት ከዘላለም መኖሩን እናስተውላለን።

ቁ. 14-22። ሐዋርያው ከቁ. 1 እስከ ቁ. 13 ድረስ በዱሮ ዘመን የኖሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ እሥራኤላውያን፥ በተለይ በጣዖት ነገር እንደ ወደቁ በመግለጥ ለጸና ክርስቲያን ስንኳ መውደቅ የሚቻል ነገር እንደ ሆነ የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች ካስረዳ በኋላ እንዲህ አላቸው፡- «ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ።» (እዚህ ደግሞ «ሽሹ» የተባለውን ቃል እናገኛለን። በም. 6፥18 ላይ ከዝሙት እንዲሸሹ እንደ መከራቸው ሁሉ እንደዚሁ በም. 10 ላይ ጣዖትን ከማምለክ እንዲሸሹ ይመክራቸዋል። ካደረጉት በኋላ እንዲሸሹ አይደለም፥ ነገር ግን አምልኮ ባዕድ ለሰው ሁሉ ክፉ ወጥመድ ነውና ሳይጠመዱበት በፊት ርቀው እንዲሸሹ ነው።) 1 ተሰ. 5፥22።) «ምነው? የቆሮንቶስ ክርቲያኖች ጣዖትን ማምለክ መቼ አሰቡ?» ቢሉ፡- እውነት ነው፥ ክርስቲያኖች ናቸውና ጣዖትን ማምለክ አያስቡም። ይሁን እንጂ ሰጣዖት የታረደውን ሥጋ መብላት ሲያስቡ ጣዖትን ማምለክ ወደሚመስል ነገር ይደርሱ ይሆናል። እንደምን? ቢሉም፥ «እውቀትና ጥበብ አለን» ብለዋልና አነርሱ አሁን ሐዋርያው በሚላቸው ነገር ይፍረዱ። ቀሳውስት በቁርባን ሰዓት «ቡሩክ እግዚአብሔር አብ፥ ወቡሩክ ወልድ፥ ዋሕድ፥ ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ» ብለው በክርስቶስ ምሳሌ እያመሰገኑ የሚባርኩት ያ የበረከት ጽዋ *ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት አለው። የሚቆርሱትም ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ዘለው። በዚያም ሰዓት የሚቆረሰው አንድ ኅብስት ብቻ ስለ ሆነ፥ እኛም ብዙዎች ስንሆን ሁላችን ያን አንዱን ኅብስት ስለምንካፈል፥ እኛ አርስ በርሳችን ደግሞ ኅብረት አለን። እንደዚህም ሁሉ ያ ጽዋ ያም ኅብስት ከክርስቶስ ደምና ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ስላለው እኛ ያን ጽዋና ያን ኅብስት ስንካፈል ከክርስቶስ ሥጋና ከክርስቶስም ደም ጋር ኅብረት አለን። የምድራዊ እሥራኤልንም ምሳሌ ስንመለከት ነገሩ አንድ ዓይነት እንደ ሆነ እናያለን። መሥዋዕቱን የበሉ እሥራኤላውያን ከመሠዊያው ጋር ተካፋዮች ወይም ማኅበርተኞች ነበሩ። እነርሱ በመሠዊያ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንደ ነበራቸው እንዲሁም እኛ ክርስቲያኖች በጌታ ማዕድ በኩል ከክርስቶስ ጋር ኅብረት አለን። ጌታ ወደ ማዕዱ ሲጋብዘን እኛም ተሰብስበን ኅብስቱንና ጽዋውን ስንካፈል ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ያለን የክርስቶስ ማኅበርተኞች ነን።

አሁንስ፥ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ብንበላስ? ሉረ ሐዋርያው ምን ማለቱ ነው? «ከጣዖት ጋር ኅብረት አላችሁ» ሊል ነውን? ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ክሌላ ሥጋ ምን

*ዮሐንስ አፈ ወርቅ «ጽዋውን በእጃችን እየያዝን ጌታን እናመሰግነዋለንና እርሱ የበረከት ጽዋ ብሎ ጠራው» ይላል።

ልዩነት አለው? ወይስ ጣዖቱ ራሱ አውነተኛ ነገር ነውን? ሉረ ጣዖት ምንም አይደለም! (ም. 8፥4።) አንግዲያስ ያን ሥጋ ብንበላ ምን አለበት? ጣዖት ምናምን አይደለምና ያን ሥጋ ብንበላ ከጣዖት ጋር ኅብረትን እንደምን እናገኛለን የጣዖትም ማኅበርተኞች እንደምን አንሆናለን? የለም! ጳውሎስ «ከጣዖት ጋር ኅብረት አላችሁ» ወይም

ደግሞ «ለጣዖት በመሠዋቱ ሥጋው ልዩ ነው» አይልም፥ ነገር ግን አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት አንዲሆን በዚህም ምክንያት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያን ሥጋ ቢበሉ ከአጋንንት ጋር ምናልባት እንዲተባበሩ ይላል፥ ይህንም አይወድም!

ሐዋርያው ይህን ሲል በዘዳግ. 32፥17 ላይ የተባለውን መጥቀሱ ነው። አጋንንት ስው ጣዖታትን ማምለክ መውደዱን በማወቅ ምክንያትን አግኝተው ጣዖታትን ሰራሳቸው አድርገዋል፤ ሰውም ይህም ሳያውቅ ፈቃዱም ሳይሆን ለጣዖት ሲሠዋ በእውነቱ ለአጋንንት ይሠዋል። ሰው ለአድባር እንደሚሠዋው ሁሉ ነው። ለዛፈቱ የሚሠዋ ሳይሆን ከዛፈቱ በኋላ ለሚገኙ አጋንንት ይሠዋል። ይሁንና ክርስቲያን ለአጋንንት ሲሠዋ ቢገኝ ምን ያለ ውድቀት ነው! ሐዋርያውም ከሁለቱ ጋር፥ ከጌታና ከአጋንንት ጋር፥ ልትተባበሩ፥ የጌታን ጥሪና የአጋንንት አድመኞች ልትሆኑ አትችሉም ይላል። እንችላለን የሚል አሳብ በፍጹም የማይቻል አሳብ ነው። ወይስ ምናልባት «እኛ ከጌታ ይልቅ እንበረታለን» ብለን በአጋንንት ማዕድ አንቀመጥና ጌታን እያስቀናን ቁጣውን እንድፈርን? ሉረ አይሆንም፥ እንድፈር! በቁጣው ቀን ማን ይቆማል? ብርቱዎች እንሁን እንጂ አርሱን ከመፈታተንና ከመድፈር እንሸሽ! ሆኖም ሐዋርያው ይህን ያህል ማስጠንቀቂያ ሁሉ ቢሰጥ አንኳ አብያተ ክርስቲያናት የወደቁበት በዚሁ ነገር መሆኑን በራእ. 2፥14፥20 አናያለን።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ፥ ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ።» (ቁ. 14።) መቼም የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጣዖትን ለማምለክ ከቶ አላሰቡም። ወደ ጣዖት ቤት ይሄዱና ግብዣን ይካፈሉ ይሆናል እንጂ ጣዖትን ማምለክ መቼ አሰቡ? ይሁንና ወደዚያ ከመሄዳቸው የተነሣ ያላሰቡትን ለመፈጸም ደረሱ!

ከአነርሱም እኛ አንማር። በአገራችን ውስጥ፥ በቤተ ክርስቲያናችንም ውስጥ እንኳ፥ እምልክ ባዕድ እንዳለ ሁላችን እናውቃለን። ሰጎን መከራ ሲደርስባት አይታ ዓይንዋን «ሉረ የለም፥ አይገኝም!» ብንል የከንቱ ከንቱ ነገር ነው። ሕዝባችን ምናልባት በንዱሕ ሕሊና ይሄዱና ይገብሩ ይሆናል፥ ጣዖትንም የሚያመልኩ በፍጹም አያስቡም ይሆናል፤ ይሁንና ሐዋርያው «ጣዖትን ታመልካላችሁ» ይላል። ወዳጆቼ ሆይ፥ በአገራችን ውስጥ እንዲህ ያለ ነገር ሲገኝ የአግዚአብሔር በረከት በአውነቱ በላያችን አንደምን ያርፋል? እሥራኤላውያን የወደቁበት በዚሁ ምክንያት አይደለምን? እኛም ክርስቲያኖች ይህን ስናደርግ ብንገኝ የእግዚአብሔር ሕዝብ ምንም ብንሆን እንደ እነርሱ እንዳንወድቅ እጅግ በጣም ያስፈራል። ስለዚህ ከዚህ ታላቅ ስሕተት ራሳችንን ብናነጻ አይሻልም ወይ?

ለ/ «ከክርስቶስ ደም ጋር ... ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?» (ቁ. 16።) በጹሮ ዘመን ሁሉ መብልን መካፈል መተባበር ነበረ። (በቁ. 18። ዕብ. 13፥10።) ላባንና ያዕቆብ ሲተባበሩ በፈለጉ ጊዜ ከምር ሠርተው «በዚያ በከምር ላይ በሉ።» (ዘፍጥ. 31፥44-46።) ካህናቱም ከእግዚአብሔር ጋር ሲተባበሩ ቢፈልጉ በመሠዊያው ላይ ከነበረው ከመሥዋዕቱ ሥጋ በሉ። (ዘሌዋ. 7፥15፥16።) በዚህም መሠረት፡- እሥራኤላውያን «የመሠዊያው ማኅበርተኞች» ሆኑ (ቁ. 18)፥ ከርስቲያኖች «ከክርስቶስ ጋር ኅብረት» አገኙ (ቁ. 16)፥ የቆሮንቶስ ሰዎችም «ከአጋንንት ጋር ማኅበርተኞች» ሆኑ። (ቁ. 20።)

መሠዊያና መሥዋዕት የሚሠዋ ካህንም በክርስቶስ ተፈጽመዋልና (ዕብራ. 10፥8-18) ዛሬ መሠዊያ የሰንም። ይሁንና በመሠዊያ ፋንታ የእራት ማዕድ አለንና (ማቴ. 26፥20) የቁርባንን ጽዋ በምንቀበልበት ጊዜ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት አለን፥ የቁርባንን ኅብስት በምንበላበት ጊዜ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት አለን። «ወይኑን በእፋችን በምንጠጣው መጠን ሁሉ በዚያው መጠን ነፍሳችን ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት አለው» ብሎ ከሊቃውንት አንዱ አስተምሮናል። ስለዚህ ቅዱስ ቁርባን ምን እንደ ሆነ ልናውቅ ብንፈልግ ይህን ነገር እናስብ። በጌታ ጥሪ በጌታ ማዕድ መመገብና ከእርሱ ጋር፥ በሥጋውም በደሙም፥ መተባበር ነው። (ይሁን እንጂ ይህ ብቻ አይደለም። በም. 11 ላይ ደግሞ ስለ ቁርባን እናነባለን እዚያ የተጻፈውን ተመልከት።)

ቁ. 23-30። ሐዋርያው ከም. 8፥1 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ ሲናገር ቆይቶአል። ይህን ያህል መናገሩ ይህ ነገር በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ዘንድ ቁም ነገር ስለ ሆነ ነው። በም. 8 መጀመሪያ ላይ እንዳየን ሁሉ በቆሮንቶስ ከተማ ከታረደው ሥጋ ሁሉ ቢያንስ ቢያንስ ጥቂቶች ጠጉሮች ለጣዖታት ይቃጠሉ ነበርና የሚገኘው ሥጋ ሁሉ ከጣዖታት ጋር ንክኪት ያለው ነበረ፥ ክርስቲያኖቹም በአምልኮ ባዕድ እንዳይረክሱ ፈሩ። ጳውሎስ ከዚህ በፊት በመጡት ምዕራፎች ላይ አሳቡን በጠቅላላ ገልጦአል፥ አሁን ትምህርቱን ሊያቆም ነው። «ሁላችን እውቀት አለን፥ ሁላችን ነፃ ነን፥ ሁሉም ተፈቅዶልናል» ብለው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የተደገፉበትን አሳብ ሐዋርያው ተቀብሎአል አምናአልም። (ም. 6፥(12፤ 8፥1-6።) ሆኖም የሚሉት ሁሉ እውነት ይሁን እንጂ ሐዋርያው «ሁሉ አይጠቅምም ሁሉም አያንጽም፤ ወንድምንም ከማሰናከል ይልቅ በመብት አለመጠቀም ይሻላል» ብሎአል። (ም. 8፥7-13።) ቀጥሎም «እኔማ ባለብዙ መብት ነበርሁ፤ ይሁንና የሚበልጡትን ለመጥቀም አክሊልም ለማግኘት ስል በመብቴ አልተጠቀምሁም» ብሎ ራሱን ምላሌ አድርጎላቸዋል። (ም. 9።) በም. 10 ደግሞ እሥራኤላውያን ይህን በሚመሳሰል ምክንያት አንደ ወደቁ። እንደ ቆመ የሚመስል ማንኛውም ሰው እንዳይወድቅ መጠንቀቅም እንዳለበት ካስረዳ በኋላ «ካጋንንት ጋር ማኅበርተኞች እንድትሆኑ አልወድም» እስኪል ድረስ ይህን ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ መብላት በጣም የሚያስፈራ ነገር መሆኑን ገልጦአል። እስከዚህ የተናገረው በጠቅላላው ነው፥ አሁን ግን ወደ ዓይነተኛ ነገር ሊገባ ነው። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የተቸገሩበት በ3 ነገር ነው፡- የከተማ ሰዎች በጣዖት ቤት ለማኅበር ሲሰበሰቡ ክርስቲያኖች ይሂዱ አይሂዱ? በገበያ የተሸጠውን ሥጋስ፥ ይብሉ አይብሉ? ያላመነ ሰው ወደ ቤቱ ቢጋብዛቸውስ፥ ይሂዱ አይሂዱ? ስለ መጀመሪያው ነገር ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ በቁ. 14-22 ላይ መልሱን የሰጠ ይመስላል። «አይሆንም» ይላል። የከተማ ሰዎች የሚሰበሰቡት ከጣዖት ጋር ለመተባበር ነው። እውነት ነው፥ ጣዖት ከንቱ ነው፥ ሆኖም ክርስቲያኖቹ አብረው የሄዱ እንደሆነ ከአጋንንት ጋር እንዳይተባበሩ ያስፈራል፤ ስለዚህም አይሂዱ። በገበያ ስለ ተሸጠው ሥጋ ግን፡- ምድርና በእርስዋ የሞላባት ሁሉ

የጌታ ነውና (መዝ. 23፥1)፥ ያም ሥጋ ከንቱ ለሆነ ጣዖት በመሠዋቱ አልተለወጠምና፥ ቢበሉት ምን አለበት? ከሕሊና የተነሣ ሳይመራመሩ ገዝተው ይብሉ። ከማያምኑም ሰዎች እንዱ ቢጋብዛቸው ነገሩ እንደዚሁ ነው። ለመሄድ ቢወዱ ይሂዱ፥ ከሕሊናም የተነሣ ሳይመራመሩ በፊታቸው የቀረበውን ይብሉ። ይሁን እንጂ መብት በፍቅር ይመሰናልና፥ ዋና የክርስቲያንም አሳብ ባልንጀራውን ማሰናከል ሳይሆን ማነጽ ነውና (ም. 8 እና ም. 9)፥ አንድ ሕሊናው ደካማ የሆነ ተጠራጣሪ ክርስቲያን «ይህ እኮ ለጣዖት የተሠዋ ነው» ብሎ ደንግጦ ቢያለታውቃቸው አይብሉ። ምነው? ቢሉም፥ አይ! ክርስቲያኑማ ለመብላት መብት አለው፤ ሳይበላ የሚቀረው ስለ ራሱ ብሎ ሳይሆን የባልንጀራውን ጥቅም እየፈለገ (ቁ. 24) እንዳይበድለውና ሕሊናውን እንዳያቆስል ነው። (ም. 8፥12።) ክርስቲያን አርነት ያለው የክርስቶስ ሎሌ ነውና ሕሊናው ደካማ የሆነ ሰው ሊፈርድበት አይችልም። (ሮሚ. 14፥4፥10።) የአርሱ ሕሊና ንጽሕ ሲሆን በሌላ ሰው ሕሊና ስለምን ይወሰናል? ሉሪ አያስፈልግም! እርሱ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ቢበላ ሰው ስለምን ይሰድበዋል? አይገባም! ለመብላት ሙሉ መብት አለው። ሆኖም የባልንጀራውን ጥቅም እየተመለከተ (ም. 9፥19-23) በመብቱ አይጠቀምም። ያ ሰው ስለ ተጠራጠረበት እርሱ መብላት አይገባውም ማለቱ አይደለም። የሚተወው ተገድዶ (መብላት ስለማይገባው) ሳይሆን ለባልንጀራው ብሎ ፈቅዶ ነው እንጂ።

ማስገንዘቢያ።

«ከሕሊና የተነሣ ሳትመራመሩ።» (ቁ. 25፡27።) «ሁሉ ተፈቅዶልኛል» የሚል የቆሮንቶስ ሰዎች የጠቀሱት የሐዋርያው ቃል ለክርስቲያን መሠረታዊ ቃል ነው፥ በዚህም ቃል ሁልጊዜ ልንጀምር እንችላለን። ቅዱስ ጳውሎስ በሌላ ስፍራ «በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር እትያዙ» ብሎ ጽፎአል። (ገላ. 5፥1።) ነፃ ነን፥ ይህንም ነፃነታችንን መጠበቅ ይገባናል። በክርስቶስ ድፍረት አለን፥ ይህንም ድፍረት ክርስቲያን ሁሉ መገንዘብ ይገባዋል። ዕድሜአችንን ሁሉ እንደሚጠራጠሩ ሕፃናት ሳንሆን ጎልምሰን የምንደፍር ሽማግሌዎች መሆን ይገባናል። እውነት ነው፥ ከዚህ በፊት እንዳየነው ሁሉ፥ ወንድማችንን እንዳናሰናክል ዘወትር መጠንቀቅ ያስፈልገናል። ይሁንና ብዙ ነገር ወንድማችንን ሳይነካ የራሳችን የግል ጉዳያችን ይሆናል፤ ይህም ሲሆን መሰናከያን ለማግኘት አብዝተን መመራመር ከጤና ያልሆነ ነገር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ አነኝህ የቆሮንቶስ ሰዎች «ይህ ሥጋ ከየት መጣ? ለጣዖት ተሠውቶአልን?» ወይም ደግሞ «እገሌ የጠራኝ እንደሆነ የሚቀርበው ሥጋ ምን ይሆን? ብለው ሳይጠይቁ ደፍረው ይግዙ ደፍረውም ወደ ባልንጀራቸው ቤት ይሂዱ አለ። ሥጋው ለመብል ተሸጠ ተጋባዡም በወዳጅነት ጠራ፤ በቃ! ሳይመራመሩና ሳይጠራጠሩ ያድርጉ። (1 ጢሞ. 4፥4። ቲቶ. 1፥15።) እኛም እንደዚሁ ፈሪዎች ሳንሆን በክርስቶስ እንድፈር። (ምሳ. 29፥25።)

ቁ. 31-ም. 11፥1። እንግዲህ ለእነዚያ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መጨረሻና ጠቅላላ አሳቡ ይህ ነው፡-የሚያደርጉት ሁሉ፥ መብላት ቢሆን መጠጣትም፥ ሌላም ማናቸውንም ነገር ቢሆን ለእግዚአብሔር ክብር ያድርጉት። አንደ ገናም ሐዋርያው የራሱን ምሳሌ ያቀርባል። በም. 9፥19፡22 ላይ እንደ ተባለው ሁሉ እርሱ ራሱ ያደረገውን አነርሱ ያድርጉ። እርሱም ባደረገው ሁሉ ክርስቶስን ለመምሰል እንዳሰበ እንዲሁም የቆሮንቶስ ሰዎች በአድራጎታቸው ሁሉ በሐዋርያው ፍለጋ ይሂዱ።

ማስገንዘቢያ።

«ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።» (ቁ. 31።) «ለክርስቲያን የተፈቀደው ያልተፈቀደውም እንዲት ይታወቃል?» ለሚለው ጥያቄ መጨረሻው ቃል ይህ ነው። አንዳች ነገር የተፈቀደ እንደሆነ ያልተፈቀደም ልናውቅ ስንፈልግ «ተፈቅዶአል» ከሚል መሠረት ተነሥተን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል።

1ኛ፥ «ይህ ነገር ይጠቅማልን?» (ም. 6፥12፤ 10፥23።)

2ኛ፥ «ምናልባት ባሪያ ያደርገኛልን?» (ም. 6፥12።)

ይህ የሕሊና ጉዳይ ነው። «ሕሊናችን ተሰማምቶበታልን?» ማለት ነው። (ም. 8፥7።)

3ኛ። «ይህን ነገር ያደረግሁት እንደሆነ ወንድሜን አሰናከለው ይሆንን?» (ም. 8፥13።) ይህም የፍቅር ጉዳይ ነው። «ፍቅር ያደረገው ነበርን?» ማለት ነው። (ም. 8፥9።)

4ኛ። «ለእግዚአብሔር ክብር ነውን?» (ም. 10፥31።)

ስለዚህ 1ኛ፥ ራሳችንን፤ 2ኛ፥ ባልንጀራችንን፤ 3ኛ፥ እግዚአብሔርን እንመለከታለን፥ ባየነውም ነገር እሳባችንን እንቆርጣለን።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 11።

1፤2፤ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ። ውንድሞች ሆይ፥ በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደ ለጠኋችሁ ወግን 3፤ ፈጽማችሁ ስለ ያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ። ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ። 4፤ ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ወንድ 5፤ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል። ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች፤ 6፤ እንደ ተላጨች ያህል እንድ ነውና። ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ጠጉርዋን ደግሞ ትቆረጥ፤ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቆረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን። 7፤ ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ ራሱን መከናነብ 8፤ አይገባውም፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት። ሴት 9፤ከወንድ ናት እንጂ ወንድ ከሴት እይደለምና። ሴት ስለ ወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ስለ ሴት አልተፈጠረምና። 10፤ ስለዚህ ሴት ከመላእክት የተነሣ በራስዋ ሥልጣን ሊኖራት 11፤ ይገባል። ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም 12፤ ያለ ሴት አይሆንም። ሴት ከወንድ እንደ ሆነች እንዲሁ ወንድ 13፤ ደግሞ በሴት ነውና፤ ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው። በእናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ፤ ሴት ራስዋን ሳትሸፍን 14፤15፤ ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ ይገባታልን? ወንድ ጠጉሩን ቢያሰረዝም ነውር እንዲሆንበት፥ ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም ክብር እንዲሆንላት ተፈጥሮ እንኳ እያስተምራችሁምን? 16፤ ጠጉርዋ መጎናጸፊያ ሊሆን ተሰጥቶአታልና። ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ፥ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም።

17፤ ነገር ግን በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለሚከፋ እንጂ ለሚሻል ስላልሆነ ይህን ትእዛዝ ስሰጥ የማመሰግናችሁ አይደለም። 18፤ በመጀመሪያ ወደ ማኅበር ስትሰበሰቡ በመካከላችሁ መለያየት እንዳለ እለማለሁና፥ በእንድ በኩልም እምንሃለሁ። 19፤ በእናንተ ዘንድ የተፈተኑት እንዲገለጡ በመካከላችሁ ወገኖች 20፤ ደግሞ ሊሆኑ ግድ ነውና። እንግዲህ አብራችሁ ስትሰበሰቡ 21፤ የምትበሉት የጌታ እራት እይደለም፤ በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና፥ አንዱም ይራባል አንዱ 22፤ ግን ይሰከራል። የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን አንዳችም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን? ምን ልበላችሁ? በዚህ ነገር ላመሰግናችሁን? አላመሰግናችሁም።

23፤ ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የለጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት 24፤ እንጀራን እንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም፦ -እንካችሁ ብሎ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዮ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዩ አድርጉት 25፤ አለ። እንደዚህም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ - ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዩ አድርጉት አለ። 26፤ ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።

27፤ ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን 28፤ ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም 29፤ ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ 30፤ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም 31፤ አንቀላፈተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም 32፤ ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ፥ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን።

33፤ ስለዚህ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ ለመብላት በተሰበሰባችሁ ጊዜ 34፤ እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ። ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ። የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ።

* * *
* * * * * *

3ኛ ክፍል።

(ም. 11።) ስለ ተደረገው ጥፋት ወቀሳ።

ስለ ሴቶች መሸፈኛና ስለ ጌታ እራት።

ምዕራፍ አሥራ አንድ።

ይህ ምዕራፍ በሁለት ክፍል ተከፍሎ ስለ ሁለት ነገሮች፥ ስለ ሴቶች የራስ መሸፈኛና ስለ ጌታ እራት (ስለ ቁርባን) ይናገራል።

ቁ. 2-16። ስለ ሴቶች የራስ መሸፈኛ። ጌታ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው» ባለ ጊዜ ጨምሮ እርሱ ያዘዛቸውን ሁሉ ምእመናን እንዲጠብቁ ያስተምሩአቸው ዘንድ ሐዋርያትን አዝዞ ነበርና (ማቴ. 28፥20) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተገባውን ወግ ሁሉ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች አስተላልፎ ነበር። እነርሱም እሁን በጻፉለት ወረቀት ላይ «አላልፈህ የሰጠኸንን ወግ ሁሉ ፈጽመን ያዝን» ብለውት ነበር፥ እርሱም ይህም ስለ መፈጸማቸው ያመሰገናቸዋል። ሆኖም ያልፈጸሙት እንድ ነገር አለና ከግመስገን ቀጥሎ ስለዚህ ስለ አንዱ ነገር ይወቅሳቸዋል። በዚያ ዘመን በዚያም ከፍስ ዓለም ሁሉ ሴቶች ራሳቸውን እንዲሸፍኑ ደንብ ነበረ። ራሳቸውን ያልሸፈኑት ሴት አዳሪዎች (ሸርሙጣዎች) ብቻ ነበሩና ሴት ራስዋን ባትሸፍን ነውር ይሆንባት ነበረ። በተለይም በቆሮንቶስ ከተማ ደጎች ሴቶች ራሳቸውን እንዲሸፍኑ ደንብ ነበረ። ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንዳየነው ሁሉ በዚያ ከተማ ሴት አዳሪዎች ስለ በዙ ነው። ይሁንና ከማን ዘንድ አንደ ሰማ እልተነገረም እንጂ፥ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አንዳንዶች ሴቶች «በክርስቶስ ነፃነት አለን» እያሉ ሲጸልዩ ወይም ትንቢት ሲናገሩ (የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስሙ ግለት) የተለመደውን የራስ መሸፈኛቸውን እንዳስቀሩ ሰምቶአል፥ በመስማቱም አዝኖአል። ምክንያቱም ያን መሸፈኛቸውን ስላስቀሩ አይደለም፥ ነገር ግን መሸፈኛቸውን ሲያስቀሩ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ስላፈረሱ ነው። ያዘነበት በዚህ ምክንያት እንደ ሆነ ቁ. 3 ያስረዳናል። ይህ ቁጥር ለዚህ ክፍል ሁሉ መሠረታዊ ቁጥር ነው። ጳውሎስ «የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነው፥ የሴትም ራስ ወንድ ነው፥ የክርስቶስም ራስ አግዚአብሔር ነው» ሲል የማይንቀሳቀስ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ያውጃል። እነኘህ 3 ቃሎች ለየዘመኑ ለያገሩም የእግዚአብሔር የማይለወጥ ሕግ ናቸው። («ራስ» ሲል መቼም «ባለ ሥልጣን» ማለቱ ነው።)

እግዚአብሔር ይህን ሥርዓት ሠርቶአል፥ ይህንም ሥርዓት የሚያፈርሰው እግዚአብሔርን ይቃወማል። የቆሮንቶስ ሴቶች የራስ መሸፈኛን ሲያስቀሩ ያደረጉቱ ይህን ነው። የሴት ራስ ወንድ ነውና (ዘፍጥ. 3፥16) በራስዋ ላይ የሥልጣን ምልክት፥ ማለት ከሥልጣን በታች መሆንዋን የሚያመለክት ምልክት፥ ሊኖራት ይገባል። የሥልጣን ምልክት የሆነውን መሸፈኛ ያስቀረችው ሴት፥ ራስዋን ከወንድ ጋር ማስተካከልዋ ነውና «የሴት ራስ ወንድ ነው» የሚለውን የእግዚአብሔርን ሥርዓት አፍርሳለች ፈቃዱንም ንቃለች። ይህም ብርቱ ነገር ታላቅም ጥፋት ነው።

በቁ. 3 ላይ ሐዋርያው መሠረታዊ ሕግን ገልጦአል፥ አሁንም ከቁ. 4 እስከ 6 ድረስ ከዚህ ሕግ የሚነሣውን ትምህርት ያስተምራል። የሚጸልይ ወይም የእግዚአብሔርን ነገር

የሚያስግ ወንድ ሁሉ መከናነብ አይገባውም፤ የምትጸልይ ወይም የእግዚአብሔርን ነገር የምታስግ ሴት ግን ራስዋን መሸፈን ይገባታል። ምክንያቱም፥ የውንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነውና ወንዱ ቢከናነብ ራሱን፥ ክርስቶስን፥ ስለሚያዋርድ ነው፤ የሴትም ራስ ወንድ ነውና ሴቲቱ ራስዋን ባትሸፍን እርስዋ ራስዋን (ወንድን) ስለምታዋርድ ነው። ወንድን የምታዋርደው ራስዋን (ሰውነትዋን) ልክ እንደ እርሱ በማድረግ ራስዋንም (ሰውነትዋንም) ክእርሱ ጋር በማስተካከል ነው። ይህን ስታደርግ ምነው ሁለመናዋ ወንድን መስላ የራስ ጠጉርዋን አታሳጥርም ወይ? ነገር ግን «አይ! ጠጉሬን እንደ ወንድ ግሳጠር ያሳፍራል» ብትል (በእውነቱም ያሳፍራል) የራስ መሸፈኛውን አትተው። ሐዋርያው መቼም የሚናገርበቱ ሴቶች ከጠቅላላው ግኅበር ውጭ ሲጸልዩ ወይም ሲናገሩ ይሆናል፤ ስለምን? ቢሉ፥ በመላ ግኅበር መካከል እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም። (ም. 14፥34፥35።)

አሁንም ደግሞ ከቁ. 7 እስከ 10 ድረስ ምክንያቱን እናገኛለን። ወንዱ ራሱን መከናነብ የማይገባበት ምክንያቱ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጨረሻና ድምድም ሆኖ በእግዚአብሔር መልክ ስለ ተፈጠረ ለእርሱም ሁሉ ስለ ተገዛ ነው። (ዘፍጥ. 1፥26፥28።) እርሱ የእግዚአብሔር ከብር እከሊልም ነውና የተገሸ ምልከት እሳይቶ ራሱን መከናነብ አይገባውም። ሴት ግን ስትፈጠር ከወንድ (ዘፍጥ. 2፥21-23) እና ስለ ወንድ ስለ ተፈጠረች (ዘፍጥ. 2፥18) እርስዋ የወንድ ከብር ናትና ከሥልጣን በታች መሆንዋን የሚያመለክተው የራስ መሸፈኛ ሊኖራት ይገባል። ምክንያቱም «የሴት ራስ ወንድ ነው» የሚለው የእግዚአብሔር ሥርዓት በሁሉ ዘንድ ስለታወቀ ነው። ሰዎች ብቻ ላያውቁት ሰዎችን የሚያዩና «መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የማላኩ የሚያገለግሉም» ቅዱሳን መላእክት ደግሞ ያውቁታል። (ዕብ. 1፥14። ማቴ. 25፥31።) ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕግ ሲፈርስ በማየታቸው መላእክት እንዳያዝኑ ሴቶች በሚገባው መሸፈኛ ራሳቸውን ይሸፍኑ።

(ሐዋርያው እንደ ተገባው ሁሉ የሴቶችን መገዛት አረጋግጦአል፤ ይሁንና ይህን ካረጋገጠ በኋላ ወንድና ሴት በጌታ ዓይን ልዩ ላይሆኑ እንድ እንደ ሆኑ ያመለክታል። (ቁ. 11፥12። ገላ. 3፥28።) የሴቶች መገዛት፥ በወንድና በሴትም መካከል ያለው የማዕረግ ልዩነት፥ በዚህ ዓለም ላይና ለዓለም ዘመን ብቻ ነው። ወንድ ለብቻው አይደለም፥ ሴትም ለብቻዋ እይደለችም። በመጀመሪያ ላይ ሴት ከወንድ እንደ ተፈጠረች እውነት ነው፤ ሆኖም ዛሬ ወንድ በሴት ይወለዳል፥ የሁለቱም መመንጪት ከእንዱ እርሱም ከእግዚአብሔር ነው።)

ወደ እሳቡም ተመልሶ ሐዋርያው ስለ ጣዖት ነገር ሲናገር እንደ ተናገረው ሁሉ (ም. 10፥15) እንዲሁም አሁን «እናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ» ይላቸዋል። በእርሱ ቃል ላይወሰኑ ሕሊናቸውን ይመርምሩ። ጎፈሬ በልዩ ዘመን ከብር ይሆናል እንጂ፥ በጠቅላላው፥ በተለይም በዚያ ዘመንና በዚያች ከተማ፥ ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንዲሆንበት፥ ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም ከብር እንዲሆንላት ተፈጥሮ እንኳ ይነግራቸዋልና ሴት ራስዋን ሳትሸፍን መጸለይ እንደማይገባት ሁላቸው ይፈርዳሉ። ረጅም ጠጉር ለሴት የተሰጠበት ምክንያቱ ራስዋን እንድትሸፍንበት ነው። ተፈጥሮ ተገቢነቱን ያመለክታል ማለት ነው። ይሁን እንጂ ስለዚህ ነገር ከሐዋርያው ጋር ሊከራከር የሚወድ ሰው ቢኖር ጳውሎስ የአብያተ ክርስቲያናትን ልማድ ብቻ ያመለከተዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች ወግን ሁሉ ሊይዙ ቢፈልጉ (ቁ. 2) እነዚያ አብያተ ክርስቲያናት

ያደረጉትን ያድርጉ። በእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሴቶች ራሳቸውን ላይሸፍኑ ለመጸለይ ወይም የእግዚአብሔርን ነገር ለመናገር ልማድ የላቸውም። የቆሮንቶስ ሰዎች ጥራዝ ነጠቆች አይሁኑ።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ ስለ ሴቶች መሸፈኛ ስለ ራሶችም ስናነብ በዱሮ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ምንኛ እንደ ሠለጠነ እንገነዘባለን። አገራችን ዱሮ የመጽሐፍ ቅዱስ አገር መሆንዋን እናስተውል።

ለ/ «ራሱን ያዋርዳል።» (ቁ.4።) ሰው በበላዩ (በባለ ሥልጣኑ) ፊት ሲቆም ባርኔጣውን እንደሚያነሣው ሁሉ እንዲሁም የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነውና ሰው በክርስቶስ ፊት ሲቆም ራሱን መከናነብ አይገባውም፤ ተከናንቦም የቆመ እንደሆነ ራሱን፥ ክርስቶስን፥ ያዋርዳል። ሰው በክርስቶስ ፊት የሚቆመው ሲጸልይ ብቻ ላይሆን ደግሞ የእግዚአብሔርን ነገር ሲያስማ መሆኑን የነቢያት ተከታዮች የሆንን የዛሬ መምህራን እናስታውስ።

ሐ/ «ከመላእክት የተነሣ።» (ቅ፪ 10።) ይህ ቃል ቢያስቸግረን መላእክት ፍጥረትን ሁሉ ይመለከቱ እንደ ነበር እንደ ተደስቱበትም እናስብ። (ኢዮብ 38፥7።) እሥራኤላውያንም ሕግን (እሪትን) የተቀበሉ በመላእክት በኩል ነበረ። (የሐዋ. 7፥53። ዕብራ. 2፥2።) እንግዲህ መላእክት የወንድንና የሴትን የመፈጠራቸው እኳኋንና የእግዚአብሔርን ሕግ አውቀዋልና ሴት በእርስዋና በወንድ መካከል ያለውን ልዩነት አጥፍታ ራስዋን ወንድ እስመስላ የሥልጣንን ምልክት የሆነ መሸፈኛዋን ብትተው መላእክት እንደሚያዝኑባት ይመስላል።

መ/ «ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም።» (ቁ. 11።) «ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ፥ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ፤ ይህን የሚያደርግ በእምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና» በማለት እሪት ሴት ወንድን እንዳትመስል፥ ወንድም ሴትን እንዳይመስል ጥንቱን ከልክሎአል። (ዘዳግ. 22፥5።) ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ የተመደበ ነገር ነው ፈቃዱም ነው፤ ቅዱስ ጳውሎስም በዚህ ምዕራፋችን ላይ ሕጉን አረጋግጦአል። ሥርዓቱ የማይለወጥ ነውና የሴት ተገዥነት ገና ዛሬ አልተሻረም ማለት ነው። ስለዚህ በቤተ ስብ ውስጥ ራስና ገዥ ወንዱ እንደ ሆነ ሴቶቹ ይገንዘቡ። ይሁን እንጂ በጌታ ዘንድ፥ በክርስቲያን ሃይማኖት ማለት የሴት ቦታ ሁለተኛ ቢሆንም የተዋረደ ቦታ አይደለም። ሴት በጌታ ዘንድ ከብርት ናት። እግዚአብሔር ውንድን እንደሚመለከተው ሁሉ እንዲሁም ሴትን ይመለከታል። የተፈጥሮ የማዕረግ ልዩነት አይቀርም፤ ቢሆንም በጌታ ፊት በጌታም ዘንድ ወንድና ሴት አንድ ናቸው። የክርስቲያን ወንዶች የሆንን ሁሉ ይህን ተገንዝበን ለሴት ሁሉ ክብርንና ገርነትን ማስተዋልን ሁሉ እናሳይ። (1 ጴጥ. 3፥7።)

ሠ/ «ሐዋርያው የሚፈልገው ያ መሠረታዊ የእግዚአብሔር ሥርዓት እንዲጠበቅ ነው እንጂ በማናቸውም አገርና በማናቸውም ዘመን ሁሉ ሴቶች ሲጸልዩ ወይም የእግዚአብሔርን ነገር ሲያስሙ ራሳቸውን እንዲሸፍኑ አይፈልግም። ሥርዓቱ ከተጠበቀ ሴት ራስዋን ብትሸፍን ባትሸፍንም ከቁም ነገር እይቆጠርም» የሚሉ

ሰዎች አሉ። ጨምረውም «ሐዋርያው እኮ ሴት መሸፈኛዋን እታውልቅ ብሎአል እንጂ ራስዋን ትሸፍን አላለም» ይላሉ። ይህን ሲሉ «የአገራችንና የዘመናችን ሁኔታ ከቆሮንቶስ ከተማና ከዚያ ዘመን ሁኔት ልዩ ነውና በዚህ ክፍል ውስጥ በተገኘው ትእዛዝ እኛ እንያዝም» ማለታቸው ነው።

እርግጥ ነው፥ ዋና የሐዋርያው አሳብ ሴት በእርስዋና በወንድ መካከል የሚገኘውን የማዕረግ ልዩነት ለመሸሸግ እንዳትሞክር ወንድንም እንዳትመስል ነው። ይሁንና በቁ. 3፡4፡5፡7 እና 10 ላይ የተሰጠው ትምህርት ጠቅላላ ሆኖ ለመቼውም ቢሆን የሚረታ ይመስላል። «በእኛ አገር ወይም በእኛ ዘመን ሴት ራስዋን ለመሸፈን ልማድ የላትም» ቢባል «በጳውሎስ አገርና በጳውሎስ ዘመን ወንድ ራሱን ላይከናነብ መጸለይ ልማድ አልነበረውም» እንላለን። አይሁድ ሲጸልዩ ራሳቸውን ሁልጊዜ ይከናነቡ ነበር እስከ ዛሬም ይከናነባሉ። ይሁን እንጂ አይሁዳዊ ጳውሎስ ክርስቲያን በሆነ ጊዜ «ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወንድ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል» አለ። (ቁ. 4።) ስለዚህ እንዳይመላለሱና ወንዶች ራሳቸውን ላይከናነቡ፥ እንዲጸልዩ ሴቶችም ራሳቸውን ሸፍነው እንዲጸልዩ የሐዋርያ የቅዱስ ጳውሎስ ፈቃድ ነው እንላለን። ልማዱም ለቆሮንቶስ ብቻ ላይሆን ለእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ መሆኑን እናስተውል።

ቁ. 17-34። ስለ ጌታ እራት። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሐዋርያውን በሁሉ ስላስቡና እርሱ አሳልፎ የሰጣቸውን ወግ ፈጽመው ስለ ያዙት ጳውሎስ አመሰግናእቸው ነበር። (ቁ. 2።) አሁን ግን ላስ መንፈሳዊ ስብሰባቸው ሲናገር ሊያመሰግናቸው አልቻለም። በመንፈሳዊ ስብሰባ የተሰበሰቡበት ሊጠቀሙ ነበር፥ እነርሱ ግን ሰጥቅማቸው ላይሆን ለጉዳታቸው ተሰብስበዋል፥ ሐዋርያውም ስለዚህ ነገር ምክር ብቻ ላይሰጥ ጽኑ ትእዛዝ ከዘሰፋ ጋር ሊሰጣቸው ነው።

ጌታ የቁርባንን ሥርዓት የሠራው በምሽቱ ሰዓት ከሐዋርያት ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ ነውና (ማቴ. 26፥20፡26) የጥንት ክርስቲያኖች ይህን ምሳሌ ተከትለው በግሪክ ቋንቋ «አገፔ» የተባለውን የፍቅር ግብኖ እስቀድመው በሉ (ይሁዳ ቁ. 12) በኋላም ቁርባንን ተቀበሉ። ሁለቱም ሥርዓቶች በአንድነት ሲደረጉ ጠቅላላው ስብሰባ «የጌታ እራት» ተባለ። በቆሮንቶስ የተደረገው ጥፋት እየበዛ በመሄዱ ምክንያት ሁለቱ ሥርዓቶች በየጥቂቱ ወይም ተለያዩ ወይም ተዛወሩ፥ በዚህም እንጻር «ጻሪቀ መበለት» የተባለው መክፈልት እዚህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናችን ከቅዳሴ በኋላ ይደረጋል። በእንዳንዶች አገሮች ደግሞ አገፔው ዛሬ በፍጹም ቀርቶአል።

በዚያ ዘመን ክርስቲያኖቹ ሁሉ እንደ ችሎታቸው መጠን ምግብን ያቀርቡ ነበር፥ ሁላቸውም የቀረበውን ምግብ ከቅዳሴው በፊት በእንድነት ይበሉ ነበር። እንደዚህም በማድረግ ጎብረታቸውን አንድነታቸውንም አመልክተዋል እጽንተውታልም። ይህንም ካደረጉ በኋላ ቁርባንን በእንድነት ተቀብለዋል። ነገር ግን በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ጥፋት ተደረገ። ምነው? ቢሉ፥ የቆሮንቶስ ሀብታሞች ብዙ እያቀረቡ ደሆችን ላይጠብቁ አስቀድመው ገብተው ከሌሎች ሁሉ ተለይተው የራሳቸውን መብል ብቻ በሉ። የድሆችን መብል አልቀመሱም ከመብላቸውም ሰድሆች አላስቀሩም። ሀብታሞች ይበሉና ይጠጡ ይሰክሩም ነበር፤ ኋላም፥ የማጎበሩ መንፈስ እንደተበላሸ ሆኖ፥ ገብተው ቁርባንን ተቀበሉ! እንደዚሁም ደግሞ ድሆች እየተራቡና እያፈሩ መንፈላቸውም እንደ ተበጠበጠ ሆኖ ቁርባንን ተቀበሉ።

ይህ ከፍል በ3 ረድፍ ይከፈላል፡-

1ኛ፥ ቁ. 17-22። የተደረገው ጥፋት። «እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላል።»

2ኛ፥ ቁ. 23-32። የጥፋቱ ውጤት። «የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት።»

3ኛ፥ ቁ. 33፡34። የጥፋቱ መበጀት። «እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ።»

1ኛ። እንደገና ሐዋርያው እንዳች ነገር ስምቶአል። የሚሰማውን ወሬ ሁሉ ወዲያውኑ ለማመን ልማዱ አይደለምና «በአንድ በኩል» ብቻ ያምነዋል። ሆናም የሰማው ታላቅ ነገር ነው። የጥፋቱ መጀመሪያ በመካከላቸው ያለው መለያየት ነው። መተባበር የተገባቸው ሲሆን ተለያዩ። ሀብታሞችና ጌቶች ለብቻቸው፥ ድሆችና ባሪያዎች ለብቻቸው እየሆኑ ወገንነትን ፈጠሩ። ሁላቸው በክርስቶስ ኢየሱስ እንድ ሰው ሲሆኑም (ገላ. 3፥28) መለያየትን መረጡ። መለያየት መጥፎ ነው፥ ሆናም እውነተኞች ክርስቲያኖች የሆኑቱ በዚህ ይገለጣሉና ወገንነት እንዲኖር የግድ ነው። ማለት፥ ከበርቴዎች የሆኑት እውነተኞች ክርስቲያኖች ከድሆችና ከባሪያዎች ጋር በክርስቶስ አንድ መሆናቸው እየተሰማቸው ከእነርሱ ጋር ለመተባበር ይፈቅዳሉ፥ በዚህም ነገር እውነተኞች ከሐሰተኞች ይለያሉ እውነተኞችም የተኛዎች እንደ ሆኑ ይገለጣል። (1 ዮሐ. 2፥19።)

በቁ.20 ላይ ሐዋርያው «የጌታ እራት የምትሉት በእውነቱ የጌታ እራት አይደለም» ይላል። እውነት ነው፥ አብረው የተሰበሰቡበት የጌታን እራት ለመብላት ነበረ። ሆናም የጌታ እራት የተሠራው ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር አንድነትን ጎብረትንም ለማድናት ነበርና በማይገባ መንፈስ የሚበላና የሚጠጣ ሥርዓቱን እፍርሶአልና የሚበላውና የሚጠጣው ተራ ግብኖ ነው እንጂ በእውነቱ የጌታ እራት አይደለም። እነዚህም የቆሮንቶስ ከበርቴዎች፥ በሥራ ላይ በመዋል ምክንያት የግድ ቆይተው የሚመጡትን ባሪያዎችን ድሆች ሳይጠብቁ እነርሱ ራሳቸው ያመጡትን ምግብ ወዲያውኑ ይበሉ ነበርና የሥርዓቱን መንፈስ አጥፍተዋል እራቱንም «ሳይገባ» (ያለ እገባብ) በሉት። ይህን በማድረጋቸው ታላቅ ጥፋት ሠርተዋልና ሐዋርያው በብርቱ ይወቅሳቸዋል። ምነው? ከተራቡና መብላት ከፈለጉ በቤታቸው አይበሉምን? እዚያ ቢበሉ አይፈረድባቸውም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ማኅበር ቢንቁና የእግዚአብሔርን ሰዎች ቢያሳፍሩ የሚሠሩት ጥፋት ታላት ነው ፍርድንም ያስከትላል። ሐዋርያው አመሰግናለችው ነበር፥ አሁን ግን ምስጋና ከቶ አይገባም።

2ኛ። ያጠፉት ጥፋት ታላት መሆኑን ይረዱ ዘንድ የሥርዓቱን ድንጋጌ ያሳስባቸዋል። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው አራቱ ወንጌል ሳይጻፍ በፊት ነውና ይህ ስለ ቁርባን ሥርዓት መጀመሪያ ታሪክ ይሆናል። የቆሮንቶስ ሰዎች መቼም ይህን ታሪክ ከዚህ በፊት ስምተዋል ጳውሎስ እንደ ወትሮውም እሳልፎ ሰጥቶአቸዋልና (ቁ. 2፡23)፤ ይሁን እንጂ እንዴት ያለ ታላት ሥርዓት እንደ ሆነ ይረዱ ዘንድና ሳይገባ በመረጸማቸው ምንኛ እንዳጠፉ ያስተውሉ ዘንድ ታሪኩን እንደገና ያሳስባቸዋል። ቅዱስ ጳውሎስ በቀጥታ ከጌታ ዘንድ በራእይ ብዙ ነገር ተቀብሎአልና (የሐዋ. 18፥ 9፡10፤22፥ 18፡21፤ 23፥11፤ 27፥ 23-25። 2 ቆሮ. 12፥7። ገላ. 1፥11፡12፤2፥2) ይህን የቁርባንን ሥርዓት በቀጥታ ከጌታ ዘንድ መቀበሉ ወይም ታሉ ከጌታ ዘንድ መንጭቶ በልዩ ልዩ እፍ እየተላለፈ ወደ እርሱ ዘንድ ደርሶ እንደሆነ ግረኩ አያስረዳንም። ሆናም ከጌታ ከራሱ መንጭቶአል፥ ወደ ሐዋርያውም ደርሶአል፥ እርሱም ተቀብሎት

አስተላልፎታል። የተቀበለው ይህ ነው፡- ሐሙስ ዕለት በምሽቱ ለዓት ጌታ ኢየሱስ እልፎ በተሰጠበት ሌሊት፥ እርሱና ሐዋርያት በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ፥ ጌታ እንጀራን አነሣና እግዚአብሔርን ከባረከና ካመሰገነ በኋላ የእርሱ ሥጋ ስለ አነርሱ እንደሚደቅ ያመለከት ዘንድ (ኢሳይ. 53፥5፡10) ቆረሰው ለሣቸውም። እንደዚሁ እራት ሲጨርሱ ጌታ፥ ደሙ ስለ እነርሱ እንደሚፈስ ያመለከት ዘንድ፥ ጽዋን አንሥቶ ለሣቸውና በየጊዜው ሁሉ እንደዚህ ያደርጉ ዘንድ አዘዛቸው። ሐዋርያውም «ይህን ስታደርጉ ጌታ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን (በሥዕል) ትናገራላችሁና» ብሎ በየጊዜው ሁሉ የሚደረግበትን ምክንያት ያስረዳል።

የሥርዓቱ ድንጋጌ አንደዚህ ሲሆን የቆሮንቶስ ሰዎች «ሳይገባ» (ያለ አገባብ) ቢፈጽሙት ያደረጉት ጥፋት ምንኛ ታላት ነው! ሐዋርያው «ሳይገባው የበላ ወይም የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት» ይላል። ማለት፥ ዋጋውን ክብሩንም ሳይለይ ጎብስቱን እንደ ተራ እንጀራ የሚበላ ሰው የክርስቶስን ሥጋ ያዋርዳል። ጎብስቱ የሥጋው ምሳሌ (እምሳል) ነውና ጎብስቱን ያዋረደ ሥጋውን አዋርዶአል። እንደዚሁ ደግሞ ጎብስቱና ጽዋው ሞቱን የሚያመለክቱ ናቸውና በምልክቶች የዘበተ በክርስቶስ ሞት ዘብቶአል። (ዕብ. 6፥6፤ 10፥29።) ይህን የሚያደርግ ሰው ፍዳን ይከፍላል። እንዴት? ቢሉ፥ ጎብስቱን ሳይገባ (ያለ እገባብ) የሚበላ ለው ፍርድን ይበላልና። ስለዚህ ሁሉ፥ ቁርባንን ለመቀበል ያለበው ለው ራሱን አሰቀድሞ ቢፈትን ይሻላል፥ ከፈተነም በኋላ ከጎብስቱ ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ። የቆሮንቶስ ሰዎች ይህን ሳያደርጉ ሰተት ብለው ገብተው ጎብስቱን ሳይለዩ እንደ ተራ እንጀራ፥ ጽዋውን ሳይለዩ እንደ ተራ መጠጥ ስላደረጉት ፍርድ ተፈረደባቸው። ፍርዱም ይህ ነው፡-ብዙዎች ደከሙ፥ ብዙዎች ታመሙ አያሌዎችም ሞቱ። የተፈረደባቸው ፍርድ መቼም የሥጋ ፍርድ ነው እንጂ የነፍሰ ፍርድ አይደለም፤ ፍርዱም ከዓለም ጋር እንዳንኮነን የጌታ ግሣጼ ነው። (ቁ. 32።) ፍርዱ ልጁን የሚቀጣበት የአባት ቅጣት ነው። (ዕብ. 12።5-13/)

3ኛ። አውንም በመጨረሻ ላይ ሐዋርያው ስለ ተደረገው ጥፋት መበጀት ይናገራል። እንዲህ ያለ ጥፋት እንዳይደረግ ምን ማድረግ ይሻላል? «የጌታን እራት ለመብላት ስትሰበሰቡ እርስ በርሳችሁ እየተጠባበቃችሁ ሁሉን በአገባብና በሥርዓት አድርጉ» ይላቸዋል። የጌታ እራት ልዩ የከበረም ነገር ነውና ለው ተራ ግብኖ ያደረገው እንደሆነ ፍርድ ይፈረድበታልና የተራበ ሰው ቢኖር ከቤቱ ይብላ። ሐዋርያው ስለ ቁርባን ሊነግራቸው የሚፈልግ ሌሎች ነገሮች አሉት፤ ሆናም ለጊዜው ይህ ይበቃል ሲመጣም የቀረውን ይደነግግላቸዋል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ቁርባን ምንድር ነው እውነተኛ አሳቡስ እንዴት ነው?» ተብሎ በመቅድሙ ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሱ ከዚህ ቀጥሎ አንደ ተጻፈ ነው።

ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች ከእንዱ ዘንድ የተገኘውን የኢትዮጵያ እርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የምሥጢረ ቁርባን ጠቅላላ አስተያየትን አስቀድመን እንገልጣለን።

«ምሥጢረ ቁርባን ክርስቶስ ሠርቶ ካሳያቸው ምሥጢራት አንዱ ነው፥ ሥራውም አጥፍ ነው። አንደኛ፥ ዓለምን ለማዳን ሲል እራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ

ያቀረበውን መሥዋዕት ሲያስታውስ የሚናር ነው፤ ይኸውም አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ግርያም «ይህም ባደረጋችሁ ጊዜ የሞቱን መታሰቢያ ታደርጋላችሁ፡ የትንሣኤውንም መታሰቢያ ትናገራላችሁ» ያለውን መመልከት ነው። ሁለተኛው ግን ሰዎች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ በልተው ደሙን ጠጥተው መንግሥተ ሰማያትን ያወርሱ ዘንድ ነው። ይኸው አባ ሕርያቆስ «ንሡ ሥጋዮን ብሉ ለዓለም መድኃኒት ይሆን ዘንድ ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዮ ይህ ነው፤ ጽዋዬንም ጠጡ ስለ እናንተ የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው» ብሎአል። ስለዚህ ምሥጢረ ቁርባን ምሥጢርና ቁርባን ነው። ምሥጢር ያለው ጎብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ሲሆን ሰበቃ እንጂ ላልበቃ ስለማይታይ ነው። መሥዋዕት ግን የምንለው ምንም እንኳ መሥዋዕቱም መሠዊያውም ተቀባዩ እርሱም ቢሆን በቅዳሴ ጊዜ ፈጣሪያችንን የምናመሰግን ስለ ተሠዋው መሥዋዕት ይቅርታን እንዲያደርግ፤ እንደ ኃጢአታችን ብዛት እንደ ሰውነታችን ክፋት ፈተና እንዳያጠፋን ስለምንለምን ነው፤»

አሁንም ደግሞ ሌላ አስተያየትን እንገልጣለን። «ቁርባን ምንድር ነው? እውነተኛ አሳቡስ እንዴት ነው?» ቢሉ፥ ሌሎች መምህራን እንዲህ ይላሉ፡-

1ኛ። ማስተባበሪያ ነው። በም. 10፥16፡17 ላይ እንዳገኘን ሁሉ ቁርባን ከክርስቶስና ከወገኖቹ ጋር ያስተባብረናል። ጽዋው ከክርስቶስ ደም ጋር፥ ጎብስቱም ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ጎብረት ስላላቸው እና ጎብስቱንና ጽዋውን ስንቀበል ከክርስቶስ ጋር ጎብረት አለን። እንደዚሁም በቁርባን ጊዜ እኛ ሁላችን አንዱን ጎብስት እንካፈላለንና እርስ በርሳችን ጎብረት አለን። በዚህ ምክንያት ቁርባን ከክርስቶስና ከወገኖቹ ጋር ያስተባብረናል እንላለን። (በጥንት ዘመን ደግሞ ከቁርባን በፊት የተደረገው የፍቅር ግብዣ ይህን ጎብረት አመልክቶአል።)

2ኛ። መታሰቢያ ነው። በም. 11፥24፡25 ላይ እንደምናየውም ጎብስቱን የምንበላበት ጽዋውም የምንጠጣበት ለመታሰቢያ ነው። ክርስቶስን እናስባለን። ጎብስቱ ሲከፈል የክርስቶስ ሥጋ ስለ እኛ እንደ ተከፈለ፥ ወይኑ ሲፈስ የክርስቶስ ደም ስለ እኛ እንደ ፈሰሰ እናስታውሳለን። እያንዳንዳችን ቅዱሳት ምሥጢራትን ስንቀበል «ያ ሥጋ የደቀቀው ያም ደም የፈሰሰው ስለ እኔ ነው» ብለን ማሰብ ይገባናል። በዚህ ምክንያት ቁርባን መታሰቢያ ነው እንላለን። ይሁን እንጂ ሥርዓቱ መታሰቢያ ብቻ ነው የሚል ሰዎች ተሳስተዋል።

3ኛ። ማስታወቂያ ነው። (ቁ. 26።) ከዚህ በፊት እንደ ተባለው፥ የቁርባን ሥርዓት በፋሲካ ሥርዓት ላይ ተመሥርቶአል። በየዓመቱ በፋሲካ ጊዜ አይሁድ ሥርዓቱን ሲያደርጉ ከየቤተሰቡ መካከል አንድ ልጅ ተነሥቶ «ይህ አምልኮ ለእናንተ ምንድር ነው?» ብሎ ጥያቄ ያቀርብ ነበር። በዚያን ጊዜ አባትየው «የእግዚአብሔር የማለፉ መሥዋዕት ይህች ናት» ብሎ ይመልስና እሥራኤላውያን ከምስር ባርነት የዳኑበትን መንገድ ያስታውቀው ነበር። (ዘፀአ. 12፥26፡27።) እንደዚሁም ሁሉ ቁርባን በሚገባ ሲደረግ ሥዕላዊ ስብከት ነው። በሥዕላዊ አነጋገር የምንድንበትን መንገድ ያሳያል። ቀላውስት በቃል ብቻ ላይሆን በምላሌም በኅልኅታ ላይ የተደረገውን ይናገራሉና የተሰበሰበው ሕዝብ በጆሮአቸውና በዓይናቸውም ታረኩን ይማራሉ። በዚህ ምክንያት ቁርባን ማስታወቂያ ነው እንላለን።

4ኛ። ማስታወሻ ነው። የቁርባን ሥርዓት የሚደረገው «ጌታ እስኪመጣ ድረስ» ነውና (ቁ. 26) ዳግም ምጽአቱን ያስታውሰናል። ይህም ምጽአት የእውነተኛ ክርስቲያን ዋና ተስፋ ነው (1 ተሰ. 4፥13-18። ቲቶ. 2፥13)፥ ቁርባንም የምንወደውን የጌታን መምጣትና ከእርሱ ጋር የሚመጣልንን ክብርና ደስታ ያስታውስናል። ሆኖም ጌታ በዚያ ጊዜ የሚመጣው በምድር ላይ ሊፈርድ ነውና (መዝ. 95፥13) ቁርባን ደግሞ ያልተዘጋጀው ሰው በመንገድ ላይ ገና ሳለ በደቀቀው ሥጋ በፈሰሰውም ደም መሠረት ከታላቁ ባላጋራው ጋር እንዲታረቅ ያስታውሰዋል። (ሉቃ. 12፥57-59።)

5ኛ። ማሳደጊያ ነው። ከርስቲያን በሃይማኖቱና በመንፈሱ የሚያድግበት ዋና ማሳደጊያ ቁርባን ነው። ሰው መብልንና መጠጥን በግዙፍ አኳኋን ወደ ሆዱ ሲቀበል በሥጋው (በሰውነቱ) እንደሚበረታና እንደሚያድግ፥ እንዲሁም የክርስቶስን ሥጋና ደም በመንፈላዊ አቀባበል ወደ ልቡ ሲቀበል በመንፈሱ ይበረታል ያድግማል። ቁርባንን እንደሚገባ የሚቀበል ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ጸጋን (ስጦታን) እንደሚያገኝ አይጠረጠርም። በሃይማኖትና በመንፈስ ደካሞችና ሕፃናት የሆኑት በመካከላችን ብዙ ሰዎች መገኘታቸውም ይኸው ቁርባንን ባለመቀበላቸው ነው። እንግዲህ ቁርባን ዋና የክርስቲያን ማሳደጊያ ነው እንላለን።

ለ/ ስለ ዮሐንስ ም. 6። በዚህ ምዕራፍ ላይ ጌታ ሥጋውን ስለ መብላት ደሙንም ስለ መጠጣት ይናገራልና (ቁ. 52-58) ብዙዎች መምህራን ወዲያውኑ ስለ ቁርባን ይተረጉሙታል። እንደዚህ ሲተረጉሙት ግን ብዙ ችግር ይፈጠራልና ሌሎች መምህራን «አይደለም! ይህ ምዕራፍ የሚናገረው ክርስቶስን ስለ መቀበል ነው እንጂ ቁርባንን ስለ መቀበል አይደለም» ይላል፥ አሳባቸውንም ለመደገፍ ሦስት ምክንያቶች ያቀርባሉ።

1ኛ ሰው የዘላለምን ሕይወት የሚያገኝ በክርስቶስ በማመን ነው እንጂ ቁርባንን በመቀበል አይደለም። ከዚህም ጋር ቁ. 47 ይስማማል።

2ኛ የቁርባን ሥርዓት የተሠራው ጌታ በተያዘበት ሌሊት እንደ ሆነ ታውቆአል። በዚህም ምክንያት ሌሎቹ ወንጌላውያን በታሪካቸው መጨረሻ ላይ ጽፈውታል። (ማቴ. 26። ማር. 14። ሉቃ. 22።) ይህ በዮሐ. ም. 6 ላይ የተጻፈው ቃል ግን ከዚያ ሌሊት ሁለት ዓመት በፊት ተነገሮአል። ጌታ ገና ከሁለት ዓመት በኋላ ስለሚሠራው ሥርዓት በዚያ ጊዜ ቢናገር ኖሮ ቃሉን ማን ባስተዋለ?

3ኛ ቁርባን የተሠራው ለምእመናን፥ የተነገረውም ለሐዋርያት ሲሆን በዮሐ. ም. 6 ላይ የተነገረው ቃል ላላመኑትና ለሕዝብ ተነግሮአል። (ቁ.22-30) እነኝህ ያላመኑት ሰዎችም ቁርባንን በመቀበል የዘላለምን ሕይወት የሚያገኙ ከሆነ ሃይማኖትና ጥምቀት ምግባርም ምን ባስፈለገ?

ነገሩ አስቸጋሪ ነው፥ መምህራንም አልተስማሙበትም። አልተስማሙበትምና እንባቢው መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራው እየለመነ (ዮሐ. 16፥13) በጥብቅ ያስብበት።

ሐ/ «ይህ እንጀራ ሥጋዬ ነው፥ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።» ቁ. 24፡25።) መቼም ኢየሱስ ያነጣው እንጀራ በእውነቱ ሥጋው አልነበረም፥ ያነጣውም ጽዋ ደሙ አልነበረም። ምነው? ቢሉ፥ እርሱ ራሱ በዚያን ጊዜ

በሥጋውና በደሙ እዚያ በመካከላቸው ነበረ፥ በእጁም ይዞ ያነሣው እንጀራንና ጽዋን ነበረ። ሐዋርያትም የበሉት እንጀራን የጠጡትም የወይን ጭማቂን ነበረ። ክርስቲያኖች እንደዚሁ። በቅሬ 28 ላይ እንደምናየው የሚበሉት «ከእንጀራው» የሚጠጡትም «ከጽዋው» ነው።

ሰው ግን «ታዲያ፥ ሥጋዱ ነው ደሜም ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?» ብሎ ይጠይቅ ይሆናል፤ ይህንም በምሳሌ እናስረዳለን።

መጀመሪያ ምሳሌ። አንድ ሰው በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የሚታዩትን ነጥቦች በጣቱ አመልክቶ ባልንጀራውን «ይህ ጎንደር ነው፥ ይህም አዲስ አበባ ነው» ይላል። መቼም በእውነቱ ጎንደር እይደለም አዲስ አበባም አይደለም። ጎንደርና አዲስ አበባ ከተሞች ናቸው እንጂ በካርታ ላይ የሚገኙት ነጥቦች አይደሉም። ታዲያስ ያ ሰው «ነው» ያለ በምን ምክንያት ነው? ውሸት መናገሩ ነውን? ሉረ አይደለም! እንግዲያስ ምን ማለቱ ነው? እነዚያ ነጥቦች የእነዚያ ከተሞች ምሳሌዎች ናቸው የእነዚያም ከተሞች ምልክቶች ናቸው። ሰውየው ግን ለባልንጀራው ሲያሰረዳ «ይህ ጎንደር ነው፥ ይህም አዲስ አበባ ነው» ይላል። እንደዚህም ሁሉ ጌታ እንጀራን አንሥቶ «ይህ ሥጋዮ ነው፥ ይህም ደሜ ነው» አለ። ካርታውም ወረቀት ብቻ ቢሆን እንኳ የከበረ ነገር ነው፥ ኢትዮጵያ ነውና! ሰው ቢያዋርደው ቢረግጠውም በደንብ ይቀጣል። ጎብስቱና ጽዋው እንደዚህ የከበሩ ምሳሌዎች (አምሳሎች) ናቸው።

ሁለተኛ ምሳሌ። በቤቴ ግድግድ ላይ የአባቴ ፎቶግራፍ ተለጥፎአል። አንድ እንግዳ በቤቴ ገብቶ ፎቶግራፉን ያይና «ማን ነው?»። ይለኛል «አባቴ ነው» እለዋለሁ። መቼም በእውነቱ አባቴ አይደለም፤ አባቴ ወይም በሌላ አገር ይሆናል ወይም ሞቶ ይሆናል። እኔ ግን «አባቴ ነው» እላለሁ። ተሳሰቼ ነውን? ሉረ እልተሳሳትሁም! ፎቶግራፉ የአባቴ ምሳሌ ነው። ምሳሌውም ብቻ ቢሆን እንኳ ሰው ቢያዋርደው ቢዘብትበትም እኔ አቀጣዋለሁ! እንደዚሁም ሁሉ ጎብስቱና ጽዋው የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ምሳሌዎች (አምሳሎች) ናቸው፥ ክቡራንም ናቸው።

ሦስተኛ ምሳሌ። ማናቸውም የንጉሥ እንደራሴ በአንድ አገር ይገኛል። ንጉሡ አይደለም፤ ሆኖም የንጉሡ እንደራሴ ነው፥ ሰውም ሁሉ እንደ ንጉሡ ያየዋል ያከብረውማል። ያ እንደራሴ ተራ ሰው፥ ከሕዝብ አንዱ፥ ዳክማም ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና እርሱ ግን እንደ ሆነ ሳይለይ እንደ ተራ ሰው ያደረገው ሰው ንጉሡን እዋርዶአል በብርቱም ቅጣት ይቀጣል። «ሳይገባ» (ያለ አገባብ) በፊቱ የቀረበ ሰው ሰራሱ ፍርድ ያሰናዳል። ጎብስቱና ጽዋው እንደዚሁ ናቸው።

አራተኛ ምሳሌ። የቁርባን ሥርዓት በፋሲካ ሥርዓት ላይ ተመሥርቶአል። በየዓመቱ በፋሲካ ጊዜ ሥርዓቱ ሲደረግ የቤተሰብ አለቃ የሆነው ሁሉ ቂጣን አንሥቶ «አባቶቻችን በምስር አገር የበሉት የመከራ እንጀራ ይህ ነው» ብሎ ይሰጣቸው ነበር። (ዘዳግ. 16፥3።) ይህ ፈጽሞ ክርስቶስ ያደረገው ነገር ነው። አይሁዳዊ የቤተ ሰብ አባት «ነው» ሲል ፍችው ምንድር ይሆን? ምሳሌ አይደለምን? ነው!

ስለዚህ ጎብስቱና ጽዋው የሥጋውና የደሙ ምሳሌዎች (አምሳሎች) ናቸው፤ እንደዚህም ደግሞ በጥምቀት ሥርዓት እንዳለው ውኃ ሆነው የአዲስ ኪዳን ምልክቶችና ማኅተሞች ናቸው። (እዚህ በ1ቆሮ. 11፥25 ላይ፥ እንደዚሁም በሉቃ. 22፥ 20 ላይ፥

ጌታ «ይህ ጽዋ አዲስ ኪዳን ነው» ማለቱን እንጂ «ይህ ጽዋ ደሜ ነው» አለማለቱን ብዙዎች መምህራን ተገንዝበዋል። «ጽዋ እንዴት አድርጎ ኪዳን ይሆናል?» ይላሉ። እውነታቸው ነው፥ ጽዋ ኪዳን ለመሆን አይችልም። ሆኖም ጌታ «ነው» ብሎአል። ሰለዚህ እላይ እንደ ተባለው ሁሉ ጽዋው የኪዳን ምሳሌና ምልክት እንደ ሆነ መተርጎም ነው። ዕብ. 9፥5-10፥18። ይሁንና በማቴ. 26፥27 እና በማር. 14፥24 ላይ ክርስቶስ «ይህ ጽዋ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው» እንዳለ ተጽፎአል። የሆነ ሆኖ ጎብስቱና ጽዋው የሥጋውና የደሙ ምሳሌዎች (እምሳሎች) የኪዳኑም ምልክቶችና ማኅተሞች እንደ ሆኑ እንረዳለን።) አዲስ ኪዳን የተባለውም በኤር. 31፥31-34 ላይ እንደ ተባለው ነው።

ሐ/ «ሳይገባው።» (ቁ. 27።) «ሳይገባው» ማለት ቁርባን ተቀባዩ የማይገባ ሰው መሆኑ ሳይሆን ተቀባዩ በማይገባ አደራረግ በማይገባም መንፈስ ሲበላና ሲጠጣ ማለት ነው። ከብሩን ሳይለይ ጎብሰቱንና ጽዋውን እንደ ተራ መብልና እንደ ተራ መጠጥ የሚያደርግ ሰው ቁርባንን «ሳይገባ» (ያለ አግባብ) ተቀብሎአል።

ሰውዬው ራሱ ያልተገባ መሆኑ እይደለም። ብዙዎች ሰዎች በዚህ ቃል ተሰናክለው፡- «ይህን ቅዱስ ሥርዓት ለመቀበል የማይገባኝ ነኝ። የተቀበልሁት እንደሆነ ለራሴ ፍርድ አበጀለሁና ራሴን ሳላሻሽልና የሚገባኝ እሰከሆን ድረስ አልቀበልም» ብለው ከቁርባን ይቀራሉ። ይህ በፍጹም ስሕተት ነው። ቁርባንን ለመቀበል «የሚገባው» ማንም የለም፤ ይሁን እንጂ ቁርባን የተሠራው ለእነርሱ፥ ለማይገባቸው ሰዎች ነው። ይህን «ሳይገባው» የተባለውን ቃል የሚፈራ ሰው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፉትን የኢየሱስ ቃሎች ይስማ፡-

«ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያሰፈልጋቸውም፤ ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ እልመጣሁምና።» (ማር. 2፥17።)

«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁም የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችሀኋለሁ።» (ማቴ. 11፥28።)

እኛ ከማዕዱ በታች የወደቁትን ፍርፋሪዎች ለመሰብሰብ እንኳ የማይገባን ነንና በራሳችን ጽድቅ ወይም በራሳችን በጎነት ታምነን ወደ ጌታ ማዕድ ለመቅረብ አንደፍርም። እርሱ ግን ጠርቶናል (ጋብዞናል)፥ እኛም ጥሪውን ተቀብለን እርሱ ሥጋውንና ደሙን በመስጠት በሠራልን ሥራ ታምነን እንቀርባለን። ግብጥው የተሠራው ለኃጥአን ነውና እንቅረብ። (ዕብ. 4፥16።) ነገር ግን ስንቀርብ በማይገባ አደራረግ በማይገባም መንፈስ ቅዱሳን ምሥጢራት እንዳንቀበል እንጠንቀቅ።

መ/ «ራሱን ይፈትን።» (ቁ. 28።) «ሰው ራሱን እንደምን ይፈትናል?» ቢሉ፥ አንጥረኛ ወርቁን አንደሚያነጥር ነው። አንጥረኛ ፈትኖ ቆሻሻውን ሁሉ እስወግዶ ጥሩውን ወርቅ ያቀርባል። እንዲሁ ወደ ጌታ ማዕድ ለመቅረብ የሚያሰበው ሰው ራሱን ይፈትን። ልቡን መርምሮ ያደረገውን ኃጢአት ያስተውል ይዘንበትም። ቀጥሎም ደግሞ የሠራውን ኃጢአት ጠልቶ ኃጢአቱን ለመተውና ወደ አባቱ ለመመለስ ይቁረጥ። (ሉቃ. 15፥17-19።) ከዚያም በኋላ ወደ ቁርባን ሄዶ የክርስቶስን ሥጋ የሚያመለክተውን ጎብሰት በእምነት በመብላት የክርስቶስንም ደም ከሚያመለክተው ጽዋ በእምነት፥ በመጠጣት ኃጢአተኛ ሰውነቱን በክርስቶስ ሰውነት ያነጻ ነፍሱንም በከበረ ደሙ ይታጠብ። በማቴ. 7፥1 ላይ «እንዳይፈረድባችሁ በሌሎች ላይ አትፈረዱ» ተባለ። ይሁን እንጂ

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 12።

1፤ ስለ መንፈሳዊ ነገርም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ታውቁ ዘንድ 2፤ እወዳለሁ። አሕዛብ ሳላችሁ በማናቸውም ጊዜ እንደምትመሩ ድምፅ ወደሌላቸው ወደ ጣዖታት እንደ ተወሰዳችሁ 3፤ ታውቃላችሁ። ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር፥ - ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ፥ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር፥ - ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።

4፤ የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው 5፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፥ 6፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ አግዚአብሔር 7፤ ግን አንድ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ 8፤ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል። ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ 9፤ አምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም 10፤ ተአምራትን ማድረግ፥ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም 11፤ ይሰጠዋል፤ ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።

12፤ አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ 13፤ አካል እንደ ሆኑ፥ ከርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው፤ አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።

14፤ አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና። 15፤ እግር፥ - እኔ እጅ አይደለሁምና የአካል ከፍል አይደለሁም ብትል፥ ይህን በማለትዋ የአካል ከፍል መሆንዋ 16፤ ይቀራልን? ጆሮም፥ - እኔ ዓይን አይደለሁምና የአካል ክፍል አይደለሁም ቢል፥ ይህን በማለቱ የአካል ክፍል 17፤ መሆኑ ይቀራልን? አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን መሰማት ወዴት በተገኘ? ሁሉም መሰማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ? 18፤ አሁን ግን እግዚአብሔር እንደ ወደደ ብልቶችን እያንዳንዳቸው 19፤ በአካል አድርጎአል። ሁሉም አንድ ብልት ቢሆንስ 20፤ አካል ወዴት በሆነ? ዳሩ ግን አሁን ብልቶች ብዙዎች 21፤ ናቸው አካል ግን አንድ ነው። ዓይን እጅን፥ - አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም፥ ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን፥ - 22፤ አታስፈልጉኝም ሊላቸው አይችልም። ነገር ግን ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው፤ 23፤ ከአካልም ብልቶች ያልከበሩ ሆነው የሚመስሉን በሚበዛ ክብር እናለብሳቸዋለን፥ በምናፍርባቸውም ብልቶቻችን ከብር 24፤25፤ ይጨመርላቸዋል፤ ከብር ያላቸው ብልቶቻችን ግን ይህ አያስፈልጋቸውም። ነገር ግን ብልቶች አርስ በርሳቸው በትከክል ይተሳሰቡ ዘንድ እንጂ በአካል መለያየት እንዳይሆን፥ ለጎደለው ብልት የሚበልጥ ክብር እየሰጠ እግዚአብሔር 26፤ አካልን አገጣጠመው። አንድም ብልት ቢሣቀይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሣቀያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል።

27፤ አናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ አያንዳንዳችሁም 28፤ ብልቶች ናችሁ። እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን፥ አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም

ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት [29] ልሳኖችንም አድርጎአል። ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን? [30] ሁሉስ ተአምራትን ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ [31] አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ።

ደግሞም ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ አሳያችኋለሁ።

* * *
* * * * * *

4ኛ፤ ክፍል።

(ም. 12-ም. 14።) ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ።

ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች።

ም. 12፥ ስለ ስጦታዎች።

ም. 13፥ ስለ ፍቅር።

ም. 14፥ ስለ ልሳኖች።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት።

በዱሮ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል በአዲስ ኪዳን ተጽፎ ከመሰማቱ በፊት ልዩ ልዩ ምልክቶች በክርስቲያኖች ዘንድ ይታዩ ነበር። (ማር. 16፥20።) በዓለ ኃምሳ በተባለው ቀን መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ሁሉ ላይ ወረደ። (የሐዋ. 2፥1-4።) ከዚያም ቀን ጀምሮ ከርስቲያን ሁሉ ባለ መንፈስ ቅዱስ ሆኖአል። (ሮሜ. 8፥9፡14።)

ይሁን እንጂ በዚያ፥ ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ዘመን መንፈስ ቅዱስ በአንዳንዶች ሰዎች ላይ በልዩ ኃይል ይመጣ ነበር፥ በቆሮንቶስ ከነበሩትም ክርስቲያኖች መካከል እነዚህን ልዩ የሆኑትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የተቀበሉ ነበሩ። እነዚህን የጸጋ ስጦታዎች በመቀበላቸው ምክንያት እነኝህ ሰዎች ከቀሩት ክርስቲያኖች ሁሉ ተግ እሉ። (ደመቁ።) መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያንነታቸውን እትሞ ነበርና እነርሱ እንደ ዋና ክርስቲያኖች ተቆጥረዋል። ከስጦታዎቹ መካከል አንዱ በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ነበረ፥ ይህም ስጦታ እጅግ የሚያስደንቅ ነበረና በቆሮንቶስ ሰዎች ዘንድ በልሳን መናገር ከሁሉ ይልቅ ተወደደ፥ ይህንም ስጦታ ያገኙቱ በሌሎች ይከበርና ስጦታውንም በመቀበል ይኮሩ ነበር። የቀሩት ስጦታዎች ይህን ያህል አላስደነቁምና ክርስቲያኖቹ ዝቅተኖች አድርገዋቸው የተቀበሉአቸውን ሰዎች ናቁ፥ የተቀበሉአቸውም እነዚህን በመቀበል አልተደሰቱም።

ነገር ግን ክርስቲያኖቹ የተቸገሩበት አንድ ነገር ነበረ፥ እርሱም እነኝህ ሰዎች በልዩ ዓይነት ልሳኖች ሲናገሩ የሚናገሩት በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማወቅ ነው። ስለዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ መንፈሳዊ አባታቸው ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሲጽፉ የጠየቁት ሦስተኛ ጥያቄ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች፥ በተለይም በልዩ ዓይነት ልሳን ስለ መናገር ነገር ነበረ፤ ሐዋርያውም በም. 12 በም. 13 እና በም. 14 ላይ መልሱን ይሰጣል።

ቁ. 1-3። ሐዋርያው በም. 10፥1 ላይ እንደ ተናገረው እንዲሁም አሁን «ወንድሞች ሆይ፥ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ» ይላል። ጉዳዩ የቆሮንቶስ ከርስቲያኖች የሚናገሩት በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ወይም በሌላ መንፈስ ለመለየት ሲሆን ቁም ነገር ነውና እንዲያውቁት ያስፈልጋል።

እነርሱ ዱሮ አሕዛብ (አረማውያን) ሆነው ሳሉ ሳይጠይቁና ሳያስተውሉ እንዲያው በጣዖታት ካህናት እየተታለሉ ተማርከው ይሄዱ ነበር። አሁን ግን ከርስቲያኖች ሲሆኑ

እየተታለሉ ላይኖሩ በእውቀት መኖር ይገባቸዋል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንፈስና ከዲያብሎስ የሆነውን መንፈስ ሊለዩ ቢፈልጉ መንፈሱ ስለ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ያድምጡ። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያከብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያዋርድ ወይም የሚሰድብ መንፈስ ከዲያብሎስ ነው። በዚያ ዘመን «እገሌ ክርስቲያን ነው» ቢባል ወደ ዳኛ ይቀርብና ይመረመር ነበር። «ኢየሱስ ጌታ ነው» የሚለው ቃል ሰው በመርማሪ ዳኛ ፊት ቆሞ ክርስቶስን የካደበት ደንበኛ ቃል ነበረ። እንዲሁም ደግሞ «ኢየሱስ የተረገመ ነው» የሚለው ቃል ሰው ለመጠመቅ ቀርቦ በክርስቲያኖች ፊት ክርስቶስን ያመነበት ደንበኛ ቃል ነበረ። እነኚህም ሁለት ቃሎች እዚህ በቁ. 3 ላይ የተጠቀሱበት መለያ ነገሩ መንፈሱ ክርስቶስን ቢክድ ወይም ቢያምን መሆኑን ለማስረዳት ነው። ክርስቶስን የሚያከብር መንፈስ የእግዚአብሔር ክርስቶስን የሚያዋርድ መንፈስ ከሰይጣን ነው። (ማቴ. 12፥30። ሉቃ. 12፥8፡9።) ሐዋርያው ክርስቲያን «ኢየሱስ የተረገመ ነው» እንዲል በእውነቱ አያስብም፥ ይህን የሚሉት ያላመኑት አይሁድ ወይም ተቃዋሚዎች የሆኑት የጣዖታት ካህናት ብቻ ይሆናሉ፤ ጳውሎስ ግን እነዚህን ሁለት ቃሎች በመጥቀስ የተናጋሪውን ዝንባሌ ያመለክታል። መለያው ክርስቶስን ቢክድ ወይም በክርስቶስ ቢያምን ነው። (1 ዮሐ. 2፥1-3።)

ማስገንዘቢያ።

«ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።» (ቁ. 1።) የምናምነውን፥ ይህንም ደግሞ በምን ምክንያት እንደምናምነው ማወቅ ትልቅ ነገር ነው እኮ! እነዚያ የቆሮንቶስ ሰዎች ክርስቲያኖች ሳይሆኑ በፊት እንዲያው እየተመሩ ወደማይረባ ተወሰዱ። ክርስቲያኖች ሲሆኑ ግን ሐዋርያው «ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ» ይላቸዋል። ክርስቲያን ሁሉ እንዲያው በሌሎች ተመርቶ ሳይወሰድ የሚያምነውን፥ ይህን ደግሞ በምን ምክንያት እንደሚያምነው ማወቅ ይገባዋል። (1 ጴጥ. 3፥15።) ስለዚህ ክርስቲያኖች ያልሆኑትን ሳንመስል የሐዋርያውን ፈቃድ እየተገነዘብን ክርስቲያኖች የሆኑትን መስለን ሃይማኖታችንን እንወቀው።

ቁ. 4-11። በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ከመንፈላዊ ስጦታዎች አንዱ ብቻ ነበረ። በመንፈስ ቅዱስ በኩል በዚያ ዘመን ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡት የጸጋ ስጦታዎች ብዙና ልዩ ልዩም ነበሩ፤ ሆኖም ሁሉም በአንድነት የሚሠሩ ነበሩ። ስጦታዎቹ ልዩ ልዩ ቢሆኑም ሁሉም የተሰጡት በአንዱ መንፈስ ቅዱስ በኩል ነው፤ አገልግሎታቸው ልዩ ልዩ ቢሆንም ሁሉ የሚያገለግሉት አንዱን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፤ አሠራራቸው ልዩ ልዩ ቢሆንም ሁሉን የሚያደርግ በተቀባዮችም ሁሉ የሚሠራ አንዱ እግዚኢአብሔር ነው። የሥላሴ ስጦታዎች ናቸው። ወልድን ለሚያገለግሉቱ አብ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ይሰጣል። (ሮሜ. 5፥5።) ስጦታውንም ሁሉ ለእያንዳንዱ ሰው ሲሰጥ ለግል ሳይሆን ለጋራ፥ ለመላው ቤተ ክርስቲያን ጥቅም ነው።

ለእንዱ ሰው ጥበብን መናገር ይሰጠዋል፤ ማለት፥ በዚያ አስቸጋሪ ዘመን ለቤተ ክርስቲያን የሚሻለውን ለማስረዳትና በቤተ ክርስቲያን ሰም ሆኖ ለዳኞች ለመናገር ልዩ ጥበብ ይሰጠዋል። (ሉቃ.21፥12-15። የሐዋ. 6፥10።) ለሌላው እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፤ ማለት፥ ሃይማኖትን ጠልቆ ለማወቅና ለማስረዳት ምሥጢርንም ለመፍታት ልዩ እውቀት ይሰጠዋል። ለሌሳውም ተአምር የሚሠራበት እምነት (ማቴ. 17፥20። 1 ቆሮ. 13፥2። ዕብ. 11፥33፡34)፤ ለሌላውም ድውያንን መፈወስ (ማር. 16፥18።

የሐዋ. 3፥6፡7፥5፥12፡15፡16፤14፥9፡10፤19፥12)፤ ለሌላውም ልዩ ነገር ማድረግ እስኪችል ድረስ ተአምራትን ማድረግ (ማር. 16፥17፡18። የሐዋ. 5፥1-10፤13፥8-11፤28፥3-6። 2 ቆሮ. 11፥23-28)፤ ለሌላውም የእግዚአብሔርን ነገር በልዩ ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መናገር፤ ለሌላውም መናፍስትን መለየት (ስለምን? ቢሉ፥ ርኩሳን መናፍስት በሰው ውስጥ የገቡ እንደሆነ እንዳይታወቁ ይደበቃሉ። ሁለተኛ ደግሞ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና ሰው በምን መንፈስ እንደሚናገር እንዳንድ ጊዜ ያጠራጥራል። 2 ቆሮ. 11፥13፡14። 1 ዮሐ. 4፥1። የሐዋ. 16፥16-18)፤ ለሌላውም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፤ ለሌላውም ያን በልዩ ዓይነት ልሳን የተናገረውን መተርጎም። እነዚህ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው፥ እርሱም እንደ ፈቃዱ ለዚህ ክርስቲያንና ለዚያ ያካፍላል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር።» (ቁ. 10።) ይህ ስጦታ በዓለ ሃምሳ በተባለው ቀን ከተሰጠው ስጦታ ልዩ ነው። በዚያ በጰንጠቆስጤ ቀን «በሁሉም መንፈስ ቅዱስ መላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር» ተባለ። (የሐዋ. 2፥4።) ሆኖም እነዚያ ቋንቋዎች የታወቁ የውጭ አገር ቋንቋዎች ነበሩ። በሐዋ. 2፥5 ላይ «ከሰማይ በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ» እዚያ ተሰብስበው ኖሮ እያንዳንዱ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ነበርና ተገርመው «እኛ እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?» ብለው እንደ ጠየቁ እናነባለን። እነርሱ ከያገሩ የመጡ ሲሆኑ «ምእመናን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን» አሉ። (የሐዋ. 2፥16።) ስለዚህ እነዚያ የውጭ አገር ቋንቋዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን።

እዚህ ግን ለቆሮንቶስ ሰዎች የተሰጠው በሌላ ልላን መናገር ልዩ ይመስላል። እንደምን? ቢሉ፥ እንደ ተናጋሪው ሆኖ ልዩ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የተቀበለ ሰው ተገኝቶ የተነገረውን ቃል ባይተረጉም ለሚሆቹ ይቅሩና ተናጋሪው ራሱ የተናገረውን ነገር አንዳንድ ጊዜ አያስተውልም ነበር። (ም. 14፥2፡13፡27፡28።)

ሁለተኛ ደግሞ፥ የቆሮንቶስ ሰዎች አንድ ሰው እንደዚህ ሲናገር በእውነት መንፈስ ቅዱስን በልዩ ዓይነት እንደ ተቀበለ እንደ ዋና ማስረጃ ይቆጥሩት ነበር። በውጭ አገር ቋንቋ መናገር ግን ተናጋሪው መንፈስ ቅዱስን በልዩ ዓይነት እንደ ተቀበለ ማስረጃ መሆኑን የሚቆጥር የለም።

ስለዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች የተናገሩበት ቋንቋ የውጭ አገር ቋንቋ ላይሆን በዓለም ያልታወቀ መሆኑን እንረዳለን። ተናጋሪው በመንፈስ ተይዞ ይናገር ነበር፥ ይህንም በማድረግ አንዳንድ ጊዜ ማጎበሩን (ስብሰባውን) ያውክ ነበር። ሆኖም ተናጋሪዎቹ መንፈሳቸውን ሊገዙ እንደሚችሉ ሐዋርያው በም. 14፥27 ላይ አስረድቶአል። እንግዲህ ይህ ስጦታ የተሰጠው ምእመናንን ለማስተማር (ለማነጽ) ሳይሆን ያላመኑትን በማስደንገጥ ለማስጠንቀቅ ነው። (ም. 14፥22።)

ለ/ «ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ያደርጋል።» (ቁ. 11።) እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ አሳብ ወይም ነገር ወይም ደግሞ ኃይል ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ምልአተ አካል እንደ ሆነ እናያለን። የጸጋ ሰጦታን ለእያንዳንዱ የሚያካፍል እርሱ ነው። እርሱ የቤተ ክርስቲያን አለቃ ነውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ፈቃዱ ያደርጋል። አስፈላጊነትን ተገንዝቦ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ስጦታዎቹን እንደ ጥበቡና እንደ ፈቃዱ ያካፍላል። (ሮሜ 12፥3-8።) እንግዲህ ያን ስጦታ ሳይሰጠን ይህን በመሰጠቱ እናጉረምርም።

ቁ. 12-31። አሳቡን ለማስረዳት ሐዋርያው አሁን የአካልንና የብልቶችን ምሳሌ ያነሣል። የሰው አካል አንድ ሲሆን በዚያው በእንዱ አካል ውስጥ የሚገኙት ብልቶች ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚያ ብልቶች በአንድነት ሲጋጠሙና ሲያያዙ እርስ በርሳቸው አንድ አካል ናቸው። (ኤፌ. 4፥16።) ክርስቶስ እንደዚሁ ነው፤ ማለት፥ በአካልና በብልቶች ዘንድ እንደ ሆነ ሁሉ እንዲሁም በክርስቶስና በክርስቲያኖች ዘንድ ነው። በዚህ ክፍል በሙሉ ሐዋርያው ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን ያመሳስላል። (ኤፌ. 1፥22፡23።) ለምሳሌ፡- በቁ. 27 ላይ «እናንተ የክርስቶስ አካል ናቸሁ» ይልና ቀጥሎ «እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አድርጎአል» ይላል። ሰው ሁሉ በተጠመቀ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ይጨመራልና (ም. 1፥13 ማሰገንዘቢያ) ሁላችንም በጥምቀት ወደ አንዱ አካል ተጨምረናል። የማንኛውም አገር ሰዎች ብንሆን፥ ሁኔታችንና ሕዝባዊ አኳኋናችንም ምንም ዓይነት ቢሆን እኛ ሁላችን አንድ አካል እንሆን ዘንድ በዚያው በአንዱ መንፈስ ቅዱስ ተጠምቀናል፥ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጣችን ተቀብለናል። (ዮሐ. 6፥53። ም. 3፥16።) ሁላችንም በአንዱ አካል ውስጥ ነንና በመካከላችን ልዩነት የለም፤ በክርስቶስ ሆነን ሁላችንም አንድ ነን። (ገላ. 3፥27፡28።) (ስለ አካልና ስለ ብልቶች በኤፌ.ም.4 ውስጥ ደግሞ እናነባለን።)

አሁንም ደግሞ ከቁ. 14-26 ድረስ ሐዋርያው ስለ ሰው አካልና ስለ ብልቶቹ ይናገራል። አካል አንድ ብልት ብቻ ሊሆን አይችልምና በአንዱ አካል ውስጥ ብዙ ብልቶች የግድ ይገኛሉ፥ አካልንም የሚሠሩ እነኝህ ልዩ ልዩ የሆኑት ብልቶች ናቸው።

በአንድ ወገን (ቁ. 15-20) አነስ ያለ ብልት ራሱን ከሌላው ጋር አመዘዝኖ «እኔ እንደ እርሱ አይደለሁም፥ እርሱ የተቀበለውን ስጦታ እኔ አልተቀበልሁም፥ ስለዚህ የአካል ብልት አይደለሁም» ማለት አይገባውም። ይህስ ቢሆንና በአካል ውስጥ የሚገኙት ብልቶች ሁሉ አንድ ዓይነት ቢሆኑ ኖሮ አካሉ ጎደሎ ይሆን ነበር። ብልቶቹ በአካል ውስጥ የተገኙት እግዚአብሔር አንደ ወደደ ቢያኖራቸው ነው እንጂ እንዲያው የተገኙ አይደለም፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነ በቀር አንድም በቦታው አልተገኘምና ከብልቶቹ አንድም በማነሱ አይዘን፥ በአካሉ መሆኑንም አይጠራጠር።

በሌላ ወገን ደግሞ (ቁ. 21-26) የከበረ ብልት በተቀበለው ስጦታ ተመክቶ አነስ ያለውን «አታስፈልገኝም» ሊል አይችልም።

ከአካሉ ብልቶች የማያስፈልገው የትኛው ነው? ሉረ ሁሉም አስፈላጊ ናቸው! ደካሞችና ጎደሎዎች፥ ያልከበሩም የሚመስሉን እንኳ ሁሉም የሚያስፈልጉ ናቸው፥ እኛም እነዚህን የምናፍርባቸውን ብልቶች ልብስ በማልበስ ተጨማሪ ክብር እንሰጣቸዋለን። ይህም ትክክለኛ ድልድል እግዚአብሔር የፈቀደው ነገር ነው። በብልቶቹ መካከል የእርስ በእርስ መተሳሰብ እንጂ መለያየት እንዳይሆን እግዚአብሔር ለደካማው

ብልት የበለጠ ክብር በመስጠት ሚዛኑን ጠብቆአል። አንዱ ብልት በማነሱ ምክንያት «የአካል ክፍል አይደለሁም» እንዳይል፥ ብርቱውም ብልት ደካማውን እንዳይንቅ፥ እግዚአብሔር የአካሉን ብልቶች ሁሉ አስተካክሎአል። ስለዚህ አሁን በአካላችን ውስጥ ከሁሉ ታናሽ የሆነው ብልት ስንኳ ቢሣቀይ ሥቃዩ ለሁሉም ይሰማል፥ አንዱም ቢከብር ክብሩ ለሁሉም ይሰማል። ቤተ ክርስቲያኒቱ አባልዎችዋ (ሕዋሳትዋ) የተዋደዱ የተሰማሙ ሕያው አካል ናትና።

እንደዚህ ምሳሌ ሁሉ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድ የክርስቶስ አካል ናት፥ ማኅበርተኞችዋ ብልቶችዋ ናቸው። በምሳሌው እግዚአብሔር እንደ ወደደ ብልቶችን እያንዳንዳቸውን በአካል እንዳደረገ (ቁ. 18) እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ልዩ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች አድርጎአል። (ቁ. 28።) በምሳሌውም ብልቶች ሁሉ አንድ እንዳልሆኑ (ቁ. 17፡19) እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሆኑት ሁሉ አንድ ዓይነት አልነበሩም። (ቁ. 29፡30።) በመካከላቸው ልዩነት ነበር፥ ይህም ልዩነት ተገቢ ነበረ።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በልዩ ዓይነት ልሳን እንደ መናገር ያለ አስደናቂ የሆኑትን ስጦታዎች ከመጠን በላይ ያከብሩና ለማግኘት ይመኙ ነበርና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሁሉም ዝቅ ያሉቱ እንኳ አስፈላጊ እንደ ሆኑ አሰረድቶአል። ይሁንና እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል በበለጠ መጠን እንዲሠራ፥ እነርሱም ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ እንዲጠቅሙ፥ የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ይፈልጉ። ሆኖም ከሁሉም ላኑት እንኳ የሚሰጥ ከዚያ ስጦታ ሁሉ የሚበልጥ አንድ ስጦታ አለና ሐዋርያው አሁን በም. 13 ላይ ስለ ፍቅር ይናገራል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው።» (ቁ. 12።) በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ሰው አካልና ስለ ብልቶቹ የተባለው ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ማኅበርተኞችዋ ይተረጎማል። በአካሉ ውስጥ ስሚገኝ ለእያንዳንዱ ብልት የአካልን ሥራ ለመሥራት የገል ስጦታ (ችሎታ) እንደሚሰጠው ሁሉ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ማኅበርተኛ እግዚአብሔር ስጦታውን ይሰጣል። የብልቶች ስጦታ ልዩ ልዩ እንደ ሆነ ሁሉ እንዲሁም የማኅበርተኞች ስጦታ ልዩ ልዩ ነውና ያን አንዱን ሥራ ለመሥራት ስሁሉም አልተሰጠም። ይህም ለአካል ሆነ ለቤተ ክርስቲያንም የግድ አስፈላጊ ነገር ነው። ብልት ሁሉ የተመደበለትን ሥራ እንዲሠራ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የግል ስጦታ (ችሎታ) መርጦ ሰጥቶአል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ 1ኛ ሐዋርያትን 2ኛ ነቢያትን፥ 3ኛ አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ አርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዕይነት ልሳኖችንም አድርጎአል። ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ እንደ ሆነ መጠን እግዚአብሔር ራሱ መርጦ ሰጥቶአል፥ ገናም ዛሬ መርጦ ይሰጣል። ስልዚህ የቤተ ክርስቲያን ብልቶች የሆንን ሁሉ የተቀበልነው ስጦታ ማንኛውም ቢሆን እርሱ ይብቃን፥ በዚያም ስጦታ አካልን (ቤተ ክርስቲያንን) በሙሉ ለመጥቀም እንትጋ። (ሮሜ 12፥3-8።)

ለ/ «እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።» (ቁ. 13።) ወደ አንዱ አካል ውስጥ የሚያጠምቀን መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እናስተውል። ይህን ሊያደርግ የሚችል ቁስም ሆነ ውኃ የለም። ይህን ሊያደርግ የሚችል መንፈስ ቅዱስ

ብቻ ነው። (ማቴ. 3፥11።) ሰው በወልድ ሲያምን በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ ያጠምቀዋል።

ሁለተኛ ደግሞ፥ መንፈስ ቅዱስ የያገሩን ሁሉ ምእመናን ወደ አንዱ አካል ውስጥ እንደሚያጠምቅ አስተውለን በእኛና በውጭ አገር ክርስቲያኖች መካከል ልዩነት ግድረግን እንተው።

ሦስተኛም፥ እኛ የምንጠመቅበት የውኃ ጥምቀት የዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምሥጢርና ምልክት መሆኑን እንወቅ። ያ የዚህ ምላሌ ነው።

ሐ/ «ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው።» (ቁ. 22።) እንዲህ ያሉ ሰዎች በየቤተ ክርስቲያኑ ይገኛሉ። የዋሆች ሆነው ሥራ ሲሠሩ እይታዩም። በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሌሎች አንዳንዶች የበረቱ ሲሆኑ እነኝህ ምንም የሚችሉ አይመስሉም። ደካሞች ናቸው፥ በልብላቸውና በንግግራቸው በሞኝነታቸውም እንሥቃለን። እነርሱም ምናልባት በደካማነታቸው አዝነውና አፍረው በውነቱ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ይጠራጠሩ ይሆናል።

ይሁንና ሐዋርያው ስለ እነዚህ ሰዎች ያለውን እንስማ። እነኝህን ሰዎች በእካሉ ውስጥ ያደረጋቸው እግዚአብሔር ራሱ ነው። (ቁ. 18።) ተጨማሪ ትርፎች ሳይሆኑ «ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው።» (ቁ. 22።) እነኝህ ሰዎች በማኅበራችን ውስጥ የሚጸልዩ ናቸው፥ በመንፈስና በእውነትም የሚሰግዱ ናቸው። (ዮሐ. 4፥21-24።) እንደ ክንድና እንደ ቅልጥም የሚመስሉት ብርቱዎች ቢቆረጡብን፥ ግድ የለም፥ እነርሱ ባይኖሩ እንኳ አካሉ ገና በሕይወት ይኖራል። ነገር ግን እንደ ልብና እንደ ሳምባ የሚመስሉት የማይታዩ ደካሞች ቢቆረጡ ጉዳቱ ምንኛ ታላቅ ነው! ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደካሞች የሚመስሉትን ሳንንቅ በበለጠ ክብር እናክብራቸው።

መ/ «እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን ... አድርጎአል።» (ቁ. 28።) እግዚአብሔር የክርስቶስ አካል በሆነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ልዩ ሰዎችን አኑሮአል፥ ልዩ ልዩ ስጦታዎችንም ሰጥቶአል። ሰዎቹ ቦታ ቦታቸውን ሳይመርጡ እግዚአብሔር እንደ ወደደ አኑሮአቸዋል። በተራው ውስጥ ለአስተማሪዎች የተሰጠውን ከፍ ያለውን ግዕረግ እንገንዘብ። ክቅሬ 8-10 ድረስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲዘረዘሩ መጀመሪያና ሁለተኛ የተጠቀሱት የመናገር ስጦታዎች ናቸው! እዚህም ደግሞ በቁ. 28 ላይ በቤተ ክርስቲያን የሚያስተምሩት ሰዎች ተአምራት ከሚያደርጉትና የመፈወስ ስጦታ ካላቸው፥ በልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችም ከሚናገሩት በላይ ቆመዋል። ይህ ነገር ለዘመናችን የሚያሳስብ ነው። በዱሮ ዘመን በቤተ ክርስቲያናችን እንደ ነበሩት ያሉ አስተማሪዎች ዛሬ የት አሉ? ካህናትና የሚያስተምሩ ብዙ ሊቃውንት ሲኖሩልን ሕዝብን የሚያስተምሩ የቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎች የት ናቸው? በዱሮ ታሪካችን ላይ የእነዚያን ዝና እንሰማለን፤ በቤተ ክርስቲያን በማስተማሩ ምክንያት ዝናው በታሪክ ላይ የሚቆይ ዛሬ ማን ነው?

«እርዳታንም» የተባለው ምን ማለት ነው? ቢሉ፥ ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት የተሰጠ ችሎታ ነው። ይህን ስጦታ የተቀበሉ ምእመናን በሐዋ. ም. 6 ላይ እንደ ተጻፈላቸው ግዕድ በግልገል የሚረዱ ይሆናሉ፥ ወይም ደግሞ በሐዋ. 20፥35 ላይ እንደ ተተረከላቸው ድውዮችን የሚረዱ ይሆናሉ። እነኝህ የቤተ ክርስቲያንን ገቢና ወጪ

ሊጠብቁ፥ የቤተ ክርስቲያንን ልዩ ስብሰባዎች ሊያደራጁ፥ የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕናና ውበት ሊጠብቁ የሚችሉ ናቸው፥ እነኝህም ከገንዘባቸው በመስጠት ቤተ ክርስቲያንን የሚረዱ ናቸው። ይህ ስጦታ በእውነት ታላቅ ስጦታ ነው።

«አገዛዝንም» የተባለውስ ምን ማለት ነው? ቢሉ፥ ጳውሎስ በጻፈው በግሪክ ቋንቋ ቃሉ መርከብን መምራት ማለት ነውና ይህን ስጦታ የተቀበሉ ሰዎች በ1 ጢሞ. 5፥17 ላይ እንደ ተጻፈላቸው «በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች» ይሆኑ ይሆናል። የመንፈላዊ መሪነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ናቸው። እነኝህም በቤተ ክርስቲያን ሲፕኙ ዋጋቸው እጅግ የከበረ ነው።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 13።

1፤ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም
እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ። 2፤ ትንቢትም ቢኖረኝ፥ ምሥጢርንም ሁሉና
እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ 3፤ ቢኖረኝ ፍቅር
ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ደሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት
መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።

4፤ ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ 5፤ ፍቅር አይመካም፥
አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም 6፤ አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥
በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ 7፤
ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።

8፤ ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ
ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል። 9፤ ከዕውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም
ከፍለን እንናገራለንና፤ 10፤ በፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል። 11፤
ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፥ እንደ ልጅም አስብ ነበር፥ እንደ ልጅም እቆጥር
ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን 12፤ የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ። ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ
እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዮ አውቃለሁ
በዚያን ጊዜ ግን 13፤ እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ። እንዲህም ከሆነ፥ እምነት
ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ አሥራ ሦስት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ሲናገር ቆይቶአል። የቆሮንቶስ
ከርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ በኩል ከእግዚአብሔር ዘንድ በተቀበሉት ስጦታዎች
እየተመኩ አስደንጋጭ የሆነውን የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖች ስጦታ በተለይ አከብረውት
ነበር። ሐዋርያው ግን በም. 12 ላይ እነዚህን ስጦታዎች ሲዘረዝር ይህንኑ የልሳኖችን
ስጦታ ሁለት ጊዜ በመጨረሻ ላይ ጽፎአል። (ም. 12፥10፡28።) አሁንም ከእነዚያ
ስጦታዎች ሁሉ ስለሚበልጥ ነገር በም. 13 ላይ ይናገራል። ለኑሮአችንና ለሥራችን
የሚሆን ከሁሉም የሚበልጥ መንገድ ሊያሳየን ነው። (ም. 12፥31።)

ቁ. 1-3። የቆሮንቶስ ከርስቲያኖች በተቀበሉት ስጦታዎች ሲመኩ ሐዋርያው «ፍቅር
ከሌላችሁ እነኝህ ስጦታዎች ምንም አይጠቅሙም» ይላቸዋል። የሚናገሩበት ልሳን
የመላእክት ቢሆን እንኳ የሚናገሩበት በፍቅር መንፈስ ካልሆነ በልሳን መናገራቸው ከንቱ
መቅጨልጨል ብቻ ሆኖአል። ወይም ምናልባት በም. 12 8-10 ላይ እንደ ተዘረዘረው
ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ሌላ ስጦታ ተቀብለው ትንቢት ቢናገሩ፥ ምሥጢርን ሁሉ
ለመፍታት እውቀት፥ ወይም ተራሮችን የሚያፈልሱበት እምነት ቢኖራቸው ፍቅር
ከሌላቸው ከንቱዎች ናቸው። በመንፈሳዊ ስጦታዎችም ዘንድ እንደ ሆነ ሁሉ እንዲሁም
በምግባራችን ዘንድ ነው። ሰውን ወድደን ጥሪታችንን ሁሉ ብንመጸውት፥
እግዚአብሔርንም ወድደን እንደ ዳንኤል ባልንጀሮች ሆነን ሥጋችንን ለእሳት መቃጠል
አሳልፈን ሰጥተን (ዳን. 3፥16-21፡28) ሰማዕታት እንኳ ብንሆን ፍቅር ግን ከሌለን
ምንም አይጠቅመንም።

ማስገንዘቢያ።

«ምንም አይጠቅመኝም።» (ቁ. 3።) ይህ ቃል ምንኛ ያስደነግጣል! ያለኝን ሁሉ
ለድሆች ባካፍል፥ ሥጋዮን ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ሰጥቼ ሰማዕት እንኳ ብሆን ፍቅር
ግን ከሌለኝ ያ ሁሉ በእውኑ አይጠቅመኝምን? ሐዋርያው «ምንም አይጠቅምም» ይላል።
እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል? (ማቴ. 19፥25፡26።) ይህም ከሆነ ከእነዚያ ስጦታዎች
ሁሉ ፍቅር ምንኛ ይበልጣል! ፍቅር ከሌለ ምግባር ሁሉ የማይጠቅም መሆኑን
እናስተውል።

ቁ. 4-7። ፍቅርስ ምንድር ነው? ዛፍ ከፍሬው እንደሚታወቅ (ሉቃ. 6፥43፡44)
እንዲሁ ፍቅር ከሥራው ይታወቃል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ባለ ብዙ ስጦታዎች
ቢሆኑም በመካከላቸው ትዕቢትና ከርከር መላያየትና ዝሙት ትምክህትም ተገኝተዋል።
ስጦታ አላቸው፥ ፍቅር ግን እርስ በርሳቸው የላቸውም፥ በዚህም ምክንያት፥ ጳውሎስ
አሁን የፍቅርን ሥራዎች ሲገልጥ እግዚአብሔርን ስለ ማፍቀር ሳይናገር ባልንጀራን ስለ
ማፍቀር ብቻ ይናገራል።

የፍቅር ሥራ እንዴት ነው? ቢሉ፥ ሰው ሲቃወም ፍቅር ይታገሣል በከፉውም ፋንታ
ቸርነት ያደርጋል (ሉቃ. 6፥27)፥ ሌሎች ሲበልጡንና እኛ ከተቀበልነው ይልቅ እነርሱ
የተሻለውን ስጦታ ሲቀበሉ ፍቅር አይቀርም፥ በተቃራኒው ደግሞ እኛ ሌሎችን
ስንበልጥና እነርሱ ከተቀበሉት ይልቅ እኛ የተሻለውን ስጦታ ስንቀበል ፍቅር እይመካም፥
እውቀት ቢኖረን እንኳ ፍቅር እይታበይም (ም. 8፥1)፥ በብልግና አያስቀይምም፥

ሁልጊዜ የራሱን ፈቃድ ለማግኘት የግድ እደልም፡ ቁርፍታም እደሆንም፡ ሰው ቢያጠፋ ፍቅር እግዚአብሔርን መስሎ በደልን እደቆጥርም ቂምም እደዝም (2 ቆሮ. 5፡19)፡ እውነት ደስ ሲለው ሲጸድቅም ፍቅር አብሮት ደስ ይለዋል እንጂ ፍቅር ስለ ዓመፃ ወይም ስለሌላ ሰው ሃዘን ደስ እደለውም (ኢሳ. 59፡14)፡ ፈተና ወይም ስድብ መከራም እንደ ነርፍ ሲመጣ ፍቅር እንደ አምባ ሆኖ ሁሉን ይታገላል (ም. 9፡12)፡ ከፍቅርም እምነትና ተስፋ ሁለቱም ይመነጫሉ (1 ዮሐ. 4፡18። ሮሜ. 5፡5)፡ ፍቅርም ስለ በደለና ስለ ተከሰሰ ስለ ታማሚ ሰው የሚሻለውን መልካም ነገር ሁሉ ያምናል ይናገራልም፡ የእግዚኢአብሔርንም ጸጋ ተመልከቶ «ቢወድቅ ይነሣል» ብሎ የዚያ ሰው ፍጻሜ መልካም እንዲሆን ተስፋ ያደርጋል (ሚክ. 7፡8)፡ ላይደነግጥና እጁንም ሳይሰጥ በክፉው ቀን ሁሉን ፈጽሞ ጸንቶ ይቆማል። (ኤፌ. 6፡13።)

ግለገንዘቢያ።

ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ ላይ የሚናገረው ፍቅር እግዚአብሔር የሚያፈቅረው ፍቅር ነው። ይህ እውነተኛ ፍቅር ነው። ሰው ሁሉ ፍቅር ይኖረዋል፡ ይህ ፍቅር ግን በኃጢአት ምክንያት ስለ ረከሰ እውነተኛ ፍቅር አይደለም። እውነተኛ ፍቅር ምን እንደ ሆነ ልናውቅ ብንፈልግ አግዚአብሔርን የግድ እንመለከታለን። «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» ተባለ 1ኛዮሐ. 4፡8፡16) ፍቅርም ከእግዚአብሔር ነው። (1 ዮሐ. 4፡7።) ከርስቲያን ሁሉ ይህ ፍቅር ሊኖረው ይገባዋል።

ፍቅር እንደ እምነት ሆኖ በሥራው እንጂ እርሱ ራሱ አይታይም፡ ያለ እንደ ሆነ እንዲያው አይታወቅም። (ያዕ. 2፡18።) ከሥራ የተለየም ፍቅር የሞተ ነው። (ያዕ. 2፡26።) ስለዚህ ከቁ. 4 እስከ 7 ድረስ የተጻፉት የፍቅር ሥራዎች ወይም የፍቅር መግለጫዎች ናቸው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተገኙት ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር የሚያደርጋቸው ነገሮች ናቸው። እግዚአብሔር እንደዚህ ያደርጋል እኛም የእግዚአብሔር ከሆንን እንደዚህ ማድረግ ይገባናል። እውነተኛ ፍቅር እንደዚህ ያደርጋል፡ እኛም ፍቅር ቢኖረን እንደዚህ እናደርጋለን። እውነተኛ ፍቅር አለንን? የምናወቀው አነኛህ የፍቅር መግለጫዎች ቢታዩብን ነው። እስቲ፡ ራሳችንን እንፈትን። ሰው ከፉ ሲሠራብን ከፉውን ታግሠን ቸርነት እናደርግለታለንን? እናደርግ እንደሆነ ፍቅር አለን፡ እናደርግ እንደሆነም ፍቅር የለንም። ሌላ ሰው በማዕረጉ፡ በችሎታው፡ በንብረቱ፡ በትምህርቱ፡በሥራው፡ በመልካም ሰሙ ሲበልጠን እንቀናበታለንን? እንቀና እንደሆነ ፍቅር የለንም። ወይም ምናልባት የበላይ እኛ ስንሆን ከሌሎች በአንዳች ነገር ብንሻል እነርሱንም ብንበልጥ እንመካለንን? እንመካ እንደሆነ ፍቅር የለንም። በእውቀታችን እንታበያለንን? እንግዲህ ፍቅር የለንም። ሰው ባልተመቹ ሰዓት ምናልባት ቢመጣብን በደግነትና በሥነ ሥርዓት እንቀበለዋለንን፡ ወይስ በማይገባ በችኮላና በንዴት መንፈስ እንቀበለዋለን? የማይገባውን ብናደርግ ፍቅር የለንም። ጌቶች ለመሆን ወድደን የራሳችንን ፈቃድ ያላገኘን እንደሆን እናኮርፋለንን? እንግዲህ ፍቅር የለንም። በትንሽ ነገር ተበሳጭተን እንናደዳለንን? ሰው እኛን ሲበድል ወይም ሌላውን እንደ በደለ ስንሰማ በደሉን አጥብቀን እንቆጥርበታለንን? (ማቴ. 18፡21-35)። እንግዲህ ፍቅር የለንም። አብዝተን የምንወደው የትኛው ነው፡ እውነትን ነውን ወይስ ዓመፃን? ጋዜጣ ስናነብ በተለይ ስለ ግፍና ስለ ዓመፃ ልናነብ እንወዳለንን? ወደ ሲኒማ ቤት የሄድን እንደሆነ በተለይ የምንወደው በደልና ግፍ፡ ነፍስ መግደልና ምንዝርነት የሞላበት ፊልም ነውን? (ለመሆኑ፡ ወደ ሲኒማ ቤት የሚሄደው

ሰው እውነትን ፈላጊ ነውን?) በመጥፎ ደስ ይለን እንደሆነ ፍቅር የለንም። በእንዲህ ያለ ነገር ፍቅር ይታወቃል። አንድ ሰው በኃጢአት ወይም በመከራ እንደ ወደቀ የሰማን እንደሆነ ነገሩን ለመሸፈን እንሞክራለንን፡ ወይስ ለሰው ሁሉ እናወራዋለን? (1 ጴጥ. 4፡8።) በዚህ ሁሉ ፍቅራችን ይፈተናል። ስለ ሰውስ ሁሉ የተሻለውን እናምናለንን፡ ወይስ በላዩ ጥርጥር ሁልጊዜ አንጥላለን? ሰውም ሲወድቅ ደግሞ፡ አንደ ገና ልናቀናው እናስባለንን፡ ወይስ በጭቃ ውስጥ አንረግጠዋለን? (ገላ. 6፡1።) ሐሜትስ? በእኛ ዘንድ መኖሪያውን ያደርጋልን? በየጊዜው ሁሉ እርዳታችንን እናስቀራለንን፡ ወይስ በምናደርገው በጎነት ሁሉ አንጸናለን?

በዚህ ሁሉ ነገር እውነተኛ ፍቅር ያለን እንደሆንና የሌለን እንደሆነ ራሳችንን ልንፈትን እንችለለን። ይህ ከሁሉ የሚበልጠው ፍቅር አኔ አለኝን? የሌለኝ አንደሆነ ብዙ ስጦታ ቢኖረኝ እንኳ ከንቱ ነኝ። (ቁ. 2።)

ቁ. 8-13። ከእነዚያ ስጦታዎች ሁሉ ፍቅር የሚበልጠው ለዘወትር የማይወድቅ በመሆኑ ነው። የቆሮንቶስ ሰዎች በእነዚያ ስጦታዎች ይመኩ ነበር፡ እነዚያ ስጦታዎች ግን፡ ትንቢት፡ ልሳኖች፡ እውቀት፡ አላፊዎች ናቸው፡ ይሻራሉ ይቀራሉም። በፍጻሜው ላይ (ቁ. 10። 1 ዮሐ. 3፡2) እኛ በመንግሥተ ሰማያት ስንቆም ለትንቢትና በልሳኖች ለመናገር በዚህ ዓለም ላይ በስንት ችግር ላጠራቀምነውም እውቀት ሰፍራ አይኖርም፡ ለፍቅር ግን ሰፍራ ለዘላለም ይኖራል።

በእሁኑ ዘመናችን የተፈጸመ ነገር የለም። በእኛ ዘንድ ዛሬ ሁሉም በከፊል ነው። እውቀት ያለን ይመስለናል፡ እውቀታችን ግን በከፊል ብቻ ነው። (ም. 8፡2።) ይህ የልጅነት ጊዜ ነው፡ የጎልማሳነት አይደለም። ከእውቀት ከፍለን እናውቃለን ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለን። አግዚአብሔር ዛሬ ሁሉንም አይገልጥልንም። ነቢያት ብዙ ጊዜ የተናገሩትን ነገር አላስተዋሉም ትንቢታቸውም በመጪው ዘመን እንዴት እንደሚተረትም አላወቁም። ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ፍጹም ያልሆነው (ተከፍሎ የነበረው) ይሻራል። አዲስ ዘመን ሲመጣ ከዱሮ ዘመን የሆነው ሁሉ ያልፋል። ሐዋርያውም ይህን ነገር እስቅድሞ በልጅ አድገት ከዚያም በኋላ በመስተዋት ይመስለዋል። ሰው ገና ልጅ ላለ እንደ ልጅ ሆኖ ይናገርና ያስብ መርምሮም ይህ ነው ብሎ ይቆጥራል። ሙሉ ሰው ሲሆን ግን ያ ከፍሉ ያወቀውና በልጅነቱ ዘመን የወደደው ሁሉ ይሻራል። አሁን ሙሉ ለው ነውና የልጅነቱ ነገሮች የማያስፈልጉ ናቸው። ለዚያ ለልጅነቱ ዘመን ደኅና ነበሩ፡ ለዛሬ ግን አያስፈልጉም። በእነዚያም ስጦታዎች ዘንድ እንደዚሁ ነው፡ ያልፋሉ። ወይም ደግሞ በመስተዋት ማየትን ፊት ለፊት ከማየት ጋር ብናመዛዝን፡ መስተዋት ለጊዜው ግለፊያ ነው ዛሬም ይጠቅማል። በድንግዝግዝታ (በከፊል) ይሁን እንጂ (በሐዋርያው ዘመን የተገኙ በተወለወለ ብረት የተሠሩ መስተዋቶች በግልጥ አያላዩም ነበርና) ፊትን ያላያል። ሆኖም ሰው በጭጋግ በኩል እንደሚያይ ነው። ፊት ለፊት ማየት ግን ሲመጣ መስተዋቱ ምን ያስፈልጋል? (ዘኍል. 12፡8።) አያስፈልግምና ይቀራል። እነዚያም ስጦታዎች እንደዚሁ ናቸው። ዛሬ እውቀትን አናጠራቅማለን እንጂ እውቀታችን ፍጹም አይደለም፡ ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን በዚያን ጊዜ በፍጹም አውቃለሁ። እንግዲህ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይሻራሉ ይቀራሉም፤ የሚቆዩና የሚናሩ ግን ሦስት ነገሮች አሉ፡ እነዚህም በሮሜ 5፡2-5። ገላ. 5፡5፡6።

ቆላ. 1፥4፥5። 1 ተሰ. 1፥3፤ 5፥8። ዕብ. 6፥10-12። 1 ጴጥ. 1፥21፥22 ላይ በአንድነት ተጽፈው የሚኖሩ እምነት ተስፋ ፍቅርም ናቸው።

እምነት ክርስቲያን በሕይወት የሚኖርበት (ሮሜ. 1፥17) መሠረታዊ ነገር ነው።

ተስፋ በክርስቲያን ሁሉ ዘንድ መገኘት የሚገባው ዋና የክርስቲያን ሀብት ነው። (1 ጴጥ. 1፥3። ቲቶ. 2፥13። ቆላ. 1፥27።)

ፍቅር የእምነትና የተስፋ የሁሉም ምንጭ ሆኖ (ቁ. 7) የሁሉም ማሰሪያ ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎች ሲሻሩ ሲቀሩም እነኝህ ሦስት ነገሮች ይቆያሉ ይኖራሉም። ስለዚህ ከሁሉም የሚበልጥ መንገድ ይዘን (ም. 12፥31) ፍቅርን እንከታተል። (ም. 14፥1።)

ማስገንዘቢያ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የተናገረው ፍቅር ምንድር ነው? ሰው ሁሉ ይወዳል፤ ልጆቹን ይወዳል፥ ሚስቱን ይወዳል፥ አገሩን ይወዳል፥ ሌላንም ብዙ ነገር ይወዳል። ሐዋርያው የተናገረው ፍቅር ይህ ነውን? ይህ ከሆነ ሁላችን አለንና ምን ያጠራጥራል? ነገር ግን ይህ አይደለም። ጳውሎስ የሚናገረው ፍቅር እግዚአብሔር እኛን የሚያፈቅርበት ፍቅር ነው። (1 ዮሐ. 4፥16። ዮሐ. 15፥13። ሮሜ 5፥6-8። 1 ዮሐ.2 3፥1፥16።) እኛ እግዚአብሔርን ልናፈቅርበት የሚገባን ፍቅር ነው። (ዘዳግ. 6፥5።) ጌታ ከጴጥሮስ ዘንድ ለማግኘት ያሰበው ፍቅር ነው። (ዮሐ. 21፥15፥16።) በማቴ.ም. 5 ላይ የተጻፉትን ትእዛዛት የምንፈጽምበት ፍቅር ነው። (ማቴ. 5፥38-48።) የተፈጥሮ ፍቅር አለ፥ የእግዚአብሔርም ፍቅር አለ። ሰው ሁሉ ያለው የሰው ፍቅር አለ፥ አንዳንዶች ክርስቲያኖች ያፓኙትም ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር አለ። ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ሁሉ የሚበልጠው ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ ሥራውንም ከቁ. 4 እስከ 7 ድረስ እይተናል። ጳውሎስ ተከታተሉት ይላል (ም. 14፥1)፥ ነገር ግን እንዴት እንደምናገኘው በዚህ ቦታ አልገለጠልንም።

ይህን ፍቅር እንዴት እናገኘዋለን? ቢሉ፥ ይህ ፍቅር እንደ አነዚያ መንፈሳዊ ስጦታዎች ሆኖ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፥ የሚሰጠውም የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑት ብቻ ነው። እግዚአብሔር እነዚያን ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ በኩል እንደሚሰጥ እንዲሁም ይህን በመንፈስ ቅዱስ ይሰጠዋል። (ገላ. 5፥22። ሮሜ. 5፥5።) ሆኖም አነዚያን ለጥቂቶች ብቻ መስጠት ሲፈቅድ ፍቅርን ለልጆቹ ሁሉ መስጠት ይፈቅዳል። ፍቅር በዋጋ የሚገዛ ወይም እንዲያው ከባሕሪአችን የሚመነጭ ወይም በመታገል የሚኖ እይደለም። የምናገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ በመቀበል ብቻ ነው። ስጦታ ነው። የእግዚአብሔርን ፍቅር ያላገኘ ግንም ሰው በማቴ. 5፥38-48 እና በ1 ቆሮ. 13፥4-7 ላይ የተጻፉትን ነገሮች ሊፈጽም አይችልም። የሚፈጸሙት በእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ ነው። ይህንም ፍቅር ያላመኑት ሳይሆን ክርስቲያኖች ይከታተሉት ዘንድ ሐዋርያው መክሮአል፥ (ም. 12፥31፤ 14፥1) እኛንም ይመክረናል፤ የምንከታተለውም እንድንደርስበት ነው።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 14።

1፤ ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም 2፤ ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ። በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፥ 3፤ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል። 4፤ በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር 5፤ ግን ማኅበሩን ያንጻል። ሁላችሁ በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር፥ ትንቢትን ልትናገሩ ግን ከዚህ ይልቅ እወዳለሁ፤ ማኅበሩ ይታነጽ ዘንድ ንግግሩን ባይተረጉም በልሳኖች ከሚናገር ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል።

6፤ አሁን ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ መጥቼ በልሳኖች ብናገር፥ በመገለጥ ወይም በእውቀት ወይም በትንቢት ወይም በትምህርት ካልነገርኋችሁ ምን እጠቅማችኋለሁ? 7፤ ነፍስ የሌለበት ነገር እንኳ ዋሽንትም ከራርም ቢሆን ድምፅ ሲሰጥ የድምፁን ልዩነት ባይገልጥ በዋሽንት የሚነፋው ወይስ በከራር የሚመታው መዝሙር እንዴት 8፤ ይታወቃል? ደግሞም መለከት የማይገለጥን ድምፅ ቢሰጥ 9፤ ለጦርነት ማን ይዘጋጃል? እንዲሁ እናንተ ደግሞ የተገለጠውን ቃል በእንደበት ባትናገሩ ሰዎች የምትናገሩትን እንዴት አድርገው ያስተውሉታል? ለነፋስ የምትናገሩ ትሆናላችሁና። 10፤ በዓለም ምናልባት ቁጥር የሌለው የቋንቋ ዓይነት 11፤ ይናራል ቋንቋም የሌለው ሕዝብ የለም፤ እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ እሆናለሁ፥ 12፤ የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል። እንዲሁም ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ።

13፤ ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ። 14፤ በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ 15፤ ፍሬ ነው። እንግዲህ ምንድር ነው? በመንፈስ እጸልያለሁ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ በአእምሮም 16፤ ደግሞ እዘምራለሁ። እንዲያማ ካልሆነ፥ አንተ በመንፈስ ብትባርክ ባልተማሩት ሰፍራ የተቀመጠው የምትለውን 17፤ ካላወቀ እንዴት አድርጎ ለምስጋናህ አሜን ይላል? አንተማ 18፤ መልካም ታመሰግናለህ፥ ሌላው ግን አይታነጽበትም። ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ 19፤ ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር አልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ።

20፤ ወንድሞች ሆይ፥ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፉት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ በአእምሮ ሽማግሌዎች ሁኑ። 21፤ ሌሎችን ልሳኖች በሚናገሩ ሰዎችና በሌላ አንደበት ለዚህ ሕዝብ እነግራቸዋለሁ፥ እንዲህም ቢሆን አይሰሙኝም ይላል 22፤ ጌታ ተብሎ በሕግ ተጽፎአል። እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ 23፤ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም። እንግዲህ ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ፡- 24፤ አብደዋል አይሉአችሁምን? ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይመቀሳል፥ 25፤ በሁሉም ይመረመራል፤ በልቡም የተሰወረ ይገለጣል እንዲሁም፡- እግዚአብሔር በእውነት በመካከላቸው ነው ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።

26፤ እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥ መተርጎም አለው፤ 27፤ ሁሉ ለግንጽ ይሁን። በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም 28፤ ይ፤ተርጉም፤ የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል 29፤ ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር። ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፤ 30፤ በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፈተኛው 31፤ ዝም ይበል። ሁሉ እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ 32፤ ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ። የነቢያትም 33፤ መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ፤ እግዚአብሔር የሰላም አማልክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው።

34፤ ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል 35፤ እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና። ለሴት በማኅበር መካከል መናገር ነውር ነውና፥ ምንም ሊማሩ 36፤ ቢወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ። ምን ነው? የእግዚአብሔር ቃል የወጣ ከእናንተ ነውን? ወይስ ወደ እናንተ ብቻ ደርሶአልን?

37፤ ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስለው ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ፤ 38፤39፤ ማንም የማያውቅ ቢኖር ግን አይወቅ። ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፥ በልሳኖች ከመናገርም 40፤ አትከልክሉ፤ ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ አሥራ አራት።

ከም. 12፥ 1 ጀምሮ ቅዱስ ጳውሎስ ለጥንት ቤተ ክርስቲያን ስለ ተሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች ሲናገር ቆይቶአል። በም. 12 ውስጥ እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ምንም እንኳ ልዩ ልዩ ቢሆኑ በእንድ አካል ውስጥ የሚገኙትን ብልቶች መሰለው እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና የሚረዳዱ መሆናቸውን ሐዋርያው ገልጦአል። አንዱ ብልት «ከእርሱ የተሻለ ስጦታ አለኝና እኔ ከእርሱ እበልጣልሁ» ብሎ በሌላው ብልት ላይ መኩራት እንደማይገባው ሁሉ፥ እንዲሁም የጸጋን ስጦታ የተቀበለ አንዱ ክርስቲያን በተቀበለው ስጦታ ምክንያት በሌላው ላይ መኩራት አይገባውም። እንደዚህም አንዱ ብልት «የእርሱን ስጦታ አልተቀበልሁምና የማልጠቅም ነኝ« ብሎ በሌላው ብልት ላይ መቅናት እንደማይገባው ሁሉ፥ እንዲሁም አነስ ያለ የጸጋን ስጦታ የተቀበለ አንዱ ክርስቲያን በሌላው ላይ መቅናት አይገባውም። ስጦታን ሁሉ የሰጠ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ለአካልም ሆነ ለቤተ ክርስቲያንም የሚያስፈልገውን አውቆ «ለእያንዳንዱ ሰብቻው እያካፈለ ያደርጋል።» (ም. 12፥11።) የአካል ሥራ ልዩ ልዩ ነው፥ ስለዚህ ለብልቶቹ ልዩ ልዩ ስጦታ ተሰጥቶአል። እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ልዩ ልዩ ነው፥ እግዚአብሔርም ለአባሎችዋ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታን ሰጥቶአል። ልዩነት የግድ አስፈላጊ እንደ መሆኑ መጠን ለሁላቸው ያ አንዱ ስጦታ አልተሰጠምና የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በልሳን መናገርን ከልክ ያለፈ ላያከብሩ የጸጋን ስጦታ ሁሉ በመጠን ያክብሩ። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ ይጠቅሙ ዘንድ ያገለግሉአትም ዘንድ እያንዳንዳቸው የሚበልጠውን ስጦታ በብርቱ ይፈልጉ። (ም. 12፥31።)

ነገር ግን ከመንፈሳዊ ስጦታ ሁሉ የሚበልጥ አንድ ነገር አለ፥ እርሱም ፍቅር ነው። ፍቅር ከሌሉ እነዚያ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ከንቱ ናቸው፥ ሰውም የሚሠራው ሁሉ ከንቱ ነው፤ ስለዚህ ሐዋርያው በም. 13 ላይ ስለ ፍቅር ይናገራል። አሁንም በም. 14 ላይ ዋና አሳቡን በመቀጠል «ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ» እያለ በልሳኖች ከመናገር ትንቢት መናገር እንደሚበልጥ ያስረዳቸዋል። ይህ «በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር» (ም. 12፥10) ወይም «በልሳኖች መናገር» (ም. 14፥5) ምን ማለት ነው? ቢሉ፥ በም 12፥4-11 በማስገንዘቢያ ‹‹ሀ» ላይ የተባለውን ይመልከቱ።

«ትንቢት መናገርስ ምን ማለት ነው?» ቢሉ፥ ይህ «ትንቢት መናገር» የተባለው ነገር ለጥንት ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ልዩ የጸጋ ስጦታ መሆኑን እንረዳለን። ለእንዳንዶች ብቻ የተሰጠ ልዩ የሆነ ስጦታ ነው እንጂ በተፈጥሮ ለሰው ሁሉ የተሰጠ የመናገር ስጦታ ብቻ አይደለም። እንደዚህ የተናገሩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነቃቁ፥ በንግግራቸውም በእርሱ ተነዱ። (2 ጴጥ. 1፥21።) ትንቢትን የተናገሩት የጥንት ክርስቲያኖች እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ሆነው ወደፊት ስለሚመጡት ነገሮች ጭምር ይናገሩ ይሆናል፥ ነገር ግን እንደ እነርሱ ደግሞ ሆነው «ትንቢት ተናገሩ» ሲባል በመንፈስ ቅዱስ ተነቃቅተው ተነድተው የእግዚአብሔርን ነገር ተናገሩ ማለት ነው እንጂ የወደፊቱን ነገር ብቻ ተናገሩ ማለት አይደለም። (ሉቃ. 1፥67።) ስብከት አለ፥ ትንቢት መናገርም አለ። ስብከት ሰው በገዛ እውቀቱና በገዛ ኃይሉ የሚያደርገው ነገር ነው። ትንቢት መናገር ልዩ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ ነው፥ ይህንም ስጦታ የተቀበለ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ ይናገራል። ይሁን እንጂ ዛሬ እንዳንድ ጊዜ እንደምንሰማው ሁሉ በመንፈስ

ተሸንፎ የግድ መለፍለፍ አይደለም። ዛር አለብን የሚሉ ሴቶች በመንፈሱ ተገዝተው ሁከት እያነሡ ይለፈልፋሉ። ይህስ «ትንቢት መናገር» አይደለም: የሚነዳቸውም መንፈስ ቅዱስ አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ የተነዱ ሰዎች ተራቸውን ሊጠብቁ መንፈላቸውንም ሊገዙ ይችላሉ፡ ሁከት አይፈጥሩም። (1 ቆሮ. 14፥29-33።) ይህ ከእግዚኢአብሔር ሲሆን ያ ከዲያብሎስ ነው።

ቁ. 1-5። ፍቅርን መከታተል የከርስቲያን ሁሉ ዓይነተኛ ተግባር እንደ መሆኑ መጠን ከጸጋ ስጦታዎችም የሚበልጠውን በብርቱ መፈለግ ተገቢ ነው። (ም. 12፥31።) ሆኖም የቆሮንቶስ ሰዎች እነዚህን ስጦታዎች ሲገምቱ በስሕተት ዓይን ገመቱአቸው የሚበልጠውም ማናቸው እንደ ሆነ አልተረዱም። እንደ አነርሱ አሳብ አስደንጋጭ የሆነው የልሳን የመናገር ስጦታ በስጠ። ሐዋርያው ግን በልሳን ከመናገር ትንቢት መናገር ይበልጣል አለ። ምክንያቱም፥ በልሳን የሚናገር ሰው ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና ሰው (ማኅበሩ፥ ቤተ ክርስቲያኑ) አልተጠቀመም። ትንቢትን የሚናገር ሰው ግን ለሰው ይናገራል በሃይማኖቱም ሊያንጸውና ሊያደፋፍረው በመከራም ጊዜ ሊያጽናናው ይችላል። ሰው (ማኅበሩ፥ ቤተ ክርስቲያኑ) ተጠቀመ ማለት ነው። በልሳን የሚናገር ሰው ራሱን ያንጽ ይሆናል፥ ማኅበሩን ግን አያንጽም፤ ትንቢትን የሚናገር ግን መላ ቤተ ክርስቲያንን ያንጻልና የእርሱ ስጦታ ይበልጣል። ሐዋርያው በልሳን የመናገርን ስጦታ እይንቅም ሁላቸውም በልሳኖች ቢናገሩ ይወድ ነበር፤ ሆኖም ከዚያ ይልቅ ትንቢትን ቢናገሩ ይወድ ነበር። ምክንያቱም እነዚያ በልሳኖች የሚናገሩ ሰዎች የተናገሩትን ነገር ባይተረጉሙ ቤተ ክርስቲያን እልተጠቀመችምና ትንቢትን ቢናገሩ ይሻላል። የሐዋርያው ዋና አስተያየት ይህ ነው:-«ቤተ ክርስቲያንን ይጠቅማል አይጠቅምም? ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል አያንጽም?» (ቁ.3፥5፥6፥12፥26) ቤተ ክርስቲያንን እንደሚጠቅምና እንደሚያንጽ መጠን ያ ነገር ተገቢ ነው።

ማስገንዘቢያ።

በቁ. 2 ላይ «ለሰው አይናገርም የሚያስተውሰው የለምና» የተባለውን የሐዋርያውን ፍርድ እንስማ። መምህሩ ለሕዝበ ክርስቲያን የሚናገር ከሆነ አነርሱ በሚያውቁት ቋንቋ መናገር እንደሚያስፈልገው ማለቱ አይደለምን?

ቁ. 6-12። አሁንም ሐዋርያው በልሳን የመናገርን ጠቃሚነት ይመረምራል። ሲነገር ሰው ፍቹን ሊለይ የማይችለው ነገር በእውኑ ይጠቅማልን? ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ መጥፎ በማለጥ በመናገር ፋንታ በተሰወሩት፥ ማለት በማያስተውሉት ልሳኖች ቢናገር፥ ሰሚዎቹም ዜማውን ያስተውሉ ዘንድ ሙዚቃው የታወቀውን (የተገለጠውን) የድምጽ ልዩነት ባይሰጥ፥ ወታደሮችም ለውጊያ ሲወጡ ይሰበስቡ ዘንድ ወይም ከጠላት ጋር ይገጥሙ ዘንድ ወይም ከሰልፍ ይመለሱ ዘንድ ሲነፋ መለከቱ ወታደሮቹ በሚያስተውሉት (በተገለጠ) ድምፅ ባይጮኽ ምን ይጠቅማል? ምንም እይጠቅምም። እንደዚሁም ሁሉ የቆሮንቶስ መምህራን የተሰወረውን፥ ማለት ስሚዎቹ የማያስተውሉትን ሳይሆን የተገለጠውን ቃል ባይናገሩ ለነፍስ የሚናገሩ ይሆናሉ። ሰሚዎች ያላስተዋሉ እንደሆነ የተናጋሪዎች ልፋት የከንቱ ከንቱ ነው። ቋንቋ ከየዓይነቱ አለ፥ ሁሉም ማለፊያ ነው ለሚያስተውለውም ጠቃሚ ነው፤ ለማያስተውለው ሰው ግን ምን ይጠቅማል? እይጠቅምም። ተናጋሪው ምናልባት መልካም ይናገር ይሆናል፥ እኔ ግን የሚሰውን የቃሉን ፍች ባላውቅ «በርበር» ብቻ የሚሰኝ ይመስለኛል። ስለዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች

መንፈላዊ ስጦታን ለማግኘት በብርቱ ቢፈልጉ ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን የምትታነጽበትን እንዲፈልጉ ሐዋርያው ይመክራቸዋል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ወደ እናንተ መጥቼ በልሳኖች ብናገር፥ በመግለጥ ወይም በእውቀት ወይም በትንቢት ወይም በትምህርት ካልነገርኋችሁ?» እጠቅማችኋለሁ (ቁ. 6።) «እኛህ አራት ነገሮች ምንድር ናቸው?» ቢሉ፥ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸውና ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያስተምርባቸው መንገዶች ናቸው።

በመገለጥ ሲነግራቸው፥ ለእርሱ የተገለጠውን ነገር ገልጦ ይነግራቸው ነበር። (ገላ. 1፥11። 2 ቆሮ. 12፥1፡7።) ደግሞ ቁ. 26 እና 30 ይመልከቱ።

በእውቀት ሲነግሩቸው፥ እርሱ የሃይማኖትን ነገር ጠልቆ እውቆእልና ምሥጢርን እያፍታታ ከእውቀቱ ይነግራቸው ነበር። (ም. 12፥8።)

በትንቢት ሲነግራቸው፥ በብሉያት ዘመን በእዲላትም ነቢያት የወደፊቱን ነገር ብቻ ላያመጡ የእግዚአብሔርን ነገር የተናገሩ እንደ እቶም ሆነው ፈቃዱን ያስታወቁ እንደ ነበሩ፥ ጳውሎስም በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ የእግዚአብሔርን ነገር ይነግራቸው ነበር።

በትምህርት ሲነግራቸው፥ የዛሬ እስተማሪ በምሳሌና በማስረጃ ያውም በሚያስተውሉት ቋንቋ ተማሪዎቹን ለማስተማር እንደሚጥር እንዲሁም ጳውሎስ በጥቂት በጥቂቱ እያስተማረ ይነግራቸው ነበር።

ለ/ «እንዲሁ እናንተ ደግሞ የተገለጠውን ቃል በእንደበት ባትናገሩ ሰዎች የምትናገሩትን እንዴት አድርገው ያስተውሉታል? ለነፋስ የምትናገሩ ትሆናላችሁና።» (ቁ. 9።) ይህን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ልብ እናድርገው። «የተገለጠውን ቃል፥ እርሱም ማለት ለሕዝብ ግልጥ የሆነውን ቃል፥ ባትናገሩ እንዴት እድርገው ያስተውሉታል?» ይላል። እውነቱን ነው፥ እንደምን ይችላሉ? ይሁን እንጂ በእውኑ ማስተዋል ያስፈልጋቸዋልን? ጳውሎስ በቁ 16 ላይ «ያስፈልጋቸዋል» ይላል። «እያስተውሉ እንደሆነ ለነፋስ የምትናገሩ ትሆናላችሁ» ይላል። ጊዜአችንን እናባክን ዳሩ ግን እስቀዳሾቹ በሚያስተውሉት ቋንቋ እንናገር!

ቁ. 13-19። ሰው የተናገረውን ቃል ካላስተዋለ ጥቅም የለምና ቤተ ክስቲያኒቱም እትታነጽበትምና ያ በልሳን የሚናገር ሰው ለበለጠ ስጦታ እርሱም ለመተርጎም ይጸልይ። በማኅበር ውስጥ በመንፈስ መጸለይና መዘመር ማመስገንም ማለፊያ ነው፥ ነገር ግን ተናጋሪው ራሱ ስሚዎቹም በአእምሮአቸው ካላስተዋሉ እገልግሎቱ የጎደለ ነው። ተናጋሪው በመንፈሱ ደኅና እድርጎ እግዚአብሔርን ያመሰግን ይሆናል፥ ሃይማኖትን ያልተማረ ሰው ግን የተናገረውን ቃል እያስተውልምና በነገሩ ውስጥ ገብቶ እንዴት እድርጎ ከተነገረው ቃል ጋር መስማማቱን ያስረዳል፥ በምንስ ይጠቀማል? ምንም እላስተዋለም፥ ምንም እልተማረም። ሐዋርያው ከቆሮንቶስ ሰዎች ሁሉ ይልቅ በልሳኖች ይናገር ነበር፥ ሆኖም በተቀበለው ስጦታ ላይመካ አብዝቶም ላያሳየው ሌሎችን ለማስተማር ብሎ በማኅበር ውስጥ ሲናገር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ እምስት ቃላት ብቻ በአእምሮው ሊናገር ይወድ ነበር።

«ባልተግሩት ስፍራ የተቀመጠው የምትለውን ካላወቀ እንዴት እድርጎ አሜን ይላል?» (ቁ. 16።) ሰው «አሜን» የሚል ከሆነ የተነገረውን እንዲያውቅ አስፈላጊ መሆኑን ሐዋርያው እንደ ገመተ እንገንዘብ። «አሜን» የሚለው ከተነገረው ቃል ጋር መስማማቱን ይገልጣልና ሰው ያላስተዋለ እንደሆነ «አሜን» ማለት አይችልም (አይገባም) ማለቱ ነው። በእእምሮ ካልሆነ ቁሱ እንዲናገርና ሰሚው «አሜን» እንዲል ተገቢ ነገር አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ በማኅበር (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ የሚገኙት ክርስቲያኖች ጸሎትን መዝሙርን እምልኮንም ሁሉ ማስተዋል እንደሚገባቸው ይነግረናል። እንግዲያውስ እኛ በተሰበሰበን ጊዜ ይህን ትእዛዝ (ቁ. 37) ልንሰማውና ልንፈጽመው ይገባናል።

ቁ. 20-25። የቆሮንቶስ ሰዎች በልሳኖች መናገርን ከመጠን በላይ በማክበራቸው የግብረ ሕፃናት አእምሮአቸውን አሳይተዋል። ጠቃሚውን በማክበር ፋንታ እንደ ልጆች አሰገራሚውንና አስደንጋጩን አክበሩ። በክፋት ነገር፥ እንኳን ልጆች መሆንና ሕፃናትም ቢሆኑ ያሰመሰግን ነበር፥ ዳሩ ግን በአእምሮአቸው ሽማግሌዎች መሆን ሲገባቸው ልጆች ሆነው ሲገኙ ያሳፍራል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንኳ ልሳኖች እንዳያስምኑ ተጽፎአል። በነቢዩ በኢሳይያስ ዘመን እግዚአብሔር የማይታዘዙትንና የማያምኑትን እሥራኤላውያንን ሌሎችን ልሳኖች ወደሚሰሙበት ወደ ባቢሎን አገር እንዲፈልሱ ፈረደ። እንዲህም ቢሆንና እነዚያን ልሳኖች ቢሰሙ እንኳ እንደማይወቅሱና እንደማይሰሙ እግዚአብሔር አሰቀድሞ ተናገረ። (ኢሳ. 28፥ 11፡ 12።) የቆሮንቶስ ሰዎች «በልሳኖች መናገር ምልክት ነው» ቢሉ፥ ለማያምኑቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚፈጸም የፍርድ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑቱ እሰፈላጊ ምልክት አይደለም። ለማያምኑቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚፈጸም የፍርድ ምልክት እንደምን ይሆናል? ቢሉ፥ ልሳኖቹን ሰምተው የጥንቱን ነገር እያሰቡ በማያምኑቱ ላይ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚፈጸምና ፍርድ እንደሚመጣ ሰለሚታወሱ ነው። ሰለዚህ በምእመናን ሰብሰባ ውስጥ በልሳን መናገር እጅግ እይጠቅምም። ትንቢት ግን በዚያ ሰብሰባ እጅግ ይጠቅማል የሚያምኑትን ያንጻልና። እንግዲህ ልሳኖች በእውነቱ የማያምኑትን የማይወቅሱና የማያሳምኑ ከሆነ ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ወደ ማኅበሩ ሰብሰባ ቢገቡ ተናጋሪዎችም ሁሉ በልሳኖች ሲናገሩ ሰምተው «አብደዋል» ይላሉ እንጂ (የሐዋ. 2፥ 13) ልሳኖችን በመስማት አይወቅሱም አያምኑምም። ዳሩ ግን ወደ ማኅበሩ ገብተው ተናጋሪዎች ሁሉ ትንቢት ሲናገሩ የሰሙ እንደሆነ በመንፈስ ቅዱስ ይወቀላሉ (ዮሐ. 16፥8)፥ ቃሉ ይመረምራቸዋል። በልባቸውም የተሰወረው ነገር ሁሉ ይገለጣል (ዕብ. 4፥12፡13)፥ አምነውም ይሰግዳሉ። ሰለዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች በአእምሮአቸው ሕፃናት አይሁኑ። ልሳኖችን ወድደዋል፥ በማኅበር ውስጥ በልሳኖች መናገር ግን እጅግ አልጠቀመም። ትንቢት መናገርን በዝቅተኛ አስተያየት ተመልከተዋል፥ በማኅበር ውስጥ ግን እጅግ የጠቀመው ይኸው ትንቢት መናገሩ ነው።

«ወንድሞች ሆይ፥ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ... በአእምሮ ሽማግሌዎች ሁኑ።» (ቁ. 20።) በዚህ ክፍል ላይ ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ተገኘ ሰለ ልሳኖች ሰጦታ ይናገራል እንጂ ሰለ ተለመዱት ስለ ዓለም ቋንቋዎች እይናገርም። ሆናም ስለ ልሳኖች የተናገረው ቃል እኛን ዛሬ ሊመራን ይችላል።

ሐዋርያው ሌሎችን የማይጠቅመውን ቋንቋ ከልክ ያለፈ ማክበር የግብረ ሕፃናትን አእምሮ ማሳየት ነው ይላል። በአእምሮአችን ሽማግሌዎች መሆን ሲገባን ሕፃናት ሆነን ለንገኝ አያስመሰግንም ይላል። የግብረ ሕፃናትን አእምሮ ማሳየት ለሽማግሌ ሰው የመንፈሳዊነቱ ምልክት አይደለም ይላል። ሽማግሌ ሰው እንድ ጠቃሚ ያይደለውን ነገር አስገራሚ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ይወደው ዘንድ አልታሰበም ይላል።

ሰለዚህ በመቅድሙ ላይ «በጥንት ልማድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ግዕዝ ነበረ። አሁን ግን በተራ ሕዝብ ዘንድ ያልታወቀ ሰለ ሆነ በአማርኛ ቢለወጥ እይሻልምን?» ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሱ እንደሚከተለው ነው። ተራ ሕዝባችን ስለማያስተውለው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በግዕዝ ቢፈጸም እይጠቅምምና በአማርኛ ቢለወጥ ይሻላል። ግዕዝ ከሞቱት ከዱሮ ቋንቋዎች አንዱ ነው እንጂ የተቀደሰ ቋንቋ አይደለም። የአማርኛና የሌላ ቋንቋዎች ሥርና መሠረት ነውና በተግሪ ቤተ ጠቃሚነት አለው፥ በቤተ ክርስቲያን ግን ጥቅም የለውም። የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ሁሉ ተራው ሕዝብ በሚያውቀው ቋንቋ እንዲፈጸሙ የተገባ ነገር ነው። ስብክት ሆነ ጸሎት መዝሙርም ሁሉ በአማርኛ ሊሆን ይገባል።

ዘመናት በዘመን ሲታደሱ እንደሚኖረው ሁሉ የዱሮውን ለመለወጥ ሳንል የዱሮውን ከነጥቅሙ ሁሉ ለመጨበጥ ወደን አንዱን ነገር በአንዱ እንደምንተካው ሁሉ፥ እንዲሁም ዛሬ የዱሮ ሃይማኖታችንን ለመጨበጥና የአዲስ ዘመን ልጆቻችንን በአባቶቻቸው ሃይማኖት ለመጠበቅና ለመምራት ብለን የአባቶችን ሃይማኖት በልጆች ቋንቋ ማስተማር ያስፈልገናል። ይህን ምነው እስከ ዛሬ ድረስ አለመገንዘባችን ወይም አለማድረጋችን? እንወቀስ የለምን? ልጆቻችን ከአባቶቻቸው ሃይማኖት ይወጡና ተመልካች የሆነ ሁሉ የተጻፈውን ቃል ከተደረገው ነገር ጋር እነጣጥሮ «ሉረ እነኘህ በእእምርእቸው ገና ያልበሰሉ (ሕፃናት) ናቸው?» ይል የለምን? ሉረ እንጎልምስ! ሽማግሌዎች እንሁን! በዚህ በግብረ ሕፃናት አእምሮ የምንኖረው እባካችሁ እስከ መቼ ድረስ ነው? ግዕዝ በአማርኛ ካልታደሰ የከበረችና የተወደደች ቤተ ክርስቲያናችን ሳትደኅይ አትቀርም።

ቁ. 26-33። ማኅበሩ (ቤተ ክርስቲያኑ) በተሰበሰበ ጊዜ በእነዚህ በጸጋ ስጦታዎች ምክንያት ሁከት ይነሣ እንደ ነበር ሐዋርያው ሰምቶአል። ክርስቲያኖች ሁሉ «መንፈስ ቅዱስ እነግሥቶናልና የገድ እንዘምራለን ወይም እንናገራለን» በማለት ይህን ሁሉ በእንድነት ያደርጉ ሰለ ነበር ሰብሰባቸው ይታወክና ይሸበር ነበር። ይህን ሰምቶ ጳውሎስ በዚህ ነገር ውሳኔውን ሰጥቶአል። አሳቡ ሁልጊዜ ያው ነው። ሁሉም ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ይሁን ይላል። በልሳን ሊናገሩ የሚወዱ ቢኖሩ ሳይበዙ 2 ወይም 3 ብቻ ይሁኑ፥ በተራ፥ በተራም እንጂ በእንድነት አይናገሩ፥ የሚተረጉምም ይኑር። የሚተረጉም ባይኖር ግን ለቤተ ክርስቲያን በፍጹም አይናገሩ፥ ሲናገሩ የሚያስተውል ካለመኖሩ የተነሣ ያ «ሁሉ ለማነጽ ይሁን» የተባለው ውሳኔ ይፈርሳልና። ሲናገሩ ቢወዱ ለብቻቸው

ሆነው ለራሳቸውና ለእግዚአብሔር ይናገሩ። ሐዋርያው ይህን ሲል እንኳ ሰዎች ዝም ማለት እንደሚችሉ እንጂ ለመናገር እንዳልተገደዱ ያመለክታል።

ትንቢት በሚናገሩቱም ዘንድ ነገሩ እንደዚሁ ነው። የተናጋሪዎች ቁጥር ይወሰን፡ የቀሩትም ሰዎች ያድምጡ የተነገረውንም ነገር ይለዩ። ያህንን በማለት ሐዋርያው «ለመናገር መንፈሱ አነሣሥቶኛል የሚል ሁሉ እንዲናገር እያስፈልግም» ሲል ነው። በስብሰባ ውስጥ ለሚቀመጥ ለሌላ ሰው ግን አንድ ነገር በመንፈስ ቢገለጥ (ቁ. 6) ፈተኛው ተናጋሪ መንፈሱን እስታግሥ ዝም ይበል። ስለምን? ቢሉ፡ በተራ በተራ ትንቢት ለመናገር ለሰው ሁሉ ቢፈቀድም ሁለት ሰዎች በአንድ ጊዜ እንዲናገሩ አልተፈቀደም። ይህን ሲል ደግሞ ሐዋርያው ትንቢት የሚናገሩቱ መንፈላቸውን እየገዙ ዝም ማለት እንደሚችሉ ያስረዳል፡ የሚነዳቸው የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሌሎች መናፍስት ሆኖ ሁክት አንሺ ሳይሆን የሰላም መንፈስ ነውና። በእብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በሥርዓት እፈጻጸም ነገር ሕጉ ይህ ነው ብሎ ሐዋርያው ስለ መንፈላዊ ነገር ትምህርቱን ያቆማል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ሁሉ ለማነጽ ይሁን።» (ቁ. 26።) በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ ለሚደረገው ሁሉ ሕጉ ይህ ቢሆን መልካም ነበረ። ስለ እያንዳንዱ ነገር «ይህ ያንጻል ወይ?» ተብሎ ቢጠየቅ ስለ ማንኛውም ነገር መልሱ «አያንጽም» የሚል ቢሆን ያ ነገር አይጠቅምምና ቢቀር ይሻላል።

ለ/ «በተራቸው ይናገሩ፤ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁክት አምላክ እይደለምና።» (ቁ. 27፡33።) ሐዋርያው በቁ. 27 ላይ «በተራቸው ይናገሩ» ሲል፡ በቁ. 40 ላይ ደግሞ «ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን» ብሎ በጌታ ትእዛዝ ሲመክረን በእንዳንድ ቤተ ክርስቲያን 2 ሰዎች ተአምረ ማርያምንና ተአምረ ኢየሱስን በእንድ ጊዜ ሲያነቡ፡ ክቅዳሴም በኋላ ምእመናን ልዩ ልዩ ጸሎት (የውዳሴ ማርያምን ማደልና እንቀጸ ብርሃንን) በእንድ ጊዜ ሲያደርሱ፡ ወይም ደግሞ ቁሱ ወንጌልን ሲያነብ መዘምራን ዳዊት ሲደግሙ የተገባ ነውን? በእንድ በኩል እንደ ሕፃናት ማድረጋችን ነውና፡ በሌላም በኩል ደግሞ የጌታን ትእዛዝ ማፍረሳችን ነውና ሉረ እንዲህ ያለውን ነገር ብንተወው ይሻላል!

ሐ/ «ሌሎችም ይለዩአቸው» (ቁ. 29።) እነዚህ «ሌሎች» የተባሉቱ እነማን እንደ ሆኑ እጅግ አልተገለጠም። መናፍስትን ለመለየት ልዩ የጸጋ ስጦታ ተቀብለው የተናጋሪዎችን መንፈስ የሚለዩ ናቸውን? (ም. 12፡10። 1 ዮሐ. 4፡1።) ምናልባት ይሆናሉ። «በመንፈስ እናገራልሁ» የሚል ሁሉ በእውነቱ በመንፈስ እይናገርም ነበርና እነኝህ ለይዎች ምናልባት ይለዩአቸው ነበር። ወይም ምናልባት «ሌሎች» ሲል እዚያ በስብሰባ ውስጥ የተገኙት፡ ተናጋሪዎች ያልሆኑት ይሆናሉ። ትርጉሙም ይህ ሳይሆን አይቀርም። ተናጋሪዎቹ ሲናገሩ ሳሉ «ሌሎቹ» ማለት እድማጮቹ የተነገረው ቃል ከእውነት ጋር የተስማማ መሆኑንና አለመሆኑን ይለዩ ነበር። ይህም ለምእመናን ሁሉ የተገባ ነገር ነው። ተናጋሪዎች በቤተ ክርስቲያን ሲናገሩ ሕዝበ ክርስቲያን ንግግራቸውን በሙሉ እእምሮ አድምጦ የተነገረውን ነገር መለየት ዓይነተኛ ተግባሩ ነው። (የሐዋ. 17፡11። 1 ተሲ 5፡21።) ተናጋሪዎቹ እንዲናገሩ ብቻ አይበቃም፡ ሰሚዎቹም እንዲለዩ ያስፈልጋል።

ቁ. 34-36። በቆሮንቶስ የነበረው የክርስቲያኖች ማኅበር በተለበለበ ጊዜ ልዩ ልዩ ስሕተቶች እንደ ተደረጉ እይተናል። በእነዚህ ነገሮች ሐዋርያው ጳውሎስ ምክሩን አንድ በአንድ ሰጥቶአል። አሁንም ደግሞ ወደ ሴቶች ነገር ደርሶአል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳንዶች ሴቶች፡ ምናልባት «መንፈስ አነሣሥቶናል» በማለት፡ በመላ ማኅበር ፊት ይናገሩ ነበር። (በቁ. 36 ላይ ሐዋርያው በነገሩ እጅግ ተገርሞ «ምን ነው?» ስለሚል ሴቶች ይህን ያደረጉ ይመስላል።) ጳውሎስ «እልተፈቀደላቸውም» ይላል። ያልፈቀደላቸው ማን ነው? ቢሉ፡ 1ኛ ሐዋርያው ነው (1 ጢሞ. 2፡11፡12) ፡ 2ኛ ሕግ ነው (ዘፍጥ. 3፡16)፡ 3ኛ ጌታ ነው። (ቁ. 37።) ሴት ሴቶች ብቻ ባሉበት ወይም በሕፃናት ማኅበር ልትናገር ትችላለች እንጂ ትምህርት መዝሙርና ጸሎት (ቁ. 26-33) በሚደረግበት በጠቅላላው ማኅበር መካከል እንድትናገር እልተፈቀደላትም። ይህም ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን «ለቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ» ነው። (ቁ. 33።) ሕጉም ጥብቅ ነውና ሴት ጥያቄ መጠየቅ እንኳ ብትፈልግ በቤትዋ እንጂ በማኅበር መካከል እንድትጠይቅ አልተፈቀደላትም። ምን ነው? አዲስ አዲስ ልማድ እንድትፈጥር የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እናትና ምንጭ ናትን? ሉረ እይደለችም! ከሌሎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በኋላ የተመሰረተች ናት። እንግዲያውስ የእነርሱን ሕግ ትጠብቅ። (ም. 11፡16።) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በዓለም ውስጥ ብቻቸውን ናቸውን? ሉረ እይደሉም! እንግዲያው በሚያደርጉት ሁሉ ከሌሎቹ ጋር ይስማሙ።

ማስገንዘቢያ።

«ሴቶች በማኅበር እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም።» (ቁ. 34።) ይህ ሕግ ነው፡ ማንም ሰው በምክንያትም ሆነ በትርጉም ሊያስወግደው አይችልም። የሕጉ ቃል ግልጥ ነው፡ አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ነው። «ምነው፡ በም. 11፡5 ላይ ራስዋን ሳትሸፍን ለለምትጸልይ ወይም ትንቢት ስለምትናገር ሴት ተናግሮ የለምን? እንግዲያውስ ሴቶች እንዲጸልዩ ወይም እንዲናገሩ ማለቱ እይደለምን?» ቢሉ፡ እውነት ነው፡ ስለምትጸልይ ወይም ስለምትናገር ሴት ይናገራል፤ ሆኖም ጉዳዩ በማኅበር ስለመናገርዋ ወይም ስላለመናገርዋ ሳይሆን ራስዋን ስለ መሸፈንዋ ወይም ስላለመሸፈንዋ ነው። የትም ዘንድ፡ በሌቶች ማኅበር በሕፃናትም፡ ስትጸልይ ወይም ስትናገር ራስዋን ትሸፍን ብሎ ያዝዛታል እንጂ በመላ ማኅበር ፊት ትጸልይ ወይም ትናገር አይልም።

ይህ ሕግ ነው፡ ለየትም ቦታ ሁሉ ነው፡ ስውም ሊለውጠው አይችልም። ይሁንና የክርስቶስ ነገር ባልታወቀበት ዘንድ፡ የሚናገርም ወንድ ባይኖር፡ ክርስቲያን የሆነች ሴት ልትናገር አትችልም ወይ? ቢሉ፡ የሁላችንም ሕሊና ሳይፈቅድላት አይቀርም። ታዲያስ? ሐዋርያው ትእዛዙን ሲሰጥ ስለ ክርስቲያን ማኅበር መናገሩ ነው እንጂ የክርስቶስ ስምና የክርስቶስ ነገር ስላልታወቀበት ሰፍራ መናገሩ እይደለም እንላለን። ሊናገር የሚችል ክርስቲያን የሆነ ወንድ ባለበት በክርስቲያን ማኅበር ውስጥ ሴት እንድትናገር በፍጹም አይፈቀድም። ክርስቲያን የሆነ ወንድ በሌለበት በአረመኔዎች ስብሰባ ግን ሴት ክመናገር አልተከለከለችም።

ቁ. 37-40። ሐዋርያው ስለ መንፈላዊ ስጦታዎች ከም. 12 ጀምሮ እስከ ም. 14 ድረስ ብዙ ጽፎአል። ወሰን የማይቀበለው እብዛኛውን ጊዜ መንፈላዊ የሚመስለው ሰው ነውና ጳውሎስ እሁን «በመንፈስ ቅዱስ ተገዝቻለሁ» የሚል ሰው ቢኖር የተጻፈው ወሰን

የሰው ምክር ሳይሆን የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነ በማወቅ በእውነት በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተገዛ ይታወቅ ይላል። ጳውሎስ የተናገረው ከራሱ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ ነውና ቃሉ የጌታ ትእዛዝ ነው። (ገላ. 1፥1፡2፡11፡12።) የጌታ ትእዛዝ መሆኑን አላውቅም የሚል ለው ቢኖር ከእግዚአብሔር ዘንድ ውጤቱን ይጠብቅና ከዕለታት አንድ ቀን እውነቱን ያውቃል። (ሕዝ. 2፥5።) (በአንዳንድ ትርጉም ግን «እይወቅ» በማለት ፋንታ «አይታወቅ» ይላልና አላውቅም የሚል ቢኖር እርሱ ራሱ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በእግዚአብሔር አይታወቅ ማለቱ ይሆናል። ም. 8፥3፤13፥12።) በልላን ከመናገር ትንቢት መናገር ይበልጣልና የቆሮንቶስ ለምች ይህን በብርቱ ይፈልጉ። (ም. 12፥31፤14፥12።) በልላን መናገርም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሆኖ ጥቅም እለውና እርሱን ደግሞ አይከልክሉ። ብቻ በስብሰባቸው ጊዜ ሁክት ሳይደረግ ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን። ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሁሉ የሚሆን መሠረታዊ ሕግ ይህ ነው።

ማስገንዘቢያ።

«የጳውሎስ ሥልጣን ከሌሎች ሐዋርያት ሁሉ ያነሰ ነው» የሚሉ ሰዎች አሉ፥ ይህንም በማለት በጳውሎስ ትምህርት ላይ ጥርጥር ይጥላሉ። ግን ጳውሎስ «የምናገርበት በእግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የምናገረውም ቃል የጌታ ትእዛዝ ነው» ብሎ ማረጋገጡን በቁ. 37 እና በም. 7፥40 ላይ ተመልከቱ። «ጳውሎስ)። ሲባል ጌታ በጳውሎስ በኩል የተናገረው ቃል ነው እንጂ የጳውሎስ ቃል አይደለም።

* * *
* * * * * *

ምዕራፍ 15።

1፤ ወንድሞች ሆይ፥ የሰበክሁላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን 2፤ ወንጌል እላለባችኋለሁ፤ በከንቱ ካላመናችሁ በቀር፥ ብታስቡት፥ በምን ቃል እንደ ሰበክሁላችሁ አላስባችኋለሁ።

3፤ እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አላልፌ ለጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፡ -መጻሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ 4፤ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው 5፤ ቀን ተነሥቶአል፥ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ 6፤ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ስሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ፥ 7፤ እንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም 8፤ ለሐዋርያት ሁሉ ታየ፤ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ 9፤ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ። እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ 10፥ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ፥ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደሰሁም። 11፤ እንግዲህስ እኔ ብሆን እነርሱም ቢሆኑ እንዲሁ እንሰብካለን እንዲሁም አመናችሁ።

12፤ ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ የሚሰበክ ከሆነ ግን ከእናንተ እንዳንዶቹ፡ - ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ? 13፤14፤ ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ለብከታችን ከንቱ ነው እምነታችሁም 15፤ ደግሞ ከንቱ ናት፤ ደግሞም፡ - ክርስቶስን እለነሥቶታል ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለ መሰከርን፥ ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፤ ሙታን ግን የማይነሡ 16፤ ከሆነ እርሱን እላለነሣውም። ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ 17፤ አልተነሣማ፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ 18፤ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ። እንግዲያስ 19፤ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ ጠፍተዋላ። በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።

20፤ አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን 21፤ ተነሥቶአል። ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ 22፤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ 23፤ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፥ በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው፤ 24፤ በኋላም፥ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ 25፤ ጊዜ፥ ፍጻሜ ይሆናል። ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ 26፤ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና። የኋለኛው ጠላት 27፤ የሚሻረው ሞት ነው፤ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአልና። ነገር ግን፡ -ሁሉ ተገዝቶአል ሲል፥ ሁሉን ካስገዛለት በቀር 28፤ መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።

29፤ እንዲያማ ካልሆነ፥ ስለ ሙታን የሚጠመቁ ምን ያደርጋሉ? ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ፥ ስለ እነርሱ የሚጠመቁ 30፤ ስለ ምንድር ነው? እኛስ ዘወትር በሚያስፈራ ኑሮ 31፤ የምንኖር ስለ ምንድር ነው? በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለኝ

በእናንተ ትምክህት እየማልሁ፡ ወንድሞች ሆይ፡ [32] ዕለት ዕለት እሞታለሁ። እንደ ሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር ከተገልሁ፡ ሙታንስ የማይነሡ ከሆነ፡ ምን ይጠቅመኛል? [33] ነገ እንሞታለንና አንብላና እንጠጣ። አትሳቱ፡ ክፉ ባልንጀርነት [34] መልካሙን አመል ያጠፋል። በጽድቅ ንቁ ኃጢአትንም አትሥሩ፡ አግዚአብሔርን የማያውቁ አሉና፡ አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን አላለሁ።

[35] ነገር ግን ሰው፡-ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ [36] ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ፡ [37] አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም፡ የምትዘራውም፡ ሰንዴ ቢሆን ከሌላም ዓይነት የአንዱ ቢሆን፡ ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል [38] አይደለም፡ አግዚአብሔር ግን እንደ ወደደ አካልን ይሰጠዋል ከዘሮችም ለእያንዳንዱ የገዛ አካሉን ይሰጠዋል። [39] ሥጋ ሁሉ አንድ አይደለም፡ የሰው ሥጋ ግን አንድ ነው፡ የእንስሳም ሥጋ ሌላ ነው፡ የወፎችም ሥጋ ሌላ ነው፡ የዓሣም [40] ሥጋ ሌላ ነው። ደግሞ ሰማያዊ አካል አለ፡ ምድራዊም አካል አለ፡ ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ [41] ነው፡ የምድራዊም አካል ክብር ልዩ ነው። የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፡ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያልና።

[42] የሙታን ትንሣኤ ደግሞ አንዲሁ ነው። በመበስበስ [43] ይዘራል፡ ባለመበስበስ ይነሣል፡ በውርደት ይዘራል፡ በክብር [44] ይነሣል፡ በድካም ይዘራል፡ በኃይል ይነሣል፡ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፡ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ [45] መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ። እንዲሁ ደግሞ፡-ፈተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፡ ኋለኛው [46] አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ። ነገር ግን አስቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ [47] መንፈሳዊው መጀመሪያው አይደለም። የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፡ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው። [48] መሬታዊው እንደ ሆነ መሬታውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው፡ ሰማያዊው እንደ ሆነ ሰማያውያን የሆኑት [49] ደግሞ እንዲሁ ናቸው። የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን። [50] ነገር ግን፡ ወንድሞች ሆይ፡ ይህን አላለሁ፡- ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፡ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም።

[51፡52] እነሆ እንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፡ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፡ መለከት ይነፋና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን። [53] ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው [54] የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና። ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፡ በዚያን ጊዜ፡- ሞት ድል በመነሣት [55] ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል። ሞት ሆይ፡ መውጊያህ [56] የት አለ? ሲኦል ሆይ፡ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ [57] ነው፡ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

[58] ስለዚህ፡ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፡ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፡ የማትነቃነቁም፡ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።

* * * * * *

5ኛ ክፍል።

(ም. 15።) ስለ ተደረገው ጥፋት ወቀሳ።

ስለ ትንሣኤ ሙታን።

ምዕራፍ አሥራ አምስት።

«ከፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፡ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፡ አንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይሆናል» ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምልክትን ለማየት ለወደዱ ፈሪሳውያን ትንሣኤን ምልክት አድርጎ ሰጣቸው። (ማቴ. 12፡ 39፡40። ዮና. 1፡17።) መነሣቱም ለእርሱና ለወንጌል አውነተኝነት የማረጋገጫ ምልክት ነውና እኛ ክርስቲያኖች በጸሎት ሃይማኖት «በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ» ብለን በትንሣኤው የጸና እምነታችንን እንገልጣለን። እንደዚህም ከሐዋርያት ዘንድ ከተቀበልናቸው ከዋናዎቹ ትምህርቶች አንዱም ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ነው። ይህ አሁን የያዝነው ምዕራፍ ስለዚህ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤና ስለ ትንሣኤ ሙታን ይናገራል፡ በዚሁም ነገር የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ምዕራፍ ነው።

የቆሮንቶስ ምእመናን የክርስቶስን መነሣት አልተጠራጠሩም፡ የተጠራጠሩት የሰውን መነሣት ነው። ሙታን እንደሚነሡ አንዳንዶቹ አላመኑም (ቁ. 12)፡ ያላመኑበት ምክንያትም የሰው ሥጋ ከበሰበሰና ከጠፋ በኋላ ሰው እንዴት አድርጎ፡ ማለት በምን ዓይነት አካል እንደሚነሣ ለማወቅ ስለተቸገሩ ነው። (ቁ. 35።) መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል ባለማወቃቸው ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉትን ሰዱቃውያንን መስለው ላቱ። (ማቴ. 22፡23፡29።)

ትንሣኤ ሙታን የተመሠረተበት በክርስቶስ ትንሣኤ ነውና ሐዋርያው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በአውነት እንደ ተነሣ በዚህ ምዕራፍ ላይ አስቀድሞ ያረጋግጣል። ይህን አድርጎ ሲያበቃ ክርስቶስ ከተነሣ ለክርስቶስ የሆኑቱ እንደሚነሡ ያረጋግጥና በምን ዓይነት አካል እንደሚመጡ ያስረዳል። ይህን ሲያደርግ፡ በክርስቶስ የሞቱ የሚነሡት በዚህ ዘመን ፍጻሜ፡ ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ ሲመጣ ነውና (1 ተሰ. 4፡14-16) ስለ ፍጻሜ ነገር ለመናገር ተመችቶት ስለ ክርስቶስ ግዛት፡ ስለ መንግሥቱ ለአግዚአብሔር መረከብና ስለ መጨረሻ ድል መንሣት ይናገራል።

«ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ቦታ ላይ ስለ ትንሣኤ ሙታን ነገር ይህን ያህል ለምን ተናገረ?» ቢሉ፡ መልስ 1ኛ፡ የክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስቲያን ሃይማኖት አውነተኝነት ዋና ማስረጃ ነውና በዚህ ነገር ተጨማሪ ትምህርት ለመስጠት ነው። 2ኛ ከቆሮንቶስ ምእመናን አንዳንዶቹ ይህን ዶክትሪን (ትምህርት) ከደው አስቸጋሪ ጥያቄ በመጠየቅ የአንዳንዶችን አምነት ገልብጠው ነበርና (ቁ. 58። 2ጢሞ. 2፡18) ይህን ስሕተታቸውን ለመቃወም ነው።

ቁ. 1-11። ከቆሮንቶስ ሰዎች አንዳንዶቹ «ትንሣኤ ሙታን የለም» ብለዋልና ሐዋርያው በቆሮንቶስ ከተማ የሰበከውን ወንጌል ያሳስባቸዋል። አስቲ ያስቡ፡ ዋጋ ያለው

ወንጌል አይደለምን? ሉረ፡ ሌላ ሰው ሳይሆን መንፈሳዊ አባታቸው የሰበከላቸው ወንጌል ነው፤ አነርሱም የተቀበሉቱ ወንጌል ነው፤ የቆሙበት መሠረት (መዝ. 39፡2። ሮሜ. 5፡2) የሚድኑበትም ወንጌል ነው! ሐሰት ነውን? በከንቱ አምነውታልን? ሉረ ይቆዩ! በምን ቃል እንኳ ሐዋርያው እንደ ሰበከላቸው ያስቡ።

ይህ ቃል ከሌላ፡ ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበለው ቃል ነው እንጂ ሐዋርያው ከገዛ አእምሮው ያወጣው አይደለም። (ገላ. 1፡ 11-2፡6።) እንደ ቅብብል ሩጫ ነገር ነው። ጳውሎስ ከሌላ ዘንድ የተቀበለውን እርሱ በተራው ለቆሮንቶስ ሰዎች አሳልፎ ሰጥቶአቸው ነበር። የሰበከውም ቃል እንደዚህ ነበረ፡- «መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፡ ተቀበረም፡ መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሥቶአል፡ ለጴጥሮስም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ።» ቅዱስ መጽሐፍ አስቀድሞ ስለ መሞቱና ስለ መነሣቱ ትንቢት ተናግሮ እንደ ነበር ሐዋርያው ገልጦላቸው ነበር (ሲላ. 53፡5-12። መዝ. 15፡9፡10። ሉቃ. 22፡37፤24፡25-27)፡ ይህንም የትንቢት ቃል ቢጠነቀቁት መልካም ያደርጋሉ። (2 ጴጥ. 1፡19።) ለመሞቱ መቀበሩ ይመሰክራል፡ ለመነሣቱም ብዙዎች ሰዎች ይመሰክራሉ። ጴጥሮስ አይቶታል (ሉቃ. 24፡34)፡ «አሥራ ሁለቱ» የተባለው የሐዋርያት ቡድን አይቶታል (ማር. 16፡14። ሉቃ. 24፡36። ዮሐ. 20፡19)፡ በማናውቀውም ጊዜ ከአምስት መቶ የሚበዙ ምእመናን አይተውታል፡ በማናውቀው ጊዜ ደግሞ «የጌታ ወንድም» የተባለው ያዕቆብ አይቶታል፡ ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ሁሉ አይተውታል (የሐዋ. 1፡1-5)፡ ከሁሉም በኋላ ደግሞ ጳውሎስ አየው። (የሐዋ. 9፡1-9፡17፤22፡14። 1 ቆሮ. 9፡1።) ጌታ ወደ ተራራ ወጥቶ ከጠራቸው አሥራ ሁለት ሐዋርያት አንዱ ጳውሎስ አልነበረም፡ ከጌታም ሞትና ትንሣኤ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን አስቀድመው ከሰበሰቡት ሐዋርያት አልነበረም፤ ነገር ግን በሐዋርያት ዘመን መካከል ላይ ጳውሎስ እንደ ጭንጋፍ ሆኖ ለሐዋርያነት ተጠራ። እንደዚህ ቆይቶ ስለ ተጠራ፡ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን አላድዶ ስለ ነበር፡ ጳውሎስ ሐዋርያ ለመሆን የማይገባ መሆኑ ሁልጊዜ ይሰማው ነበር። (1 ጢሞ። 1፡12-16።) ሆኖም በእግዚአብሔር ጸጋ ተጠራ፡ ያም ጸጋ ከንቱ አልነበረም (2ቆሮ. 3፡5) ጳውሎስ ከቀሩት ሐዋርያት ሁሉ ይልቅ በሥራ ደክሞአልና። (2ቆሮ. 11፡16-28፤ 12፡12።) የሆነ ሆኖ እርሱም ቢሆን አነርሱ፡ ማለት ሐዋርያት «መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፡ ተቀበረም፡ መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሥቶአል» ብለው ወንጌልን ሰብከዋል፡ የቆሮንቶስም ሰዎች ይህንኑ አመኑ።

ማስገንዘቢያ፡

ሀ/ «የሰበከሁላችሁን ወንጌል አሳስባችኋለሁ።» (ቁ.1።) ቅዱስ ጳውሎስ በአነዚህ ቁጥሮች ውስጥ መላ ወንጌልን ለማስታወቅ አላሰበም፡ ያስታወቀው ፍሬ ፍሬ ነገሩን ብቻ ነው። «ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፡ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ።» የሚለው የወንጌል ልብ ነው፡ ይህንም በማመን ሰው ከኃጢአቱ ሁሉ፡ ካለፈውና ከአሁኑ ከሚመጣውም ሁሉ (1ዮሐ 1፡7፡9) ይነጻል ይጸድቃል ይድናል። (ሮሜ 4፡23-25።) በዚህ የወንጌል ልብ በሆነ ቃል ውስጥ ጉዳዩ ክርስቶስ ስለ ሠራልን ሥራ እንደ ሆነ እንጂ እኛ ለክርስቶስ ስለምንሠራው ሥራ እንዳይደለ የምንገነዘበው ነገር ነው። ደኅንነት በተሠራልን ሥራ በማመን ነው እንጂ ሥራ በመሥራት አይደለም። (ኤፌ 2፡8፡9።ቲቶ.3፡5።) ሰው የሚድንበት በእምነት ብቻ ነው፤

ሆናም የሚያድን እምነት ከቶ ብቻውን አይሆንም። የሚያድን እምነት ሥራ ሁልጊዜ ይኖረዋል፥ ሥራም የሌለው እምነት የሞተ ነገር ነው እንጂ የሚያድን እምነት አይደለም። (ያዕ. 2፥26።) እውነተኛ እምነት ማመን ብቻ አይደለም። (ያዕ. 2፥19።) በእውነተኛ እምነት ውስጥ ኃጢአተኞች እንደ ሆንንና ደኅንነትን ካላገኘን እንድንጠፋ መገንዘብ፥ ንስሐ መግባት፥ በጌታ የሆነውን የእግዚአብሔርን ጸጋ መቀበልና በጌታ ሥራ መታመን፥ ከዚያም በኋላ ከኃጢአት ርቀን እንደ ጌታ ፈቃድ ሁሉ መመላለስ ተጠቅልሎ የገኛል። ከዚህ ያነስ ነገር ሁሉ የሚያድን እምነት አይደለም። የክርስቶስን ታሪክ ማወቅና ማመን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ዓይነት «እምነት» አይደለም። የምንድንበት፥ ሥራ ባለው እምነት ነው፤ ይህ ዓይነት ሥራም እንዲያው ከልብ መንጭቶ ከተሠራ የእውነተኛ እምነት መገለጫ ነው። (ማቴ. 25፥31-46። 1 ዮሐ. 3፥7።)

ለ/ «በእርሱ ደግሞ የምትድኑበት።» (ቁ. 1።) ይህን ወንጌል በመቀበል፥ በእርሱም ላይ በመቆም፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ድነዋል፤ ገናም ሐዋርያው ሲጽፍ ይድናሉ። «ገናም ይድናሉ» ምን ማለት ነው? ቢሉ፥ እነዚህ ሰዎች የደኅንነትን መንገድ የያዙና የሚሄዱበት ናቸው እንላለን። ከኃጢአት ዋጋ (ከኩነኔ) ድነዋል (ኤፌ. 2፥5፡8)፥ አሁንም ከበለጠ ወደ በለጠ፥ ከጽድቅ ወደ ቅድስና፥ ከቅድስናም ወደ ከብር («ቤዛነት» ም. 1፥30) ይራመዳሉ። ከእንዱ አስተያየት ደርስዋል፥ ከሌላው ግን ገና አልደረሱም። (ፊልጵ. 3፥12።)

ሐ/ «ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ፥ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል።» (ቁ. 6።) ጌታ ለእነዚህ ሰዎች መቼ እንደ ታየ እርግጠኛውን አናውቅም። ይሁንና ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ «ከእነርሱ የሚበዙቱ» ገና በሕይወት መኖራቸው ትልቅ ነገር ነው። ተጠራጣሪ ቢኖር ሄዶ ከእነርሱ ዘንድ እውነቱን ለመጠየቅ ይችላል ማለት ነው። እነኝህ ሰዎች ሁሉ በገዛ ዓይናቸው ጌታን አይተውት ነበርና መነሣቱ እጅግ የተረጋገጠ ነገር ነው። እዚህ ላይ ከተጻፉትም ሌላ የታያቸው አሉ። ለሴቶች ታይቶአል (ማቴ. 28፥9። ዮሐ. 20፥11-18)፥ ወደ ኤማሁስ ለሄዱት ለሁለቱ ሰዎች ታይቶአል። (ሉቃ. 24፥13-31።) «እርባ ቀን እየታያቸው ሕያው ሆኖ ለመረጣቸው ምስክሮች ራሱን አሳያቸው» ሲባል (የሐዋ.1፥3፤ 10፥40፡41) «ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ» ለሚለው ትምህርት መሠረቱ ምንኛ ጽኑ ነው!

«አንቀላፍተዋል» የተባለው ቃል ለምእመናን ሞት ደንበኛ ቃል ነው። (ዮሐ. 11፥11። የሐዋ. 7፥60። 1 ቆሮ. 11፥30፥15፥18፡20። 1 ተስ. 4፥13-16።) ለእነሱ «ሞት» የእንቅልፍ ያህል ብቻ ነው በኋላም ነቅተው ይነሣሉ።

መ/ «ያዕቆብ።» (ቁ. 7።) ይህ ያዕቆብ የተባለው ሰው ከሐዋርያት አንዱ እንደ ሆነ አልታሰበም። ጌታ ለሐዋርያት ሁሉ በተገለጠ ጊዜ ያዕቆብ የተባሉት ሁለት ሐዋርያት በመካከላቸው ነበሩና ጌታ በተለይ ለእነርሱ የሚገለጥበት ምክንያት የለም። ከሐዋርያት አንዱ ላይሆን «የጌታ ወንድም» የተባለው ይሆን ይሆናል። (ማቴ. 13፥56።) ይህ ሰው አስቀድሞ በጌታ አላመነም (ዮሐ 7፥5)፥ ነገር ግን ጌታ ከተነሣ ከጥቂት ቀን በኋላ በምእመናን መካከል ተገኘ። ይህን ልዩነት ያደረገው ጌታ ቢታየው አይደለምን? ያዕቆብ እንደ ጳውሎስ ሆኖ አየው፥ አመነም፥ ከዚያም

በኋላ ደግሞ የሐዋርያት አለቃ ሆነ። (የሐዋ. 12፥17፤15፥13። ገላ 1፥19።) መልእክት የጻፈም እርሱ ነው። (ያዕ. 1፥1።)

ቁ. 12-19። ጳውሎስ ራሱ የቀሩትም ሐዋርያት ወንጌልን በሰበኩ ጊዜ «ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ» ብለው ከሰበኩ ከቆሮንቶስ ምእመናን እንዳንዶቹ «ትንሣኤ ሙታን የለም» ያሉት እንዴት ነው? ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ላይ የሚወቅሰው ይህን ቃላቸውን ነው። ክርስቶስ ተነሥቶአልና ትንሣኤ ሙታን እንዳለ ግልጥ ነው፤ በተቃራኒው ግን ትንሣኤ ሙታን ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣም። የማን ቃል ይርጋ? ወይም ሐዋርያት የሰበኩት ቃል (ቁ. 2) እውነት ነው፥ ወይም የቆሮንቶስ ሰዎች ቃል (ቁ. 12) እውነት ነው፤ ሁለቱም እውነት ሊሆኑ አይችሉም።

ትንሣኤ ሙታን ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣም ክርስቶስም ካልተነሣ የሚከተለው ፍሬ መራራ ነው። «ትንሣኤ ሙታን የለም» የሚሉ ሰዎች ይህን አሰቡን? ክርስቶስ ካልተነሣ፡-1ኛ፥ ሐዋርያት የሰበኩትና የቆሮንቶስ ሰዎች የተቀበሉት ወንጌል ዋጋ የሌለው ነው። 2ኛ፥ ሐዋርያት «እግዚአብሔር ክርስቶስን አስነሥቶታል» ብለው ሲያወሩ እግዚአብሔርን እንደ መክሰስ አደረጉ፤ ነገር ግን ክርስቶስ አልተነሣምና የሐሰት ምስክሮች ሆነው ተገኙ። ሐዋርያው ነገሩን ለማጽናት ብሎ ቃሉን ይደግማል፡-ከቆሮንቶስ ሰዎች እንዳንዶች እንዳሉት ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣም የእነርሱም እምነት ከንቱ ናት። በክርስቶስ የተፈጸመ ነገር የለምና ገና በበደላቸውና በኃጢአታቸው ሙታን ናቸው። (ኤፌ. 2፥ 1።) ክርስቶስም ካልተነሣ 3ኛ ፍሬ፡- በሞት የተለዩአቸው ዘመዶቻቸው ሁሉ ጠፍተዋል! ተስፋ እድርገውላቸው ነበር፤ አሁን ግን ክርስቶስ ካልተነሣ ተስፋቸው ተቆረጠ፥ ጠፍተዋል!

«ትንሣኤ ሙታን የለም» የሚል ትምህርት በእውነቱ መጥፎ ትምህርት ነው! ትንሣኤ ሙታን ከሌለ የሚከተሉት ፍሬዎች እጅግ በጣም የሚያሳዝኑና የሚያስቅቁ ናቸው። እኩሌቶችን በዚህ ክፍል ላይ አይተናል፥ እኩሌቶችንም ደግሞ ከቁ. 29 እስከ ቁ. 34 ድረስ እናያለን። ትንሣኤ ሙታን ከሌለ ክርስቲያኖች ከሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ናቸው። «በወዲያኛው ሕይወት ብፅዕናን እናገኛለን» ብለው ተስፋ በማድረግ ሁሉን ዛሬ ይታገሣሉ (ማቴ. 5፥3-12)፥ ተስፋ የሚያደርጉበት ያ የወዲያኛው ሕይወት ከሌለ ግን መላላታቸው ምንኛ የሚያሳዝን ነው!

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «እንዳንዶቹ፡-ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ?» (ቁ. 12።) እንደዚህ ያሉቱ ከአይሁድ ወገን የመጡት መሆናቸው አይታመንም። ስለምን? ቢሉ፥ ትንሣኤ ሙታን ከጥንት ጀምሮ የጸና የአይሁድ ተስፋ ነበረ። (የሐዋ. 13፥32፡33፤23፥6፤24፥15፤26፥6-8፤28፥20።) «የለም» ያሉት ከአሕዛብ ወገን መጥተው በክርስቶስ ያመኑት ይሆናሉ።

ለ/ «ክርስቶስ ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፥ አምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት።» (ቁ. 14።) በዚህ ቁጥር ላይ፥ ደግሞ በቁ. 16ና 17 ላይ፥ ክርስቶስ ያልተነሣ እንደሆነ የሚከተሉትን ፍሬዎች እናያለን። «ስብከታችን ከንቱ ነው፥ አምነታችሁም ከንቱ ናት፥ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ» ይላል። «ይህስ ስለ ምንድር ነው? ክርስቶስ ለኃጢአታችን እንደ ሞተ ታውቆአልና

ከሙታን ባይነሣ ምን ቁም ነገር አለ?» ቢሉ፥ የክርስቶስ ሞት ጥቅም ያለው ከሙታን ቢነሣ ብቻ ነው። ከሙታን ካልተነሣ ሞቱ ጥቅም የሌለው ነው። ምክንያቱም፦ -1ኛ፥ ክርስቶስ ራሱ «እነሣለሁ» ብሎ ደጋግሞ ተናግሮአል (ማቴ! 16፥21። ዮሐ 2፥19። ማቴ. 27፥63። ሉቃ. 9፥22) መነሣቱም ለአውነተኛነቱ የማረጋገጫ ምልክት ነው። (ማቴ. 12፥38-40። ሮሜ 1፥4።) ስለዚህ ክርስቶስ ከሙታን ያልተነሣ እንደሆነ አርሱ አውነተኛ አይደለም። አውነተኛ አይደለምና አላዳነንም ሊያድነንም አይችልም። ይህም ከሆነ የሐዋርያት ስብከት ከንቱ ነው የቆሮንቶስም ሰዎች አምነት ከንቱ ናት። አነርሱ ክርስቶስ ላይመጣ በፊት እንደ ነበሩ ሁሉ ዛሬም እንዲሁ ናቸው፥ እኛም እንደዚሁ ነን። 2ኛ ትንሣኤው አግዚአብሔር መሥዋዕቱን እንደ ተቀበለ ማስረጃ ነው። (ሮሜ 4፥24:25። የሐዋ. 17፥30:31።) እንግዲህ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን ተገንዝበን (የሐዋ. 2፥24:32፤5፥30-33፤ 10፥40-42። ኤፌ 1፥ 18-22። 1 ጴጥ. 1፥21) አግዚአብሔር ፊጽሞ እንደ ታረቀን እንመን። (2 ቆሮ. 5፥18:19።)

ቁ. 20-28። ትንሣኤ ሙታን ከሌለ ክርስቶስ ያደረገው ሁሉ ለዚህች ሕይወት ብቻ ነውና እኛ ክርስቲያኖች ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን። ነገር ግን አንዲህ አይደለም። አላይ እንዳየነው ሁሉ ክርስቶስ ከሙታን በእርግጥ ተነሥቶአል። «ትንሣኤ ሙታን የለም» የሚሉት ሰዎች ቃል አውነት ቢሆን ኖሮ በዚህ ቃላቸው የሚከተለውን ፍሬ አስበውበታልን? ያስቡበት አይመስልም። አሁን ግን «ክርስቶስ ተነሣ» ሲባል ከዚህ ቃል የሚከተለውን ፍሬ ያስቡ፤ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ ለክርስቶስ የሆኑት (ምእመናን) ደግሞ እንዲነሡ ታውቆአልና! በፋሲካ በዓል በሁለተኛው ቀን አንደ ተደረገው ነገር ነው። በዚያን ዕለት እሥራኤላውያን ለአህላቸው እንደራሴ የሚሆነውን አንድ ነዶ ለአግዚአብሔር ያቀርቡ ነበር። ይህ «በኩራት» ካልቀረበ ከመከሩ አይበሉም ነበር፥ ነዶው (በኩራቱ) ሲቀርብ ግን መከሩ በሞላ ተቀድሶአልና በሉ። (ዘሌዋ. 23፥10-14። ሮሜ. 11፥16።) ያ ነዶ (በኩራት) በኋላ የሚመጣው የመከር አንደራሴ ሆኖ መከሩን ሁሉ አንደ ቀደሰ እንዲሁም ያንቀላፉት በኩራት የሆነው ክርስቶስ (ቆላ. 1፥18) ለአርሱ የሆኑትን ሁሉ አንደራሴ ሆኖ አነርሱን በትንሣኤው ያስከትላቸዋል። አርሱ ቢነሣ አነርሱ ደግሞ ይነሣሉ። ክርስቶስ የሞተ የተነሣም ለዚህ ነው። (ዕብራ. 2፥14።) ሞት በሰው ስለ መጣ ሰው አንደገና የሚነሣ ከሆነ በሰው አንዲነሣ ያስፈልጋል። (ይህንም በማለት ሐዋርያው የክርስቶስን አውነተኛ ትስብአት ይገልጣል።) አዳም ብቻውን አልሞተም፥ ክርስቶስም ብቻውን አልተነሣም። አዳም ሲሞት ለአርሱ የሆኑት ሁሉ አብረው አንደ ሞቱ (ዘፍጥ. 2፥17። ሮሜ. 5፥12)፥ አንዲሁም ክርስቶስ ከሙታን ስለ ተነሣ ለአርሱ የሆኑት ሁሉ ሕያዋን ይሆናሉ። ሆኖም እስከ ፍጻሜው ድረስ ተራ በተራ ይኖራል አንጂ አንዳንዶች ሰዎች እንዳሉት ሰው ሁሉ በአንድ ጊዜ አይነሣም። (2 ጢሞ. 2፥18።) ክርስቶስ በኩራት ሆኖ አስቀድሞ ይነሣል፤ በኋላም፥ አርሱ በዳግም ምጽአቱ ሲመጣ ለአርሱ የሆኑት ይነሣሉ (1 ተስ. 4፥15:16)፤ ከዚያም በኋላ ደግሞ ክርስቶስ መንግሥቱን ለአግዚአብሔር ለአባቱ ያስረከብና ፍጻሜ ይሆናል። ነገር ግን የትንቢት ቃል «እግዚአብሔር ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአል» ብሎአልና ይህ ፍጻሜ ከመሆኑ በፊት ቆይታ የግድ ይኖራል። ስለምን? ቢሉ፥ ተቃዋሚ የሆነውን አለቅነት ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም ከንቱና ባዶ አስኪያደርጋቸው፥ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስኪያደርግ ድረስ ክርስቶስ ሊነግሥ ይገባዋል፥ ቁርጥ የሆነ የአባቱ ፈቃድ ነውና። (መዝ.

8፥6፥109፥1። ኤፌ. 1፥21፥22። ቆላ. 2፥15።) ክርስቶስም ከንቱና ባዶ የሚያደርገው የጓለኛው ጠላት ሞትን ነው። (ቁ. 54።) መቼም «ሁሉን ይገዛል» ሲል አግዚአብሔርን አንዳይገዛ የታወቀ ነው። አምላካዊ ዓላማ (ፍጻሜ) እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ ነውና በፍጻሜ ዘመን ንጉሡ (ልጁ) መንግሥቱን ለአግዚአብሔር ለአባቱ ያስረክባል ራሱም ለአግዚአብሔር ይገዛል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ሊነግሥ ይገባዋል።» (ቁ. 25።) «ይገባዋል» የተባለው በምን ምክንያት ነው? ቢሉ፥ መንገሥን አግዚአብሔር ለመሢሕ የመደበው ሥራ በመሆኑ ነው። (መዝ. 2። ዕብራ. 2፥6-8።) መሢሕና መድኅን ሆኖ ከሚሠራቸው ሥራዎች አንዱ መንገሥ ነው። አግዚአብሔር ክርስቶስን ንጉሥ አድርጎ ሾሞአል፥ አርሱም አለቅነትን ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም፥ ለአግዚአብሔር መንግሥት ጠላት የሚሆነውንም ሁሉ ከንቱና ባዶ አስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋል። መንግሥቲቱ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ብለው መጥምቁ ዮሐንስ፥ ጌታም ራሱ፥ ሐዋርያትም የሰበኩዋት መንግሥት ናት። (ማቴ. 3፥2፥4፥18:23፤10፥7።) ሐዋርያው ጳውሎስም የሰበካት መንግሥት ናት። (የሐዋ. 20፥25።) አኛም የምንጸልይላት መንግሥት ናት። (ማቴ. 6፥10።) የዚህች መንግሥት ንጉሥ ክርስቶስ ነው። (ማቴ. 25፥34:40። ራእ. 11፥15፤12፥10።) ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ የምንልበት ተጨማሪ ምክንያት ይህ ነው። ክርስቶስ ከሙታን ካልተነሣ ይነግሣል የሚል የአግዚአብሔር አላብና ውሳኔ ላይፈጸም በቀረ ነበር።

ለ/ «ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።» በቅዱስ አትናቴዎስ የሃይማኖት ሥርዓት ላይ፡- «የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስም መለኮት አንዲት ናት። ከብራቸውም የተተካከለ ነው። ግርማቸውም የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናት። በዚህችም ሦስትነት መቅደም መከታተል የለም፤ ከባልንጀራውም የሚበልጥና የሚያንስ የለም፤ አየራሳቸው የተተካከሉ ናቸው» ተብሎ ስለ ተጻፈ አንዳንዶች ሰዎች በክርስቶስ መገዛት ነገር ይቸገራሉ። ሆኖም ይህ መቸገራቸው አስፈላጊ አይደለም። ምሥጢረ ሥላሴ ታላቅ ምሥጢር ነው፥ ጠልቀን ልንገባበትም አንችልም። ሆኖም እዚህ ላይ ስለ ሥላሴ መናገሩ አይደለም። አባት ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን አንደ ላከው የተረጋገጠ ነገር ነው። (1 ዮሐ.4፥14) ኢየሱስም «አኮኛል» ብሎ ደጋግሞ አስታውቆአል። (ዮሐ.5፥36፤6፥38-40፤ 11፥42።) ልጅ መሆኑን ሁላችን እናውቃለን። ላኪ ከተላከው፥ አባትም ከልጁ አንደሚበልጥ የማይካድ ነው። ታዲያስ ተላኪው ለላኪ፥ ልጁም ለአባት ቢገዛ መጥፎ ነውን? ሉሪ መጥፎ አይደለም የተገባ ነው አንጂ! የአግዚአብሔር ልጅ ተገድዶ ሳይሆን በገዛ ፈቃዱ ለአባቱ ሲገዛ ሕላዌው ምንም እይቀነስም መለኮቱም በፍጹም አይነካም። (ደግሞ በም. 3፥18-23 ላይ የተጻፈውን ማስገንዘቢያ ተመልከቱ።)

ቁ. 29-34። ከቁ. 12 ጀምሮ አስከ ቁ. 19 ድረስ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ ከሙታን ያልተነሣ አንደሆነ ስለሚከተሉት ፍሬዎች ሲናገር ንበር። ከዚያም ቀጥሎ «ዳሩ ግን ተነሥቶአል!» ብሎ ከመነሣቱ የተነሣ ስለሚከተሉት ፍሬዎች ከቁ. 20 እስከ ቁ. 28 ድረስ በእጭሩ ተናግሮአል። አሁንም ወደ ፊተኛው አላቡ ተመልሶ፥ ትንሣኤ ሙታን ከሌለ ክርስቲያኖች ከሚያደርጉአቸው ነገሮች ብዙዎቹ ከንቱ መሆናቸውን ይገልጣል።

ትንሣኤ ሙታን ከሌለ 1ኛ፥ ስለ ሙታን የሚጠመቁት በምን ምክንያት ነው የሚጠመቁት? ሰው የሚጠመቅበት የወዲያኛውን ሕይወት ተመልክቶ ነው እንጂ በዚህ ሕይወት ጥቅሙን ሁሉ ለማግኘት አያስብም። እንግዲያስ ሙታን ባይነሡና የወዲያኛውም ሕይወት ከሌለ ለምን ይጠመቃሉ? ሉረ ጥምቀት እንኳ የትንሣኤ ሙታን ማስረጃ ነው! 2ኛ፥ ደግሞ፥ ሐዋርያው ከርስቲያኖቹም ዘወትር በሚያስፈራ ኑሮ ለምን ይኖራሉ? ጳውሎስ በሐዋርያነቱ ዘመን ሁሉ በችግርና በመከራ እንደ ኖረ እናውቃለን። (2 ቆሮ. 11፥23-28።) ከርስቲያኖችም በየጊዜው ስደት ሲነሣ «ቀኑን ሁሉ ይገደሉ ነበር፥ እንደሚታረዱም በጎች ተቆጠሩ።» (ሮሜ. 8፥36።) ሐዋርያው ደግሞ በቆሮንቶስ ሰዎች ዘለዓለማዊ መዳን ይመካ በነበረው መጠን በዚያ መጠን በትንሣኤ ሙታን እውነተኛነት እየተመካ ሕይወቱን ዕለት ዕለት ያስረከብ ነበር። (የሐዋ. 20፥24።) ትንሣኤ ሙታን ግን ከሌለ ይህ ሁሉ ለምንድር ነው? በኤፌሶንም እርሱ ሰው ሆኖ የምድር አውሬ ከሚመስለው ጋር ቢታገል ሙታን የማይነሡ ከሆነ ምን ይጠቅመዋል? ሙታን የማ ይነሡ ከሆነ ራሳችንን ከዓለም ተድላ ሁሉ ለምን እንከለክላለን? (ም. 9፥27።) ሕይወታችን ይህችው ብቻ ናትና ሉረ እንብላና እንጠጣ ደስም ይበለን! (ኢሳ. 22፥13። ሉቃ. 12።19፥20።) ነገር ግን አንደዚህ ከቶ አይደለም። ከርስቶስ ከሙታን ተነሥቶአል፥ ትንሣኤ ሙታንም አለ። የቆሮንቶስ ምእመናን ይጠንቀቁ። መናንደር የተባለ ግሪካዊ የቅኔ ሊቅ ታይስ በሚባለው መጽሐፍ ላይ ጽፎ እንደ ነበር «ከመጥፎ ባልንጀራ ጋር መዛመድ የራስን አመል ያጠፋል።» ትንሣኤ ሙታንን ከሚክዱ ሰዎች ጋር አይዛመዱ፥ የተዛመዱ እንደሆነ ክርስቲያናዊ አመላለሳቸው ሳይረክስ አይቀርም። እውነት ያልሆነ ዶክትሪን (ትምህርት) እውነት ወዳልሆነ አመላለስ (ሞራል) ያደርሳል ማለት ነው። ስለዚህ ክሰካር መንፈላቸው በጽድቅ ይንቁ፥ ወደ አእምሮአቸውም ይመለሱ። (ሮሜ. 13፥11-14። 1 ተስ. 5፥6-8።) የእነዚህ ሰዎች ጥፋት እግዚአብሔርን ባለማወቃቸው ነው። ታላቅነቱንና የማዳኑን ፍጹምነት አላወቁም። (ሮሜ! 1፥20፥21። ማቴ. 22፥29።) ምእመናን የተባሉት ከሃዲዎች ሆነው ሲገኙ ምንኛ ያሳፍራል! ጳውሎስ ሊያሳፍራቸው አልወደደም፥ ነገር ግን በእፍረት ወደ እውነት ሊመልሳቸው ሲል ይህን ጊዜ በግልጥ ጽፎአል። (ም. 4፥14፤6፥5።)

ግስገንዘቢያ።

ሀ/ «ስለ ሙታን የሚጠመቁ።» (ቁ. 29።) ሐዋርያው በጻፈው በግሪክ ቋንቋ እንዲህ ተጽፎአል፥ ፍቹን ለማወቅ ግን ሰው ሁሉ ተቸግሮአል። «ስለ ሙታን» ወይም «በሙታን ፋንታ» መጠመቅ ምን እንደ ሆነ አናውቅም። አንዳንዶች መምህራን፡- በስደት ወይም በበሽታ በአደጋም ምክንያት ሳይጠመቁ ለሞቱት ከርስቲያኖች ከርስቲያናዊ ዘመዶቻቸው ይጠመቁ ነበር ይላሉ፥ በ2ኛውም መቶ ዓመት እንዲህ ይደረግ እንደ ነበር እናውቃለን፤ ሆኖም የተደረገው በመናፍቃን መካከል ነው እንጂ በከርስቲያናች ዘንድ አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስስ? እርሱ አንዱ ሰው ስለ ሌላው እንዲጠመቅ የሚፈቅድ ይመስላል? ከቶ አይመስልም! ለእነዚህ ቃሎች ሌላ ልዩ ልዩ ፍች ተሰጥቶአል፥ ነገር ግን የሚታመንበት ወይም የሚያጠግብ ፍች የለም። ግዕዙ «ወእመ አኮሰ ከመ ምንትኑ ያጠምቁ አኮኑ ከመ ያሐይው ምውታን። ወእመስኬ ኢይትነስኡ ምውታን ለምንትኑ አንከ ያጠምቁ» ይላል። ይህም ‹፥እንዲህ ግን ካልሆነ እንደምን ያጠምቃሉ? ሙታን እንዲነሡ አይደለምን? ሙታንማ ካልተነሡ አንግዲያ ለምን ያጠምቃሉ?» ማለት ነው። ይህ የተሻለ ፍች

ቢሰጥም ግሪኩን አይተረጉምም፥ ከየት ዘንድ አነደ ተገኘም አልታወቀም። ይሁን እንጂ፥ ሰው የሚጠመቀው ትንሣኤ ሙታን እንዳለ ስለሚያምን እንደ ሆነ እርግጥ ነው። (ሮሜ 6፥3፡5።) ትንሣኤ ሙታን ግን ከሌለ ጥምቀት ለምንድር ነው? ቀሳውስትም ለምን ያጠምቃሉ።

ለ/ «በኤፌሶን ከአውሬ ጋር ከታገልሁ።» (ቁ. 32።) «አውሬ» የተባለው በእርግጥ አውሬ ነውን ወይስ ሰው ነው? ከርስቲያናችን ባሳደጉ ጊዜ የሮም መንግሥት ባለ ሥልጣናች ከርስቲያናችን ትይንት እድርገው በሕዝብ ሁሉ ፊት ከልዩ ልዩ አራዊት ጋር እንዲታገሉ ግድረጋቸው የታወቀ ነገር ቢሆንም ቅዱስ ጳውሎስ እንደዚህ ከአራዊት ጋር የታገለ አይመስልም። ምክንያቱም፥ 1ኛ፡ጳውሎስ የሮሜ ዜግነት ነበረው። (የሐዋ. 16፥37፤22፥25-28) በሮማውያንም እስረኞች ዘንድ እንዲህ እጅግ አይደረግም ነበር። 2ኛ፡- ከተደረገ ኖሮ ጳውሎስ በ2 ቆሮ. 11፥23-33 በተጻፈው ዝርዝር ውስጥ በጨመረው ነበር፥ ሉቃስም በሐዋርያት ሥራ ላይ በጻፈው ነበር። የለም፥ ከአውሬ ጋር ሳይሆን አውሬ ከሚመስል ሰው ጋር የታገለ ይመስላል። «በኤፌሶን» ስለ ተባለ ብዙዎች ሰዎች በሐዋ. 19፥23-41 ላይ የተጻፈውን ነገር አይተው «አውሬው ድሜጥሮስ ነው» ይላሉ። ነገር ግን ይህ እውነት ሊሆን አይችልም። ስለምን? ቢሉ፥ ያ ሁከት ገና አልተደረገም ሐዋርያውም ይህን የቆሮንቶስን መልእክት ሊጽፍ በኤፌሶን ተቀምጦአል ሊስነብትም አስቦአል።(ም. 16፥8።) ያ የኤፌሶን ሁከት ግን በተደረገ ጊዜ ጳውሎስ ወዲያውኑ ከከተማው ወጣ። (የሐዋ. 20፥1።) ስለዚህ ከአውሬ ጋር መታገሉ በ2 ቆሮ. 1፥8-11 ላይ የተመለከተው ነገር ይሆን ይሆናል እንላለን።

ቁ. 35-50። በከርስቶስ ትንሣኤ መሠረት ላይ ሐዋርያው ትንሣኤ ሙታን እንዳለ በፍጹም አስረድቶአል። አሁን ግን «ትንሣኤ ሙታን የለም» ከሚሉ ሰዎች አንዱ፡- ይህስ እንዴት ይቻላል? ሥጋቸው በሰብሶ ወይም ተቃጥሎ ጠፋ፥ እንግዲያስ እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? ብሎ ይከራከር ይሆናል፥ ይህንም ሲያደርግ ላነሣሁት ክርክር መልስ መስጠት ያስችግራል በማለት ጥበቡንና አስተዋይነቱን እንደሚያሳይ ያስብ ይሆናል። ወይም ምናልባት ሌላ ሰው ጥያቄውን ያቀርብ ይሆናል፥ ነገሩ የሚያስችገር ሆኖ ይታየዋልና። የሆነ ሆኖ፥ ሐዋርያው ሁለቱንም ሞኝ ይላቸዋል። ስለምን? ቢሉ፥ ነገሩ የሚያስችግር ወይም የማይቻል ሳይሆን በየዕለቱ የሚደረግና እነርሱ ራሳቸው የሚያምኑበት ነገር ነው! እነርሱም እንደምን? ቢሉ፥ ሐዋርያው ክቁ. 36 ጀምሮ እስከ 41 ድረስ የምንነግበት አካል ልክ እንደ ዛሬው አካላችን እንዲሆን አስፈላጊ አለመሆኑንና ልዩ ልዩ ዓይነት አካሎች መኖራቸውን በዘር ምሳሌ ያለረዳል። እነኘህ የቆሮንቶስ ሰዎች የሚዘሩቱ ዘር አስቀድሞ ይበሰበስ የለምን? ከበሰበሰም በኋላ ተመልሶ ሕያው ይሆን የለምን? እንዴት ይነሣል? ወይስ በምን ዓይነት አካል ይመጣል? የሚዘሩት መቼም ቅንጣት ብቻ ነው። የሚነሣውስ? የሚነሣውማ ሌላ አካል ነው! የሚነሣው አካል የተዘራው ዘር አካል ነው፥ ሆኖም ልዩ ነው፥ የሚነሣው ያው የተዘራው አይደለም። ያ ቅንጣት በመሬት ገብር ይበሰብሳል፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ወደደ ሁሉን አካልን ይሰጠዋል፥ በዚያም አዲስ አካል ይነሣል። የአህልም አካል ሁሉ አንድ ዓይነት አለመሆኑ ታውቆአል፤ የስንዴ አለ፥ የገብስ አለ፥ የማሽላም አለ፤ አካሎቹ ልዩ ልዩ ናቸው። በዘሮች ዘንድ እንደ ሆነው ሁሉ እንዲሁም በሰው በእንስሳ በወፍ በዓሣም ዘንድ ነው፤ ሥጋ ሥጋቸው ሌላ ሌላ ነው። እንደዚህም ደግሞ ለሰማይ የሚሆን አካል አለ፥ ለዚህችም

ምድር የሚሆን አካል አለ። በሰማይ አካሎች፥ በፀሐይና በጨረቃ በከዋክብትም መካከል የክብር ልዩነት እንዳለ እንዲሁም በምድራዊ አካልና በሰማያዊ አካል መካከል የክብር ልዩነት አለ። ስለዚህ ብዙ ዓይነት አካሎች እንዳሉ እናያለንና ሰው ከሙታን የሚነሣበት አካል ፈጽሞ እንደ ዛሬው አካል እንዲሆን አሰፈላጊ አለመሆኑን እንገነዘባለን።

የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንደ ዘር ነገር ነው። የሰው ሥጋ እንደሚዘራው ዘር ሆኖ በመበስበስና በውርደት በድካምም ይቀበራል፥ ባለመበስበስና በክብር በኃይልም ይነሣል። የሚቀበረው የቅንጣት ዓይነት አካል ነው፥ የሚነሣው የእህል ዓይነት አካል ነው። የሚቀበረው አካል ለዚህ ለምድራዊ ሕይወት የሚሆን ፍጥረታዊ አካል ነው የሚነሣው ሌላ፥ እርሱም ለመንግሥተ ሰማያት የሚሆን መንፈሳዊ አካል ነው። ምነው? መንፈሳዊ አካል አለ ወይ? ቢሉ፥ አዎን አለ! ፍጥረታዊ አካል እንዳለ ሁሉ እንዲሁም መንፈሳዊ አካል አለ። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ጋር የሚስማማ ነው እንጂ የጳውሎስ ቃል ብቻ አይደለም። ነገሩ እንደ አዳምና እንደ ክርስቶስ ነገር ነው። መጽሐፍ እንደሚለው (ዘፍጥ. 2፥7) «አዳም ሕያው ነፍሪ ሆነ።» እርሱም ማለት፥ አዳም ሕይወትን የተቀበለ ፍጥረት ነው። ኋለኛው አዳም ግን፥ እርሱም ክርስቶስ፥ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ እርሱም መንፈሳዊ ሕይወትንም ትንሣኤንም። (ዮሐ. 5፥21-29፤ 11፥25፥26) ይህን እንጂ ፍጥረታዊው (ሕያው ነፍሪው) ያን ጊዜ እንደ ቀደመ ሁሉ እንዲሁ ዛሬ የሚቀበረው ፍጥረታዊው አካል ይቀድማል፥ ቀጥሎም የምነሣው መንፈሳዊ አካል ይመጣል። አዳም የወጣው (ሥሩ፥ አብነቱ) ከመሬት ነውና (ዘፍጥ. 3፥19) አካሉ መሬታዊ ነው፥ ልጆቹም መሬታውያን ናቸው የመሬታውያንም ልብስ (አካል) ለብሰዋል። ከርስቶስ የመጣው ከሰማያት ነው (ዮሐ. 3፥2፥13፤8፥23) የትንሣኤ አካሉም ሰማያዊ ነው፥ ለእርሱ የሆኑትም ሰማያውያን ናቸው (1 ዮሐ. 3፥2። 2 ቆሮ. 5፥17) መልካቸውም ተለውጦ የሰማያውያን ልብስ (አካል) ይለብሳሉ። (ፊልጵ. 3፥21።) አንዳንዶች ሰዎች ይህ የአሁኑ አካላችን እንዲነሣ ይመስላቸዋል፥ ነገር ግን ይህ ከቶ ልክ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህ ሥጋችን መንግሥተ ሰማያትን ሊወርስ እንደማይችል በግልጥ ተናግሮአል። ይህ ለጊዜው ብቻ የሚሆን የሚበሰብስም አካላችን ዘለዓለማዊነትን ከቶ ሊወርስ አይችልም።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።» (ቁ. 44።) በዚህ ክፍል በሁሉ በኩል ሰው ከሙታን ሊነሣ ባለ አካል ሆኖ እንዲነሣ እናያለን። እራቁቱን የሆነ መንፈስ ብቻ መሆኑ አይደለም፥ ልብስ ይኖረዋል እንጂ። ጳውሎስም በ2 ቆሮ. 5፥1-5 ላይ ይህን ልብስ «ድንኳን» ይለዋል። ይህ ልብስ (አካል) የአሁኑ ዓይነት ሥጋችን አይሆንም፤ ይሁን እንጂ አካል ነው። በዚህ ዓለም ላይ የአዳም ልጆች ነንና የዘር አባታችንን የአዳምን መልክ ለብሰናል፥ ፍጥረታዊም አካል አለን። በዚያ ጊዜ ግን እኛ ለክርስቶስ የሆንን ሁሉ የዘር አባታችንን የክርስቶስን መልክ እንለብሳለን፥ መንፈሳዊም አካል ይኖረናል። ስለ አካሉ ዓይነት ግን የተገለጠ ብዙ ነገር የለም። ይህን እንጂ የምንቀበለው አካል የክርስቶስን የትንሣኤ አካሉን ሳይመሳሰል አይቀርም። የክርስቶስ የትንሣኤ አካሉ የዱሮ አካሉን ቢመስልም እንድ አልነበረም። ሰዎች ሲያዩ ወዲያውኑ አላወቁትም። (ሉቃ. 24፥15፡16። ዮሐ 20፥14።) የትንሣኤ አካሉ መንፈሳዊ ሆኖ ግዙፍ በሆነው

በር አልተከለከለም (ዮሐ. 20፥19)፥ ከለውም ዓይን ይጠፋ ነበር። ይሁንና እውነተኛ አካል ነበረ እንጂ መንፈስ ብቻ አልነበረም። (ሉቃ. 24፥39።) የተገለጠላቸው ኢየሱስ ራሱ ነበር፥ ሌላ አልነበረም፥ በእጆቹና በእግሮቹም የችንካር፥ በጎኑም የጦር ምልክቶች ገና ታይተዋል። (ሉቃ. 24፥38-40። ዮሐ 20፥ 27።) ይህ የትንሣኤ አካሉ ደግሞ ወደ ሰማይ ሊያርግና ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ ቻለ (ሉቃ. 24፥51። የሐዋ. 1፥9)፥ ኢየሱስም በዚያው አካል ተመልሶ ይመጣል። (የሐዋ. 1፥11።) እርሱ እንደ ሆነው እንዲሁ እኛም እንሆናለን። በተነሣን ጊዜ አካል ይኖረናል፥ አካላችን ግን መንፈሳዊ ይሆናል እንጂ የዛሬ አካል አይሆንም።

ለ/ «ኋለኛው አዳም ... ሁለተኛው ሰው።» (ቁ 45፥47።) ከርስቶስ «ኋለኛው አዳም» እና «ሁለተኛው ሰው» የተባለው በምን ምክንያት ነው? የሚል ሰው ይኖራል። አዳም የዘር ወይም የትውልድ አባት እንደ ሆነ እንዲሁም ከርስቶስ የዘር ወይም የትውልድ አባት ነው። (ቁ. 21፥22። ሮሜ 5፥12-19።) የሚሞተውን አካላችንን ከፊተኛው ሰው እንዳገኘን እንዲሁም የማይሞተውን ከሁለተኛው ሰው እናገኛለን። ፊተኛው አዳም ሕያው ነፍስ ለሆነ ሁሉ አባት እንደ ሆነ እንዲሁም ኋለኛው አዳም የትንሣኤን አካል ለሚያገኙት ሁሉ አባት ነው። ኋለኛው አዳም የተባለበት ምክንያት ከርሱ በኋላ የሰውን ሁሉ ነገር የሚነካ ስለማይመጣ ነው።

ቁ. 51-58። ሐዋርያው ቀድሞ ምሥጢር የነበረውን በሐዋርያት ዘመን ግን በእግዚአብሔር የተገለጠውን ነገር አሁን ይነገራቸዋል። በማቴ. 24፥31 እና በ 1 ተስ. 4፥13-17 ላይ የተጻፈችው ነገር ነው። ነገሩም ይህ ነው፡- «ከሞት የሚቀር የለም» የተባለው ቃል እውነት አይደለም። ምነው? ቢሉ፥ እኛ ለክርስቶስ የሆንን ሰዎች ሁላችንም በሞት አናንቀላፋም። ከርስቶስ ተመልሶ ሊመጣ እንዳዶቻችን ገና በሕይወት እንሆናልን። በዚያን ጊዜ እንሞትም፥ ነገር ግን እንደ ሄኖክና እንደ ኤልያስ ሆነን ወደ ሰማይ እንነጠቃለን። (ዘፍጥ. 5፥24። 2 ነገሥ. 2፥ 11።) ይሁን እንጂ ይህ አሁን የለበሰነው ሥጋ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ አይችልምና (ቁ. 50) ሁላችን በቅጽበተ ዓይን ተለውጠን መንፈሳዊ አካላችንን መልበስ የግድ ያስፈልገናል። በዚያን ጊዜ በክርስቶስ አምነው የሞቱቱ መንፈሳዊ አካላቸውን እንደ ለበሱት ይነሣሉ፥ ገና በሕይወት ያሉቱም ላይሞቱ ወዲያውኑ ይለወጣሉ። ይህም ሊሆን መጨረሻው ጠላት ተሸሮአልና (ቁ. 26) እንደ መጽሐፉ ቃል ሁሉ መጨረሻው ድል ተገኘ። (ኢሳ. 25፥8። ሆሴ. 13፥14።) ይህም ቤዛነት የተባለው የመዳናችን ፍጻሜ ነው። (ም. 1፥30፥ ሮሜ. 8፥23።) አንድ ሰው፡- ነቢዩ ሆሴዕ «መርዝ» ወይም «መውጊያ» ሲል ምን ማለቱ ነው? ቢል፥ ጳውሎስ በቁ. 56 ላይ የነቢዩን ቃል ይተረጉማል። ኃጢአት መርዝ የሞላበት የጊንጥን መንደፊያ መስሎ ሞትን ያሰመርዛል። ለኃጢአትም ኃይል የሚሰጥ ሕግ ነው። (ሮሜ. 7፥7-11።) እንደምን? ቢሉ፥ ሕግ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ እያስታወቀን ያንን ፈቃድና ትእዛዝ ለመፈጸም ኃይል ስለማይሰጠን የሁላችን ፈራጅ በመሆኑ ነው። ነገር ግን በክርስቶስ የኃጢአት ኅይል ከሆነ ከሕግ ስለ ተፈታን (ሮሜ. 7፥6። ገላ. 3፥13። ቆላ. 2፥14) በክርስቶስም የሞት መውጊያ የሆነ ኃጢአት ስለ ተወገደ (ዮሐ. 1፥29) ድል ለእኛ ተሰጥቶአል እንጂ ሞት ዛሬ በእኛ ላይ ድሉን ሊነሣ አይችልም። ሞትንና ሲኦልን አስከናሽንፍ ድረስ ፍጹም የሆነውን ደኅንነት በጌታችን

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ለዘላለም ይሁን። (ሮሜ. 6፥23፤ 8፥37።)

ስለዚህ፥ ትንሣኤ ሙታን ስላለ፥ ሰውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በሞትና በሲኦል ላይ ድል አግኝቶ ለዘላለም ስለሚኖር፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ለጌታ የሚሠሩት ሥራ፥ ለአርሱም የሚጋደሉት ገድል ከንቱ እንዳይደለ አሁን አውቀዋልና (2 ጢሞ. 2፥7፡8) በሐሰት ትምህርት (ቁ. 12) ላይነቃነቁ በጌታ ሥራ የሚተረፈረፉ ይሁኑ።

ግስገንዘቢያ።

ሀ/ ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ ላይ ስለ ትንሣኤው ሕይወት የተናገረውን ቃል እንገንዘብ። ሐዋርያው ከዛሬ ሕይወታችን ይልቅ የወደፊቱ ሕይወት እንደሚሻል ያረጋግጣል። የዚያ ኑሮ ሕይወት በሁሉም በኩል እንደሚበልጥ እንጂ ከመልካም ነገር እንድም እንደማያንስ እናምናለንን? ብዙዎች ሰዎች ስለዚያ ሕይወት ሲያስቡ ጥላዊ የማይጨበጥ ነገር ይመስላቸዋል። «እርስ በርሳችን እንተዋወቅም፥ አዚህ ላይ የተደሰትንበት ሁሉ ይቀራል» ብለው ያስባሉና ይፈሩታል፥ ወደዚያም ለመሄድ አይናፍቁም። (ፊልጵ. 1፥23።) አግዚአብሔር ግን ለልጆቹ ያሰበውና ያስናዳው ነገር እንደዚህ አይደለም። የተሻለውን አሰናድቶአል እንጂ ያነሰውን ከቶ አይደለም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፥ በተለይም በመጨረሻው ክፍል ላይ፥ ከሞት አንቅልፍ በኋላ የምናገኘው ሕይወት ከዚህ ከለመድነውና ከወደድነው ሕይወት በክብሩ ከልክ ያለፈ አጅግ በጣም እንደሚበልጥ ተገልጦአል። (ሮሜ 8፥18፡23። 1 ቆሮ. 2፥9።) አዚህ በዚህ ዓለም ላይ የምናገኘውና የምናየው ነገር ሁሉ ሙሉና ፍጹም ላይሆን በሰማያት ላለው ነገር ምሳሌና ጥላ ብቻ ነውና አዚህ ላይ ያገኘውን ሁሉ አዚያ፥ እውነተኛ ሆኖ፥ በበለጠና በገነነ መጠን እናገኘዋለን። (ቆላ 2፥17። ዕብ 8፥5፤ 9፥23፤ 10፥1።) አውነተኛ ደስታና ሕይወት የዚህች ዓለም ሳይሆን የዚያች ነው። በክርስቶስና ለክርስቶስ ለሆኑት ሁሉ የሞት አንቅልፍ ወደ በለጠና ወደ ተሻለ፥ ወደ አውነተኛና ወደ ተትረፈረፈ ሕይወት የሚያደርስ በር ብቻ ነው። ሰው በቤቱ በር አልፎ ክቤት ጨለማና ወሰን ወጥቶ ወደ ውጭው ብርሃንና ነፃነት እንደሚደርስ አንዲሁም ለክርስቶስ የሆነ ሰው በሞት እንቅልፍ በር አልፎ ወደ ተዘጋጅለት ደስታ ይገባል። (ማቴ. 25፥34።) ለዚያም ሰው «ከሁሉም ይልቅ አጅግ የሚሻል ነው።» (ፊልጵ. 1፥23።) አንባቢ ሆይ፥ በአርስዎ ዘንድ እንደምን ይሆን ይሆን? የክርስቶስ ነውትን?

ለ/ «የጌታ ሥራ።» (ቁ. 58።) የጌታን ሥራ ለሚሠራ ሰው የሚረባ ዋጋ በእውነት አለን? እንዲህ ያለ ሰው በማቴ. 5፥ 3-12 ላይ የተጻፈውን እየተመለከተ ከወጣትነት ዘመኑ ጀምሮ አስከ ሽምግልናው ድረስ በሚበዙት ሰዎች ዘንድ የተናቀ ሆኖ በችግርና በውርደት ይኖራል። «ምነው፥ ሌላ አንዳች የሚረባ ሥራ ቢይዝ አይሻልምን? ከዚህ ከጌታ ሥራ ምን ያገኛል?» ብሎ ዓለም ይገምተዋል ይመክረውማል። የጌታን ሥራ የያዘ ሰው በሐዋርያው በኩል የመጣውን የጌታን ቃል ያስብ፡- «ድካማችሁ በጌታ ከንቱ አንዳይሆን አውቃችኋል።» አይዘህ፥ ወንድሜ ሆይ! የማይታየውን አንደምናይ አድርገን አንጸናለንና (ዕብ 11፥27) ድካምህ በጌታ ከንቱ አይሆንም።

* * *

ምዕራፍ 16።

1፤ ለቅዱሳንም ገንዘብን ስለ ማዋጣት፥ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደነገግሁት አናንተ ደግሞ አንዲሁ አድርጉ። 2፤ እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ አንዳይሆን፥ ከአናንተ አያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ 3፤ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ። ስመጣም ማናቸውም ቢሆኑ የታመኑ የሚመስሉአችሁ ሰዎች ቸርነታችሁን ወደ ኢየሩሳሌም ያደርሱ ዘንድ ደብዳቤ ሰጥቼ አልካቸዋለሁ፤ 4፤ እኔ ደግሞ ልሄድ የሚገባኝ ብሆን ከእኔ ጋር አብረው ይሄዳሉ።

5፤ በመቄዶንያም ሳልፍ ወደ አናንተ አመጣለሁ፤ በመቄዶንያ 6፤ አድርጌ አልፋለሁና፥ አናንተም ወደምሄድበት ወደ ማናቸውም ሰፍራ በጉዞዬ አንድትረዱኝ ምናልባት በአናንተ 7፤ ዘንድ አቆይ ወይም አከርም ይሆናል። አሁን እግረ መንገዴን ላልፍ ልኅበኛችሁ አልወድምና፤ ጌታ ቢፈቅደው የሆነውን ዘመን በአናንተ ዘንድ ልሰነብት ተስፋ አደርጋለሁና 8፤ በኤፌሶን ግን አስከ በዓለ ኃምሳ ድረስ አሰነብታለሁ። 9፤ ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው።

10፤ ጢሞቴዎስም የመጣ እንደ ሆነ በአናንተ ዘንድ ያለ ፍርሃት አንዲኖር ተጠንቀቁ፤ አንደ አኔ ደግሞ የጌታን 11፤ ሥራ ይሠራልና፤ አንግዲህ ማንም አይናቀው። ነገር ግን ከወንድሞቹ ጋር አጠብቀዋለሁና ወደ አኔ ይመጣ ዘንድ በሰላም በጉዞው እርዱት።

12፤ ስለ ወንድማችን ስለ አጵሎስ ግን ከወንድሞቹ ጋር ወደ አናንተ ሊሄድ አጅግ አድርጌ ለምኘው ነበር፤ ዛሬም ለመምጣት ከቶ ፈቃድ አልነበረውም፥ ሲመቸው ግን ይመጣል።

13፤14፤ ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ፥ ጎልምሱ ጠንከሩ። በአናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን። 15፤ ወንድሞች ሆይ፥ የእስጢፋናስ ቤተ ሰዎች የአካይያ በኩራት እንደ ሆኑ ቅዱሳንንም ለማገልገል ራሳቸውን 16፤ እንደ ሰጡት ታውቃላችሁ፤ እንደ እነርሱ ላሉትና አብሮ ለሚሠራ ለሚደክምም ሁሉ አናንተም አንድትገዙ እለምናችኋለሁ። 17፤ በእስጢፋናስና በፈርዶናጥስ በእካይቆስም መምጣት ደስ ይለኛል፥ አናንተ ስለሌላችሁ የጎደለኝን ፈጽመዋልና፤ 18፤ መንፈሴንና መንፈላችሁን አሳርፈዋልና። እንግዲህ አንደነዚህም ያሉትን አወቁአቸው።

19፤ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። አቂላና ጵርስቅላ በቤታቸው ካለች ቤተ ክርስቲያን ጋር 20፤ በጌታ እጅግ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ።

21፤ እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላምታ በገዛ አጂ ጽፌአለሁ። 22፤ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ 23፤ ይሁን። ጌታችን ሆይ፥ ና። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከአናንተ 24፤ ጋር ይሁን። ፍቅሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሁላችሁ ጋር ነው። አሜን።

* * *
* * * * * *

6ኛ ክፍል።

(ም. 16።) ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ።

ለቅዱሳን ገንዘብን ስለ ማዋጣትና ስለ አድሎስ መምጣት።

ምዕራፍ አሥራ ስድስት።

ሐዋርያው ወደ መልእክቱ ፍጻሜ ደርሶአል፤ ነገር ግን በዚያ የቆሮንቶስ ሰዎች በጻፉለት ደብዳቤ ላይ ሁለት ጥያቄዎች ገና ቀርተዋልና መልእክቱን ከመጨረሱ በፊት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። ጥያቄዎቹ 1ኛ፥ ስለ አስተዋጽኦ ገንዘብ፤ 2ኛ ስለ አድሎስ መምጣት ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ እርሱ ከአቋቋማቸው አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሁሉ በኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች መካከል የነበሩትን ድሆች ስመርዳት ገንዘብ ለማጠራቀም ቆርጦ ነበር። (ሮሜ. 15፥ 25-28።) ይህን ያደረገው የኢየሩሳሌም ቅዱሳን ከቀሩት ክርስቲያኖች ይልቅ ድሆች ስለ ነበሩ እንደ ሆነ፥ ወይም እርሱ በአሕዛብና በአይሁድ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረውን አንድነት ለመግለጥ ስለ ወደደ እንደ ሆነ እናውቅም፤ ነገር ግን ጳውሎስ ድሆችን ያለብ ዘንድ ሁልጊዜ እንደ ተጋ እናውቃለን። (ገላ. 2፥10።) አንዳንዶች መምህራን ደግሞ የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች በተለይ ድሆች የሆኑ በእስጢፋኖስ ነገር በተነሣው ስደት ምክንያት ነው ይላሉ። (የሐዋ. 8፥1።) የሆነ ሆኖ ሐዋርያው ራሳቸው ድሆች ከሆኑ ከመቄዶንያ ሰዎች እንኳ እየተቀበለ ይህን አገልግሎት ወደ ግብ እንዳደረሰው እናውቃለን። (2 ቆሮ. 8፥1-4፤9፥1፤2፥11። የሐዋ. 24፥17።) በዚያ በቆሮንቶስ ሳለ ስለዚህ አስተዋጽኦ አጫውቶአቸው ይሆናል፥ እነርሱም አሁን በጻፉት ደብዳቤ ላይ «ለኢየሩሳሌም ቅዱሳን ገንዘብ ስለ ማዋጣት ነገር እንዴት ብናደርግ ይሻላል?» ብለው ጠይቀውት ይሆናል። መጀመሪያው ጥያቄ ይህ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ፥ በመልእክቱ እንዳየን ሁሉ በመካከላቸው በተገኘ ክርክርና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጊዜ በተደረገው ጥፋት ምክንያት የቆሮንቶስ ሰዎች ተቸግረዋልና አድሎስ ይመጣላቸው ዘንድ የጠየቁ ይመስላል። 9ቁ. 12።)

ቁ. 1-4። ስለ እርዳታ ገንዘብስ፥ ጳውሎስ በገላትያ ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ዘዴውን ከዚህ በፊት ገልጦ ነበር፥ የቆሮንቶስም ሰዎች እንደ እነርሱ ያድርጉ። እሑድ እሑድ ከሳምንት ገቢ እያስቀሩ እርሱ እስኪመጣ ድረስ ገንዘባቸውን ለብቻው ያስቀምጡት። ሐዋርያው ሲመጣ በሕዝበ ክርስቲያን የተመረጡት የታመኑ ሰዎች ከእርሱ ዘንድ ወረቀት ተቀብለው የተጠራቀመውን ገንዘብ ወደ ኢየሩሳሌም ያድርሱ። ጳውሎስም ራሱ ምናልባት ወደዚያ መሄድ በድንገት ቢኖርበት ወረቀት አያስፈልጋቸውም፥ ከእርሱ ጋር ይሄዳሉ እርሱም ይነግርሳቸዋል።

ማስገንዘቢያ።

ሀ/ «ለቅዱሳን ገንዘብ ስለ ማዋጣት።» (ቁ. 1።) «ቅዱሳን» የተባሉቱ እነማን እንደ ሆኑ ከዚህ በፊት አይተናል። (ም. 1፥1-3። ማስገንዘቢያ ሀ።) «ቅዱሳን» የተባሉቱ

በክርስቶስ ያመኑትና ለእርሱ የተለዩት ናቸው። ሐዋርያውም እዚህ ላይ የሚናገረው «ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ» ወይም «ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት» ምጽዋትን ስለ መስጠት ሳይሆን በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ለነበሩት ድሆች ከርስቲያኖች የእርዳታን ገንዘብ ስለ ማዋጣት ነው።

ለ/ «ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት።» (ቁ. 1።) ገላትያ እንደ ቆሮንቶስና እንደ ኤፌሶን፥ እንደ ፊልጵስዩስና እንደ ተሰሎንቄም ከተማ ሳይሆን አገር ነው። ገላትያ ዛሬ ቱርክ በሚባል አገር ውስጥ ተገኝቶ በዚያ ዘመን በሮማ መንግሥት ውስጥ አንድ ጠቅላይ ግዛት ነበረ። በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ አያሌ አብያተ ክርስቲያናት ትቋቋመዋልና ወደ ገላትያ ሰዎች የተጻፈው መልእክት ወደ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይጻፍ ወደ አያሌዎች እንደ ተጻፈ በገላ. 1፥2 ላይ እናያለን። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የት የት እንደ ነበሩ በእርግጥ ባናውቅም በአንጾኪያ፥ በኢቆንዮን፥ በልስጥራንና በደርቤን ሳይሆኑ አይቀሩም። (የሐዋ. 13፥14፥48-52፤ 14፥1፥5-7።)

ሐ/ «ከእናንተ እያንዳንዱ።» (ቁ. 2።) በመቅድሙ ላይ «ስለ ገንዘባችንስ? ለቤተ ክርስቲያን መስጠት በእውነቱ ይገባናልን?» ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ መልሱ ይኸው ተገኘ 1 ይገባናል። እውነት ነው፥ ሐዋርያው ጳውሎስ እዚህ ላይ በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ለነበሩት ድሆች ገንዘብ ስለ ማዋጣት ይናገር ነበር። ይሁንና ዛሬ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አስፈላጊ እንደ ሆነና ክርስቲያን ሁሉ መስጠት እንደሚገባው አይጠረጠርም። ይኸውም ለባለጠጋዎች ብቻ ሳይሆን «ከእናንተ ለእያንዳንዱ» እንደ ተባለ ልብ እናድርግ!

መ/ «በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን።›› (ቁ. 2።) የቀድሞ ክርስቲያናች አሁንን እንዳከበሩት የሚያመለክት ይህ መጀመሪያ ምልክት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ «በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን አስቀርታችሁ አስቀምጡ» በማለት ያ ቀን ለጌታ ልዩ አገልግሎት ተመድቦ እንደ ነበር ያስረዳል። ይህም «የጌታ ቀን» በኢየሱስ መገለጥ ምክንያት ከመጀመሪያ ጀምሮ እንደ ተከበረ በፍጹም ታውቆአል። (ዮሐ 20፥19፥26። የሐዋ. 20፥7። 1 ቆሮ. 16፥2። ራእ. 1፥10።) ከብዙ ዘመን በኋላ የሮማ ጳጳስ ይህን ቀን አጸና ቢባል፥ እውነት ነው፤ ሲያጸናም ከዚያ በፊት የነበረውን አጸና ማለቱ አይደለምን? ነው! አንዳንዶች ሰዎች ግን «ከርስቲያኖች ይህን ቀን ሲያከብሩ ሕግን ያፈርሳሉ» ይላሉ። እንደምን ተብሎ? ዘፍጥ. 2፥2፥3 እንደዚህም በዘፀአ. 20፥8-11 ላይ ሰው ስድስት ቀን ሠርቶ ሲያበቃ ስባተኛውን እንዲያከብር ታዝዞአል። ታዲያሳ? ክርስቲያኖች የሚያደርጉት ይኸው አይደለምን? ነው! ሕጉን መቼ አፈረሱ? ሉረ አላፈረሱም! መጽሐፍ ቅዱስ «ስድስት ቀን ከሠራችሁ በኋላ ሰባተኛውን አክብሩ» ይላል እንጂ «ቅዳሜ ዕለት አረፉ» አይልም።

ሠ/ «እንደ ቀናው መጠን።» (ቁ. 2።) ምን ያህል መስጠት ይገባናል? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ይህ ነው። ሰው ሁሉ እንደ ቀናው መጠን ይስጥ። ብዙ የገባለት ሰው በብዙ፥ ጥቂት የገባለትም በጥቂት ይስጥ። እንደ መጠኑ ይሁን ተባለ። (2 ቆሮ. 8፥12-14።) እግዚአብሔርም በደስታ የሚሰጠውን ይወዳል እንጂ በኃዘን ወይም በቢስነት የተሰጠውን አይቀበልም። (2 ቆሮ. 9፥7።) በብሉይ ኪዳን ዘመን

የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑቱ ከአሥር አንድ ያወጡ ነበር። (ዘፍጥ. 14፥20። ዘሌዋ. 27፥ 30።) እኛ ዛሬ ከዚህ ሕግ በታች አይደለንም፤ ይሁንና እግዚአብሔር ክርስቶስን በመስጠት ለእኛ ታላቅ ነገር አድርጎአልና (2 ቆሮ. 9፥15) ከእነርሱ ያነሰውን መስጠት ከቶ አይገባንም። ሕጉ ይኸውልህ! ምን ያህል መስጠት እንደሚገባን ልናውቅ ብንፈልግ፥ «እንደ ቀናው መጠን» ተባለ። የምንሰጠው አንድ ጊዜ ብዙ፥ አንድ ጊዜ ጥቂት ይሆናል። እንደዚህም ደግሞ መቼ መስጠት እንደሚገባን ልናውቅ ብንፈልግ፥ «በየሳምንቱ» ተባለ፤ ግለት በሥርዓት በተወሰነ በተቆጠረም ጊዜ መስጠት ይገባናል። ይህም ሕግ «ከእናንተ ለእያንዳንዱ» ነው።

ረ/ «እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ።» (ቁ. 2።) እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚሰጠውን ያህል በልቡ ቆርጦ የእግዚአብሔርን ገንዘብ ከራሱ ገንዘብ ለይቶ በቤቱ ቢያስቀምጥና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እምጡ ሲሉ ቢያቀርበው ኖሮ፥ ወይም አስቀምጦት በእንድ በኩል አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ በወንጌል ሥራ ላይ ቢያውለው፥ ለእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ የሚሆነው ገንዘብ ከቶ አያንስም ነበር።

ሰ/ «ስመጣ ያደርሱ ዘንድ።» (ቁ. 3።) ሐዋርያው ይህን አስተዋጽኦ በምን ያለ ጥንቃቄ እንዳደራጀው እንመልከት። «ገንዘቡ ለእኔ እንደ ሆነ እንዳይባል፥ ስውም ሲያዋጣው በእኔ ተገድዶ ያዋጣው እንዳይመስል፥ እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ አይሁን» ብሎአል። (ቁ.።2) ቀጥሎም ገንዘቡ ለእርሱ ሳይሰጥ በቤተ ክርስቲያን አባሎች እጅ ብቻ እንዲቀመጥ አደረገ። (ቁ. 2።) አሁንም ደግሞ እርሱ ገንዘቡን ሳይወስድ ቸርነታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም የሚአደርሱ ሰዎች ምእመናን ራሳቸው እንዲመርጡ ያሳስባቸዋል። እንዲህም ያለ ጥንቃቄ የተገባ ነው። በማኅበር ውስጥ ብጥብጥ የሚፈጥር እንደ ገንዘብ ያለ ነገር የለም። መጠራጠር ገብቶ ወደ መካሰስ ያደርሳል፥ መላ ማኅበርም ይሸበራል። በዚህ በገንዘብ ነገር እንዳንነቀፍ በብርቱ መጠንቀቅ ያስፈልገናል። (2 ቆሮ. 8፥20፡21። ሮሜ. 12፥17።)

ቁ. 5-9። ሐዋርያው ይህን መልእክት ሲጽፍ የነበረው በኤፌሶን ነው። (ቁ. 8።) ወደ ቆሮንቶስ ለመሄድ ቆርጦአል (ም. 4፥18፡19)፥ ነገር ግን አሁን በመቄዶንያ በኩል ሊመጣላቸው አስቦአል። ወደ መቄዶንያ ሄዶ እዚያ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ጎብኝቶ አልፎ ወደ ቆሮንቶስ ይመጣል። በመቄዶንያ «ያልፋል»፥ በቆሮንቶስ ግን «ይቆያል»፤ በዚያን ዘመን በክረምት ወራት መርከቦች አይነሡም ነበርና ምናልባት ደግሞ በእነርሱ ዘንድ ይክርማል፥ መንገዱንም በሚቀጥልበት ጊዜ መርከብ በማግኘት ወይም አስፈላጊውን ዕቃ በማሰናዳት በጉዞው ይረዱታል» አሳቡ፥ ጌታ ቢፈቅድ (ያዕ. 4፥13-16)፥ በቆሮንቶስ ለመሰንበት ነው እንጂ አልፎ ለመሄድ አይደለምና አስቀድሞ ወደ መቄዶንያ ሄዶ ወደ እነርሱ ዘንድ ይመጣል። ይህ ግን ለወደፊቱ ነው፥ ለአሁን አይደለም። አሁን ለሥራው ምቹ በር ተከፍቶለታል የሚቃወሙትም ብዙ ናቸው፤ ስለዚህ ዘመቻውን አቋርጦ ሊሄድ አይወድምና እስከ ጰንጠቆስጤ ቀን ድረስ ገና ጥቂት መቆየት ያስፈልገዋል።

ማስገንዘቢያ።

«ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛል ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው።» (ቁ. 9።) ወደ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያደርስ ብዙ ጊዜ «በር» ወይም «ደጅ» ይባላል» (የሐዋ. 14፥27። 2 ቆሮ. 2፥12። ቆላ. 4፥3። ራእ. 3፥8።) በኤፌሶን ከተማ ለሐዋርያው ጳውሎስ የተከፈተው ትልቅ በር ነበረ። ወንጌልን ለመስበክ ምቹ ጊዜ ስለ ሆነለት በእስያ ጠቅላይ ግዛት የኖሩት ሁሉ የጌታን ቃል ሰምተዋል። ጌታ ከእርሱ ጋር ይሠራ ነበርና በጳውሎስ እጅ የሚያስገርሙ ተአምራት ይደረጉ ነበር፥ በዚህም ምክንያት የኢየሱስ ስም ተከበረ እጅግም ሰዎች አመኑ። (የሐዋ. 19፥10-20። ማር. 16፥20።) ተቃዋሚዎች ግን ተነሥተዋል፥ ድሜጥሮስና ጓደኞቹ ሊያሳድዱት አስበዋል።

ለሚጠብቅ ለክርስቶስ አገልጋይ እንዲህ ያለ በር አንዳንድ ጊዜ ይከፈታል። ሁሉም ይከናወንለታል ለሥራውም እጅግ ምቹ ጊዜ ይሆናል። ይሁን እንጂ ለዘላለም ነው ብሎ ከቶ አያስብ። በሩ ገና ተከፍቶ ባለ በብርቱ ይሥራ የሚችለውንም ሁሉ ያድርግ። ምነው? ቢሉ፥ እንደዚህ እንዲሠራ ዲያብሎስ አይፈቅድም። እጅግ ሳይቆይ ሰይጣን ጭፍሮቹን ሰብስቦ ይመጣል ሥራውንም ለማቆም ያንም አገልጋይ ለማባረር ይጥራል፥ እንዳንድ ጊዜም በሩ ይዘጋል። አብዛኛውንም ጊዜ እንዲህ ያለ በር ለአጭር ጊዜ ብቻ ይከፈታል። ይሁን እንጂ «ዲያብሎስን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል» ተብሎአልና (ያዕ. 4፥7) ሰይጣን እንደዚህ ሲቃወመን ወዲያውኑ ከእርሱ ለመሸሽ ሳናስብ በርትተን እንቃወመው። (ኤፌ. 6፥10-13።)

ቁ. 10፡11። ጢሞቴዎስ ከአርስጦን ጋር ወደ መቄዶንያ ሄዶአል (የሐዋ. 19፥22) ወደ ቆሮንቶስም እንዲመጣ ታስቦአል። (ም. 4፥17።) የጳውሎስ መልእክት ግን በቀጥታ በባህር መንገድ ስለሚሄድ ቀድሞ ቆሮንቶስን ይገባል። በቆሮናቶስ በጥበባቸውና በኃይላቸው እየተመኩ ጳውሎስን ራሱን የደፈሩት ሰዎች አሉ። እንግዲያውስ ጢሞቴዎስ በመካከላቸው ሲገባና ክፍል ክፍላቸውን ለማስማማት ሲሞክር እንደምን ይሆን? እንኾህ ሰዎች እያሳፍሩትምን? ሐዋርያው ከዚህ አያሌ ዓመታት በኋላ «ማንም ታናሽነትህን አይናቅ» ብሎ የሚጽፍ ከሆነ (1 ጢሞ. 4፥ 12) ጢሞቴዎስ አሁንም ገና ወጣት ይሆናል፥ የቆሮንቶስም ሰዎች ሳይንቁት አይቀሩም። ጳውሎስ ግን «ጢሞቴዎስ እንደ እኔ የሐዋርያን ሥራ ይሠራልና ማንም አይናቀው» ይላል። (1 ተስ. 5፥12፡13።) ከሚመጡቱ ወንድሞች ጋር ይጠባበቀዋልና ሳያሳፍሩት፥ ጳውሎስን ራሱን በኋላ በሚረዱት ዓይነት (ቁ. 6) እየረዱት በጉዞው ያፋጥኑት።

ማስገንዘቢያ።

«ጢሞቴዎስ ያለ ፍርሃት እንዲኖር ተጠንቀቁ።» (ቁ. 10።) በጢሞቴዎስ ፊት እንዲህ ያለ አስቸጋሪ ጉዳይ ሲኖር ሐዋርያው እንደ ጢሞቴዎስ ያለውን ዓይነ አፋር ወጣት ለምን ላከ? ቢሉ፥ እንደ ጢሞቴዎስ ያለ ታማኝ ሌላ ባለማግኘቱ ነዋ! (ፊልጵ. 2፥ 19-23።) ጳውሎስ ወደ ብዙ አገሮች ሄዶ ነበር፥ ብዙዎችን ሰዎች በክርስቶስ አሳምኖ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት (ማህበሮች) ስብስቦ ነበር፤ ይሁን እንጂ እንደ እርሱ ሆነው አብረውት የሚሰሩ ብዙ ሰዎች አላገኘም በመጨረሻም ላይ ብቻነቱ እጅግ ተሰማው። (2 ጢሞ. 4፥9-12።) ጢሞቴዎስ ግን ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከጳውሎስ ጋር ሆኖ ለወንጌል አገልግሎአልና ጳውሎስ ሊታመንበት ቻለ፥ እንደ ቆሮንቶስ ጉዳይ ያለውንም ነገር ሰንኳ አደራ ሊሰጠው ፈቀደ።

ዛሬም እንደዚሁ አይደለምን? የራሳቸውን ሳይፈልጉ (ፊልጵ. 2፥21) እንደ ጱሮ ሐዋርያት የሚሠሩ የክርስቶስ አገልጋዮች ስንት ናቸው? እንሰው የለምን? መንፈስ ቅዱስ እንደ ጢሞቴዎስ ያሉትን ዛሬ ምነው ባሰነሣልን!

ቁ. 12። አጵሎስ ከጳውሎስ ጋር በኤፌሶን ነበረና የቆሮንቶስ ሰዎች በደብዳቤአቸው ላይ «አጵሎስ ይምጣልን» ብለው እመልክተው ይሆናል፥ ጳውሎስም ይህን መልእክት ከሚይዙት ከነእስጢፋናስ ጋር እንዲሄድ በብዙ ሰምናት ነበር። አጵሎስ ግን አሁን ለመሄድ በፍጹም አይመቸኝም ብሎ እለመፍቀዱን በቁርጥ አስታውቆአል።

ማስገንዘቢያ።

አጵሎስ እጅግ መልካም ተናጋሪ ነበረና ከጳውሎስ ይልቅ አጵሎስን የወደዱና የተከተሉ ብዙዎች የቆሮንቶስ ሰዎች እንደ ነበሩ አናውቃለን። ይህ ስለ ሆነ፥ ጳውሎስ ገና በኤፌሶን ሳለ አጵሎስ ወደ ቆሮንቶስ ቢሄድ ጳውሎስ ምናልባት ቅር በተሰኝና ሊጠይቀው ስንኳ ባልወደደም ነበር። ነገር ግን በዚህ ቁጥር ላይ እንደምናየው ሁሉ ሐዋርያው ቅር መሰኘት ይቅርና ይሄድ ዘንድ እጅግ አድርጎ ለመነው። እንደዚሁም አጵሎስ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቢሆን ኖሮ «ሰው ሁሉ እኔን ፈልጎአልና ሄጀ ደስታዬን ልይ» ብሎ ምቹ ጊዜ ያገኘ መስሎት ቀልጥፎ በሄደ ነበር። ዳሩ ግን ምናልባት በዚሁ ምክንያት፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ከሐዋርያው ይልቅ እርሱን እንደ ወደዱና ለመከተል እንደ ፈለጉ ስለ ተገነዘበ፥ ለመሄድ ከቶ አልፈቀደም።

በእነዚህ የክርስቶስ አገልጋዮች መካከል የነበረውን የእርስ በርስ ስምምነትና መተግመን መፈቃቀርም እንገንዘብ። ጳውሎስ አጵሎስን «ወንድማችን» ብሎ ይጠራውና ለመሄድ ይለምነዋል፤ አጵሎስ ግን ራሱ እንዳይላቅ ይፈራና ለመሄድ ከቶ አይፈቅድም። በቆሮንቶስ ክፍሎች መካከል ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር አገልጋዮች መካከል ወደረኝነት በፍጹም የለም። በክርስቲያን ሠራተኞች ሁሉ ዘንድ እንዲህ መሆን ይገባል። (ፈልጵ. 2፥3። ሮሜ. 12፥10።)

ቁ. 13፥14። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ሐዋርያው በመልእክቱ ውስጥ የመከራቸውን ሁሉ በአጭሩ ያሳስባቸዋል። ንቁ! (ም. 15፥34።) ቁሙ! (ም. 15፥1።) ጎልምሱ!˜ (ም.14፥20።) ወደ ፊትም ስደትና መከራ ቢመጣ ጠንከሩ! ይላቸዋል። በጠቅላላው ደግሞ ፍቅር መሪአቸው ይሁን። ፍቅር የሚያደርገውን ማናቸውንም ነገር እነርሱ ያድርጉት፥ ፍቅር የማያደርገውንም አያድርጉት። (ም. 8፥ 9-13።)

ቁ. 15-18። አሁንም ሐዋርያው የቆሮንቶስን ደብዳቤ ወደ እርሱ ዘንድ ስላደረሰና ተመልሶ የእርሱን መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ስለሚያደርስ ስለ አስጢፋናስና ስለ ቤተ ሰዎቹ ጥቂት ይናገራል። እስጢፋናስና ቤተ ሰዎቹ በአካይያ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ መጀመሪያ በክርስቶስ ያመኑ ቤተ ሰብ ነበሩ። ያመኑት ጳውሎስ አስቀድሞ ወደ ቆሮንቶስ የሄደ ጊዜ ይሆናል፥ ጳውሎስም ራሱ አጥምቆአቸው ነበር። (የሐዋ. 18፥1-11። 1 ቆሮ. 1፥16።) ይህ ሰው ከፈርዶናጥስና ከአካይቆስ ጋር መጥቶአል፥ ጳውሎስም አጵሎስን ‹‹ከወንድሞቹ ጋር» ይሄድ ዘንድ ሰምናት ነበርና (ቁ. 12) ከእነርሱ ጋር የሚመሰስ ይመስላል። እስጢፋናስና ቤተ ሰዎቹ፥ ይኸው ደብዳቤ በማመላለስ ዓይነት፥ ምእመናንን ለማገልገል ራሳቸውን ሰጥተው ነበር፥ ነገር ግን ጥቂት ነገር ለጳውሎስ ያዋየ ይመስላል። የቆሮንቶስ ሰዎች በእውቀታቸውና በነፃነታቸው ተመክተው የእስጢፋናስን ቃል ለመቀበል አሁን አልፈቀዱም ይሆናል፥ እስጢፋናስም ችግሩን ለሐዋርያው አጫውቶ ይሆናል። ስለዚህ አሁን ጳውሎስ «ተገዙላቸው፥ በእውነትም አነግን እንደሆኑ

እወቁ፤ እትናቁአቸው፥ እታዋርዱአቸውም፥ ነገር ግን እንደሚገባ ሁሉ ተቀበሉአቸው የሚሉአችሁንም ሰሙ» ብሎ የቆሮንቶስን ሰዎች አደራ ይላቸዋል።

ማስገንዘቢያ።

«በመምጣታቸው ደስ ይለኛል፥ እናንተ ስለሌላችሁ የጎደለኝን ፈጽመዋልና።» (ቁ. 17።) ሐዋርያው «የጎደለኝን» ሲል ምን ማለቱ ይሆን? ምን ነገር ጎደለበት? «እናንተ ስለሌላችሁ» ይላል። እንግዲህ የጎደሉበት እነርሱ ናቸዋ! ከፍቅሩ የተነሣ ሐዋርያው እንደ ታመመ ሆኖአል። (መኃ. 2፥5፤5፥8።) በወንጌል ወልዶአቸው ነበር (ም. 4፥15)፥ ወደዳቸውም። በምእመናን መካከል ክርክር እንደ ተነሣ በቁርባን ሰዓትም የማይገባውን እንደ ሠሩ ወሬ ሰማግኘት በናፍቆት ላይ ሆኖ ቆይቶአል፥ መንፈሱም ታወከ። ከቆሮንቶስ ከተማ ሰው አንዲመጣ ማን በሰጠኝ! እያለ ጭንቅ አለው።

አሁንም ሦስት ወንድሞች መጥተዋል፥ በመምጣታቸው የጎደለውን ፈጽመዋል፥ መንፈሱንም አሳርፈዋል! እንደ ፈራው ሁሉ አልሆነም፥ አብዛኛው ነገር በቆሮንቶስ ደህና ነው። እፎይ! በመምጣታቸውም እነዚያ ወንድሞች የቆሮንቶስን ሰዎች መንፈስ ደግሞ እሳርፈዋል። እንደምን? ቢሉ፥ ከሐዋርያው ጋር ግንኙነት በማድረግ በአርሱና በቆሮንቶስ ሰዎች መካከል የነበረውን ቅሬታ ለማስወገድ ቻሉ፥ ለጥያቄአቸውም ሁሉ መልስ አስገኙ።

ግንኙነት ማድረግ ምንኛ መልካም ነገር ነው! እርስ በርስ በመገናኘት ስንት እለመግባባትና ስንት ፍርሃት ይወገዳል! በርቀት በተለያዩ ሰዎች መካከል ስንት ጥርጥር ይገባል! ጥርጥርም ሳይወገድ የቆየ እንደሆነ ስንት ኃዘን ይፈጠራል! ለምሳሌ፥ በሩቅ የተቀመጠው የወንጌል አባት የወለዳቸውን ልጆች የግድ ይናፍቃል ለደኅንነታቸውም ይፈራል። (2 ቆሮ. 2፥4፥13። 1 ተሰ. 3፥5።) እርስ በርስ መገናኘት ምንኛ ማለፊያ ነገር ነው! በመገናኘት የሁለቱም መንፈስ እረፍትን ያገኛል። የወንጌል አባቶች ከልጆቻቸው ጋር፥ ቤተ ክርስቲያንም (ማኅበርም) ከቤተ ክርስቲያን (ከማኅበር) ጋር ቢገናኝ እጅግ መልካም ነገር እንደ ሆነ ልብ እናድርግ።

ቁ. 19፥20። መልእክቱ አሁን ተፈጸመ ወደ ሰላምታም ደረስን። ሐዋርያው በእሲያ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ በኤፌሶን ተቀምጦ በጠቅላይ ግዛቱ ያሉትን የሰባት አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ እስቀድሞ ያቀርባል። (ራእ.1፥4፥11።) ቀጥሎም የረዳቶቹን የአቂላንና የጵርስቅላን በቤታቸውም ያለውን የቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ያቀርባል (በመቅድሙ ላይ ተራ ቁጥር 2 ተመልከት)፥ ቀጥሎ ደግሞ በኤፌሶን የነበሩትን የምእመናን ሁሉ ሰላምታ ያቀርባል። ስላምታውን የሚሰጣቡ በተቀደሰ አሳሳም ነው።

ማስገንዘቢያ።

«በቤታቸው ያለች ቤተ ክርስቲያን።» (ቁ. 19።) ቤተ ክርስቲያን በሰው ቤት ውስጥ ሲገኝ ያስገርም የሰም ወይ? ይሁን እንጂ ይህ የጥንት ልማድ ነበር (ሮሜ. 16፥5። ቆላ. 4፥15። ፊልሞ. ቁ. 2።)፥ ሐዋርያትም ተስግሙበት ወድደውታልም። ጸሎት፥ መዝሙር፥ ስብከትም የትም ዘንድ፥ በሰው ቤት ስንኳ፥ ሲደረግ ይችላል አያስቀይምም፤ ይኸው በሐዋርያት ዘመን ይደረግ እንደ ነበረ አይተናል። «መንፈሳዊ ነገር በደንበኛ ሕንጻ

(ቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ብቻ ይሁን» የሚሉ ሰዎች ዛሬ አልጠፉም፤ አሳባቸው ግን ክሐዋርያት አላብና ትምህርት የራቀ ነው።

ቁ. 21-24። አሁንም ፊርማው ይፈረማል። እስከዚህ ድረስ እንደ ተለመደው ሁሉ አንድ ጸሐፊ ጽፎለታል። (ሮሜ. 16፥22። ቆላ. 4፥18። 2 ተሰ. 3፥17።) እሁን ግን ሐዋርያው ብርዑን አንሥቶ በገዛ እጁ ይፈርማል ፡-ጳውሎስ። የቆሮንቶስ ሰዎች ይህን ፊርማ ላያውቁት አይቀሩም። ደግሞ ጥቂት ይጨምርና «አሜን» እስከ ተባለው ቃል ድረስ ይጽፋል መጀመሪያ፥ የቆሮንቶስ ሰዎች ከተጨቃጨቁበት ነገር ሁሉ ይልቅ ጌታን መውደድ ይበልጣልና ኢየሱስ ክርስቶስን በማይወድ ሰው ላይ እርግማን ይናገራል። ቀጥሎ፥ ትርጓሜው «ጌታ ይመጣል» ወይም ይበልጡን «ጌታችን ሆይ ና» የሚሆነውን በጽርእ ቋንቋ «ማራን አታ» ወይም «ማራነ ታ» የሚለውን በዚያን ዘመን በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዘንድ የታወቀውን ቃል በዕብራይስጥ ፊደላት ይጽፋል። ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር ጌታችን ሊመጣ ይበቀለዋል ማለት ይሆናል። (2 ተሰ. 1፥8።) ቀጥሎ ደግሞ፥ እርሱ ራሱ የተቀበለውና የሆነው ሁሉ በጸጋ ነውና (ም. 15፥10። 1 ጢሞ. 1፥12-14)፥ ስውም የሚድንበትና በእምነት ጸንቶ የሚቆምበት በዚያው ጸጋ ብቻ ነውና (ኤፌ. 1፥5፡6፤2፥5፡8። 2 ጢሞ. 2፥1)፥ እንደ ልማዱ ሁሉ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ ይመኝላቸዋል። (ም. 1፥3። 2 ቆሮ. 13፥14።) በመልእክቱ ውስጥ ብርቱ የሆኑትን ብዙ ነገሮች ጽፎአል፤ ይሁን እንጂ መጨረሻው ቃል የፍቅር ነው። በመካከላቸው የበደሉ አሉ፥ እርሱንም የጠሉ አሉ፥ ሐዋርያው ግን አንድም ሳይቀር ሁላቸውንም ወድዶአል! የወደዳቸውም «በክርስቶስ ኢየሱስ» ነው፥ ሁሉም ከእርሱ ነውና!

ማስገንዘቢያ።

«ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን።» (ቁ. 22።) አንባቢ ሆይ፥ እርስዎ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ወድደዋልን? እርሱ ታላቅ ሥራ ሠርቶልዎታል። እኛ የአዳም ልጆች ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአል። (ሮሜ. 5፥6-8።) እርሱ ወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ አጠበን። (ራእ. 1፥5።) አሁንም እርሱ አስቀድሞ ስለ ወደደን እኛ እንወደዋለን። (1 ዮሐ. 4፥19።) ስለ እርሱ ብሎ የሞተውን ክርስቶስን የማይወድ ሰው ክርስቲያን አይደለም። አንባቢ ሆይ፥ እርስዎ ወድደውታልን?

እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሰው ኃጢአት የማይሠራው በዚህ ምክንያት ነው። «ክርስቶስ ለዘላለም አድኖኛልና (ዕብ. 10፥14) ኃጢአት ብሠራ ምን አጎዳለሁ?» የሚል ጥያቄ በፍጹም ያለ አገባብ ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ኃጢአት ሊሠራ አይፈልግም፥ በድንገት የሰራም እንደሆነ እንደ ቅዱስ ዳዊት ሆኖ ያፍርና ያዝናል። (መዝ. 50።) ክርስቶስ የተቀሠፈበትን መቅሠፍት (ኢሳ. 53፥4-6)፥ ከኃጢአትም ሊያድነን ያፈሰሰውን ደም (1 ጴጥ. 1፥18፡19) ያየ ሰው ክርስቶስን ይወዳል፥ በሸከሙም ላይ ለመጨመር ጠልቶ ኃጢአትን በፈቃዱ ሁለተኛ አይሠራም። የእግዚአብሔርን ልጅ ረግጦ ያንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ ሰው የእግዚአብሔር በቀል ይበቀልበታል። (ዕብ. 10፥29-31።) «ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን» ተባለ። አንባቢ ሆይ፥ እርስዎ ክርስቶስን በእውነት ወድደውታልን?

አነጣሥቶ ላስጀመረን፥ አስጀምሮ በጸጋው ላስጨረሰን ለአግዚአብሔር
ክብር ምስጋና ይግባው ለዘላለም። አሜን።